# የበደል ካሳ



ታሪካዊ ልብ ወለድ

በአጥናፍ ሰገድ ይልማ

ሰኔ 1997 ዓ.ም

# የበደል ካሳ

ታሪካዊ ልብ ወለድ

በአጥናፍሰገድ ይልማ
ሰኔ ---1997
አዲስ አበባ

# የበደል ካሳ

## ምዕራፍ 1

ቀኑ እሁድ ጧት ነው። ያልገረረው የፀሐይ ሙቀት ራቁት ሆኖ ለመሞቅ ያዳዳል። የግቢ ቅዱስ ገብርኤል፣ ቅድስት ኪዳነ ምህረት፣ ቅድስት ባዐታ፣ የካዛንቺዙ ቅዱስ ዑራኤል አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትና አድባራት የቸኮሉ ተሳላሚዎች « እሜን ሳይባል» መመለስ ጀምረዋል።

ከመንፈቀ-ሌሊት ጀምሮ ሲዜም በነበረው ቃለ እግዚአብሔር ሲመሰጥ የቆየው የምዕመን ጆሮ አሁን ሌላ ድምፅ እየተቀበለ ነው። የሠፈሩ ጥገቶች እዚህም እዚያም «እምቧ! እምቧ! እምቧ» እያሉ ናቸው። የእምቧታው ድግግሞሽ «ከጥጆቻችን አገናኙን፣ ግታችን ወጠረን፣ ወተቱን ተቀበሉንና በጧት አሠማሩን» የሚል አቤቱታ ይመስላል።

የእነአባ ምትኬ ወደል አህዮችም ስለትናንቱ ውሏቸው ወይም ስለአዳራቸው ጥያቄና መልስ ይሰጣጡ ይመስል አንዱ «ሀ! ሀ! ሀ! » ብሎ እንዳበቃ ሌላው ለጥቆ ያናፋል።

አስገደች በእንቅልፍ ልቧ ጭምር ስታዳምጥ ለነበረው የተለያየ ድምፅ የራሷን ትርጉም ስትሰጥ ቆይታ ከአልጋዋ ውስጥ ወጣች። ከአልጋዋ ጫፍ ላይ ቁጭ እንዳለች ጆሮዋን ጣል አደረገች። የሰው ድምፅ የለም። ብድግ ብላ በር ከፍታ ወጣች። ትንሽ ቆይታ ወደ ቤት ስትመለስ ሁሉም ነቅተዋል፣ ግን ለመነሳት እዚያው ይተሻሻሉ።

«እናንተ ልጆች ተነስታችሁ ላሞቹን አታገናኙም?» አለች።

«አገናኝተን፣ ወተት ሰተከናታሪዎች ሰጥተን ነው ተመልሰን ጋደም ያልነው» አሰ ወንድሟ ሠይፈ ሥላሴ::

«ጥሩ የእነአባዬ መምጫ ደርሷል፣ በቤቱ ጨሰ አጭሱበት» ብላ ወደመኝታ ክፍሏ ገባች:: ጊዜ ሳታጠፋ ሰባብሳ ነጠላዋን እንደ አንገልብስ አጣፍታ የዋናውን በር መቃን በግራ እጇ ይዛ ከደፉ ላይ ቆም አለችና ሠይፈ ሥላሴን ጠቀስ አደረገችው::

«ያው መቸም ገና ከውጭ ስትገባ <እገሊት የታለች፣ እገሌስ?> የምትለው እማዬ ነች:: እኔን ከጠየቀችህ <እዚሁ ቅርብ ደርሼ መጣሁ> ብላ ነው የወጣችው በላት::»

«እሺ እኔን ውሸታም እንዳታደርጊ ቶሎ ተመለሽ» አለና የማለዳዋን ፀሐይ ለመሞቅ ወደ አጥሩ ጥግ ተመለሰ::

ከአንድ ወር በፊት እንዲሁ እንደዛሬው ማልዳ ስትሔድ እናቷ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ድንገት መንገድ ላይ ተገጣጠሙና «የት ልትሔጂ ነው? በሰንበት ምድር፣ ገና በጧቱ ምን ያንቀዠቅዥሻል? የታደለ ቤተ ክርስቲያን ይስማል፣ ያስቀድሳል፣ ተሰጥኦ ይቀበላል፤ ይቆርባል፤ አንቺ ግን ከነዚህ ሁሉ አንዱም ውስጥ የለሽበት» ያሏትን ስታስታውስ እናቷ እንደ አባጨጓሬ ኮሰኮሷት:: የአባቷና የእናቷ አታካች ንዝንዝና ለከተቢስ አነጋገር አሰገደችን እሬት እሬት ብሏታል:: የእነሱ መነፋሰል አንዳንድ ጊዜ ምንም ጉዳይ ሳይኖራት ከቤት እንድትወጣ፤ ውጭውን እንድትናፍቅ አድርጓታል::

የእነሱን ሰድቦ ለሰዳቢ የሚሰጥ ንድፋት ሽሽት፣ አንድ ዳንስ ያሰ መጽሐፍ ይዛ ባደረ አፏ ከቤት ውልቅ አለች:: ወላጆቿ ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ የሚያዘወትሩትን መንገድ በከለላ



እያየች ቁልቁል ወደ ካዛንቺዝ በሚያመራው ኮረኮንች መንገድ መረሸች::

የመንገዱን ግራና ቀኝ ባጣበበው ሰንሰል ሥር ሥር እየሠረገ መንገዱን ያበከተውን የሽንት ቤት ጥላይ ትንፋግ አፍንጫዋ መቋቋም አልቻለም:: ሰነፈጣት:: አሰነጠሳት:: ክርፋቱን ሰመከላከል ፊቷን የመሸፈን ያህል በነጠላዋ ጀቡና የርምጃዋን ፍጥነት ጨመረች::

«ዛሬ ደግሞ ብሶበታል» አሉ አንድ የአሰገደችን መጀበን ያስተዋሉ መንገደኛ አሮጊት:: አሰገደች የአሮጊቷን አስተያየት ሙሉ በሙሉ ብትጋራም፤ መልስ ሰመስጠት ጊዜ አልነበራትም:: ይልቁንም ፍጥነቷን ጨመረች:: ፍጥነቷ የፈጠረው አካላዊ እንቅስቃሴ ካፍንጫዋ ላይ ያንሸራተተባትን ነጠላ እየመለሰች «አይ የእኔ አፍንጫ መቸ ይሆን ፋይዳ የሚኖርህ? አንተኑ ከክርፋት ሰማዳን ነጠላ ብሸፍንህ ቀስቶ መያዝ አቅቶህ ለቀቅኸው:: የታደለ አፍንጫ ከሽቶ፣ ከዕጣን፣ ከሎሚ ፣ ከጤናዳምና ከጠጅሣር የሚወጣ መዓዛን ያሸታል:: ያጣጥማል:: ይረካል:: አንተ ግን ክርፋት ሲሆን ከዚህ አይደለም፣ ካዛንቺዝ ሆነህ የመርካቶውን ታሸታሰህ» ብላ በግራ እጇ ከግንባሯ እስከ ከንፈሯ ያለውን ዳበስ አደረገች:: «ፉንጋ፣ ፉነቲ፣ ጎማዳ ታስብለኛለህ:: ሰው እንዴት የገዛ አካሉ ጠላት ይሆነዋል?» በማለት እንደገና ጣቶቿን አፍንጫዋ ላይ አሳረፈች:: መነካካቱና መጥላላቱ አስቆጥቶት ያኮረፈ ይመስል አነጠሰ::

በሁለቱም ቀዳዳዎች ኮሰል ያለውን ንፍጥ በነጠላዋ እየጠረገች «አዎ አንተ ከፊቴ ላይ የተለጠፍከው ለዚህ ነው:: የንፍጥ ቦይ:: የንፍጥ ቧንቧ:: የዚህ የዚህ ቢቀርስ፣ቅርት ጥንቅር

ባለ፣ ትንሽ አፍንጫ ለምን ለእኔ ብቻ? እናቴ፣ አባቴ፣ እህቶቼ፣ ወንድሞቼ ቤተሰቡ በሙሉ ከእኔ የተሻለ፣ እረ በጣም የተሻለ አፍንጫ ነው ያላቸው:: ምነው እኔ ብቻ?» የጥያቄዋ ክብደት ያመቃት ይመስል አስገደች ድንገቷ ቆም አለች:: «እንዴት! ዲቃላ እሆን እንዴ? አይደረግም <ያለ ደምሴ ጭኑን የደፈረ ወንድ የለም> የሚለው የእናቴ የዘምዘም ቃል መታመን አለበት» አለች እስከ ዛሬ ልብ ብላ ያላስተዋለችው አዲስ ጥርጣሬ ሠርጾባት::

አስገደች ፊቷን ወደ ግቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አዙራ «ምን አልኩህ ገብሬልዬ፣ ዲቃላ! እኔ ዲቃላ! አታደርገውም፣ የሰይጣን ጆሮው ይደፈን» በማለት አማተበች::

በድንገት ከወረራት የመንፈስ ሽብር ቅዱስ ገብርኤል እንዳላቀቃት የተሰማት አስገደች እንደገና ተረጋግታ ወደ ዮሐንስ ሁንዴ ቤት የሚያሻግረውን፣ ዘነበ ወርቅ ት/ቤት አጠገብ ያለውን ድልድይ አየት አደረገች:: «በጧት ያውም በሰንበት፣ እሰው ቤት መሄድ ይከብዳል» በሚል ይሉኝታ ተረትታ አቅጣጫዋን ለወጠች::

«የአንዳንድ ቀን ሰንበት ከአርብ ሮብ ይብሳል የተባለው ልክ ነው:: ገና ከጧቱ ሀሳቤን አዋኸቆ ያባዘነኝ የዛሬው ሰንበት እስከ ማታ የት ያደርሰኝ ይሆን?» አስገደች ለዚህ ጥያቄ መልስ ሳትሻ ወደ መሀል ካዛንቺዝ አዘገመች::

በጠዋት ከቤት የወጣችበትን ጉዳይ በይሉኝታ ቸል ብላ፣ መድረሻዋ የት እንደሚሆን ወደ አላወቀችው አድራሻ ደመ ነፍሷን መንገላወዷ «ምን እየሆንኩ ነው? ምን እያረኩ ነው?» የሚል ጥያቄ በውስጧ አጫረባት::



«የተዋስኩትን መጽሐፍ ካገኘሁት ለራሱ ለዮሐንስ፣ ከሌለ ላገኘሁት የቤተሰቡ አባል መመለስ ለችል ምን አስጨነቀኝ? በማለት ወደ ኋላዋ ተመለሰች:: ፈጠን ባለ የ5 ደቂቃ ርምጃ ከዮሐንስ ቤት ደርሳ የውጪውን በር አንኳኳች:: ዘበኛው በር ከፍቶ ቆም አለ:: አስገደች የዮሐንስን አለመኖር በግቢው መኪና አልባ መሆን ብትረዳም «አቶ ዮሐንስ አሉ?» በማለት ዘበኛውን ጠየቀች::

«ያው እየመጡ ነው» አሉ አረጋዊው ዘበኛ በእጃቸው ወደ መንገዱ እያመለከቱ:: ዮሐንስ በአዲስ አፔል አውቶሞቢል ገጭ አለና የተለመደ ፈገግታውን በማስቀደም ከመኪና ወርዶ ሰላም አላት::

«መምጣትሽን ባውቅ ኖሮ ራሔልን አቆያት ነበር» አለ ዮሐንስ፣ አብራው ያደረችውን ራሔል አበራን ሸኝቶ መመለሱን ለማሳወቅ::

«ከውጪ በር የቆምሽው ወደቤት ሳትገቢ ልትመለሽ ነበር?»

«ባለቤት ሳይኖር?» ብላ ትከሻዋን ጨመቅ አረገች::

«ምን አለ፣ የወንድም ቤት አይደለም እንዴ? ያው አሁን ባለቤት መጥቷል ግቢ» አለ ዮሐንስ በእጁ ወደ በረንዳው እያመለከተ::

«እሺ» አለች አንገቷን ሰበር አድርጋ::

«በረንዳ ላይ ብንሆንስ» ለሚለው የዮሐንስ ጥያቄ መልስ ከመስጠቷ በፊት አምረው ከተሠሩት የበረንዳ ወንበሮች አንዱ ላይ ዘፍ አለች::

«ለእኔ ቡና፣ ለአለጉ የስንበት ቁርስ» አለ ዮሐንስ አስገደች ያመጣችውን መጽሐፍ ከእጇ እየተቀበለ::

«እኔም ቡና ይብቃኝ» የሚለውን የአስገደች መግደርደር የተረዳው ዮሐንስ «እንዲያውም የጠበቃ ቁርስ ይሁንላት» አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ::

«የጠበቃ ቁርስ ደግሞ ምን ይሆን?»

«መግለጫ አያስፈልገውም ሲቀርብ ታይዋለሽ::»

አስገደች በዮሐንስ መስተንገዶ የተሰማትን ደስታ በትሁት የፈገግታ ለዛ ገለፀች::

«ለፉንግነት ማካካሻ ባቄላ ከሚገድብ ቅንድብ ስር ጥሬ ብር የመሰሉ ዓይኖች፣ ከናፍር በለዛ ሲላቀቁ ብቅ የሚሉ የወተት አረፋ የመሰሉ ችምችም ጥርሶች» አለ ዮሐንስ በፉንግነት ውስጥ ድብቅ ውበትን እያጣጣመ::

«ለዛ ያለው የሞናሊዛ ፈገግታ፣ ቆንጆ ነን የሚሉ ብዙ ሴቶች ውስጥ የሌለ.....» አለና ዮሐንስ «ታዲያ መጽሐፉን እንዴት አገኘሽው?» በሚል ጥያቄ ከተመስጦው ወጣ::

«ማር ነው::»

«ጥሞሻላ!»

«እንዴታ! ደግሜ ነው ያነበብኩት::»

«ምኑ ነው ይበልጥ ያስደነቀሽ - ታሪኩ፣ ትልሙ፣ ገፀ ባሕሪያቱ፣ ግጭቱ?»

«የዘረዘርካቸው የመጽሐፍ ፍሬ ነገሮች፣ ሥነ ጽሑፋዊ ውበትና ብስለት ተላብሰው ቀርበውበታል:: በዚህ ላይ ተአማኒነቱ የልብ - ሰቀላው ድንቅ ነው» አለች አስገደች ስንና ብርት ይዞ ወደ ቀረበው አስታጣቢ እጇን እየዘረጋች::



«አንተም እንዳነበብከው እርግጠኛ ነኝ::»

«አልተሳሳትሽም::»

«ምኑ ነበር የማረከህ?»

«እንዳነበብሽው የታሪኩ ፍሰት ያለመደናቀፍ ኮለል ይላል:: የታሪኩ አንዱ አንጓ ከሌላው አንጓ ጋር ሲገናኝ እንኳ አይንገጫገጭም:: ልብ ሰቀላው የሚመጣው አንጓዎቹ ላይ ነው::

«ፍቅር መስጠት፣ ፍቅር መቀበል ይበዛበታል:: ብዙ ብዙ ማለት ይቻል ነበር፣ ግና በእንደዚህ ያለ ጭውውት ላይ ለማንሳት አይመችም - ከእኛ ባህል አኳያ ማለቴ ነው::»

አስገደች ዮሐንስ በሰጠው አስተያየት ላይ የምትለው የሌላት ይመስል አፏን እህል አስያዘችው::

ዮሐንስ ከአስገደች የሚሰነዘር ተጨማሪ አስተያየት እንደማይኖር በመገመት ፍንጃሉን አንስቶ ቡናውን ፉት ፉት አለ:: ለአጭር ጊዜም ቢሆን እርስ በእርስ የመናበብ ዝምታ ዋጣቸው::

«ምን ይጨመር?» አለ ዮሐንስ ዝምታውን ለመስበር::

«ከጠበቃ ቁርስ በላይ እንዲሆን ነው?» አለች አስገደች በዓይኖቿ ጭምር ፈግጋ::

«በነገራችን ላይ ጠበቃ ሆዳም........» አስገደች የጀመረችውን ጥያቄ ሳትጨርስ ዮሐንስ ያለወትሮው ከጣራ በላይ እየተንከተከተ «አይደለም! አይደለም!» አለ::

«እህሳ?»

«ነገሩ እንደዚህ ነው:: ጠበቃ ብዙውን ጊዜ በጧት ከቤት ይወጣል:: ከአንዱ ችሎት ወደ ሌላው ችሎት ሲራወጥ ይውላል:: ምን ሰዓት ወደ ቤቱ እንደሚመለስ የሚወስነው የየችሎቱ

ሙግት መርዘም ወይም ማጠር ነው:: ምሳው ታስቦ የሚውልበት ጊዜም ብዙ ነው:: ስለዚህ ምሳ - አከል ቁርስ ከሰክሶ ነው የሚወጣው::» አለ ዮሐንስ::

«ችግሩ የፈጠረው ብልሃት ነው፣ ይገባዋል:: ይህ ካልሆነማ ረሃቡን ሲያዳምጥ አንቀጹን ይረሳዋል፣ ሙግቱም ይጠፋዋል» አለችና «የለንበት እረፍትህን እንዳልሻማህ» በማለት አሰገደች ስንብት ጠየቀች::

«የመጽሐፍ ግምገማው ሳያበቃ!» አለ ዮሐንስ ጭውውቱ ይበልጥ እንዲለጠጥ ያለውን ፍላጎት በማሳየት::

«ማር! ማር ነው አልኩህ□ኮ! አይበቃም?»

«መጽሐፍ እንዴት ማር እንደሚሆን ለእኔ ግልጽ አይደለም፣ ምስጢር ካለው::»

«መጽሐፍ! ከማርም ማር <መጽሐፍ ያለም ምሬት ማጣፈጫ ማር ነው> ሲባል እንደሰማህ እርግጠኛ ነኝ::»

«መስማትስ ሰምቻለሁ ብታብራሪው::»

«ምን ማብራሪያ ያስፈልገዋል፣ አባባሉ ራሱን በራሱ የሚገልጽ ይመስለኛል::»

«ግልጽ ነው አልሽ? ታዲያ የዚህ ኃይለ - ቃል መልእክት ወይም ምስጢር በሁሉም አንባቢ ዘንድ ተገቢውን ግንዛቤ የሚያገኝ ይመስልሻል?»

«ያለም ምሬት፣ እንደዚሁም የማሩ ጥፍጠት አንፃራዊ ነው:: እንደየሰዉ ይለያያል:: መልእክቱንም የመቀበልና የማጣጣሙ ብቃት ልዩነት ይኖረዋል::»



«በነገራችን ላይ ያለም ምሬት እንዳልሽውም አንፃራዊ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን የማር ጥፍጠት አንፃራዊነት ለእኔ አይታየኝም:: ማር የማይጣፍጠው አህያ ብቻ መስሎኝ?»

አሰገደች በፈገግታ ወደ ዮሐንስ አሰግጋ «አህያ ማር አይጥመውም ይባል እንጂ፣ አህያ ማር እንደማይጥመው በሙከራ ያረጋገጠ ሰው መኖሩ አጠራጣሪ ነው:: ፈረስና በቅሎስ ማር ይጥማቸዋል ወይስ አይጥማቸውም? ለምን አህያ ብቻ? ነገሩን እንሰብስበውና አንተ እንዳልከው አህያ ማር እንደማይጥመው እንገምት:: አህያ ከሌሎች የጭነት እንስሳት ይልቅ ቻይ ወይም ከአቅም በላይ ቢጭኑትም የሚሸከም ነው ይባላል:: ታዲያ አንዳንድ ጊዜ ሰው አህያ - አህያም ሰው ሲሆን አጋጥሞህ አያውቅም? የሕይወቱ እሬት የማይመረው ሰው ከአህያ በምን ይሻላል? እንደኔ እንደኔ እሬት ካልመረረው ማሩም አይጥመውም::»

«የማይካድ ሀቅ» አለ ዮሐንስ ሳያቅማማ፣ ይልቁንም በአቀረበችው ንጽጽር እየተገረመ::

«ምነው ዛሬ ፈጥነህ እጅህን ሰጠህ?»

«በማሰረጃ ሲረቱ እጅ መስጠት ያለ ነው፣ ያለዚያማ፣

<ሞኝ ያሸንፋል
እንዴት ብሎ
እምቢ ብሎ>

እንደተባለው ይሆናል::»

«ጭራቅ ነህ» አለች አሰገደች፣ ዮሐንስ «ተረትቻለሁ» በማለት ላሳየው ትህትና ያላትን አድናቆት በሚያንፀባርቅ ፈገግታ::

«ይቅርታ አስገደች፣ እንዳየሁት፣ ብርቱ የንባብ ፍቅር አለሽ፣ ይህ ደግሞ ብዙዎች ልጃገረዶች የምትታሙበት ጊዜ ማሳለፊያ (ሆቢ) አይደለም:: የንባብ ፍቅርሽ ከምን መነጨ?»

አስገደች መልሱን ግቢው ውስጥ ፈክተው ከሚታዩት አበቦች ላይ ትቀስም ይመስል፣ እኒያ የባቄላ አበባ የመሰሉ ዓይኖቿን እንከራተተቻቸውና «ከመራራው ዓለም» አለች ቃላቱን ረገጥ አድርጋ::

«ከእንቺ አንፃር ምሬቱ እንዴት ነው?»

«እንዴት ልበልህ፣ እሬት ቀምስህ ታውቃለህ? እጅግ ሲበዛ መራራ ነው::»

«የሆነስ ሆነና መጻሕፍቱ የቱን ያህል አጣፍጠውልሻል?»

«ጥፍጠቱን በአሃዝ ቀምሬ፣ በሚዛን ሰፍሬ፣ መግለጽ ያስቸግረኛል:: ቢያንስ በንባብ ጊዜ እመስጣለሁ:: መጽሐፉ ወይም ደራሲው ከፈጠረው ዓለም ውስጥ ገብቼ እዋኛለሁ:: አስምጣለሁ:: ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከመራራው ዓለሜ ገለል እላለሁ:: መራራውን ዓለም እረሳዋለሁ፣ እርሱም ይረሳኛል» አለች እርካታው አሁን አሁን ያሳት ይመስል::

«ጓደኞችሽ፣ ይቅርታ የሁላችንም ጓደኞች፣ ከመጽሐፍ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዴት ታይዋለሽ?»

«እነሱንማ የምናውቃቸው እኩል ስለሆነ ጥያቄውም መልሱም ያንተው ቢሆን ይመረጣል:: ካለዚያም እነሱኑ ብትጠይቃቸው ነው የሚሻለው» አለች ለመልሷ ማዳመቂያ ከሆነ ፈገግታ ጋር::



ዮሐንስ ባልጠበቀው የአስገደች መልስ ሳቅ ብሎ «መልስሽ ስለታም ነው! ይሳጫል» አለ በአድናቆት::

«መልሴ ስል ሆኖ ከሆነ ምረዱ ንባብ ነው» አለች በትህትና ዓይኗን ሰበር አድርጋ::

«እውነትሽን ነው፣ እነርሱ ለንባብ ጊዜ የላቸውም፣ ትያትሩ፣ ሲኒማው፣ ፓርቲው፣ ሽርሽሩ፣ ናይት ክለቡ እንኳንስ እነሱ ሲያነብቡ እኛንም ጊዜ አሳጥተውናል::»

በዚህኛው የዮሐንስ አስተያየት ላይ አስገደች በአዎንታም ሆነ በአሉታ የምትለው እንደሌላት በእንቅስቃሴ - አንገትን ነቅነቅ፣ የዓይን ቀዳዳን ጠበብ፣ ግንባሯን ቋጠር በማድረግ «ጥሩ ጊዜ አሳለፍን፣ በአጭር ጊዜ ብዙ ነገር ዳሰስን» አለች::

«ደህና እንዳልሽውም ለዛሬ ይብቃን፣ ግን በዚህ የንባብ ጉዳይ ተሳትፎውን አስፍተን እንደገና ልንመለስበት ይገባል::»

«እንደዚህ እንደዛሬው አሳለዘብን ይሆናል እንጂ፣ ያው በየጊዜው መነጋገራችን መቸ ቀረ?» አለች አስገደች የዛሬው ጭውውት ከመጽሐፍ ግምገማ በላይ መሆኑን በሚያንጸባርቅ ድምፀት::

ዮሐንስ የስልክ ጥሪ ለመመለስ «ይቅርታ መጣሁ» ብሎ ወደ ቤት ገባ::

«ምንም አይደል» በማለት አስገደች አቀማመጧን አደላደለች:: የጓደኛዋ የራሔል አበራ ጓደኛ የሆነው ዮሐንስ፣ እሷ በሌለችበት በዚህ መልኩ ለምን እንዳነጋገራት ስታወጣና ስታወርድ ሠራተኛዋ እንደገና ቡና ይዛ ቀረበች:: ዮሐንስም መጣ:: ቡናውን እየተቋደሱ ሳለ:-

«አባባ ጌቶች ጠርተውኛል» አለ ዮሐንስ

«በደህና ነው?»

«ምሳ እነሱ ዘንድ እንድበላና ስለሌላም የቤተሰብ ጉዳይ ለመነጋገር ነው የተጠራሁት::»

«አ! መልካም ግብዣ::»

«መቸ ግብዣ ሆነ፣ ቅዕዛዝ ነው:: የእኔ ሃሳብ አብረን ወጥተን ራሔልን ይዘን ራስ ሆቴል ምሳ እንድንበላ ነበር» አለ ዮሐንስ በቁጭት::

«ግድ የለም፣ በበኩሌ ቁርሱ፣ በዚህ ላይ ውይይቱ ከምጠብቀው በላይ ነው የረካሁት፣ ከልብ አመሰግናለሁ» በማለት አስገደች ለመሔድ ብድግ አለች::

«ቆይ እንጂ እሸኝሻለሁ::»

«የዕለቱ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዬ ስለሆነች ቀስ እያልኩ በእግሬ እንዳዘግም ፍቀድልኝ::»

«እንደሱ ከሆነ እሺ» አለ ዮሐንስ፣ ራሔል በሌለችበት ጓደኛዋን በመኪና ይዞ ሲሔድ ቢታይ የሚናፈሰውን አሚታ በማሰብ::

ዮሐንስና አስገደች የተሰነባበቱት አንዱ በሌላው ልብ ውስጥ ቦታ ተደላድለውና በስሜት ተናብበው ይመስላል::

አስገደች እንደዚህ ደርዝ ያለው ጭውውት ከወንድ ጋር ያደረገችበት ጊዜ መኖሩን ለማስታወስ ሞክራ አልሆነላትም:: «ራሔል ምንኛ ታድላለች፣ እንኳን ፈልጎና ለምኖ፣ ተለምኖ ከማይገኝ ዮሐንስ ጋር አንሶላ መጋራቷ:: ከመልኩ፣ ከትክለ ሰውነቱ፣ የጠባዩ፣ በዚህ ላይ ምሁራዊ ብስለቱ:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ጌታ የጌታ ልጅ፣ ቢጠሩት የማይሰማ፣ እግር ጆሮ እስኪደርስ ቢኬድ የማይገኘውን ዮሐንስን ትታ ወደ ፓሪስ



ለመሔድ መወሰኗ ስህተት ነው:: ትልቅ ስህተት! ዮሐንስ ለሌላ አሳልፎ የሚሰጡት ጓደኛ አልነበረም። ብታውቅበት ኖሮ! ራሔል ግን አትረባም:: በዮሐንስ ላይ ደግሞ ያንን ውርጋጥ ነብያት ተሰማን መደረቧ! ራሷን አትጠብቅም:: ሰውም አትመርጥም፣ ጥርሱን ላሳያት ሁሉ ወዲያው ወከክ ትላለች:: ወንድ በፍቅር ቢጥል እንኳ ችላ መባል እንዳለበት አልተረዳችም:: መሽኮርመም ከ የሴትነት ወግ ነው:: ወንድ ችላ ሲባል በውስጡ የሚንተከተከው የፍቅር ስሜት ይፈላል:: ግለቱን መቋቋም ሲያቅተው እጁን ሰጥቶ ይንበረከካል:: ፍቅረኛውን መውደድ አይደለም፣ እንደ ጣዖት ያመልካታል:: አዎ! በአንድ በኩል፣ በአጉል መሽኮርመም የሰውየው የፍቅር ስሜት ተንተክትኮ፣ ፍላቱ መቶ ድግሪ ሴንቲግሬድ እስኪደርስ መጠበቅ ግን አያስፈልግም:: ቶሎ እጅ በመስጠትና በመሽኮርመም መካከል ያለው ሚዛን መጠበቅ አለበት፣ በእርግጥ ይህንን በተግባር የማረጋገጥ ዕድል ባይገጥመኝም፣ ያነበብኳቸው ወሲብ-ነክ መጻሕፍት ያረጋገጡት ሐቅ ነው:: ራሔል ይኸንን ሚዛን ጠብቃ ካልተጓዘች መጨረሻዋ አያምርም:: ብቻ ወደ ውጭ አገር መሔጃዋ ስለተቃረበ፣ ለእንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ቁብ ላይኖራት ይችላል» አለች አስገደች ገርበብ ያለውን የቤታቸውን የውጭ በር ከፍታ እየገባች::

* * *

እንደውሻ አፍንጫ የቀዘቀዘው፣ እንደ መቃብር እርጭ ያለው ምድረ ግቢያቸው አስገደችን ቀፈፋት:: እንደገና ተመልሳ ለመውጣት ምክንያት ፈለገች:: ቆም ብላ «የት ይኬዳል? ቢኬድስ

የማታ ማታ ተመልሶ እዚሁ ነው» በማለት በመሸፈት ላይ የነበረውን መንፈሷን አረጋግታ ወደ ቤት ገባች:: እንዳከረፈ ሰው ማንንም ምንም ሳትል ወደመኝታዋ ሔደች:: ጫማዋን በቁሟ ወርውራ: ከነልብሷ አልጋዋ ላይ ተዘረረች:: የቆየችበትን በማስታወስ «ከገነት ወደ ገሀነም እስከመቼ? እረ በቃሽ በለኝ ፈጣሪ አምላኬ» በሚል ተማፅኖ በመንፈስ ወደ ሰማየ ሰማያት አረገች:: በዚያው እንቅልፍ ይዟት ጥርግ አለ::

***

«ይች ሰው የጤና ነው? ምስጥ እንዳይወጣበት» አሉ እናቷ የአሰገደች ያልተለመደ ከአልጋ ጋር ተጣብቆ መዋል አስገርሟቸው::

«ነቅታ ነበር ተመልሳ ነው የተኛችው» አለች እህቷ ታንጉት

«እሁድ እሁድ ወደማታ ሥላሴ ትሄዱም አልነበር፣ ለምን ቀረ?»

«አይ አልቀረም፣ አንዳንድ ጊዜ እኔም ፈተና ሲመጣ ለጥናት፣ እሷም ጉዳይ ሲኖራት ካልሆነ እንሔዳለን::»

«አንቺስ እሺ፣ እሷ ደግሞ ከጠሎትና ከወንጌሉ ትምህርት ምን የበለጠ ጉዳይ ኖሯት ነው: የምትቀረው? ሲሆን ሲሆን ወንድማችሁንም፤ ብትጨምሩት ደግ ነበር::»

«ሠይፈ ኳስ እርግጫውን ትቶ ቤተ ክርስቲያን መሔድ የሚፈልግ አይመስለኝም» አለች ታንጉት:

«ወደል አህያ ይመስል ሲራገጡ መዋል እንጀራ ይሆን መስሎታል:: ደግነቱ ከርግጫው በኋላም ቢሆን እስ ከደብተሩ



ጋር ሳይገናኝ አያድርም:: በዚህ ላይ ሁሌም እንደተሸለመ ነው» አሉ እናት ለልጆች ጎበዝ ተማሪ መሆን ያላቸውን አድናቆት በሚገልጽ ርካታ::

«እሱ□ኮ የጓዳ ሥራ የለበትም፣ ግፋ ቢል ለላሞች ድርቆሽና አተላ ቢሰጥ ነው» በታንጉት መልስ ውስጥ የተላለፈው መልእክት ወዲያው የገባቸው እናት «ሙያ መማር አያስፈልግም፣ ሴት ልጅም እንደወንድ ውጭ ውጭውን ትዳሰቅ ነው የምትይ? የባል ዱላ ሲሳይ መሆን ካማረሽ ተራገጭ፣ እኔ ዘምዘም እንደሆንኩ ለምድጃዬ አልሰንፍም» አሉ ተግሳፅና ምክር በተቀላቀለበት ድምፅት::

«እሙ! ዱላው እንኳ እኔን ብዙም አያሳስበኝም፣ አንቺን ግን ማገዝ እንዳለብኝ ይገባኛል» አለች ታንጉት በጓዳ ጉዳይ በእሷና በእናቷ መካከል ያለውን ያመለካከት ልዩነት ለማጥበብ::

«ባይገባሽ እንጂ ለሴት ልጅ ጓዳዋ መናገሻዋ፣ ክብሯና ሰሟ ነው:: ጓዳሽን አንቺ ካላከበርሽው እሱም በረከቱን ይነሳሻል:: በመጨረሻም ባልሽ ቡሃቃ አሳዝሎ ወደ መጣሽበት ይመልስሻል:: ያ ደግሞ ያንቺ ብቻ ሳይሆን የእኛም በተለይ የእኔ የእናትሽ ሞት — አክል ውርደት ነው የሚሆነው» አሉና ተከዙ:: «አይዞሽ እማዬ::»

«በስማብ ወልድ!» አሉና ውርደቱ አሁን አሁን የሆነ ያህል ተሰማቸውና፣ «በይ በቃሽ! ምነው ልጄ! በሰንበቱ ምድር ክፉ አናገርሽኝ፣ ሥላሴዎች ይቅር ይበሉኝ» አሉ::

የእናቷን በመንፈስ መሸበር ያስተዋለችው ታንጉት «እሺ እማዬ፣ አንቺ ከምትዋረጂ፣ አንቺ ከምትሰደቢ እኔ ሥራዬ ብቻም

አይደል መቃብሬም ጓዳ ውስጥ ይሁን» አለችና እናቷን አቅፍ አድረጋ ሳመቻቸው::

አስገደች ከእንቅልፏ የነቃችው ከምሽቱ በሁለት ሰዐት ገደማ «ለምን በር ቶሎ አልተከፈተም? እርሱ የትሂዶ ነው አንቺ በር የከፈትሽው? ውሾቹስ ለምኜን አስካሁን አልተለቀቁም? የውጭ መብራት ለምን በጊዜ በራ?»፥ በሚለው የአባቷ የአቶ ደምሴ ተሰማ ማንባረቅ ነው::

ከተለመደው የጠጅ ቤት ቆይታ በኋላ የሚመጡት አቶ ደምሴ ወደ ቤት ሲገቡ አንድም ቀን እንኳን በስህተት «እንደምን ዋላችሁ-አመሻችሁ» በሚል አባታዊ ሰላምታ ቤተሰቡን የተቀላቀሉበት ጊዜ የለም:: ይልቁንም በተቃራኒው ለትንሹም ለትልቁም በሚያሳዩት የኮሶ-ግሣት ፊታቸው ሁሉ ሰው እንዲርድ ይሻሉ::

እነአስገደች ቤት እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት ሰንባብ ቀርቶ ለእንቅልፍ ሽልብታም አያመችም:: ሌሊቱ አየተገባደደ፣ የአቶ ደምሴና የወ/ሮ ዘምዘም ንትርክ ጋብ ሲል «ተኙ፣ በጊዜ ተኝቶ በጧት መንቃት ነው» ይባላል:: ወ/ሮ ዘምዘም ወደ አልጋቸው ከማምራታቸው በፊት፣ ብዙ እንዳይቆጥር የሁሉንም ክፍሎች መብራት ራሳቸው ድርግም ያደረጋሉ::

***

ዮሐንስ ከአስገች ጋር በአደረገው ቆይታ ልጅቱን እያወቃት ሳያውቃት፣ እያያት ልብ-ሳይላት መኖሩን ተረድቷል:: «ይህች ጎማዳ ለካስ ውስጧ ቀለም ነው:: ተስፋ ያላት ግልግል ምሁር:: ራሷን በራሷ ጥረት የቀረጸች:: ከጓደኞቿ መካከል አቻም



የሌላት:: የቤተ ክርስቲያን አካባቢ ቆይታዋ መሰለኝ እንዲህ የሳላት:: ጓደኞቻችን አነብልጭልጭ፣ ውጦ - ቀልጭ የማያፈሩ አበቦች ናቸው:: ምንና ምን» አለ በመደመም::

«ትንሽም ቢሆን የእኔይቱ ራሔል ትሻል እንደሆን እንጂ ሌሎቹ ዘልዛሎች፣ ሐይ ባይ የሌላቸው፣ በወጡበት ውለው የሚያድሩ ወሮበሎች ናቸው» አለ ዮሐንስ በአንድ በኩል የራሔል ፓሪስ ጉዞ መቃረብ ከወዲሁ የፈጠረበትን ብቸኝነት እያሰበ::

ዮሐንስ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ የመሆኑን ያህል ብዙ የሴት ጓደኞች የሉትም:: በራሔል እግር ተተኪ የምትሆነውን ጓደኛ መርጦ መያዝ ቀላል ውሳኔ እንደማይሆን ተረድቶታል:: ዮሐንስ ጥቂት እንደመተከዝ አለና አገሊት ከአገሊት ትሻል ይሆናል ወደሚል ግምገማ ገባ:: «ቆይ! ቆይ!» አለ ዮሐንስ «መደበኛና የዘለቄታዋ ጓደኛ እስክትገኝ አንዷን ሻል ያለችዋን በመሸጋገሪያነት ማስጠጋት ይቻላል:: አዎ! ራሔልን ለመርሳት የአዲሲቱን ራሔል የጭን ሙቀት መቀበል ግድ ይሆናል» በማለት በምርጫ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ያላቸውን ታሳቢዎች ስም በወረቀት ላይ ጫር ጫር አደረገ:: አስገደች ደምሴ አንዷ ነበረች::

# ምዕራፍ 2

## የአስገደች ሕይወት

አስገደች የቤተሰቡ አኝጋፋ ልጅ ናት። ዕድሜዋ ወደ ሃያ አምስት ተጠግቷል። የከፍትኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ባልተሳካ ውጤት ካጠናቀቀች ሦስት ዓመት ሆኖታል።

ጓደኞቿ ሥራና እጮኛ ሲያማረጡ እሷ ግን ሁሉን-አጥ በመሆኗ፣ ከዚህም በላይ ደግሞ በዚህ ዕድሜ በቤተሰብ ላይ በመዘፍዘፏ ታፍራለች፣ ትበሳጫለች፣ ታዝናለች።

አስገደች ከጓደኞቿ መካከል በዕድሜ የሚጠጋት የለም። እንጋፋዋ ነች። በሌለችበት ጓደኞቿ «እማሆይ» ይሏታል። ይኸንን ተቀጥላ መጠሪያ ማን እንዳወጣላት ባትደርስበትም ሰምታዋለች። ብትሰማም እንዳልሰማች መሆንን ነው የመረጠችው። «ወጣትነቴ ባደለኝ ተፈጥሮአዊ ፀጋ እንኳ ለመደሰት - ለመርካት እንዳልችል ፋንጋ አድርጎ ፈጠረኝ። በዚህ ላይ ድኽነት ምን ዓይነት የአርባ ቀን ዕድል ነው? የተረገመ ክፉ ዕድል» አለች ፊቷን ትራሷ ውስጥ እየቀበረች።

እምብዛም ብርሃን በማይገባበት ትንሽ ክፍል ውስጥ ከእህቷ ጋር በምትጋራት ትንሽ አልጋ ላይ እንጼ በደረት እንጼ በሆዷ ተገላበጠች።

«ነፍስ ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ ሕይወቴ እንደ ኩሬ ረግቶ ነው የቆየው። አሁን አሁን ግን ኩሬው እየደረቀ የእኔም ትግሥት እያለቀ መሰለኝ። ይህ እሬት እሬት የሚል የኑሮ ሥቃይ እስከመቸ ነው የሚቀጥል?..... እስከ ሞት!» አለች አስገደች



ሳይታወቃት ድምጿን ከፍ አድርጋ። በገዛ ድምጿ በርግጋ ካንገቷ ቀና አለችና፣ «የእስካሁኑም ጨለማ፣ የዛሬውም ጨለማ፣ የነገውም ሕይወቴ እንደዚሁ ጨለማ ከሆነ የእኔ የመኖር ትርጉም ምን ሊባል ነው? ጨለማን በጨለማ ውስጥ..... በዚህ የቀን ጨለማ በሆነ ክፍል ውስጥ ጨለማውን ሕይወቴን ይበልጥ እያጨለምኩት መሰለኝ አዎ! ሆነም ቀረ ጨለማን በብርሃን ማየቱ ሳይሻል አይቀርም» ብላ ብድግ አለችና ሽክም እንደ ከበደው ሰው በዝግታ ወደ ሳሎን አመራች።

«በጨለማ ተፀንሼ፣ በጨለማ ተወለድኩ። በጨለማ አደግሁ-ጋመርኩ። ሚስት ሳልሆን፣ እናት ሳልሆን፣ ተምሬ ተመራምሬ ባለሙያ ሳልሆን፣ ሠራተኛ ሳልሆን ወደሚቀጥለው የመቃብር ጨለማ ልወርድ! ምስኪን አስገደች» አለች እንደ መንጎራደድ እየቃጣት።

ሳሎን ተብየው ክፍል ስፋት ከ8x5 ሜትር ካሬ አይበልጥም። ይህ ክፍል የቤተሰቡ መመገቢያና ማረፊያ (መሰብሰቢያ) ሲሆን፣ ጥግ ጥጉ የልጆች መኝታ ነው። አባት ወደ ሥራ፣ እናት ወደ ጉልት፣ ልጆች ወደ ት/ቤት ስለሄዱ ቤቱ ለጊዜው ጭር ብሏል። በዚያ ፀጥታ በነገሠበት ቤት ውስጥ አልፎ አልፎ አስገደች ሳይታወቃት የምታስወጣው ድምጽ ያስተጋባል።

ብርግድ ብሎ በተከፈተው ትንሽ መስኮት የገባው ብርሃን በአስገደች ትካዜ ላይ ብርሃን የፈነጠቀበት ይመስል ዓይኗ ሳይሰበር ወደ መስኮቱ ቀረብ አለች። ከየካ ሰንሰለታማ ተራራ ጋር ገጥ ለገጥ ግጥም አሉ።

አስገደች በመስኮቱ ስፋት ልክ የካንና ዙሪያ-ገባውን ተመለከተች። ከድኽነት ቀለበት አዙሪት ውስጥ ሰብሮ

ለመውጣት በተለያየ ጊዜ ያደረገችውን የተለያየ ሙከራ በዓይነ ኅሊናዋ መለስ ብላ እየቃኘች «ብዙ ነገር ለመሆን ሞከርኩ፣ አንዱንም እንኳን ሳልሆን ቀረሁ:: አንዱን ችግሬን ለመፍታት የወሰድኩት ርምጃ መፍትሔ በማምጣት ፋንታ በራሱ አዲስና ተጨማሪ ችግር ይሆናል:: ሕይወቴ ውሉ የጠፋ ልቃቂት ሆነ:: ከምጣዱ ወደ ረመጡ - ከዚያስ! በቃ! የአሰገደች ነገር ተከተተ ነዋ!!» በማለት ለአንድ አፍታ ቆዘመች::

«ለምን? ለምን?» አለች የመስኮቱን ደፍ በሁለት እጆቿ ጥርቅም አድርጋ እየያዘች:: «ተስፋ መቁረጥ የለብኝም:: ተስፋ መቁረጥ ከመሞት በፊት ሞት ነው» ብላ ወደኋላዋ ገልመጥ አለች:: ባጠገቧ ያገኘችውን በርጩማ ሳብ አድርጋ ተወዘፈችና ምልከታዋንም መንፈሷንም እንደገና የካ ተራራ ላይ አሳረፈች::

«ለአዲስ አበባ ከተማ ዘብ የቆመ ተራራ፣ የአዲስ አበባ ጌጥ፣ የአዲስ አበባ አለኝታ፣ ውብ ለምለም ተራራ - የካ!» አለች:: የአሰገደች የየካ አድናቆት እንደ ሰዓሊ ወይም እንደ ደራሲ ውበትን ከማጣጣም የሰረጸ ሳይሆን፣ የታላላቅ ሰዎች ርስት በመሆኑ መሬት እንኳ እንደዚህ ሲያምርና ሲከበር፣ እኛ ድኾች ግን አክባሪም አስከባሪም ስለሌለን ዝንተ-ዓለም በውርደትና በድኽነት እንማቅቃለን ከሚል ምሬትና ቅናት የመነጨ ነው::

«አቤት! ያለው ሰው ማማሩ! ጊዜ ለሰጠው ሰው፣ ይቅር ቤተሰቡ መሬቱ፣ ንብረቱ እንኳ ክቡር ነው:: ደኻ ግን ክብር የለውም:: ክብር ከሜዳ አይታፈስማ!» አለች ዓይኗን ከየካ ላይ ሳትነቅል::

«የካ የደኻ ሰው ይዞታ ቢሆን ኖሮስ? አይ የእኔ ነገር የየካ ባለይዞታ የሆነ ሰው እንዴትና ለምን ደኻ ሊሆን ይችላል?



ድኽነትን ከድንበሩ አሳለፍኩት:- ባለርስት ሆኖ ደኻ? አሁንስ የተምታታብኝ መሰለኝ» በማለት አሰገደች መቀመጫዋን ከበርጩማ፣ ዓይኗን ከየካ ላይ አነሳች::

እንደገና ቆም ብላ ፊቷን አኮሳተረች:: «አልተሳሳትኩም እንዲያውም አንዳንድ የትልልቅ ሰው ልጆች በውርስ ያገኙትን ሀብትና ንብረት በማባከን፣ የዕለት ጉርስ ያመት ልብስ እያረረባቸው መንጠው ወደ ደኻ ጎራ መቀላቀላቸውን እያየንና እየሰማን የባለርስት ደኻ የለም ብሎ መደምደም አይቻልም:: ስለዚህ የካም ሳያጣ ያጣ፣ ዋልጌና ከንቱ ባለርስት ይዞታ የመሆን አሳዛኝ ዕድል ሊገጥመው እንደሚችል ማሰብ ይቻላል::» አሰገደች ቀን የጎደለበትን የካን በምናቧ ለመፍጠር፣ አሚጋች ጭብጦችን አፋጭታና ራሷን በራሷ ሞግታ በመርታቷ ደስ አላት::

«የካ የደኻ ይዞታ ቢሆን ኖሮ፣ ደኑ ተመንጥሮ፣ ግርማ ሞገሱ ተገፍፎ፣ ገመናውን መሸፈን የተሳነው አሳዛኝና አስቀያሚ ተራራ ይሆን ነበር:: በደነዘ - ምላጭ እንደ ተበደለ ራስ እዚህም እዚያም ደኑ ሲመነጠር (ሲጨፈጨፍ) ተገጣጥቦ፣ ውበቱና ልምላሜው ወደ ዓይን - ቃር በተለወጠ ነበር:: የካም እኮ ማን ያውቃል አንድ ቀን ቀን ይጎድልበት ይሆናል» አለች በቅናትና በቁጭት::

«የዚህ እሰጥ ገባ ድምዳሜ:-

ከትልቅነት ወደ ትንሽነት፣
ከሀብታምነት ወደ ድኽነት፣
ቁልቁል እንደካሮት ማደግ ካለ፣
በግልባጩም ከትንሽነት ወደ ትልቅነት፣
ከድኽነት ወደ ባለጸግነት፣

ሽቅብ የማደግ የመመንደግ

ተስፋ መኖሩ አያጠራጥርም::

ዋናው ነገር እንደምንም ታግሎ

የድኽነትን ቀለበት መስበሩ ላይ ነው»

በማለት የመጽናናት ተስፋ ፈንቅሎ ባወጣው ስሜት ተሞልታ፣ አቋርጣ ወደ ነበረው ንባቧ ተመለሰች::

አሰገደች አንዱና ዋናው ጊዜ ማሳለፊዋ መጽሐፍ ማንበብና ስፖርት ነው:: ቅኔ የቆጠረችበትን የበዐታ ገዳምና በዘማሪነት ያገለገለችበትን ቅድስት ሥላሴ ካቴድል አሁንም አልፎ አልፎ ትጎበኛቸዋለች:: ሲኒማ፣ ትያትር፣ ፓርቲ፣ ሽርሽር ያስዚያም መኪና ውስጥ እየተዝናኑ ኬክ፣ ለስላሳ፣ ቡና በወተት መጠጣት፣ ማጣጣም፣ መደሰት ለእሷ እንግዳ ነገሮች ናቸው::

አንዳንድ ጊዜ መልእክቱ ጠጠር ቢልባትም የአሰገደች የንባብ ምርጫ ከአማርኛ ይልቅ የእንግሊዘኛ መጻሕፍት ናቸው:: መጻሕፍቱን የምታገኘው ከቤተ መጻሕፍትና ከአንዳንድ የጓደኞቿ ከንፈር ወዳጆች ነው:: ባነበበቻቸው መጻሕፍት ላይ አልፎ አልፎ የሚከፍቱት ሒሳዊ ግምገማ ዮሐንስ ሁንዴንና ተስፋዬ አስራትን ይበልጥ እንድትቀርባቸው አድርጓታል:: በግምጋሜው ከእነ ዮሐንስ አንሶ ላለመገኘት አሰገደች አንዳንዶቹን መጻሕፍት ደጋግማ የምታነብበት ጊዜ አለ::

«የተዋሱትን መጽሐፍ አዘግይቶ በመመለስ እንደ እኔ እሚወቀስ ደንበኛ ይኖር ይሆን?» አለች አሰገደች ከዩናይትድ ስቴትስ ኢንፎርሜሽን ሰርቪስ፣ በተዋሰችው አንድ መጽሐፍ የጀርባ ሽፋን የውስጥ ገጽ ላይ ከተጣበቀው ኮሮጆ ያወጣችውን የጊዜ ሰሌዳ እያገላበጠች::



«የተዋስኩት መጽሐፍ ሲጥመኝ ደግሜ ለማንበብ ወይም ለጓደኞቼ መልሼ በማዋስ በጊዜ ባልመልስም እንደ ሌሎቹ ምክንያት ፈጥሬ የተዋስኩትን መጽሐፍ የግል አላደርግም:: ቢያንስ በዚህ ረገድ የተሻልኩ ደንበኛቸው ሳልሆን አልቀርም» በማለት ራሷን በራሷ ለወቀሰችበት ድክመቷ ማካካሻ አገኘችለት::

በቤትና በግቢውም ጭምር የነበረው ፀጥታ «ልጆች-ማነሽ! አሰገደች ምነው ድምፃችሁ ጠፋ? ልጆቹ ከት/ቤት አልመጡም እንዴ? ለመሆኑ እነዚህ እንስሶች ውሃ አገኙ? እናንተ ምንተዳችሁ፣ አንቺማ ደብተራ ይመስል መጣፍ መነዝነዝ ነው ሥራሽ፣ ጓዳውን እንደሆን እርም ብለሽዋል» በሚል የእናቷ ጩኸራ ድምጽ ተሰበረ::

«እማዬ! አባዬን ይመስል ገና ከውጭ ስትገቢ .... የምን ንትርክ ነው? በሌሰና ባልተፈጸመ ጥፋት ነው□ኮ የምትቆጪው:: ዛሬ ገበያ እንዴት ነው? ቀናሽ?» በማለት እያለሳለሰች ከጀርባቸው ላይ መፍታት የጀመሩትን ቅራንቅበ አውርዳ አስቀመጠች::

«ምን ይቀናኛል፣ ለልፋት የጣፈው ቢነግድ አይተርፈው:: አሁንስ አቅሜም ደከመ ገበያውም ለገመ» አሉ በታከተ ስሜት

«..... እንባ ሲሻኝ፣ ዓይኔን ጪስ ወጋኝ፣ እንደ ተባለው» ብላ አሰገደች ትረባዋን ሳትጨርስ፣ «ነገር መብላት ሙያ መስሎሻል፣ ጋት ፈቀቅ የለ፣ ከርሞ ጥጃ» አሉ የልጃቸውን ሥራም፣ ባል - አጥም ሆና ቆማ መቅረት ያንገሸገሻቸው መሆኑን ላለመሸሸግ::

«ምነው እማ! ክፉኛ ተገተግሽኝሳ» ብላ መልስ ሳትጠብቅ አሰገደች ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች::

# ምዕራፍ 3

## የራሔል አበራ ጉዞ

ራሔል አበራ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ፓሪስ የምትሔድበት ቀን እየተቃረበ መጥቷል:: ከቤት ለንቅ፣ ከውጭ ትጥቅ ዝግጅቱ ቀጥሏል:: ጨኮው፣ ቋንጣው፣ ሚጥሚጣው በየዕቃው ተከትቶ ታሽጓል:: ያገር ልብሱ፣ ድሪው፣ አልቦው፣ አሸንክታቡ፣ የገርዳሳ ሻሽ፣ ብር አምባሩ፣ በሌላም በኩል የአክሱም ሐውልት፣ የጎንደር አብያተ መንግሥታትን፣ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናትን የሚወክሉ አነስተኛ ቅርፃ ቅርፆች፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ፣ የአማርኛ መጻሕፍትን የመሳሰሉ መታሰቢያዎች በመልክ፣ በመልክ ተሰናድተዋል::

ጓደኞቿ ዮሐንስ ቤት ዲል ያለ የሙሉ ሌሊት የራትና የዳንስ ግብዣ እያዘጋጁላት ናቸው:: እናትና አባቷ ሠርግ - አከል፣ ዛጥ ያለ የመሸኛ ግብዣ በመኖሪያ ቤታቸው ለማድረግ ጠጁ ተጥሏል፣ ጠላው ተጠምቋል:: የውጭ አገር መጠጦች እነ ውስኪ በደርዘን በደርዘን ተገዝተው መጋዘን ገብተዋል:: የቁርጥ ሰንጋዎች ከሐረርጌ በባቡር ተሳፍረው ተልከዋል::

በዚህ የመሸኛ ግብዣ ላይ ራሔል በለጠታ ጎርፍ እንደምትጥለቀለቅ ይጠበቃል:: ዮሐንስ በቤቱ ለሚደረገው ግብዣ ዋና አስተባባሪ ሲሆን፣ በእሱ ጥቆማ አሰገደች በምክትል አስተባባሪነት እንድትሰየም ሆኗል::



አሰገደች የተጣለባትን ከባድ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ችሎታው ቢኖራትም የገንዘብ አቅሟ ደካማ መሆኑን የተረዳው ዮሐንስ የማይመለስ አምስት መቶ ብር ሰጥቷታል:: «ይህ የገንዘብ ጉዳይ በእኔና በአንቺ መካከል ተቀብሮ የሚቀር ምስጢር ነው፣ አደራ» ብሏታል::

አሰገደች እንደ ማንኛውም የቡድኑ አባል የገንዘብም የአገልግሎትም ድርሻዋን በብቃትና በንቃት እየተወጣች ነው:: ይህ የአሰገደች ንቁ ተሳትፎ የአንዳንድ ጓደኞቿን ትኩረት በመሳብ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኗል:: በፓርቲው ላይ አሰገደች እንደ አንዳንዶቹ ጓደኞቿ ከላውንደሪ የወጣ ውራጅ ሳይሆን አዲስ በተሰፋ ልብስ ተውባ እንደምትገኝ ጭምጭምታ የሰሙ አሉ:: ሆኖም ጓደኞቿ የአሰገደችን የገንዘብ ምንጭ ሊደርሱበት አልቻሉም::

«ይህች ያህያ ውሃ ጠጪ እንጀትና ምን አድርጋ ነው? እንደዚህ በአንድ ጊዜ የተስፈነጠረችው? ወዟ ሳይቀር እየተለወጠ መምጣቱን ልብ ብላችኋል?» አለች ገነት አብተው ቅናት ትክን ያደረገው ስሜት::

«.......<አማሆይ> በጾም በጸሎታቸው የሎተሪ ባለእድል የሆኑ መሰለኝ» አለች ሠናይት ሰይፉ እያሌጠች::

«የሎተሪ ቲኬት መግዣውስ መች ነበራት» አለች ገነት እንደገና በብሽቀት::

«ግድ የላችሁም አባቷን አስቸግራ አንዲት ጊደር ሸጠው ረጥበዋት ይሆናል» አለ ተስፋዬ አሥራት::

በተስፋዬ አፌ-ወሪሳ የበሸቀው ዮሐንስ «ለምን ያልበላችሁን ታክካላችሁ? በማይመለከታችሁ ጉዳይ ላይ ጊዜያችሁን በከንቱ

ባታጠፉ ይሻላል:: በገዛ ጓደኛችሁ ድኽነት ላይ ይኽንን ያህል ስትሳለቁ አታፍሩም? ድኽነትን እንደ ነውር መቁጠር በራሱ አሳፋሪ ነው:: ድኽነትን ከገንዘብ አኳያ ብቻ መመልከት ራሱ የግንዛቤ ድኽነት ነው:: የዕውቀት ድኽነት፣ የተመክሮ ድኽነት፣ የሥነ ምግባር ድኽነት፣ የሞራል ድኽነት፣ የህቅ ድኽነት፣ የብዙ ነገር ድኽነት በሰፈነበት አገር እየኖርን ስለድኽነት አለማወቃችን ያሳፍራል፣ ያስገርማል:: ድኽነት በነገሠበት አገር በድኽነት ማፈር ምን ይባላል? መመፃደቅ፣ አለማወቅ፣ ድንቁርና ቢባል ቃሉ ይከብድ ይሆን? አለ እንደ አለንጋ በሚሸነቁጥ ውረፋው::

«ጆኒ እኛን ለቀቅ እማሆይን ጠበቅ» አለች ገነት እንደለመደችው አሞጥሙጣ::

«ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ» ሆነ□ኮ ነገሩ! በአስገደች ድኽነት አሳብቦ ጆኒ ስለእኛ ለማለት የፈለገውን ሁሉ ብሏል፣ ምን ቀረው? በሚለው የተስፋዬ አነጋገር ዮሐንስ እንደገና በሽቀ::

«በየሽርንቁላው አፍላፍ ገጥሞ መሞዳሞድ እንደማይሆንልኝ ከማንም ይልቅ ተስፋዬ ታውቃለህ:: ግልጽ እንሁን፣ አንመጻደቅ ነው እኔ ያልኩት:: ደግሞም እኮ! አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አካፋን አካፋ ለማለት ድፍረቱ ሲኖረን ይገባል::»

«ዮሐንስ! አቁም! አቁም! በቃህ! ከዚህ በላይ ባትሔድ ደስ ይለኛል» በማለት ከቤት ምንጥቅ አለ ተስፋዬ:: የተስፋዬ ውልቅ ማለት ያልጠበቀው ዱብዳ የሆነበት ዮሐንስ «ደህና በድኽነት ላይ ላለመግባባት እንግባባ፣ የቀረነው አጀንዳችን ወደሆነው ድግሥ ጉዳይ እንመለስ» በማለት ቀስ በቀስ ንትርኩን ለማርገብ ቢሞክርም አልሆነለትም::



ሲዋደዱ ጾም ገደፉ፣
ሲጣሉ ተዋረፉ::

እንደተባለው ሆነና እኒያ ፍቅራቸው ነፋስ እንኳ አያስገባም የተባለላቸው ጓደኛሞች ተፈነጋገጡ::

ዮሐንስ አንዳንዶቹን በስልክም በግምባርም አግኝቶ «ጥፋት ካለ በግልጽ እንነጋገር፣ አጥፊ ይቀጣ! ይካስ!» ብሎ ነበር:: ለፋቸው «እሺ እንመጣለን» ቢሉትም ብቅ ያለ አልነበረም::

በመጨረሻ ራሔል «እሺ ፓርቲው ይቅር አይደገስ፣ እናንተ ግን ታረቁ» በማለት ስለተማፀነቻቸው «እሺ» አሰኝታ ዮሐንስ ቤት ሳይሆን እሷ ቤት አገናኘቻቸው::

«በተፈጠረው አለመግባባት በግልጽ እንነጋገር፣ በበኩሌ ጥፋተኛ ነህ ከተባልኩ ጀርባዬን ልካስ» የሚለውን የዮሐንስን አስተያየት አፈንጋጩ ብድን አልተቀበለውም::

«የለም የለም!» አለ ተስፋዬ ብድግ ብሎ «ውሸን ያነሳ ውሻ ይሁን ተባብለን እህታችንን እንሸኝ፣ መወቃቀስ ካስፈለገ ወደፊት ያደርሰናል፣ አሁን ጊዜ የለም» አለ::

ካንጀትም ባይሆን ካንገት የተስፋዬ ሃሣብ ከሁለቱም ወገን ድጋፍ አገኘና የድግሡ ዝግጅት ቀዝቀዝ ባለ ተሳትፎ እንደገና ቀጠለ::

የጠቡ መነሻ የእሷ ድኽነት መሆኑን የደረሰችበት አስገደች ተሳትፎዋን እስከ ድግሱ ዋዜማ ቀጥላ በግብዣው ላይ «አሞኛል» በሚል ሰበብ ራሷን ለማግለል አሰበች:: ይኽንኑ ለዮሐንስ ለማሳወቅ አንድ ቅዳሜ ጠዋት እቢሮው ስልክ ደወለች::

የእግዜር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ «የደወልኩት አንድ ጉዳይ ላማክርህ ፈልጌ ነው» አለች አስገደች ትሁት በሆነ ድምፀት::

«እሺ በስልክ ወይስ በግንባር እንገናኝ?»

«ጊዜህን እንዳልሻማ እንጂ በስልክም ሊሆን ይችላል::»

ዮሐንስ ትንሽ አሰብ አደረገና «ዛሬ 12 ሰዓት ገደማ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትያትር ቤት መግቢያ ላይ ጠብቂኝ በግንባር መገናኘቱ ይሻላል::»

«እሺ» አለች አስገደች ዮሐንስ ጥያቄዋን በመቀበሉ የተሰማትን ደስታ ለመግለጽ ቃሉን ረገጥ አድርጋ::

ዮሐንስ የስልኩን እጀታ በቀስታ ከስልኩ ቀፎ ጋር አዋደደና ወደ ኋላው ለጠጥ አለ:: ዓይኑን የፊት ለፊቱን የመስታወት ግድግዳ ለማስዋብ ሺ ብሎ ከተጣለው መጋረጃ ላይ ተከለ:: በምናቡ የአስገደችን ተክለ ሰውነት፣ እንደ ልብስ ሰፊ ከኋላ - ከፊት - ከላይ - ከታች አገላበጠ::

«ትታይ! ምናለ ፈተናውን ካለፈች አለፈች፣ ከወደቀችም የእስካሁኑ ይበቃታል» በማለት ጀምሮት ወደነበረው ሥራ ተመለሰ::

ትንሽ እንደቆየ አንድ ሀሳብ ራሱን መታው «ራሔል ካገር ሳትወጣ ከሌላ ሴት ጋር በዚህ ደረጃ ግንኙነት መፍጠር......» አለና ዓይኑን ጭፍን አድርጎ ላፍታ ቆየ::

ራሔል ዛሬ ማታ ያላትን ፕሮግራም ለማወቅ ስልክ ደወለላት:: «ሃይ ራሔል!»

«አ! አለህ እንዴ! መቸም የሒያጅ ዘመድ የለውም ብለህ ነው?»



«ወቀሳሽ የምር እንዳልሆነ አውቃለሁ::»

«የምር፣ በጣም የምር ነው::»

«እስቲ ሙት በይኝ!»

«እኔ ማላ አልወድም - ደግሞም እትማሉ ተብሏል□ኮ!»

«እሺ አሁን ልምጣ?»

«ዛሬ እስከማታ ከቤተሰብ ጋር የተያዘ ፕሮግራም ስላለኝ ከመጣህ ነገ ይሻላል::»

«ደህና ደውየልሽ እመጣለሁ፣ እስከዚያው እሚ!» ብሎ የመሳም ድምጽ ካሞጠሞጠ ከናፍሩ አወጣ::

ዮሐንስ የዕለቱን መደበኛና የነገውንም ሥራ ከወንበሩ ላይ ተተክሎ እስከ ዘጠኝ ሰዓት አከናውኖ፣ ቀሪውን ጊዜ ከወላጆቹ ጋር ለማሳለፍ ግቢ ሔደ:: እንደ ደረሰም እህቱ ዓለሚቱ ተፍተፍ ብላ ገበታ አሰርታ ምሳ በላ:: ቤት ሙሉ ሠራተኛ እንትትን ለእንትትን በሚጋፋበት ግቢ የዓለሚቱ ተፍ ተፍ ያስደመመው ዮሐንስ

«እህቴ እንዲህ ተፌ ኖረሻል እንዴ!» አለ

«እኔ ዓለሚቱ ማን መሰልኩህ! የእመቤት ጽዮን ሞገሳ ግርፍ ነኝ□ኮ! ብላ ወደ ሌላ ክፍል ለመግባት ራመድ አለች:: ዓለሚቱ ለእንጀራ እናቷ ያላት ፍቅር መለኪያ የለውም ባይ ነች::

«ስሚ ዓለም» አለ ዮሐንስ ፈገግ ብሎ «አጎታችን ፊታውራሪ ደቻሳ <በሰው ገንዘብ መቸርና በሙቅ ውሃ መታጠብ አይጠገብም> ሲሉ ስምተሻቸው ነበር?»

«እኔ እንደዚህ ላለ የንፍገት ስብከት የማውለው ጆሮ ኖሮኝ አያውቅም» ብላው ሔደች::

ዮሐንስ ባገኘው አጋጣሚ ከዓለሚቱ ጋር ስለራሔል የመሸኛ ግብዣና ስለሌላም የባጡን የቆጡን ሲያወራ ቆይቶ ዋናው አልፍኝ ውስጥ ከእንግዶች ጋር ወግ ላይ ያሉትን ወላጆቹን ተሰናብቶ ወጣ::

ዮሐንስ አውቶሞቢሉን በዝግታ እያሽከረከረ የተግባረ ዕድ ት/ቤትን አለፈ:: ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት አጠገብ ሲደርስ ሰዓቱን ሲመለከት 12:10 ሰዓት ሆኗል:: ቀጠሮ ማክበር እንዳለበት ተሰማውና ፈጠን አለ:: ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትያትር ቤት ጋር ወደተያያዘው አደባባይ ክልል ከመግባቱ በፊት ራሔልና ወላጆቿ በትያትር ቤቱ የላይኛው በር ሲገቡ አያቸው:: ራሔል ባታየውም ከአስገደች ጋር ሆኖ ያየችው ያህል ተሰማው:: በጣምም ደነገጠ:: በታክሲ አንዳድ ሽው! ሽው! በማለት የሥራ መውጫ ሰዓት ያጨናነቀውን የመኪና ጥቅጥቅ ሸልኮ አስገደች ቆማ ከምትጠብቀው የትያትር ቤቱ በር ላይ ደረሰ:: ከመኪናው ሳይወርድ «ራስ ሆቴል አጠገብ እጠብቅሻለሁ፣ ፍጠኚ» ብሏት አለፈ::

አስገደች የሩጫ ያህል በፈጠነ እርምጃ ራስ ሆቴል እንደ ደረሰች የመኪናውን በር ከፍታ እንድትገባ በግራ እጁ አመለከታትና መኪናውን አንቀሳቀሰ:: በደሴ መንገድ ወደ ሽላ ላምበረት ለመሔድ በፊት በር በኩል መረሸ::

የዮሐንስ መደነባበር ግር ያሰኛት አስገደች «ደህና ዋልክ» ለሚሰው ሰላምታዋ «ደህና ነኝ» የሚል መልሱን ተቀብላ ዝም አለች::



የፊት በርን ጠመዝማዛና ደረቱን የሰጠ ዳገት ተንደርድሮ ከወጣ በኋላ «የቀጠሯችንን ቦታ የለቀቅነው ከሰው ጋር እንዲያዩኝ የማልፈልጋቸው ሰዎች ስላጋጠሙኝ ነው»

«አንተም ትፈራለህ!»

«አለመፈለግ መፍራት ነው እንዴ!»

አስገደች ለዮሐንስ አፃፋ ጥያቄ መልስ ለመስጠት የአእምሮዋን ጓዳ በመፈተሽ ላይ እንዳለች፣ «መፍራት ካለብኝ እግዚያብሔርን ብቻ ነው» አለ ዮሐንስ በራስ መተማመኑን በሚያንፀባርቅ ድፍረት::

«ይቅርታ በቃላት ትርጉም ፀጉር ስንጠቃ ጊዜ ላለመግደል.....» ዮሐንስ አስገደች የጀመረችውን ዓረፍተ ነገር ሳትጨርስ ከልብ ባንከተከተው ሳቅ አቋረጣት:: አስገደችም የሱን ያህል ባትንከተከተም በሳቋ አጀበችው::

የአስገደችን ሞጋችነት በልቡ እያደነቀ «ምን ወሬ አለ?» በማለት ፊቱን ወደፊቷ አዙሮ ተመለከታት::

አስገደች ዓይኗንም አንገቷንም ሰበር አድርጋ «ምን ወሬ ይኖራል?» እኔ ትናንትና ዛሬ ከማንም ጋር አልተገናኘሁም:: ወደፊትም ለተወሰነ ጊዜ ራሴን ማግለል አስቤአለሁ:: የፈለግሁህም ይኸንኑ ላማክርህ ነበር» አለች ረገብ ብላ::

«ለምን?» የዮሐንስ ጥያቄ ምክንያቱን ለመስማት ከመፈለግ በላይ የአስገደችን ስሜት የሚፈነቅል ነበር::

«አሁን አሁን ሳስበው፣ እኔ ከ ከዚህ ቡድን ጋር ያለኝን ግንኙነት ማቋረጥ የነበረብኝ ዘንድሮ ሳይሆን ድሮ! ገና ድሮ! የፌደራል ዘማሪነትና የወወክማ ተሳትፎአችን በከሰመበት ወቅት ነበር:: በርግጥ ከዚያ ወዲህ ያለው ግንኙነቴ በድርበቡ ነው::

እሱም ቢሆን ካንዳንዶቻችሁ ጋር መጽሐፍ ከመዋዋስ እንዲያም ሲል መጽሐፍ ከመገምገም ያሰፈ አልነበረም።»

«መጽሐፍ የምንዋዋስ በይበልጥ እኔና አንቺ ነን፣ እስካሁን የኔና ያንቺን ግንኙነት የሚጎዳ ችግር የተከሰተ አልመሰለኝም» አለ ዮሐንስ የውይይቱን አድማስ ወደ ሁለቱ ግንኙነት አጥብቦ ለመምጣት።

አሰገደች ለዮሐንስ ፈታኝ ጥያቄ መልስ ስትሻ «በቃ! ለዚህ ነበር የፈለግሽኝ» በማለት ጠየቃት።

«አዎና!» አለች አሰገደች ኮስተር ብላ ሳይታወቃት ብሶት ባገነፈለው ድምጽ።

«ከኔም ጋር መጽሐፍ መዋዋሱ ሊቀር?»

«ያ የተናጠል ሳይሆን በጋራ የምናየው ሊሆን ይችላል» አለች አሰገደች ቅንድቧን ሰበር አንገቷን ዘለስ አድርጋ።

«አምርረሻል ማለት ነው!»

«የማምረር ጉዳይ አይደለም- የሚያቀራርበን የሚያስተሳስረን የጋራችን የምንለው ፋይዳ በሌለበት ጓደኝነት.....» ብላ አሰገደች ንግግሯን ቆም አድርጋ የተናነቃትን ሳግ ለመዋጥ ፊቷን ከዮሐንስ በተቃራኒ ወዳለው አቅጣጫ ዞር አደረገች።

«የጓደኝነታችን ዘላቂነት አይታየኝም እያልሽ መሰለኝ?»

«አዎ!»

«ስሚ አሰገደች ጓደኝነታችን□ኮ ከወወክማና ከካቴድራል ስብስብ ብቻ የመነጨ አይመስለኝም። አብዛኞቻችን እንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ምኒልክ ትምህርት ቤት በነበርንበት ጊዜ ገና ጨጩ ሳለን የምንተዋወቅና የምንቀራረብ ነበርን። በስፖርትና በስካውት በተለይ አንቺ ታዋቂ ነበርሽ። እንዲያውም አንዳንዶቹ



የሰፈርሽ ልጆች ነበሩ። ቅርበትና ትስስሩ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እየዳበረ የመጣ ነው የሚመስለኝ አይደለም እንዴ!» አለ ዮሐንስ አሰገደችን በሚያጽናና ትህትና።

አሰገደች ማስተባበል ያልቻለችውን የዮሐንስን አባባል ጥያቄዋን ካነሳችበት ምክንያት ጋር እንዴት ለዘብ አድርጋ እንደምታቀርብ እያሰላሰለች ዝም አለች።

«በኑሮና በትምህርት ረገድ በአንዳንዶቻችን መካከል ልዩነት ያለ ቢመስልም አልተለያየንም። በርግጥ አልፎ አልፎ ረገብ ቢልም በቀላሉ የሚረሱ አይደሉም» አለ ዮሐንስ ለግንኙነታቸው መቀጠል ያለውን ፍላጎት እያሳየ።

እሷ በሱ፣ እሱ በእሷ መረታቻ ንግግር እየተደመሙ ከከተማው ሰሜን ጠርዝ ደረሱ። ሾላ - ላምበረትን አለፍ እንዳሉ ዮሐንስ ከመንገዱ በስተግራ ወዳለው ኮረብታ የሚወስደውን መጋቢ መንገድ ያዘ። የጨዋ ግቢ የሚመስል አንድ አጥር አልፎ ወደ ውስጥ ዘለቀ።

አሰገደች ፈቃደኛነቷ ሳይጠየቅ ከዋናው አውራ ጎዳና በመውጣታቸው የተደበላለቀ ስሜት መጣባትና ዝም አለች።

«መክሰስ እየቀማመስን እንድንነጋገር ብዬ ነው» አለ ዮሐንስ የአሰገደችን ስጋት የተረዳ መሆኑን በሚገልጽ ፈገግታና አካላዊ እንቅስቃሴ።

«እኔማ ንግግሩን የጨረስን መስሎኝ» አለች።

«ሳይጀመር!» አለ ዮሐንስ ሌላ ገና ያልተነካ ጉዳይ ወደፊት እንደሚኖር በሚያስተጋባ ድምጽ።

አሰገደች መልስ ሳትሰጥ ቀደም ሲል ነፍሷ ሹክ ያለቻትን የዮሐንስን «ሳይጀመር» ከሚለው ገነን ካሰ ቃል ጋር ለማዛመድ ሞከረች፡፡

ዮሐንስ የአሰገደችን መልስ እየጠበቀ መኪናውን አስተካክሎ አቆመ፡፡ የመኪናዋን ተስተካክሎ መቆም በቅርብ ርቀት ላይ ሆኖ ይጠባበቅ የነበረው ሳተና አስተናባሪ በሹፌሩ በኩል ጠጋ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ ትዕዛዝ ለመቀበል አሰፈሰፈ፡፡

አሰገደች ሰቅዞ በያዛት ድብልቅልቅ ስሜት ውስጥ ተዘፍቃለች፡፡ «ምን ልበል? እንዴት?» በሚል የሀሳብ ሙግት ነፈለለች፡፡ ዮሐንስ ከመኪናው ሲወርድ ውረጂ ሳትባል ወርዳ ቆመች፡፡ የአሰገደችን መሽበር ያስተዋለው ዮሐንስ ክንዷን እፈፍ አድርጎ በዝግታ እየተራመደ «ማረፊያ ክፍል ስጠን» አለ እጁን ወደኋላው አድርጎ ከተል ያለውን አስተናባሪ፡፡

«እሺ!» ብሎ አስተናባሪው እፊት እፊት አለና የጠፋውን መብራት ፏ አድርጎ አንዱን ክፍል ከፈተው፡፡ የአሰገደችም ልብ አብሮ ተከፈተ፡፡ አሰገደች ስሜቷን እምቃ ያዘች «የሚሆነው መሆኑ ላይቀር በከንቱ መሽበር» አለች ራሷን አረጋግታ፡፡

ዮሐንስ ከውጭ ወደ ቤት ሲገባ ሁኔታዎች ካላስገደዱት በስተቀር ኮት ማውለቅ የመጀመሪያ ሥራው ነው፡፡ እንደ ልማዱ ኮቱን አውልቆ ከወንበሩ መደገፊያ ላይ ሲሰቅል «አይበርድህም!» አለች አሰገደች፡፡ የአሰገደች ጥያቄ ከመብረድ በላይ መሆኑ የገባው ዮሐንስ «የልማድ ጉዳይ ነው፣ ኮት እንደለበስኩ መቀመጥ አይሆንልኝም» አለና አስተናባሪውን ለመጥራት ደወል አንቃጨለ፡፡



እዚያው አካባቢ ኖሮ አስተናባሪው ገርበብ ያለውን በር ከፍቶ ዘው አለና እጁን ወደኋላ አጣምሮ ቆመ፡፡ «ምን ይምጣ? እኔ ጂን ልጠጣ አንቺስ!» አለ ዮሐንስ ወንበሩን ወደ ወንበሯ እያስጠጋ፡፡

«ለስላሳ» ብላ ዝም አለች፡፡

«መክሰስ ምን አለ?» የዮሐንስ ጥያቄ ገና ከከናፍሩ ሙሉ በሙሉ ሳይላቀቅ «ልዩ ጭቅና ጥብስ፣ የበግ ጥብስ......» እያለ ድርደራውን ሊቀጥል ሲል «ተወው! ተወው! ጭቅናውን እንሞክረው» አለ ዮሐንስ በትዕዛዙ አሰገደች እንድትስማማ ፊቱን ወደ ፊቷ መለስ አድርጎ፡፡

አሰገደች ጭቅና ምን እንደሆነ ባትረዳም በመግደርደርም ጊዜ ላለማጥፋት «እሺ!» አለች፡፡

«ያሳማ ሥጋ ይሆን? አምላኬ የዛሬን እንዴት ከጉድ ታወጣኛለህ!» አለች አሰገደች ራሷ ለራሷ፡፡

አሰገደች ብዙም ሳትሽኮረመም የፍርሃት ጭንቀት ሳያርበደብዳት በርጋታ ድባብ ሁሉንም እሺ ማለቷ ዮሐንስ አስደሰተው፡፡

«እጃችንን ታጥበን እንቆየው?» አለና ዮሐንስ ቀድሞ ወደ መታጠቢያ ክፍል ገባ፡፡ እሱ እጁን ታጥቦ ሲወጣ እሷ ገባች፡፡ ቦርሳዋን ይዛ የገባችው አሰገደች በሩን ዘግታ ጥቂት ጊዜ ቆየች፡፡ የመጸዳጃ ቤቱ መቀመጫ ውሃ ተለቅቆ ፏ! ፏ! ሲል ተሰማውና ዮሐንስ ስለ ዝግጅቷ ከወዲሁ እርካታ ተሰማው፡፡

አሰገደች ከመታጠቢያ ክፍል ስትወጣ ዮሐንስ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ ጠበቃት፡፡

አስገደች አልጋውንና ዮሐንስን አልፋ ወንበር ላይ ተቀመጠች::

«ምነው ዝም አልሽሳ!» አለ ዮሐንስ ጥያቄው ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ መሸጋገሪያ እንዲሆነው::

«እንዲያው ዝም ብዬ ነው» አለች አስገደች አሁንም የተበታተነ ሀሳቧን እየሰበሰበች::

«ታዲያ ተጫወቺ!»

«ቀጣዩ ጨዋታ በጭቅና መሰለኝ» አለች የጭቅና ነገር ከንክኗት ፈገግ ብላ::

ዮሐንስ ካልጋው ላይ ተነስቶ አስገደች ወደ ተቀመጠችበት ወንበር ቀረብ በማለት እጇን ከጭኗ ላይ አንስቶ ጨበጥ ጨበጥ አደረገና:: «ከወንበሩ እኮ አልጋው ይመቻል» አላት::

«አልጋ መመቸቱን አውቃለሁ» አለች የዮሐንስን አባባል እንደቀልድ በመቁጠር::

«አዎ» አለች አስገደች ራሷ ለራሷ «አዎ! ዮሐንስ ዛሬ ሒሳቡን ማወራረዱ ነው:: የ500 ብር ሒሳብ:: ከዚያ በኋላስ?» አስገደች እንደገና በሀሳብ ባህር ላይ ተንሳፈፈች::

ዮሐንስ ከአስተናባሪው ጋር ጥግ ይዛ በተደረደረችው ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ምግብና መጠጡን ካሰናዱ በኋላ «ራት ተዘጋጅቷል!» አለ አስገደችን ወደ ገበታው እየጋበዘ::

«ማስተናበር ትችልበታለህ::»

«ሌላስ ምን የማልችለው ነገር ያለ ይመስልሻል?»

«ምንም» አለች አስገደች በዮሐንስ መቻልና አለመቻል ላይ ሙግት ለመግጠም ባለመፈለግ::



«ይህማ ስጋ ጥብስ ነው፣ ጭቅና የተባለው የት አለ?» አለች አስገደች:: በውስጧ ጭቅና የሚለው የለስላሳ ሥጋ ስም አስገደች ጆሮ የገባው ለመጀመሪያ ጊዜ ያን ምሽት ነበርና::

የመክሰሱ ተቋድሶ እንዳበቃ እጆቻቸውን በየተራ ተጣጥበው አልጋው ላይ አረፍ አሉ::

«በሩ□ኮ አልተዘጋም» አለች አስገደች ሰው ውልብ ሲል አይታ::

«እውነትሽን ነው» አለና ዮሐንስ ብድግ ብሎ ዘጋው::

ከዚያ በኋላ የነበረው ውይይት ድምጽ አልባ ሆነ:: ጣራ ላይ የተንጠለጠለው የመብራት አምፑል ጠፍቶ በራስጌ መብራት ደብዛዛ ብርሃን ውስጥ ሆኑ:: የብርሃኑ መደብዘዝ መተፋፈሩን መሽኮርመሙን ሸፈነላቸው:: ዮሐንስ ደራ:: አምቃ ይዛው እንጂ ቀድማ የደራችው እሷ ነች:: ጉያዋ ረጥቧል:: በሙታንታዋ አበስ አበስ እያደረገች ጠበቀችው:: አስገደች ደብዛዛውን የራስጌ መብራት ብርሃን ስላልፈለገች አጠፋችው:: የቀሚሷን ዚፕ ዮሐንስ ቁልቁል መገምገግ ሲጀምር እሷም አገዘችውና ሁለቱም በወዘከላ (ካናቴራና ውስጥ ልብስ) ቀሩ:: ከንፈር በከንፈር በመደሳሰስ ወገብን በእቅፍ በመከነዳዳት ተቃብጠው ወደቀጣዩ ምዕራፍ ተሸጋገሩ::

# ምዕራፍ 4

## የራሔል ስንብት

ፊታውራሪ አበራና ወ/ሮ ሴቱሰጋ ያሚን ባልና ሚስት ሲሆኑ ጋብቻቸው የተፈፀመው በግርማዊ ጃንሆይና በግርማዊት እቴጌ መነን መልካም ፈቃድ (ቡራኬ) ነው። ፊታውራሪ አበራ፣ በልዑል ራስ ካሳ ዳርጌ ዘርፍ ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘውድ ቅርበት ያላቸው መስፍን ናቸው። የዝርያቸውን ድር-ማግ ልጆቻቸውና ከዚያም አልፎ ግበረ-በላው ሁሉ ሳያዛባ ይመዘዋል። ይህም ፊታውራሪን በእጅጉ ደስ ያሰኛቸዋል። በየምክንያቱ በግቢያቸው የሚጣለው ግብር የማንነታቸው መግለጫ እንዲሆን ወግ ማረጉን ያስጠብቃሉ። ይህ ነው ለራሔልም መሸኛ ትኩረት ያሰጠው።

«ልጄ ከመሔዷ በፊት የግርማዊ ጃንሆይንና የግርማዊት እመቤቴን ጫማ ስማ ቡራኬአቸውን መቀበል ይገባታል። መሔዷን የስሚ ስሚ ሰምተው ቢጠይቁኝ ምን መልስ እሰጣለሁ? የሚያሳፍር ነገር....» አሉ ፊታውራሪ እሁድ ጧት ቁርስ ላይ የቀረቡትን የቤተሰብ አባላት አንድ ባንድ እየተመለከቱ።

«ቀደም ብለው ዐቃቤ ሰዓት ሳያስይዙ አሁን ከመሸ ተነስተው...» የባለቤታቸውን ንግግር አቋርጠው፣ «ግድ የለም፣ እሱን እሱን ለኔ ተይው፣ እኔ አበራ እንኳን ለልጄ! ሆ!ሆ!ሆ!» አሉ።

«ይሁና! የሚሳካ ከሆነ ከመሸኛው በፊት ቢሆን ይመረጣል!» አለ የበኩር ልጃቸው ልዑለ ቃል።



«ጊዜውን በተመለከተ ደግ ብለሃል። <የሚሳካ ከሆነ> ማለት ግን በእኔ የቤተ መንግሥት ሰውነት ላይ ጥርጣሬ ያለህ ይመስላል።»

«ምነው አባባ፣ እንዴት ሆኖ! ምን ቢገድ እንደሱ ይታሰባል? አገር ያወቀውን ፀሐይ የሞቀውን፣ ታሪክ የመዘገበውን» አለ ልዑልቃል እያንዳንዱን ነገር እየረገጠ።

«አልከውና! አልከውና!» አሉ ፊታውራሪ በልጃቸው አድናቆት የረበበባቸውን ደስታ በሚገልጽ መጀነን።

«ጃንሆይ የትምህርትን ጉዳይ አጥብቀው የያዙት ገና አልጋወራሽ ሳሉ ነው። የደኻውን ልጅ እረኝነቱን አሰልጥለው አዳሪ ትምህርት ቤት የከተቱ የኢትዮጵያ የትምህርት አባት ናቸው። ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር የሚሔዱትን ጫማ አስመውና መክረው ያሰናብታሉ። ተምረው የሚመለሱትንም መቋቋሚያ ሰጥተው ይሾማሉ። አዎ! ራሔልም የምትቀርበው ለዚሁ ነው» አሉ ፊታውራሪ ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸውን አድናቆት በማስረገጥ።

«ዘወትር በሁዳዴ ጾም በየት/ቤቱ እየተገኙ የወይን ፍሬና ብርቱካን በመስጠት፣ ተማሪውን ራሱን እያሻሹ የሚያሳዩት አባታዊ ፍቅር ጃንሆይ ለትምህርት ያላቸውን ልዩ ትኩረት የሚያንፀባርቅ ይመስለኛል» አለ ልዑለ ቃል የአባቱን አስተያየት በመጋራት።

፨

ሞአ አንበሳ ዘ እምነገደ ይሁዳ፣ ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ስላሴ፣ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ የሚለው አጠራር እየተለመደ ከመሔዱ የተነሳ እንደ መደብዘዝ ማለቱ ያሳሰባቸው

የስርዓቱ ካድሬዎች (አወዳሾች)፣ ለጃንሆይም ለሕዝባቸውም ጆሮዎች የሚጥሙ አዳዲስ ሞጋሳዎችን በየጊዜው ይቀርፃሉ፡፡

- ፀሐዩ ንጉሥ፣
- የኢትዮጵያ ብርሃን፣
- የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መስራች፣
- የኢትዮጵያ የትምህርት አባት፣
- የኢትዮጵያ የነፃነት አባት፣
- አባባ ጃንሆይ የሚሉት ከሞጋሳዎቹ ጥቂቶቹ ነበሩ፡፡ «ኃይለ ሥላሴ ይሙት» የሚለው የወጣቱ፣ የመሰዮ ለባሹና የሌላውም የሌላውም ሁሉ መሐላ ከጃንሆይ የአባትነት ፍቅር የሰረፀ ነው የሚለውን አስተያየት ማስተባበል አስቸጋሪ ነው፡፡ ፊታውራሪ አበራም አዘውትረው የሚያንፀባርቁት ይህንኑ ነው፡፡

ፊታወራሪ ባላቸው ተሰሚነት፣ በዚህም በዚያም ብለው፣ ራሔል ቤተ መንግሥት የምትቀርብበትን ዐቃቤ ሰዓት አስይዘዋል፡፡

«ጃንሆይ ፊት የምትቀርቢበት ለየት ያለ ልብስ ከእናትሽ ጋር ተመካከሩና አስፉ፡፡ ያበሻ ልብስ ቢሆን ደስ ይለኛል» አሉ ፉታውራሪ፡፡

«አንድ ፍሬ ልጅ፣ ምን ለየት ያለ ልብስ ያስፈልጋታል? ተማሪ መሆኗ ቀረ!» አሉ እናቷ የባለቤታቸውን አስተያየትና ፍላጎት ገርቶ ፈር በሚያስይዝ አነጋገር፡፡

«መቸም አንቺ ካልመሰለሽ......» ፊታውራሪ የጀመሩትን ሳይጨርሱ አቋርጠው «የታላላቆች ሰዎች ልጆች ጃንሆይ ዘንድ



ቀርበው አይቻለሁ፡፡ አንድም ጊዜ የተለየ ልብስ ለብሰው አላየሁም፡፡ ልብ ባይሉ ነው እንጂ፣ አንዳንዶቹን አብረን ነበር ያየናቸው» አሉ ወ/ሮ ሰጋ - ሴቱ ፈርጠም ብለው፡፡

«ይልቁንም» አሉ ፊታቸውን ወደ ራሔል መለስ አድርገው «እኔ የምፈራው ያቺ ጦልጧላ ውሻቸው ልጄን እንዳታስደነግጣት ነው፡፡ በሰው ትጮኻለች፡፡ ምናልባት እግርሽን ባፍንጫዋ እየነካካች ታነፈንፍሽ ይሆናል፡፡ ስለማትናከስ ዝም በያት፡፡ እንዳትፈሪ» አሉ እናቷ በአደራ ጭምር፡፡

«እማማዬ እኔ ውሻ አልወድም፣ ታውቃላችሁ፡፡ የጃንሆይ ውሻም ብትሆን እግሬን ባፍንጫዋ እየነካካች ካነፈነፈችኝ ሲሆን ‹ዋይ> እላለሁ፡፡ <ዋይ> ማለቱ ቢቀር መንፈራገጤ የማይቀር ነው፡፡»

«ሆ! ሆ! ሆ! ጉድ እኮ ነው! ኧረ በሽዋታጠቅ ሞት! እንዴት ያለው ጉድ ፈላ! የምትቀርቢው□ኮ! ንጉሥ ፊት ነው፣ ‹ዋይ እላለሁ> አልሽ?»

«ግድ የለም፣ ድንክ ውሻ ፈልጌ አለማምዳታለሁ፡፡ ያበቃል፣ እርሶ ይኽን ይኽንን ለእኔ ይተውት» አሉ እናቲቱ የባለቤታቸውን ሥጋት መጋራታቸውን በሚገልጽ ማጽናኛ፡፡

«ብቻ እንዳንዋረድ፣ ያገር መሳቂያ እንዳታደርጊን ልጄ! ልጄ! አደራሽን» ብለው ፊታውራሪ ከሳሎን ወደ በረንዳ ወጡ፡፡

ወ/ሮ ሰጋ ሴቱ የባለቤቻቸውን አደራና የራሳቸውንም ስም ለመጠበቅ ራሔልን በሥልጠና ሲያሾሯት ነው የከረሙት፡፡

«የጃንሆይን ጫማ ከመሳምሽ በፊት በቅርብ ርቀት ሁለት ሦስቴ ራመድ ብለሽ ትቆሚያለሽ፣

- የእልፍኝ አስከልካዩ <ቀረብ በይ> ካለሽ እጅ ነስተሽ አንድ ወይም ሁለት እጫጭር ርምጃዎች ያህል ጠጋ ትያለሽ፣

የእልፍኝ አስከልካዩ <እጅ ንሺ> ሲልሽ፡-

- ግንባርሽ ምንጣፉን እስኪነካ፣
- ከጉልበትሽ እጥፍጥፍ ብለሽ፣
- ጣቶችሽን ምንጣፉ ላይ ተክለሽ ዝንጥፍ ትያለሽ፣
- ከዚያም ሳትረገደገጂ ቀና ትይና እጅሽን አጣምረሽ ትቆሚያለሽ፣
- እልፍኝ አስከልካዩ <ጫማ ሳሚ> ሲልሽ፣ ጠጋ ብለሽ ጫማቸውን ትስሚያለሽ::

ጃንሆይ ፊታቸው እንደ እሳት ነበልባል ስለሚጋረፍ በወላፈኑ ሳትደናገጭ፣ ጫማ ከሳምሽ በኋላ ጀርባሽን ሳትሰጪ ፣(ፊትሽን ሳታዞሪ) አንገትሽን ሰበር አድርገሽ፣ በቀስታ ሁለት ሦስት ርምጃ ወደኋላሽ ፈቀቅ ብለሽ ትቆሚያለሽ::» ራሔል ይህን እናቷ በእንቅስቃሴ ጭምር ያሳዩዋትን ልምምድ በስሜት ነው ደጋግማ ያደረገችው::

ራሔል ባጭር ጊዜ የተካነችውን የቤተ መንግሥት እጅ አነሳስ ሥርዓት ላባቷ በማሳየት «ጎሽ! ጎሽ! የአጅሪት ልጅ አይደለሽ! እናትሽ እኮ ከመሰላት እንኳን ሰው አውሬ ታሰለጥናለች» አሉና ግንባሯን ሳሟት::

ወዲያው ቀጠል አድርገው፣ «አንድ ነገር የቀረ ይመስለኛል!» አሉ ፊታውራሪ ወደ ባለቤታቸው ዞር ብለው::

«እሱ ደግሞ ምን ይሆን?» አሉ እናቲቱ እንደመገረም እያሉ::



«ጃንሆይ ሲጠይቁ፣ መልስ አሰጣጡ ነዋ! አሉ ፊታውራሪ ድምፃቸውን ናር አድርገው::

«አባባዬ! የምን ጥያቄ ነው! ፈተና አለብኝ እንዴ! ጉዴ ፈላ!»

«አይዞሽ ፈተና አይደለም::»

«እህሳ?»

የአባትና ልጅ ግራሞት ትንፋሻቸው እስኪቋረጥ ያሳቃቸው ወ/ሮ ስጋ ሴቱ ከሳቃቸው መለስ ብለው «ደህና! ደህና! እሱንም እኔው አለማምዳታለሁ» አሉ::

«ለጃንሆይ ጥያቄ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠው

<አዎ ግርማዊ ሆይ!

እሺ ግርማዊ ሆይ! ወይም፣

አይደለም ግርማዊ ሆይ!

የሚል መልስ ነው::»

«ለመሆኑ ምን የሚጠይቁኝ ይመስልሻል እማማዬ?»

<ምንድነው የምትማሪው?>

<ምን እንድናደርግልሽ ትፈልጊያለሽ?>

<ወንድምና እህት አሉሽ?>

ብለው ይጠይቁሽ ይሆናል:: ሌላም ሌላም ምናልባት <ስትመለሽ እኛ ነን የምንድርሽ> ይሉም ይሆናል፣ አይታወቅም::»

«ይህም አለ?» አለች ራሔል ፈገግ ብላ::

«ምናልባት» አሉ እናቷ ከተቀመጡበት እየተነሱ::

ራሔል መኝታ ቤቷን ዘግታ የተነገራትንና ያሳዩዋትን ሁሉ ስትለማመድ ከርማ በራሷ ተማምናለች:: ቤተ መንግሥት

የምትቀርብበት ቀን አንድ ሳምንት ሲቀረው አባቷ ከአልፍኝ አስከልካይ ጽ/ቤት ጥሪ ደርሷቸው ሔዱ::

«ግርማዊ ጃንሆይ ሰሞኑን በአስቸኳይ ሥራ ስለተያዙ፣ የዚያን ዕለቱ ዐቃቤ ሰዓት ተሰርዟል:: የእርሶን ልጅ እመቤቴ ልዕልት ተናኜ ወርቅ ተቀብለው እንዲያሰናብቱ የልዕልት አልፍኝ አስከልካይ ዐቃቤ ሰዓት ይዟል:: ሌሎች በቡድን ቀርበው ሊሰናበቱ የነበሩትን ተማሪዎች የትምህርት ም/ሚኒስትሩ ተቀብለው እንዲያሰናብቱ ፕሮግራም ተይዞላቸዋል» የሚለውን የፕሮግራም ለውጥ ፊታውራሪ የተቀበሉት፣ «ልዕልት እመቤቴስ ቢሆኑ ያሳደጓት አይደሉ! ጥሩ ነው!» በማለት ነበር::

የራሔል ወላጆች ከቅዳሜ ምሳ እስከ እሁድ ራት የጣሉት ሙሉ ግብር የራሔልን ማንነት በውል ያረጋገጠ ፊንጠዝያ ነበር:: ከግብሩም በላይ በማግሥቱ ሰኞ ጠዋት ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ዘንድ ቀርባ እጅ እንድትነሳ የተሰጣት ዕድል የራሔልንና የወላጆቿን ማንነት አስመሰከረ::

«አገርሽንና ወገንሽን አስታውሽ፣ እንዳትረሽ፣ ስትመለሽ የምንድርሽ እኛ ነን» በማለት ልዕልት ሰባ አምስት ግራም የወርቅ ሐብል ሲያጠልቁላት፣ ፊታውራሪ አበራና ወ/ሮ ሰጋ ሴቱ ሲቃ እየተናነቃቸው «የእመቤታችንን ሕይወት ያስምልምልን» በማለት ደስታቸውን መሬት እየሳሙ ገለፁ::

ራሔል በውጭ አገር ከፍተኛ ትምህርት ለመማር ካገኘ ቸው ዕድል ይልቅ በዚህ ሳቢያ በልዕልት ዘንድ ያገኘችው ሞገስ ፋይዳ ያበልጥ ገነነ::



ራሔል የልዕልትን ቡራኬ ተቀብላ እቤት ከመድረሷ በፊት ዜናው ቀድሞ ደርሶ ኖሮ ወዳጅ ዘመድ በዕልልታ፣ በዘፈንና በጭፈራ ተቀበላቸው::

ፊታውራሪ እንኳን ደስ አላችሁ በማለት ለሚመጣው የደስታቸው ተካፋይ ግብር እንዲጣል ትዕዛዝ ሰጡ:: ፊንጠዝያው ራሔል ካገር እስከ ወጣችበት ቀን ዋዜማ ድረስ ቀጠለ:: ራሔል ለሌላ ግብዣ ጊዜ ሲተርፋት ስላልቻለ እነዮሐንስ አቅደውት የነበረው የራትና ዳንስ ምሽት ፕሮግራም ተድበስብሶ ቀረ::

ግብዣው ቢሰረዝም ጓደኞቿ በመዋጮ የገዙላትን ስጦታዎች፣ ቡድኑን በመወከል፣ ዮሐንስ፣ ዓለሚቱና አስገደች እቤቷ ድረስ በመውሰድ ለራሔል አበርክተውላታል:: በጓደኞቿ መካከል፣ በእርሷ ምክንያት የተፈጠረውን አለመግባባትና መቀያየም በማስታወስ ሆድ ብሷት አለቀሰች::

ዮሐንስና ዓለሚቱ «ራሔል ምን ማለትሽ ነው? ምን ያስለቅስሻል?» እያሉ ሲያጽናኗት አስገደች በለቅሶው ስታጅባት ነበር:: «ራሔል! እንባሽን በከንቱ ለምን ታፈሻለሽ? ለሠርግሽ ዕለት መቆጠብ ይኖርብሻል» በማለት ዓለሚቱ የሰነዘረችው ያልተጠበቀ አስተያየት ለቅሶዋን አስትቶ በፈገግታ ዮሐንስን አትኩራ እንድትመለከት አደረጋት::

***

ራሔል የምታፈቅረውን ዮሐንስንና ሮጣ ያልጠገበችባትን አዲስ አበባን ትታ፣ እንደ ፀሐይ ከሚሞቀው የወላጆቿ ጉያ ወጥታ፣ በባዕድ አገር ፈታኝ የትምህርት ዓለም ውስጥ ከገባች ከረምረም ብላለች::

እዚህ አዲስ አበባ በእሷ ካገር መልቀቅ በተፈጠረው ክፍት የፍቅር ቦታ ራሳቸውን ለመተካት አንዳንድ ጓደኞቿና ሌሎችም ጭምር ዮሐንስን ተጫርተው ነበር:: በስውርም በግልፅም በተደረገው ጨረታ፣ የሰማይ መላእክት፣ የምድር ሠራዊት ጨረታውን ታሸንፋለች ብለው ያልጠበቋት ልጅ መርታቷን ከጨረታው ተሸናፊዎች አንዷ አልማዝ ተስፋ እግዚአ፣ ስለጨረታው ከርቀት ለምታ የታዘበች በመምሰል፣ በእግረ መንገድም ነፃ የትምህርት ዕድል እንድታፈላልግላት በመጠየቅ፣ ለራሔል ደብዳቤ ጽፋ አረዳቻት:: አልማዝ የራሔልን አድራሻ ያገኘችው በአስኮላርሽፕ ሰበብ ከራሔል እህት ከሠናይት አበራ ነው:: ሁለቱም የኢትዮጵያ አየር መንገድ መ/ቤት ባልደረቦች ናቸው::

ራሔል ደብዳቤው እንደደረሳት ለጓደኞቿ መልስ ልፃፍ ወይስ ነገሩን ንቄ ልተወው በሚል የሀሳብ ሙግት ውስጥ ከረመች:: በመጨረሻ ራሔል ደብዳቤ መፃፍ እንዳለባት ወሰነች::



## የራሔል ደብዳቤ

የተወደዳችሁ ጓደኞቼ፣

ዮሐንስ ሁንዴ፣

ዓለሚቱ ሁንዴ፣

ተስፋዬ አሥራት፣

አስገደች ደምሴ፣

እንደምን አላችሁ፣ እኔ ደህና ነኝ:: ወደ ፓሪስ እንደመጣሁ ስለ አጭሯ ቆይታዬ እንዲሁም ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተሰብና እናንተን ከመሳሰለ ጓደኛ መለየት ስለፈጠረው ስሜት ደብዳቤ መጻፍ ጀምሬ ነበር:: እያንዳንዳችሁን ሳስታውስ ቁም ነገራችሁ፣ ቀልዳችሁ፣ በተለይ ዮሐንስ ፍቅርህ ይመጣብኝና ሆድ ይብሰኛል:: ድንገት የሚንዠቀዠቀው እንባዬ ወረቀቱን ላይ እየተንጠባጠበ ደብዳቤዬን ያበላሽብኛል፣ ይህም እንደገና ያናድደኛል:: በሌላ በኩል ማልቀሴን ሰው እንዳያይብኝ ራሴን ደብቃለሁ:: የናፍቆት በሽታ ነበር::

ይኸንን ደብዳቤ የጻፍኩት ግን ከበሽታዬ ተፈውሼ ነው:: ዘመድ አይጥፋ፣ አስገደች ደምሴ ሎተሪ እንደወጣልሽ ሰማሁ:: እንኳን ደስ አለሽ:: ዮሐንስም እንኳን ደስ አለህ:: ዓለሚቱንና ተስፋዬን ምን እንደምል ግራ ስለተጋባሁ እንዲሁ ብርታቱን ይስጣችሁ::

ዮሐንስ «ወንድ ልጅ ጀለ ተቃራኒ ፆታ ጭን ሙቀት ውሎ ማደር የለበትም» በማለት እንደዋዛ ጣል ታደርግ የነበረውን ቀልድ አስታውሳለሁ:: በፊት ከትምህርት ቤት በኋላም ከሥራ ሁታ በየጊዜው ታስኮበልለኝ እንደነበር ታስታውሳለህ:: አንተ ብቻ ሳትሆን እኔም ካንተ እቀበል በነበረው ሙቀት እረካ እንደነበር

አልደበቅሁም:: ያም ሁሉ ሆኖ በስተመጨረሻ እንደማንጋባ ሳውቀው ፊቴን ወደ ትምህርት አዞርኩ:: ከእኔ ጋር ከተለያየን በኋላ ያለ ጭን ሙቀት ትቆያለህ የሚል ግምት አልነበረኝም:: በእኔ ቦታ ስለምትተካዋ ወጣቷ አስብ ነበር:: ቅናት ቢጤም ጎንታትላኝ ነበር:: «ትውሰደዋ! ትራፊዬን ነው የተውኩላት! ድሮስ ቢሆን እኔ ትቸው ስሄድ ያለ ሴት ሊቀር ነው እንዴ!» በሚለው በራሴ ሙግት ራሴን ረትቼ ስፅናና ነበር::

አሁን ግን የአንተንና <የእማማ> አሰገደችን መሻረክ ስሰማ በሸቅሁ፣ ልብ በል ቀናሁ ማለቴ እንዳይመስልህ - ማንም ሰው ቢሆን ቁልቁል አይቀናማ! ደግሞ እኔ ራሔል አበራ! «አህያና ፈረስ እኩል ፈሰስ!» አይሆንም! ዮሐንስ ሙት ሊሆን አይችልም:: አንተን ካሰገደች ጋር ማመን ያቅተኛል:: ካልጠፋ ልጃገረድ! አንተን ማግኘት አይደለም፣ ቀረብ ብሎ ለማጫወት ስንቶቹ ቆነጃጅት ይቋምጡ እንደነበር አስታውሳለሁ::

ዓለም! ተስፍሽ! እናንተስ ምን አላችሁ? ደግሞስ ለምንድነው ያልጻፋችሁልኝ? ግን□ኮ! ምን ተብሎ ይፃፋል? ተውት! ችግራችሁና ጭንቀታችሁ ይገባኛል::

በሉ እንግዲህ ከዚህ በላይ ጊዜዬን ልሰጣችሁ አልችልም:: ይህም ሲበዛባችሁ ነው:: ለዮሐንስና ለእማማ አሰገደች ማለቴ ነው:: ዓለሚቱና ተስፋዬ ግን በዚሁ ጉዳይ ላይ ሳይሆን ሌላ ሌላውን በተመለከተ ከፃፋችሁልኝ እኔም እጽፍላችኋለሁ:: በተረፈ ለዓይነ ሥጋ በሰላም ያብቃን::

አክባሪያችሁ

ራሔል አበራ



# ምዕራፍ 5

## የአሰገደች አዲስ ሕይወት

አሰገደች በአለባበስ ተሰውጣለች:: ሲኒማና ቲያትር ማዘውተር ጀምራለች:: አልፎ አልፎ ዮሐንስ ያጅባታል:: ከጓደኞቿ መካከል ገነትና፣ ተስፋዬ ሲቀሩ ከሌሎቹ ጋር ፀጉር ለፀጉር ባናጩ ጠብ ተለያይተዋል:: እነተስፋዬም ቢሆኑ ለዮሐንስ ፍቅርና ውለታ ሲሉ እንጂ ለአሰገደች ከበሬታ ኖሮአቸው እንዳልሆነ ታውቋል::

የራሔል እህት አልማዝ አበራ፣ የአቅም ማነስ ነው እንጂ፣ ዛሬም ለግድያ ነው የምትፈልጋት:: «ይህች ለቃቃሚ፣ ትናንት ፍርፋሪ ትቀላውጥ ነበር:: ዛሬ ደግሞ የሰው ትራፊ ትቃርማለች» በማለት ዘምታባታለች::

የዮሐንስ እህት ዓለሚቱ አፍ አውጥታ ባትናገርም አሰገደችን ትጠላታለች «መሰሪ፣ ቀፋፊ፣ ሾካካ» ትላታለች::

«እውን አሰገደች መጽሐፍ የሙጥኝ የምትለው እውነት ዕውቀትንና ውበትን ፍለጋ ነው? ተሸከማ የምትንቀዋለለውን መጽሐፍ ሁሉ አንብቦ ለመረዳት ብቃቱ አላት?» በሚለው የዓለሚቱ ተረበኛ ጥያቄ ዮሐንስ አይስማማም::

«በመሰረቱ ጥያቄው ራሱ ከቅን አመለካከት የመነጨ ባለመሆኑ መልስ አይገባውም» በማለት ይዘጋዋል::

«መልከ ቀና መውደድ ለዝና ለወሬ፣
የማይጠገቡት ፋንጊትና ጥሬ::»

እያለች አሰገደች ባለችበት ዓለሚቱ ታንጎራጉራለች:: ዮሐንስ ይኽንን ለመሳሰለው የዓለሚቱ ፉገራ ቦታ አይሰጠውም::

አስገደች ከዮሐንስ ጋር ገባ-ወጣ ከማለት አልፋ እቤት ውላ ማደር ጀምራለች:: ወላጆቿም ስለግንኙነታቸው ከማወቅ ባሻገር፣ ግንኙነቱ ካስገኘው በረከት ትንሽ ትንሽ መቋደስ ጀምረዋል:: «የት ነበርሽ?» ከማለትም ተቆጥበዋል::

የዮሐንስ ወላጆች በልጃቸው የግል ሕይወት ውስጥ ጣልቃ የመግባት ፍላጎት ባይኖራቸውም፣ አንዳንድ ጊዜ ጋብቻን አስታከከው በሚሰነዝሩት አስተያየት «ያለብንን የሠርግ (ጥሪ) ዕዳ ዮሐንስን ስንድር እንከፍለዋለን» ይላሉ:: የዮሐንስ ጋብቻ በሀብትም ሆነ በማዕረግ ከወላጆቹ አቻ ከሆነ ቤተሰብ ጋር እንዲሆን የሁሉም የዮሐንስም ጭምር ፍላጎት ነው::

***

ራሔል የጋብቻ ፕሮግራሟን ሰርዛ ፊቷን ወደ ትምህርት ዓለም የመለሰችው ዮሐንስ ቢያፈቅራትም ሊያገባት ዝግጁ እንዳልሆነ ከተረዳች በኋላ ነው:: ራሔል ከሔደች በኋላ የዮሐንስ ውሎ ከማን ጋር እንደሆነ ወለጆቹ መረጃ እንዳላቸው ዮሐንስ ደርሶበታል:: ዮሐንስ ከአስገደች ጋር የመሠረተው ጊዜያዊ ጓደኝነት ጥያቄ ከማስነሳቱ በፊት እንዲቋረጥ መላ እየመታ ነው::

አንድ ቀን ዮሐንስ ፊራ ተባ እያለ «የዘለቄታ ዓላማሽ ምንድነው?» የሚል ጥያቄ ለአስገደች እንደ ዋዛ ወርወር አደረገ::

«ይቅርታ! ጥያቄህ ግልጽ አልሆነልኝም::»

«ሳይንቲስት፣ ደራሲ፣ ያገር መሪ፣ ነጋዴ ወይስ ሌላ ሌላ፣ ምን ለመሆን ትፈልጊያለሽ? አሁንስ ግልጽ ነው?»

«ጥያቄው ግልጽ ነው፣ ብቻ ምን ያደርጋል፣ እኔ ግን ለመሆን የምችለው ነገር የለኝም እንጂ» አለች አቀርቅራ::



«ተይ እንጂ! እንዴት እንደዚህ ትያለሽ? ማንም ከምንም ተነስቶ ምንም በሚሆንባት አገር፣ አንቺ ምንም ለመሆን አልችልም ማለት ያለብሽ አይመስለኝም::»

«በየት ታልፎ፣ የት ተደርሶ፣ ምን ሲኮን? ምስኪን አስገደች.....»

«እሱን እርሺው፣ እኔ ይኸንን ጥያቄ ያነሳሁት ያስምክንያት አይደለም፣ ፍላጎትሽን ንገሪኝ፣ አቅሜ በፈቀደ መጠን መንገዱ ላመቻችልሽ ዝግጁ ነኝ::»

«አንድም ከደግ ተወለድ፣ አሊያም ከደግ ተጠጋ እንደተባለው ሆነልኝ ማለት ነው» አለች በፈገግታ ዮሐንስ እቅፍ ውስጥ እየገባች::

ድንገት ብልጭ ያለው ብሩህ ተስፋ በተራክቦተ ከናፍር ለመለመ:: እሱ የእሷን፣ እሷ የእሱን አልባሳት አወላለቁ:: የመኝታ ክፍሉን በር ለመዝጋት እንኳን ጊዜ ስላልነበራቸው የአልጋ ልብሱን ሰበስ አድርገው አልጋው ውስጥ ገብተው ጠፉ::

***

በዮሐንስ ብርቱ ጥረት አስገደች የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ት/ቤት የማታው ክፍለ ጊዜ ተማሪ ሆናለች:: ጠንክራ እንድትማር ሁሉም ነገር ተመቻችቶላታል:: ዮሐንስ ያስጠናታል፣ አንዳንድ ጊዜ አልጋ ውስጥ ሳይቀር አስተማሪና ተማሪ ይሆናሉ:: ይሁንና የጥናት ጊዜዋን ላለመሻማት በሚል ሰበብ ግንኙነታቸው ላላ ብሏል:: ይህ መላላት ያሳሰባት አስገደች እንደቀልድ እያዋዛች «ጆኒ አንድ ነገር እየላላ ሲመጣ ዝም ካሉት ሊላቀቅ ይችላል፣ አይመስልህም?» ትለዋለች::

«ዐሣብ አይግባሽ፣ አንቺ ያለብሽ በርትተሽ መማር ነው፣ የሚያዛልቅሽ ትምህርቱ ነው» በማለት ያጽናናታል:: አሰገደች በየአጋጣሚው አባባሉን ለወጥወጥ በማድረግ ብትደጋግመውም የዮሐንስ መልስ ሁልጊዜም «አንቺ ያለብሽ በርትተሽ መማር ነው»የሚል ነው::

ዮሐንስ ከግንኙነታቸው ጋር የተያያዘ ውይይት ለመክፈት አለመፈለጉን እንድታውቅበት አይሻም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን ቁጥብነት አሰገደች ባትወደውም ታከብርለታለች::

እሷ ግንኙነታቸው ሳይቋረጥ ተጠናክሮ መቀጠል እንዲችል ለማድረግ መላ እየመታች ነው::

«እራሴን ችዬ ለመኖር ያለኝ ተስፋ ከመቸውም ይልቅ እየለመለመ መጥቷል:: በተቃራኒው ደግሞ ከዮሐንስ ጋር ያለኝ ግንኙነት ላልቷል:: ዮሐንስ የግንኙነታችንን ቋጠሮ እየፈታው ነው ልበል? ለምን?» አለችና ግንባሯን ቋጠር፣ አንገቷን ነቅነቅ ትከሻዋን ጎለም አደረገች::

«ቋጠሮ በቀላሉ የሚፈታው ካልደበነ ነው:: መድበን አለበት:: ይህ ደግሞ የእኔ የሥራ ድርሻ ነው:: ግንኙነታችን የተቋረጠበትን ገመድ ባንድ በኩል ዮሐንስ በሌላ በኩል እኔ ስንስበው ውሉ ይጠብቃል እንጂ አይላላም:: ከጠበቀ ደግሞ አይፈታም::» በማለት አሰገደች አንዴ ገመዱን አንዴ ዮሐንስን በዐሳብ ማየት ጀመረች:: ይኸንኑ ስታወጣና ስታወርድ «ትኩሱ እሬሳ የቆየውን አስነሳ» እንዲሉ፣ አሰገደች አንድ ሰሞን ከነቢል አብዱራዛቅ ጋር ሽርካ የነበረው ጓደኝነት እሷ ባላሰበችው ጊዜና ሁኔታ ተሽረክርኮ በጮርቃ ሕይወቷ ላይ የተወውን ጠባሳ አስታውሳ ተንሰፈሰፈች::



«ወንድን ማመን ቀብሮ ነው፣ እርግጠኛ ነኝ በዚህ አባባል የእርኩስ ወንዶች ከንቱ ድለላ ሰለባ የሆኑ ልጃገረዶች ሁሉ ይስማማሉ» አለች ኮስተር ብላ::

«ሰው ያደርገኛል፣ ያሳልፍልኛል፣ አንድ ቀን ከጓደኞቼ እኩል ያደርገኛል በሚል ተስፋ ክብረ - ንጽሕናዬን በፍቃዴ ያስረከብኩት ነቢል አንድ ጊዜ አታልሎኛል:: ዮሐንስ ደግሞ ሊያታልለኝ አልፈቅድለትም:: ከአንድ ጊዜ በላይ መታለል ደደብነት ነው:: የምን ደደብነት ብቻ አህያነት እንጂ» አለች ከዮሐንስ ብትለይ አዲስና ብትጠበስ እንኳ ለማንም የማትሸት አሰገደች ሆና እንደምትቀር ራሷን በምናቧ እየሳለች::

«በእርግጥ ከዮሐንስ ይልቅ ነቢል አብዱራዛቅ በገንዘብ ሊተመን የማይችለውን ታላቅ ስጦታ ተለግሷል:: በአንፃሩ ከእሱ ወደ እኔ የተላለፈ ችሮታ የለም፣ ኪሣራ እንጂ:: የሰባት ክርስቲያን ልጅ ማተቤን በጥሼ፣ ድንግሌን አስገስሼ ያተረፍኩት ነገር ቢኖር በሽታ ነበር:: ምን በሽታ ብቻ?» አለች አሰገደች ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ «በእምነት ርክሰት፣ በሞራል ድቀት፣ በሥነ ምግባር ብልሹነት ዝንተ ዓለም ራሴን በራሴ እንድከስ ተደርጌአለሁ:: አተርፍ ባይ አጉዳይ:: ባላስታውሰው ይሻለኝ ነበር፣ ያለፈው አለፈ» ብላ ወደ ተነሳችበት ዮሐንስን እስከ ዘለቄታው በእጅ የማድረግ ሕልሟን በቁም ማየት ቀጠለች::

* * *

ወሩ ሰኔ፣ ቀኑ ቅዳሜ የዓመቱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መጠናቀቂያ ዋዜማ ነው:: በፈተናው መቃረብ ሳቢያ የተለመደው የዳንስ ምሽት ፕሮግራማቸው ተሰርዟል:: አሰገደች ቀኑን ሙሉ ደብተርና መጽሐፍ ስታገላብጥ ውላ ደክሟታል::

«ባለፈው ሁለት ተርም ትምህርት ያመጣሁት አማካይ ውጤት ከ80% በላይ ነው:: ከክፍሌም ሁለተኛ ነው የወጣሁት፣ እስከዚህ የሚያሳስበኝ ነገር የለም::» አለችና የያዘችውን ደብተር አጠፈችው::

«ጥናቱንስ እቆምኩ፣ ቀኑ እኝዴት መሽቶ ሌሊቱ እንዴት ይነጋልኛል፣ ዮሐንስ በሌለበት?» ክንዷን ከጠረጴዛው ላይ ተክላ፣ አገጯን በመዳፏ አስደግፋ ተከዘች::

«ሰምን ስልክ ደውዬ <ጆኒ ምን እየሠራህ ነው? እኔ ጥናቱን አገባድጄ አልጋዬ ላይ ገደም ብያለሁ> አልለውም» አለችና የስልኩን እጀታ አንስታ ወደ ጆሮዋ ጥግ አቀረበች:: ገና ሁለት ቁጥሮችን እንዳዞረች መደወሏን አቋርጣ ተመልሳ ወደ ትካዜዋ ሰመጠች:: መንፈሷ ክፉኛ ተቃወሰ::

«እኔ እዚህ ደብተር ሳገላብጥ እሱ አንዷን «ካፕሬቶ» ራቁቷን አልጋው ላይ እንደበቆሎ እሸት እያገላበጠ እንደሆነስ ማን ያውቃል?» በሚል የዮሐንስ ስስት በገነች:: ከሰለች:: የዮሐንስ ከእጇ መውጣትና ማምለጥ እሁን እሁን አላትና እንደመባነን ባለ ስሜት ብድግ ብላ ቆመች::

***

አሰገደች በንግድ ሥራ ትምህርት ዘርፍ ትምህርቷን ጨርሳ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተናን አልፋ ከአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ት/ቤት በማዕረግ ተመርቃ የቢስ ኩባንያ ተቀጣሪ የሆነችው ከመመረቋ ስድስት ወር በፊት ነበር - እድሜ ለዮሐንስ::



የአሰገደችን መመረቅ ምክንያት በማድረግ ዮሐንስ አንድ መለስተኛ ግብዣ ለማዘጋጀትና ስጦታም ሊያበረክትላት ማሰቡን ለተስፋዬ አማከረው::

«የምረቃው ዕለት ያንበሸበሽከን አይበቃም!» አለ ተስፋዬ የዮሐንስና የአሰገደች ከታሰበው በላይ መቀራረብ ያሳደረበትን ስጋት በሚገልጽ ስሜት::

«ሲሆን ሲሆን ሁላችንም - ጓደኞቿ በኅብረት ደግሠን <እንኳን ደስ አለሽ> ማለት በተገባን ነበር» አለ ዮሐንስ::

«በምን እንቀጽ?» አለ ተስፋዬ ኮስተር ብሎ::

አሰገደችና ዮሐንስ በየበኩላቸው የጀመሩት የደፈጣ ቤት ሥራ ቅድመ ዝግጅት መነሻ፣ መገስገሻና መድረሻ በድል እስኪጠናቀቅ

«ብልህ እንደ እባብ
የዋህ እንደ ርግብ» ሆነው ቆዩ::

<u>ካፕሬቶ</u>:- በአስብና በምጽዋ መንገድ ላይ በታወቁ ምግብ ቤቶች የሚዘጋጅ ተበልቶ የማይጠገብ፣ ጣት የሚያስቆረጥም የፍየልና የበግ ግልገል ጥብስ ነው:: የቪላ ቬርዴና ቪላ ደናፖሊ ደንበኞች የሆኑ አንዳንድ ጣሊያናውያን የሚያስደንሷቸውን ቆነጃጅት ካፕሬቶ እያሉ ያቆላምጧቸዋል::

***

«ፈተና እንደብቸኛና እውነተኛ የዕውቀትና የተሳለ አእምሮ መለኪያ ተደርጎ መወሰድ የለበትም:: ከዓለም ስመ-ጥር መሪዎች አንዱ የነበሩት እንግሊዛዊ ሰር ዊንስተን ቸርችል ያገሩቸውን የጦር አካዳሚ መግቢያ ፈተና ሁለት ጊዜ ወስደው ማለፍ ተስኖአቸው «ሰነፍ» ተብለው እንደነበር ታውቃላችሁ» አለ ዮሐንስ እነተስፋዬ አሰገደች ያስመዘገበችውን ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ሲያብጠለጥሉ ሰምቷቸው::

«ዮሐንስ አሰገደችን ለውድድር ባሕር ማዶ ባታሻግራት ደስ ይለኛል፣ ምናለ! ከአቅሟ በላይ መሸከም የማትችለውን ትልቅነት ባትጭንባት.....::»

«ተስፋዬ ላቋርጥህ፣ አሰገደች የኢትዮጵያ ቸርችል የማትሆንበት ምክንያት የለም»፣ አለ ዮሐንስ ከመቀመጫው በከፊል ብድግ ብሎ::

«እንቧጮ አድባር የሚሆንበት አገር ውስጥ አይደለንም::»

«ተው ባክህ የጊዜ ጉዳይ ነው፣ የማይለወጥ ነገር የለም::»

«እዚህ ላይ ወራጅ አለ፣ ዮሐንስ ይኸንን የተጋነነ አመለካከት አሰገደች ራሷም እንኳ የምትቀበል አይመስለኝም»

«ካልከስ ንትርካችን ሌላ የነገር ጉጥ ሳያወጣ፣ ላለመስማማት ተስማምተን እዚህ ላይ ልናቆመው እንችላለን» አለ ዮሐንስ በታከተ ስሜት::

«ስለ አሰገደች ከዚህ በላይ መነጋገር ጊዜንና ውይይትን ዋጋ ማሳጣት ነው:: እንዳልከውም እዚህ ላይ ማቆሙ ይመረጣል» አሰና ተስፋዬ የዮሐንስን መልስ ሳይጠብቅ ከሳሎን ወደ በረንዳ ወጣ::

ዮሐንስ የጓደኞቹን አፍ በመፍራት ግብዣውን ትቶ አሰገደችን ኦሜጋ የእጅ ሰዓት ገዝቶ ሸለማት::



# ምዕራፍ 6

## የዮሐንስ - ስብእና

ዮሐንስ ፈረንጆች «የብር ማንኪያ ባፉ ይዞ የተወለደ» እንደሚሉት ዕድለኛ ልጅ ነው:: ቢጠሩት ወይ የማይል ቤተሰብ አባል ነው:: የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአዲስ አበባው ዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ጨርሶ ከዩንቨርስቲ ኮሌጅ በኢኮኖሚክስና በሕዝብ አስተዳደር በማዕረግ የተመረቀ ነው:: ዮሐንስ ሲናገር ረጋ፣ ሲሔድም ረጋ፣ ስለሚል የቤተሰብ ስሙ «ደበሽ» ነው:: ሳቅና ጨዋታ ይወዳል:: ስፖርት በተለይም የጠረጴዛ ቴኒስ ያዘወትራል:: ቅጽል ስሙ «ቄንጦ» ነው::

ስልክክ ያለው የቀይ ዳማ መልኩ ዘለግ ካለ ቁመናው ጋር ተጋግዘው ዓይነ - ግቡ አድርገውታል:: ዘወትር ሽክ ያለው አለባበሱ «ሙሽራው» አሰኝቶታል:: ቁልምጫውን እሱም ቢሆን በትህትና ይቀበለዋል::

ዮሐንስ ቸር ነው:: አንዳንድ ጊዜ ቸርነቱን «አበዛሽው» የሚሉት አሉ:: እሱ ግን ይህንን አስተያየት አይቀበልም::

«መቸርን ባህል ካደረገ ቤተሰብ ተወልጄ ንፉግና ቆጥቋጣ ልሆን አልችልም:: በቸርነትና በአባካኝነት መካከል የተራራና የሜዳ ያህል ልዩነት አለ:: ቸርነት ለእኔ ታላቅ መንፈሳዊ እሴት - ኢንቨስትሜንት ነው:: በአንፃሩ ብኩንነት፣ ማንዘራሽነት ዋልጌነት ነው» በማለት ይከራከራል::

«ዮሐንስ ሙት አንተ□ኮ! ዮሐንስ ሳይሆን አጎናፍር መባል ነበረብህ፣ ስምህ ከባሕሪህ ጋር ኅብር ይሆን ዘንድ» አለ ተስፋዬ ስለ አጎቱ አቶ አጎናፍር ስም ትርጉም የሰማውን በማስታወስ::

በተለመደ ርጋታው «የዚህን ቃል ትርጉም ባውቅ ደስ ይለኛል» አለ ዮሐንስ በተስፋዬ አስተያየት እየተደመመ::

ተስፋዬ የቃሉን ትርጉም አስታውሶ ለመናገር «እ - እ - እ- » በማለት ሲጀምር፣ ዮሐንስ አቋረጠውና «ተስፍሽ አትቸገር፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ያውልህ በእሱ ተጠቀም» አለው፣ በጣቱ ወደ መጽሐፍ መደርደሪያው እያመለከተ:: ተስፋዬ በርከክ ብሎ መጽሐፉን ፈለግ ፈለግ በማድረግ አወጣና ለአንድ ደቂቃ ያህል ቃሉን ፈለገ:: እንዲህም ሲል ትርጉሙን አነበበ::

«**አጎናፈረ** - እንዳፈር፣ እንደራስ ፀጉር አብዝቶ በላይ በላዩ አብዝቶ ሰጠ:: አለልክ ቸረ፣ ለገሠ::

**አጎናፍር** -የሰው ስም፣ ሀብታም ልጅ፣ ቸር፣ ዕድሉ አጎናፍር፣ እንደዝማ የሆነ - ያቶ አገሌ ቤት አጎናፍር ነው እንዲሉ» የሚለውን ተስፋዬ አንብቦ ሲጨርስ፣

«ተስፉ ሙት እንደ ዛሬ ተሳክቶልህ አያውቅም» አለ ዮሐንስ በአድናቆት::

«አንተ አምልጦሃል ከልጆችህ የአንደኛው ስም አጎናፍር ሊሆን ይችላል፣ እናቱ የምትስማማ ከሆነ» አለ ተስፋዬ አስገደችን በሹፈት መልከት ብሎ::

ዮሐንስ ከተመረቀ በኋላ ሥራ የጀመረው በኢትዮጵያ አየር መንገድ መሥሪያ ቤት ነው:: በአየር መንገድ የሦስት ዓመት ቆይታው ባገኘው ልምድና ከወላጆቹ በተለገሰው ጎጆ መውጫ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ ቤትና ቁሳቁስ ተደራጅቷል::

በኮሚሽን ኤጀንትነት የጀመረውን የግል ሥራ ወደ አስመጪና ላኪነት ኩባንያ ለማሳደግ ቅድመ ዝግጅቱን



አጠናቋል:: ዮሐንስ ያለበቂ ጥናት የሚያከናውነው ሥራ የለውም:: ጥንቁቅ ነው:: ጥራት ባለው ሥራ ያምናል::

«ዮሐንስ በአጭር ጊዜ ቀጭን ጌታ ለመሆን ቆርጦ ተነስቷል» አለ ተስፋዬ ሥላቅኛውን አንድ ቀን ስለሥራ ጎደኛ ሞች በብርጭቆ ዙሪያ ተኮልኩለው ሲጫወቱ::

«የአንድ ሥራ ቁምነገር ገንዘብ ማስገኘቱ ብቻ አይደለም» አለ ዮሐንስ አቋሙን ግልጽ ለማድረግ::

«በኢኮኖሚክስ ጠበል እስቲ በል አጥምቀን» አለ ተስፋዬ አግበውን::

«ትልቁ ቁምነገር ዛሬ የተገኘችው ሳንቲም ነገ ሌላ አዲስ ሣንቲም ወልዳ አንድታድር ከማድረጉ ላይ ነው:: ይህን ለማደረግ የሚያስችለው ዕውቀትና ተመክሮም ከአንዱ ወደሌላ መተላለፍ መቻል አለበት:: እያንዳንዱ ባለሙያ የዜግነት ግዴታውን በብቃትና በንቃት የመወጣት ኃላፊነት አለበት:: የአገርና የወገን ጥቅምና ፍላጎት መሣሪያ ያልሆነ ዕውቀት የጋን መብራት ነው» አለ ዮሐንስ::

«ዮሐንስ! ይህ ቁምነገራም አስተያየትህ ትክክል የሚሆነው ተገቢ የሥራ ሁኔታ የሚፈጥር የፖለቲካ ሥርዓት በሰፈነበት አገር ነው:: ስለዚህ አስተያየትህን ባልጋራ አይደንቅህም» አለ ተስፋዬ ዘና ብሎ::

ስለ አንድ ነገር በሚያስረዳበት ጊዜ ታዳሚዎቹ እንደ ክፍል ውስጥ ተማሪ በተመስጦ እንዲያዳምጡት የሚፈልገው ዮሐንስ በተስፋዬ ጣልቃ መግባት ጎሸት አለ::

«ተስፋዬ የችሎት እስጥ አገባ አይደለም የያዝነው» ለሚለው ግሳፄ ተስፋዬ ሳይበገር «አንተ□ከ ዝም ብለው ካዳመጠህ ስትናገር ውለህ ታድራለህ» አለ ተስፋዬ።

«በእኔ እምነት» አለ ዮሐንስ «ሙያዊ ግዴታን የመወጣት ኃላፊነት ከሙያዊ ሥነ ምግባሩ ውጭ ሲታሰብ አይችልም። ይኸንን የምልበት ምክንያት አለኝ፡ በምሳሌ ላስረዳ፣ ጎረቤቱ ጠጅ ቤት ከፍቶ ለብርሌ ወረፋ ተገብቶ መጠጣቱን በማየት አንድ የኢኮኖሚክስ ምሩቅ ባለሙያ ያንኑ መሰል ጠጅ ቤት እዚያው መንደር ውስጥ ከፍቶ ገበያውን በመሻማት ቢኮምር፣ ንግድ ተሠራ ማለት ይቻል ይሆናል። ነገር ግን አንድ ነገር መታመን አለበት። ይኸውም፣ በዚህ ሰው ትምህርት ላይ አገሪቱ ያፈሰሰችው ገንዘብ፣ ዕውቀትና ጉልበት በከንቱ የተከሰረ መሆኑን፣ በትምህርት ቤት ያሳለፈው ጊዜ በከንቱ የባከነ መሆኑን ክዶ መሟገት አይቻልም።»

«የተከበራችሁ ሲቃነ ሲቃውንት» አለ ተስፋዬ በሹፈት «ከዚህ በላይ እንድትጠቀጥቁኝ ዕድል አልሰጣችሁም። ጉንጭ - አልፋ ንትርካችሁን ተንግዲህ የምትቀጥሉ ከሆነ ስጋበዛችሁኝ መጠጥ አመስግኜ መሰናበቴ ነው።»

«ከኖሩ ልጥቅ፣ ከሔዱ ምንጥቅ» በሚለው የአስገደች መልስ እየተገረመ ተስፋዬ ብድግ ሲል ዮሐንስ «እዚህ ላይ ይቁም» በማለት መልሶ አስቀመጠው።

* * *

አስገደች ዘወትር ረቡዕና ቅዳሜ ሌሊቱን የምታሳልፈው ከዮሐንስ ጋር ነው። በእነዚህ ዕለታት በጊዜ ታጥባ፣ ታጥና ፀጉር ሠሪ ቤት ብላ ከቤት ትወጣለች። የፀጉር ሥራው እንዳበቃ ለዮሐንስ ስልክ ትደውልለትና መጥቶ ይወስዳታል። ይህ ፕሮግራም በተፈጥሮአዊ ግዴታ (የወር አበባ ጊዜ) ወይም ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር አይተጓጎልም።



አዲስ ትያትር ወይም ፊልም ካለ በመኪና ውስጥ መቀያቸውን ከስክሰው ወደዚያው ያመራሉ። ከሌለ ራት በጊዜ በልተው ለናይት ክለብ ጭፈራ ይዘጋጃሉ። ቪላ ዲ-ናፖሊ፣ ቪላ ቬርዴና ራስ ሆቴል የእነ ዮሐንስ ምርጫ ናቸው። ዮሐንስ ወደ ናይት ክለብ ሲያስብ የጨዋ ልጅነቱን፣ ጭምትነቱንና ርጋታውን ከቤት ትቶ ነው የሚወጣው። የየምሽቱን የናይት ክለብ ቆይታ የተፈቀደ «የትንሽ ዕብደት» ጊዜ ይለዋል።

በለስላሳው ቧልስ የሚጀመረው መውረግረግ ሩምባ፣ ሳምባ፣ ታንጎ፣ ቻቻ እያለ ወደ ቡጊ ቡጊ፣ ሮክ ኤንድ ሮል ይሸጋገራል።

ዳንሰኞችን ያሰውድ በግድ ተቃቅፈው እንዲሽከረከሩ የሚያስገድደውን ቧልስን የአካል ማፍታቻ፣ የስሜት ማማሟቂያ ይሉታል። አካል ለአካል መፋተጉ፣ መተሻሸቱ፣ የሽቶው እወዳ፣ የመጠጡ ግፊት ሲታከልበት ይደራሉ። ስብ ያሰው ስሜት ወደ ግለት ይለወጣል። ዳንሰኛው ይቁነጠነጣል። እዚህ ደረጃ ሲደረስ ዳንሱ ይቋረጣል። ከአዳራሽ ይወጣል። ከአጭር ጊዜ ማረፊያ ክፍል ቆይታ በኋላ እንደገና ወደ አዳራሽ ይመጣል። ይኸንን ነው ዮሐንስ «የትንሽ ዕብደት» ጊዜ የሚለው።

ዮሐንስ ዘፈን ይወድዳል፣ ዳንስም ነፍሱ ነው። «ዳንስ ጠግቤና ረክቼ ከዳንስ መድረክ የተላቀቅሁበት ጊዜ የለም። ድካም ሲጫነኝ፣ ከዚያ በላይ ቆይቶ ለመደነስ አቅም ሲያንሰኝ የዳንሱን

ወለል እስናበታለሁ:: ዘፈንና ዳንስ በተጨመረ መጠን ይበልጡን ያስኘኛል:: እንደ ምግብና መጠጥ ጭማሪው ቁንጣን አያስይዝም::» የሚለውን የዮሐንስ አስተያየት አሰገደች ታደንቃለች:: አሰገደች ዮሐንስ የሚወድደውን ሁሉ መውደድን እየተለማመደች ነው::

እየደነሰ ዳንስ የሚራበው ዮሐንስ ከናይት ክለብ የሚወጣው፣ ሙዚቀኞቹ መሣሪያዎቻቸውን መሰባሰብ ሲጀምሩ ነው:: ከዚያ በኋላ ከጓደኛው ጋር ወደ ቤቱ ይመርሻል:: የተዛባባቸውን የሌሊትና ቀን ፍርቅርቅ ለማስተካከል ጧ ብለው ይተኛሉ:: እንደ ምንም ለቁርስ ይነሳሉ:: ብርቱ ጉዳይ ከሌላቸው ተመልሰው ይተኛሉ:: ፍቅራቸው ዮሐንስ ከጠበቀው በላይ እየጠና ሔዷል:: «አሰገደች ከ የዳንስ ወለል ከከብ፣ የአልጋ ንግሥት ብትባል አይበዛባትም» የሚለውን የዮሐንስን አድናቆት ተስፋዬ አይቀበልም:: አለመቀበል ብቻ አይደለም «ዮሐንስ በፈጠረህ ፊት አትስጣት:: አካሔድህ አላማረኝም:: ከወላጆችህ እንዳትቆራረጥ አስብበት» በማለት የመገሰጽ ያህል ይመክረዋል:: ዮሐንስ ግን በአሰገደች ሁለንተና መማረኩን መደበቅ እያቃተው ነው::

ወንድሟን ከአሰገደች ለማላቀቅ ዓለሚቱ የተቻላትን ሁሉ እየሞከረች ነው:: ሙከራው ያተኮረው ዮሐንስ ሌላ አማራጭ እንዲኖረው በማድረግ ነው::

«ለውጥ የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም ነው» ትለዋለች ዓለሚቱ ወንድሟ ከአንድ ሴት ጋር መሟዘዙ ተገቢ አለመሆኑን ለማስረዳት::



አባባሉን እየለዋወጠች እህቱ ለማስተላለፍ የምትሞክረውን መልእክት ዮሐንስ ገሸሽ ስለሚያደርግባት ዓለሚቱ አታኮርፍም::

አንድ ሌላ ቀን ዓለሚቱና ተስፋዬ የፆታ ጓደኝነትን በተመለከተ ሲጨዋወቱ፣ «ወንድ ልጅ ባቡር ይመስል ዘላለም በአንድ ሐዲድ ላይ ሲሔድ መኖር የለበትም» በማለት ተስፋዬ የሰጠውን አስተያየት «አንተና እህቴ□ኮ የፆታ ጓደኝነትን ወደ ሸቀጥነት ዝቅ እያደረጋችሁት መሆናችሁን የተረዳችሁት አይመስለኝም» በማለት ጠቅ አደረጋቸው::

«ዮሐንስ የጭቃ ጅራፉን አመጣ፣ ለዛሬ በዚሁ ይብቃን፣ ካስፈለገም ሌላ ጊዜ እንመለስበታለን» በሚለው የዓለሚቱ አስተያየት ተስማምተው የጭውውታቸውን ርዕስ ለወጡ::

ዮሐንስ አሰገደችን የያዛት ለመሸጋገሪያነት ነበር:: ከዚህ በኋላ ጎጆ በሚያስወጣት ድጎማ አግባብቶ ሊያገላት አቅዶ ነበር:: አሰገደች በበኩሏ ዮሐንስ ከእጇ እንዳይወጣ አቅሟ የቻለውን ያህል አጥብቃ ይዛዋለች:: አንዱ የሌላውን (እሱ የእሷን፣ እሷም የእሱን) ድብቅ አጀንዳ አያውቁም::

# ምዕራፍ 7

## ሹመት ያዳብር

❖

«ሹመት ያዳብር» ለማሏት የመጣው ወዳጅ ዘመድ የተስፋዬ አሥራትን ቤት ሞልቶ ግቢው ጭምር ሰው በሰው እየሆነ ነው:: የማስተናገዱን ሥራ ወላጆቹ፣ እህትና ወንድሞቹ ሌላ ሰው ጣልቃ ሳያስገቡ ቀጥ አድርገው ይዘውታል::

የደስ ደስ የመጣው መጠጥ ከላይ ከላዩ ቢጠጣለትም አንዱን ክፍል የመጠጥ መጋዘን አስመስሎታል:: ሬድ ሌብል፣ ብላክ ሌብል፣ ሺቫስ ውስኪ፣ ናፖሊዮን፣ ሬሚ ማርቲን ኮኛክ፣ ቢፍ - ኢተርና ድራይ ጂን እንደዚሁም ሻምፓኝ በደርዘን በደርዘን አንዱ በሌላው ላይ ተከምሯል:: አንዳንድ የኤምባሲ ሰዎች ከውስኪ ጋር ምርጥ ምርጥ የወይን ጠጅ በደርዘን አምጥተዋል::

በተስፋዬ ረዳት ሚኒስትር ሆኖ መሾም - የማስታወቂያ ሚኒስትሩን ያላመሰገነ ሠራተኛ አልነበረም::

ተስፋዬ አንቱ የተባለ ጋዜጠኛ ነው:: በየጋዜጠቹ በተለያየ ደረጃ ተመድቦ አገልግሏል:: በምሥጉን ባለሙያነቱ ተመርጦ ወደ አሜሪካ ተልኮ ከኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ በጋዜጠኝነት የመጀመሪያ ድግሪውን አግኝቷል::

ተስፋዬ አባቱ የቅዱስ ራጉኤል ደብተራ እንደነበሩ፣ እርሱም በዚያው ደብር በዲቁና ማገልገሉን የሚያውቁ ጓደኞቹ «ደብተራ» በሚል የቅፅል ስም ይጠሩታል - ብልህ አዋቂ የቀለም ሰው ለማለት::



ተስፋዬ ስለ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ካለው ፍቅር የተነሳ እስላሙንም፣ ጴንጤውንም፣ ካቶሊኩንም፣ ሃይማኖት የለሹንም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ መስበክ ይከጅላል::

ከቅድስተ ሥላሴ ካቴድራል ዘማሪ ደናግል አንዷ የነበረችው አስገደች ወዳጁ ተስፋዬ ጊዜ፣ ቦታና ሰው ሳይመርጥ የሚነዛውን ስብከት «የተራራው ስብከት!» በማለት ታሾፍበታለች:: ሁለቱ ተስፋዬና አስገደች የትም ይሁን የትም ሳይቀር ስለሃይማኖት ያነሳሉ፣ ይተቻቸሉ፣ ይከራከራሉ::

«አንተ ዲቁናህን፣ አንቺ ደግሞ ዘማሪነትሽን አፍስሳችሁ - ክዳችሁ ከቤተ ክርስቲያን ፈርጥጣችሁ ከወጣችሁ በኋላ አሁን እንደገና እዚህ እኛን በጉንጭ አልፋ ክርክር ታታክቱናላችሁ» በማለት ዮሐንስ በየጊዜው የሚሰነዝረውን ትችት ተስፋዬ «አስማወቅህ በጀህ» ወይም «አንተ ምን ታደርግ ይኸን የተንሸዋረረ ትችት ከአንተ አንደበት እንዲወጣ ቃሉን ከንፈርህ ላይ የሚያስቀምጥልህ ኃይል ማን እንደሆነ አውቄዋለሁ:: ስነገሩማ ባይሆንልህ ነው እንጂ አንተስ እንዳቅምህ ዘማሪ አልነበርክ!» በማለት ይነድፈዋል::

ማስታወቂያ ሚኒስቴር አካባቢ ዝክር - አከል እንኳ መሰባሰቢያ ካለ የኤምባሲ ሰዎች ይገኛሉ:: አንዳንድ ጊዜ ሳይጋበዙም ነው የሚመጡት - አነፍንፈው:: እንዴትና ለምን እንደሚመጡ አይታወቅም:: ሹማምንቱም ሆኑ ተራ ሠራተኞቹ «ለምን መጣችሁ፣ ማን ጠራችሁ?» ብለው ሲጠይቋቸው አይሰማም:: ይግረማችሁ ብለው አንዳንድ ፕሬስ አታሼዎች ከተጋባዡ በፊት ቀድመው የሚመጡበት ጊዜ አለ::

የተስፋዬን ቤት «ሹመት ያዳብር» መስተንግዶ በስጦታም በጨዋታም ያደመቁት እነርሱ መሆናቸውን የታዘበው የኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ መዝገቡ አብተው «አንዳንድ የፕሬስ አታሼዎች ሳይነግሩህ፣ ሳያስፈቅዱህ በድንገት ውስኪ ወይም ያገራቸውን ወይንጠጅ ፀደርዘን በደርዘን ይዘው ከተፍ ይሉብሃል፣ አጋጥሞህ አያውቅም?» የሚለው ትዝብት ትዝታውን የጫረበት የቴሌቪዥኑ ጌታቸው ክፍለ ማርያም «የቆየ ወዳጅነትና ትውውቅ ያላቸው ፕሬስ አታሼዎች ይህንን ቢያደርጉ ላያስደንቅ ይችላል:: እኔን የሚገርመኝ ስምና አድራሻህን እንኳ በውል ሳያውቁ የመጠጥ ወይም ሌላ ስጦታ የሚያጎርፉት ናቸው» አለ::

የሄራልዱ ፀጋዬ ታፈሰ ቀበል አድርጎ «ቁምነገሩ የእነርሱን ጥቅምና ፍላጎት ለማስተናገድ፣ ወይም መሣሪያ ለመሆን ያለህ ብቁነት እንጂ ትውውቅህ ወይም የደረጀ ወዳጅነትህ እንዳልሆነ ግልጽ ነው» በማለት ድርጊቱ በሌላም አካባቢ የተለመደ መሆኑን አስረዳቸው::

«ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲሬክተሮች አንዱ በሆነ አጋጣሚ ያጫወተኝን ልንገራችሁ:: መጠጥ፣ ዕቃ፣ አልፎ አልፎም በየምክንያቱ ዶላር ጭምር ያስታቅፋታል:: በመኖሪያ ቤታቸው <ለመጠጥ for a drink ለምድጃ ዳር ወግ -for a fire side chat> እያሉ የየኤምባሲው ወዳጆቹ ፋታ በሚነሳ ግንኙነት (ግብግቦ) ይቀስፉታል::

«ወጉ ከወሲብ ጅምሮ ከሆነ፣ ስለሚጎነጩት ወይን ጠጅ ጣዕም፣ ስለአገራቸው የወይን ተክል፣ የአየር ጠባይ፣ ስለአገራቸው የቢራ፣ የኮኛክ፣ የአረቄ ፋብሪካ ብዛትና ዓይነት ይነገራል:: ወጉ ሞቅ ደመቅ የሚለው ከማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ



ጉዳዮች ወደ ፖለቲካና ሥነ መንግሥት ሲሸጋገር ነው:: በመንግሥት ጉዳዮች አወሳሰን የሕዝብ ተሳትፎ ምን ይመስላል? ወደፊትስ ምን መምሰል አለበት? የመንግሥት አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል፣ የምሑሩ ሚና፣ የተማሪው እንቅስቃሴ፣ መለዮ ለባሹ ለንጉሡ ያለው ታማኝነት፣ የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ያለገደብ ይሰለቃሉ:: ብርጭቆዎችና መለኪያዎች መቸ ጎድለው መቸ እንደተሞሉ አይታወቅም:: ይጠጣል፣ ይወራል:: መቸ ይህ ብቻ......» ብሎ ፀጋዬ አካባቢውን ቃኘት አድርጎ ይኸንኑ የጓደኛውን ገጠመኝ ሲቀጥል ሲል ተስፋዬ መጥቶ «ጎበዝ እንዴት ነው» ብሎ ተደባለቃቸው::

«ጨዋታው የደራ ይመስላል! «መቸም ጳውሎስ ያሰበት የሚያስቅ፣ ካልሆነም፣ የሚመስጥ ወግ አይገድም» አለ የጳውሎስን ትከሻ በአንድ እጁ ቸብ አድርጎ::

«አይምሰልህ እስካሁን ፀጋዬ ነው አፋችንን ያስከፈተን - የጓደኛውን ገጠመኝ አንስቶ ሲነግረን ነበር:: ነገሩ በተዘዋዋሪም ቢሆን ስለሚመለከትህ አንተ ባትሰማው ይመረጣል:: ጨዋታው ስለ ወዳጆቻችን እናባ - መስጠት ነው:: ሌላ ቀን ትሰማዋለህ::» አለና ጳውሎስ መለኪያውን ብድግ አደረገ::

«እነማናቸው አባ - መስጠቶች» የተስፋዬ የገራሞት ጥያቄ ነበር:: ጳውሎስ ከፊት ለፊት ወደ ተቀመጡት ፕሬስ አታቼዎችና የሮይተር፣ የኤ ኤፍ ፒና የታንጁግ ዜና ወኪሎች አገጩን አሾሎ ጠቆመው::

«ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ፣ እንደሚባለው ካልሆነ በስተቀር ለውን ለምን ቸር ሆነ ብለን የምንተችበት ምክንያተ አይታይም» አለ የራዲዮው ሞገስ ታደሰ::

«በሉ እናንተ ወጋችሁን ቀጥሉ፣ ታዲያ እየጠጣችሁ» ብሎ ተስፋዬ ተለያቸው::

ፀጋዬ ያቋረጠውን ወሬ ለመጀመር ጉሮሮውን ሲጠራርግ «ኧረ ፍጆታ» አለ መዝገቡ:: በመዝገቡ የፍጆታ ጥያቄ ሁሉም ስለተስማሙ «አንዳንዶቹ ዲፕሎማቶች ስለሌሎች ኤምባሲዎች እንቅስቃሴ ያለህን መረጃ ሳይጠይቁህ እንድትናዘዝ የማድረግ አዚም እንዳላቸው ታውቃላችሁ? ባጭሩ ቅድም ፀጋዬ ካጫወተን ገጠመኝ እንደዚሁም በራሳችን ላይ ከደረሰው መታለል ብዙዎቻችን ሳናውቀው የየኤምባሲው ሰላዮች ሆነናል» አለ መዝገቡ::

«መዝገቡ የምትጠቀምባቸውን ቃላት ብትመርጥ ይሻላል፣ ተስፋዬ እንዳይሰማህ» አለ ዮሐንስ::

«መልካም የጆኒን ምክር ተቀብያለሁ፣ እንግዲያው ስለራሴ ገጠመኝ በትንሹ ልንገራችሁ የምትታገሱኝ ከሆነ?» አለ መዝገቡ::

«ምንነካችሁ ፀጋዬ ጅምሩን ሳይጨርስ» አለ ጳውሎስ::

«በኋላ ይጨርሳል፣ ለጊዜው መዝገቡ ይቀጥል» አለ ሞገስ::

ሞገስ ባቀረበው ሃሳብ ሌሎቹም ስለተስመሙ መዝገቡ ቀጠለ::

«አንድ ዘመን ከፕሬስ አታቼዎች ጋር እፍ ብዬ ነበር:: ይኸንን በሥራቸው አጋጣሚ የተረዱ አንድ የፀጥታና ደህንነት የአፃፋ ስለላ (Counter Intelligence) መ/ቤት ኃላፊ <አንተ ሰው ከእነዚህ የኤምባሲ ሰዎች ጋር ያለህ ግንኙነት ጤናማ አልመሰለንም:: አንተ ጨዋታ ላይ ስምትሰጠው አስተያየትና ስምታቀርብላቸው መረጃ በስጦታ መልክ ዋጋውን እየከፈሉህ



ናቸው:: ይህን አንተ አላስተዋልከው ይሆናል:: ከእንግዲህ ግን ቢበቃህ ይሻላል> በማለት የማስጠንቀቂያ ምክራቸውን ሲሰጡኝ የደነገጥኩትን መደንገጥ ልነግራችሁ አልችልም::»

«ምን አልካቸው» የዮሐንስ ጥያቄ ነበር::

«ደሞ ምን እላለሁ! ለራሴ የጨው አምድ ሆኜ»

ፀጋዬ «አንድ ጊዜ፣ አንድ ጊዜ» አለና እንዲያዳምጡት ተማጸነ «ባይገርማችሁ ታሪኩን ያወጋኋችሁ ጓደኛዬ ከዚያን ጊዜ ወዲህ የኤምባሲ ሰዎችን አይደለም፣ ግሪክና አርመን ነጋዴ እንኳ መንገድ ላይ ሲያይ ይበረግጋል:: ይህም የሆነው እርሱም እንደ መዝገቡ ከፀጥታና ደህንነት ሰዎች ምሱን ከተቀበለ በኋላ ነው:: - አባብ ያየ በልጥ በረየ እንዲሉ» በማለት ፈገግ አሰኛቸው::

«በቃ! በቃ! በእናታችሁ ሌላ ወሬ» አለች ዓለሚቱ::

«ቸከሽ?» አለ ዮሐንስ::

«መቸክ ብቻ? እጅ እጅ ነው ያለኝ::»

«አዎ የተነሳው ጉዳይ አንቺን ስለማይመለከት ሊገለማሽ ይችላል:: ለእኛ ግን ራሳችንን ወደ ውስጥ ያየንበት አጋጣሚ ስለሆነ ቁምነገር አለው» አለ ፀጋዬ ራስን በመታዘብ::

«እናንተ□ኮ ይህን ሀራም - ኢሲቢስ! ነጂስ! ስትቀምሱ እንኳን መረጃ ሌላም ትሸጣላችሁ:: ምናለ ባትጠጡ? ወይም በልክ ብትጠጡ:: አዳሜ በየኤምባሲው እየዞረ ምናምንቴውን ከሥር ወትፎ ባፍንጫው ጠብ እስኪል ይጋትና መጨረሻ ላይ ምን ተናግሬ ይሆን? ማን ሰምቶኝ ይሆን? ብሎ መጨነቅ......» አለ የዓለ ዓለሙ ኢብራሒም ኑር::

«ኢብራሒም በዚህ ባልተገራና ባለተሞረደ ቃል ብዙም ስለማታውቀው ጉዳይ ባትዘባርቅ መልካም ነው::» የሚለውን

የመዝሙን ተግሳጽ «እም! እራ.ጋቢ ወደ ውጭ» በማለት ዮሐንስ ኢብራሒምን ዝም አሰኘው።

«ለዛሬው እዚህ ላይ ቢበቃን የቀረን ነገር ካለ ነገ እንመለስበታለን» አለ ሞገስ።

«አዝማሪና ጋዜጠኛ ድኻሥ...» ኢብራሒም የጀመረውን አስተያየት አቋርጦ ፀጋዬ «ኢብራሒም አትዘባርቅ ተብለህ ነበር፣ ከዚህ ጠንከር ባለ ቃል እንድትነገር ትፈልጋለህ?» በማለት ሞገስ እንደገና አፈጠጠበት።

«የነገ ሰው ይበለን» ተባብለው ተስፋዬን ተሰናብተው ወጡ።

***

ለለ ተስፋዬ ሹመት ጓደኞቹ በራስ ሆቴል ያሰናዱት የራትና የዳንስ ምሽት ላይ መንፈቀ ሌሊቱ አለፍ እንዳለ አሰገደችና ዮሐንስ በጊዜ ወደያዙት መኝታ ክፍል ደረስ በለው ተመለሱ።

አንዳንዶቹ ጥንዶች መኝታ ቤታቸውን የኀበኙት ገና በጊዜ ራት እንደተበላ ነበር። በየእንዳንዱ ጠርሙስ የቡሽ (ኮርኬጅ) ሆቴሉ አሥር አሥር ብር እያስከፈለበት ቢሆንም መጠጡ በሙሉ በገፍ የመጣው ከተስፋዬ ቤት ነው።

ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት በኋላ ያልሰከረ ሰው ቢኖር አሳላፊዎቹ ብቻ ነበሩ። ከተስፋዬ ቤተሰብ አዛውንቶቹ በጊዜ ተሸኝተዋል።

የሙዚቃ መሣሪያ በየፊናው ይጮኻል፣ ዘፋኙ የመሣሪያውን ጩኸት አልፎ ዜማውንና ግጥሞቹን ለማሰማት



ከልክ በላይ ይጮኻል። መጠጥ - ጩኸት - የተቃራኒ ፆታ መተሻሸት፣ እንዲያም ሲል ጉያ ለጉያ መደባበስ፣ ሁሉንም ሰው ስሜቱን ሊቆጣጠር ወደ ማይችልበት ደረጃ - የፈንጠዝያ ሰማየ ሰማያት አኀነው።

አንዳንድ ኮረዶችና ጎረምሶች ከማን ጋር፣ ስንት ጊዜ የትኛው መኝታ ክፍል፣ ደርሰው እንደተመለሱ እንኳ ማስታወስ አልቻሉም።

አንዳንዶቹ ጥንዶች ለአጭር ጊዜ ጉድጉድ ወደ ክፍል ደረስ ብለው ለመመለስ ሔደው በዚያው እንቅልፍ ጥሏቸው አድረው ጧት ሲነቁ፣

«እንዴ አንተን ደግሞ እዚህ ምን አመጣህ»

«እኔ እንጃ! አንቺስ እንዴት መጣሽ» በመባባል የእፍረት ፈገግታ ተለዋውጠው በየፊናቸው ሹልክ ሹልክ ያሉም ነበሩ።

አሰገደችና ዮሐንስም ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠፋፍተው አድረው ንጋት ላይ ተገናኙ።

«የት ነበርሽ?»

«እኔማ ሲደክመኝ ወደ መኝታ ክፍላችን ሔጄ ጋደም እንዳልኩ ዕንቅልፍ ይዞኝ ጥርግ አለ።»

«ለመሆኑ አንተ የት ነበርክ?»

«እኔ ይቅርታ አድርጊልኝ የት እንደነበርኩም አላስታውሰውም። ካንቺ ጋር ያለሁ ነበር የመሰለኝ።» አሰገደች «አንድ - ላንድ» አለችና በልቧ «ተጠልፈህ ነበር ማለት ነው?»

«ኧረ እሱ ምን ያደርግልሻል፣ ይልቁንም ወደ ቤታችን ሔደን እንተኛ» አለና ዮሐንስ ወጣ፣ አሰገደችም ተከተለችው።

አስገደች እርግዝናን የምትከላከለው በእንክብል (ፒልስ) እና በወር አበባ የጊዜ ሰሌዳ ነው:: ይኸንን ዮሐንስም ያውቃል:: በዚያን የእብደት ምሽት እንክብሉን መውሰድ አለመውሰዷን አታስታውስም::

ሃያ ስምንቱን እንክብሎቿ በየምሽቱ ወደ አልጋ ከመሔዷ አንድ ሰዓት በፊት መውሰድን የተለማመደችው ከዮሐንስ ጋር ግንኙነት ከጀመረች በኋላ ነው:: ከዚያ ቀደም ከተቃራኒ ፆታ ጋር እምብዛም ግንኙኘት ስላልነበራት አሳስቧት አያውቅም::

አንዳንድ ጊዜ እንክብል መውሰድ ዘንግታ አልጋ ብትወጣም ስህተቷን ለዮሐንስ ነግራ አታውቅም፣ የግቢው ቅዱስ ገብርኤል ከጉድ እንዲያወጣት ተማጽና ጭጭ ትላለች::

***

ከአንድ ወር በኋላ አንድ ምሽት ዮሐንስና አስገደች መታጠቢያ ቤት ሲፋተጉ ቆይተው ለመውጣት መልበሻ ክፍል ውስጥ እንዳሉ «አንተ የወር አበባዬ ቀረ□ኮ!» አለች እንደዋዛ::

«መርዶ ነው - የምሥራች ለይው!» አለ ዮሐንስ ምንም ዓይነት ስሜት ሳያሳይ::

«እ - እ - እኔ አላውቅም» ብላ እንደማፈር ባለ ስሜት አንገቱ ሥራ ልጥፍ አለች::

ዮሐንስ የሚለው ጠፍቶ ራቁት ጀርባዋን በቀኝ እጁ እያሻሸ በግራ እጁ እንዳቀፋት ትንሽ ቆየ:: ግን ደንግጧል::

«አሁን የሆነው ሆኗል፣ ብቻ እነ ዓለሚቱ፣ እነ አባባ ጌቶች መስማት የለባቸውም» አለ ራሱ ለራሱ::



ከመልበሻ ክፍል ወደ መኝታ ክፍል በመግባት ላይ እንዳሉ «ይኸን ነገር ከእኔና አንቺ ሌላ ማንም ሰው፣ በምንም መልኩ ማወቅ የለበትም» ለሚለው የዮሐንስ ማስጠንቀቂያ አስገደች «እሺ! እሺ» በሚል የተስረከረከ ድምጽ ታዛዥነቷን ገለጸች::

«አንቺ ተኚ እኔ ትንሽ እቆያለሁ» ብሎ የአስገደችን ስምምነት ሳይጠብቅ ዮሐንስ ጽ/ቤት ገብቶ ለአንድ አፍታ ፊት ለፊቱ ካለው ግድግዳ ላይ አፈጠጠ::

«ይህች የዛሬ ቀን የእንጀራ ገመዴ መበጠሻ፣ ወይም የውርደት፣ የድኸነት፣ ከሁሉም በላይ የቆሞ ቀርነት ሕይወቴ መጨረሻ ነች» አለች አስገደች እየተንጎራደደች::

«ብርሃን የፈነጠቀበትን ሕይወቴን በገዛ እጄ አጨልሜው ይሆን? የእኔና የዮሐንስ ግንኙነት በፅኑ መሠረት ላይ እንዳልተገነባ አውቃለሁ:: ለእኔ እንደ ዛፍ ላይ እንቅልፍ ነው - ያባንነኛል» ብላ የወሊድ መቆጣጠሪያ እንክብል የያዘውን ፓኮ ከኮመዲኖው ውስጥ አውጥታ አፈጠጠችበት:: «ውጤቱ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ የሆነው ሆኗል! ባወጣ ያውጣው!» በማለት ፓኮውን ወርውራ ፀጉሯን መጠቅለል ጀመረች:: ብዙም ሳትቆይ ወደ ቁም መስታወት ዞር አለች:: ሁለት እጇቿን ሆዷ ላይ አሳርፋ ጫን ጫን አደረገች:: ፊቷ በፈገግታ ብርሃን ወገግ አለ:: ፈንቅሎ በወጣ ስሜት ተሽቀንድራ አልጋው ላይ ዘፍ አለች::

ዮሐንስ በበኩሉ ግርግዳው ላይ ሰክቶ ያቆያቸውን ዓይኖቹን ሰበር አድርጎ ወረቀትና ብዕር ማገናኘት ጀመረ:: መጀመሪያ የጻፈው ዐረፍተ ነገር እንዲህ የሚል ነው::

«አንድ ሰው የማንነቱን ልክ የሚያውቀው የገጠመውን ፈተና ከሆነለት ያለ ኪሣራ፣ ካለዚያም በአነስተኛ ኪሣራ በድል ለመወጣት ካለው ብቃት መሆኑን አውቃለሁ::» ዮሐንስ ይህን ዓረፍተ ነገር ካለፈረ በኋላ ለጠጥ አለና ዓይኖቹን እንደገና ከፊት ለፊቱ ግድግዳ ላይ ለካቸው:: ፈስተያየቱ ግድግዳውን «አባክህ መፍትሔ የሚሆን ሃሳብ አፍልቅ» ብሎ መማፀኛ ይመስላል::

በግራ ከንዱ ጠረጴዛውን ደገፍ አለና ከ1-10 ያሉትን ቁጥሮች ወደታች ጻፋቸው::

ውርጃ

መውለድ

ማደጎ

መጋባት

ማባረር

በሰላም መለያየት

በስኮላርሽፕ ካገር ማስወጣት

ተቆራጭ እየሰጡ ልጅ ማሳደግ

አላውቅልሽም ብሎ መካድ

አስገደችን መግደል - አዎ! መግደል! .....መግደል!

ከዚህ ውጭ ምን የቀረ አማራጭ ይኖራል? ዮሐንስ ለጥያቄው መልስ ከማሰላሰል ይልቅ የገነፈለ ቁጣውን አቀዝቅዞ በይደር አንጠልጥሎ መተውን መረጠ::

ዋል አደር ብሎ ዮሐነስ ሲያብሰለስለው ስለከረመው የአስገደች እርግዝና የእሷን አቋም ለማወቅ «ቅሪት ስለመሆንሽ እስካሁን ያልሽው ነገር የለም» አለ ዮሐንስ ጥያቄውን አስበበት ሳይሆን እንደዋዛ ያነሳው መሆኑን በሚገልጽ ቸልታ::



«ምን ማለት ነበረብኝ ጆኒ!»

«እኔም አንቺም አልተዳርን፣ ከጋብቻ በፊት ልጅ ሆነ□ክ! ይኽንን ደግሞ ያንቺም የእኔም ወላጆች በፀጋ የሚቀበሉት መርዶ አይመስለኝም» አለና ቀና ብሎ ተመለከታት::

«ጆኒ እንዴት ነው፣ መርዶ አልከውሳ!»

«ታዲያ ምን ይባል? በተለይ ለየወላጆቻችን መርዶ እንደሚሆን ገመቼ ነው::»

«የእኔ ማርገዝ ይህን ያህል ካሳሰበህ፣ እንዲህ መኪና እየነዳህ ሳይሆን ረጋ ብለን በሰከነ መንፈስ መነጋገሩ ይሻል መሰለኝ» አለች አስገደች ለዘብ ብላ::

«ጥሩ ብለሻል መቼ እናድርገው?»

«ነገ ተነጎዲያ - ጊዜ አለን::»

«መልካም» አለና ዮሐንስ ዝም አለ::

# ምዕራፍ 8

## ዓለሚቱ፣ ዮሐንስና ተስፋዬ

ቀኑ ቅዳሜ ነው፣ ዮሐንስና ተስፋዬ ዓለሚቱ ቤት ምሳ እየተስተናገዱ ናቸው::

«የተሟላ ግብዣ ለጤናችን!» አለ ተስፋዬ ብርጭቆውን ወደ ዓለሚቱ ብርጭቆ እያስጠጋ::

«ተቢዳኝ ቢኖረው ይበልጥ የተሟላ በሆነ ነበር» አለ ዮሐንስ ዓለሚቱ እንድትናገር በሚኮረኩር ፈገግታ እያጮለገ::

«እንደ ወህኒ ፖሊስ ስትወጣ ስትገባ የምታጅብህን ጓደኛ ተብዬ ባለመጋበዜ ይቅርታ::» አለች ዓለሚቱ እንደመጎሻመጥ ብላ::

«ዓለም የእኔይቱ ትቅር፣ እሺ የተስፋዬ እጮኛስ!»

«እሷም ብትሆን ይፋዊ እውቅና ገና ያልተሰጣት ስለሆነች እንደዚህ ባለ ጠባብ ቤተሰባዊ ፕሮግራም ላይ ልትገኝ አይገባትም:: የጥቂት ጊዜ ደጅ ጥናት ይቀራታል:: ይህን ጥንቅሽ የመሰለ ልጅ ባንድ ለሞን የናይት ክለብ ሆያ ሆዬ የግሏ እንድታደርግ አንፈቅድላትም፣ ማንነቷ ይረጋገጥ::»

«ዓለም የእኔ ባትሆኚ እንዴት በቆጨኝ» አለ ተስፋዬ በፊት ሙሉ ፈገግታ:: ገበታው ከፍ እንዳለ « ይህ በፆታ ያልተቀናጀ ቡድን በዚህ ምሳ ላይ እንዲገኝ የተደረገበትን ምክያንት እገልጽ ዘንድ ይፈቀድልኝ» አለች ዓለሚቱ ለዘብ ባለ አነጋገር::



ዮሐንስና ተስፋዬ እንደ መገረምም ግራ እንደ መጋባትም ባለ ስሜት ተያዩ፣ ተጠቃቀሱና ፊታቸውን ወዳለሚቱ አዞሩ:: ሁለቱም ባንድ ድምጽ፣ ባንድ ጊዜ «ተፈቅዶልሻል» አሉ::

ዮሐንስ ወዲያው ቀጠል አድርጎ «መቸም ያንቺ ነገር...» ብሎ የጀመረውን ዓረፍተ ነገር ሳይጨርስ «ወደ ቁምነገሩ እንምጣ» አለች ዓለሚቱ ኮስተር ብላ:: «የእኔ ወንድም በወግ በማዕረግ ሳትሠረግ፣ ራስህን ከዳርክ ቆየሕ:: ወላጆቻችን እኔም እንደ እህትነቴ ከአሰገደች ጋር ስላለህ፣ ወይም ወደፊት ስለሚኖርህ ግንኙነት ማወቅ እንፈልጋለን::»

«የእኔና የአሰገደች ግንኙነት የእኔና የእሷ ጉዳይ መሰለኝ»

«ዮሐንስ! የወላጆቻችን አንድ ለናቱ መሆንክን አትርሳ::»

«አታክርሪው እንጂ ዓለም::»

«ጥያቄው የመክረርና ያለመክረር ጉዳይ አይደለም፣ የሁንዴ ዝርያ መቀጠል አለበት:: እኔና አንተ ላይ ሲደርስ መቋረጥ የለበትም:: የአንተና የአሰገደች ግንኙነት መታየት ያለበት ከዚህ አኳያ ይመስለኛል::»

«......<መቋረጥ የለበትም> በሚለው ሀረግ እኔም እስማማለሁ፣ የእኔንና የአሰገደችን ግንኙነት ከመቋረጥና አለመቋረጥ ጋር ለምን እንዳገናኘሽው ግን አልገባኝም::»

«ግንኙነታችሁ አቻ አይደለም ለማለት ፈልጋ መሰለኝ» አለ ተስፋዬ ሲፈራ ሲቸር ጣልቃ ገብቶ::

ዓለሚቱ ብድግ ብላ ተስፋዬን ግንባሩን ሳም አድርጋ «አፌ ይቆረጥ» አለች::

«ይህ ነገር የምር ነው እንዴ?» አለ ዮሐንስ በግራሞት::

«አዎ የምር ነው፣ ዮሐንስ አትቀልድ:: አባባ ጌቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ሊያነጋግሩህ አስበው ነበር:: ከእሳቸው በፊት እኔ ባነጋግርህ እንደሚሻል ተስማምተን ነው ዛሬ ተስፋዬ ባለበት እንድንገናኝ ያደረግሁት::»

«እማማስ ምን ይላሉ?»

«የእሳቸውንም በቅደም ተከተል እናነሳዋለን፣ እንደርስበታለን::»

«እንደኔ እንደኔ በተገቢው ጊዜ የተነሳ ተገቢ ጥያቄ ይመስለኛል:: ዮሐንስ ፈቃድህ ከሆነ አባባሌን ግልጽ ላድርግ» አለ ተስፋዬ የመቅርቀር ስሜት እያሳየ::

«እሺ ቀጥል»

«እመሰግናለሁ ጆኒ፣ <ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ> እንዲሉ ከመሰረቱ እንነሳ::»

«ሁላችንም የምናውቀውን ዝባዝንኬ ታሪክ እንደ አዲስ ለመስማት...» በማለት ዮሐንስ የጀመረውን አስተያየት ሳይጨርስ አቋረጠችውና «የተስፋዬን አነጋገር ታሪክ በለው ተረት እንዲጨርስ ዕድል እንስጠው፣ ፈሩን ከሳተ እናስቀመዋለን» አለች ዓለሚቱ ግንባሯን ከስክሳ::

ዮሐንስ ባይስማማም ተስማማና አፉን ተመተመ::

«......እፀድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች እንደተባለው ሆነና ሁላችንም በምናውቀው ግርግር ውስጥ አስገደች ተጠጋችህ ወይም አንተ በእዘኔታ አስጠጋኻት፣ አስጉም ተሰሳልሳ ስትጠጋ - ስትጠጋ - እንደገናም ስትጠጋ አሁን ከመጠጋት እልፋ ውኅድ ሆነች:: በቁጥጥር ሥር አዋለችህ ማለቱ ከብዶኝ ነው» አለ ተስፋዬ አባባሉን ረገጥ - ጣፈጥ እያደረገ::



«ተራቀቅ የእኛ ሊቅ፣ ዘርጋ የነገር ጉባኤ» አለ ዮሐንስ ተስፋዬን ለማሽሟጠጥ::

«ዮሐንስ የምንነጋገረው የምር ነው ብለናል፣ አይደለም እንዴ? አስገደች ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ የወረሰችውን የድኽነትን እዙሪት ቀለበት ሰብራ ወጥታለች:: ትምህርቷን ጨርሳ ባለ ሥራ ሆናለች:: ምን ቀራት? አንተም በይሉኝታ ታስረህ እንጂ ወደህ አይመስለኝም:: አሁን ግን ይብቃ፣ ቢበቃ የሚሻል መሰለኝ::» የሚለውን የተስፋዬ ምክር ዮሐንስ ገሸሽ አድርጎ «እንቼስ ምን ትያለሽ የምታክይው ካለ?» አለ ዮሐንስ ፊዝኛውን:: ቀጠል አድርጎም «በነገራችን ላይ እየለገሳችሁኝ ያላችሁት ምክር መሰለኝ?»

«እንዴት! ምን ለማለት ፈልገኽ ነው?» የዓለሚቱ ኮስተር ያለ ጥያቄ ነበር::

«እይ ትዕዛዝ ቢጤ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ብዬ ነው» አለ ዮሐንስ ከተቀመጠበት እየተነሳ::

«ዮሐንስ በእናትህ ቁምነገር እንነጋገር፣ የእኔ ወንድም□ኮ ካልመሰለህ ቅቤ በወስፌ አይወጋልህም አውቃለሁ::»

«እስከ አሁን ስለ እኔና ስለ አስገደች ግንኙነት ለማለት የፈለጋችሁትን ሁሉ ብላችኋል:: የቀረ ነገር ያለ አይመስለኝም፣ የቀረ ነገር ቢኖር የእኔ ወይም እኔና እሷ በጋራ የምንሰጠው ውሳኔ መሰለኝ:: ለዚህ ደግሞ ጊዜ ያስፈልጋል:: እንድናስብበት ጊዜ ስጡን፣ ይሁንና ስለምክራችሁ አመሰግናለሁ::»

«ደህና! ደህና! ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራት፣ ዓመታት ስንት ጊዜ እንስጥህ?»

በዓለሚቱ የብሽቀት አጠያየቅ ውስጥ የታመቀው ኃይለ - ቃል ዮሐንስንም ተስፈዬንም ክፉኛ ቢያስፈራቸውም ከጣራ በላይ አሳቃቸው::



# ምዕራፍ 9

## የዮሐንስና አሰገደች ጋብቻ

ለዮሐንስ አባባ ጌቶች ስለጋብቻ ሕይወቱ ሊያነጋግሩት ማሰባቸውን ዓለሚቱ ከነገረች ውሎ አደሯል::

እርሱም «እስከመቸ ስሸማቀቅ እኖራለሁ? የአሰገደችም ሆድ እየገፋ ነው:: የጋብቻ ሕይወቴ ወላጆቼና እኔም ለመቀየስ ያሰብነውን ፈር ስቶ፣ አጋጣሚ የወሰነውን አቅጣጫ መያዙ አሳዛኝ ምናልባትም አሳፋሪ ክስተት ሆኗል:: ቢሆንም በግንባር ቀርቤ አባባ ጌቶችን ስለ አጋጣሚው የማስረዳት ኃላፊነት አለብኝ» በማለት ዮሐንስ ራሱን በራሱ በመውቀስ ወደ ግቢ ስልክ ደወለ::

«ደህና አደርሽ ደጊቱ፣ አባባ ጌቶች አሉ እንዴ..... ካሉ ተይው ወደዚያው መጣሁ» ብሎ ስልኩን ዘግቶ ወጣ::

ዮሐንስ ግቢ ደርሶ ወደ እልፍኝ ሲገባ፣ ለቁርስ የተጣለው ገበታ ከፍ ብሎ፣ ደገፉ ድግድጋቱን አሳምሮ፣ ለንና ብርት ይዞ የጣት ውሃ በማቅረብ ላይ ነበር::

«ዮሐንስ ነህ እንዴ!»

«አዎ አባባ» ብሎ ጫማ ለመሳም ዝቅ ሲል ጉንጫቸውን ሰጡትና «ምነው ገበታ ሲነሳ? ከመጣህ አይቀር ቀደም አትልም ነበር?»

«አሁንም እደርሳለሁ» በማለት ፊቱን ወደ እናቱ አዙሮ እጅ ነሳና ጉልበታቸውን ሳመ:: እሳቸውም አገጩን በቀኝ እጃቸው ቀና አድርገው ጉንጩን ሳሙት::
ዮሐንስ ለምግብ ጠረጴዛው ቀረብ ባለው ፎቴ ላይ አረፍ አለ::

«ወደዚህ ሁን፣ ማነሽ ቁርስ አምጡለት» አሉ እናቱ ፊታቸውን አደግድጋ ወደ ቆመችው ሠራተኛ በከፊል ዞር አድርገው።

«ቁርስ አድርጌ ነው የመጣሁት» አለ ዮሐንስ ብድግ ብሎ በአክብሮት ካንገቱ ዝቅ አያለ።

«ብላ አልበላም ይኸ እያጣላም፣ ተውት ከበላ» አሉ አባቱ። የአባቱን አባባል በመቀበል ዮሐንስ ፈገግ አለ።

ፈረስ የሚያስጋልብ ከመሰለው ምግብ ቤትና ሳሎን ውስጥ ተገቢ ቦታቸውን ይዘው የተሰተሩትን ብርቅና ወግ ያላቸው ዕቃዎች እንደ እንግዳ እየተመለከተ አባቱ እስኪያናግሩት ጠበቀ። በዚህ መኻል የሚንጫረረውን ስልክ ደጊቱ እያነሳች የምትለጠው መልስ ባይሰማውም፣ ጌቶች ወይም እሜቴ በቅርብ አለመኖራቸውን አስረድታ ደዋዩ ማን እንደሆነ መጠየቅ እንደሚሆን በመገመት፣ የቤቱን ሥርዓት በአድናቆት ያስተውል ነበር።

ጌቶች ከምግብ ጠረጴዛው ብድግ ሲሉ በሳሎን ውስጥ የነበሩት እናቱና ዮሐንስም ብድግ ብለው ቆሙ። ጌቶች ፎቴ ላይ አረፍ እስኪሉ ድረስ ቆመው እሜቴ ወደ ሌላ ክፍል ሲያመሩ ዮሐንስ አባቱ ወደ ተቀመጡበት ፎቴ ቀረብ ብሎ ተቀመጠ። ደጊቱና አጋፋሪው ዘመድኩንም ከሳሎኑ ወጡ።

«የምሰማው ምንድነው በል?» አሉ ጌቶች የቆይታውን ዝምታ በሚሰብር ምልከታ።

ዮሐንስ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት ከተቀመጠበት ቀስቀስ ሲል «ግድ የለም ተቀመጥ» አሉት።



«ትዳር» አለና ዮሐንስ ሲቃ ያዘው፣ የብር አለሎ የመሰሉ ዓይኖቹ ተጎልጉለው እንባ አዝለውና ቀልተው ወለሉ ላይ ዱብ ዱብ የሚሉ መሰሉ።

ጭንቀቱን የተረዱት አባቱ «ደህና! ደህና! ተረጋጋ» አሉት።

«የእኔ፣ አንድ ልጃችሁ የጋብቻ ሕይወት እናንተ ወላጆቼ እኔም ጭምር እንደምንፈልገው ባለመሆኑ በጣም አዝናለሁ።»

«ምነው አንተ ዓለሚቱስ?» አሉ ውጥረቱን በሚያረግብ ፈገግታ።

«እርግጥ ነው ዓለሚቱ አለች፣ ያም ሆኖ፣ ወላጆቼ ለእኔ ያላችሁን ልዩ ግምት ሳስበው እንደፍላጎታችሁ ባለመሆኔ ከሐዲነት፣ ጎደሎነት ይሰማኛል» አለ ዮሐንስ የአባቱን አዘኔታና ርሕራሔ ለማግኘት።

«የነገሩን ዳርዳርታ ሰምተናል። ተፈለገም አልተፈለገም የሆነው ሆኗል። የወደፊት ዐሳብህ ምንድነው? በእሱ ላይ እንነጋገር» በማለት ዮሐንስ የሚለውን ለመስማት ጆሯቸውን አቀኑ።

«ወደፊት የሚባል ነገር የለውም አልቋል። ያስጨነቀኝም ይኸው ነው» አለና እጆቹን ወደኋላ አጣምሮ ቆመ።

«ገባኝ አርግዛለች ማለት ነው?»

«አዎ አባባ።»

አባቱ የማርገዟን መርዶ ሲሰሙ እንደቁጣ ቃጣቸው፣ ሆኖም የዮሐንስን መጨነቅ በማየት መልሰው ረገብ አሉና «መተዳደሪያ ቢቀረጥላትስ» በማለት የመፍትሔ ሃሳብ ጠቆሙ።

«ይሄ ነው የከበደኝ:: የእኔን ልጅ ይዛ እድሜ ልኳን ተጠብቃ ልትኖር አለመቻሏን ሳስበው....» ብሎ ዮሐንስ የጀመረውን ዐሣብ አቋረጠው::

«ምን አለ አንተ ጋብቻህን በሕግ መሰርት፣ እሷንም መፍቀድ ትችላለህ:: ሴትም መሰለት» ብለው ምክራቸውን ሳይጨርሱ «አባባ የልጄን ሸናት ከሌላ ሰው ጋር መጋራት አይሆንልኝም:: ይህ ነው ችግሬ» አለና ዮሐንስ ሆድ - ባሰው እንባም ተናነቀው::

«ጉድ□ኮ ነው! ወይ ልጄን በምን ቀን ለከፈችህ?» አሉና «ማነህ አንተ እመቤትን ነይ በላት» ብለው ዓይናቸውን ባለቤታቸው ወደ ሚመጠበት እቅጣጫ እንደወረወሩ ቆዩ:: ለጊዜው በሳሎኑ ውስጥ ዝምታ ነገሠ::

እመቤት ጽዮን ሞገሳ ደብረክ ደብረክ እያሉ ሲገቡ ዮሐንስ ብድግ አለ:: ጌቶች በቀኝ እጃቸው እያመለከቱ « ወደዚህ ሁኚ» አሉ::

እመቤት ለምን እንደተጠሩ ቢጠረጥሩም ባለቤታቸው እስኪናገሩ መጠበቅ ነበረባቸው::

«ዮሐንስ ተቸግሯል» አሉ ጌቶች በለሆሳስ::

«የማይፈታ ችግር ነው?» የእመቤት ጽዮን ጥያቄ ነበር::

«መሆኑ ነዋ!» የጌቶች መልስ::

«ዮሐንስ! እባ መላ አባትህ ሊፈቱት ያልቻሉት ችግር ምንድነው? ዛሬ በወጣትነተ ስሜት ተገፋፍተህ ካልሆነች ሴት ላይ ብትወድቅ ነገ ይጸጽትሃል:: ያጋጠመህን ችግር ለመፈታት ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ ዋል አደር ብለን እንደገና እንመለስበት:: አይመስልዎትም ጌቶች!» አሉ በትህትና ወደ ባለቤታቸው እየተመለከቱ::



«ካልሸስ ዓለሚቱም ብትገባበት ደግ መሰለኝ» አሉ ጌቶች የባለቤታቸውን ዐሳብ በመደገፍ::

«ካለሚቱ ጋር ተነጋግረን ጨርሰናል:: የቀረን ነገር የለም» በማለት እናትና አባቱ ከአለገደች ጋር የወጠነውን ጋብቻ እንደፈቅዱለት ከአባቱ ጫማ ላይ ወደቀ::

«እናትህ እንዳለችው ከማትሆን ሴት፣ ዝርያዋ ካልታወቀ ሴት ጋር በጋብቻ ተቆራኝተህ የማታ ማታ ፍዳህን እንዳትቆጥር እንጂ እኛማ ምን ተዳችን፣ እንደፈቃድህ ይሁንልህ» አሉትና ዮሐንስ የአባቱን ጫማ ስሞ ከተነሳ በኋላ የእናቱን ጫማ ስሞ ቆመ::

***

አለገደች በጀመረችው ቆጥ አሠርነት ቀጠለች:: የከበሮ ድምድም የሚዜ እሽክም እሽክም በሌለበት በዚያው ለሞን ባልና ሚስት ሆኑ::

«የሠርጋችን ሥነ ሥርዓት የጋብቻችንን 10ኛ ዓመት በምናስብበት ዕለት እናከብረዋለን» አለ ዮሐንስ «እንደፈቃድህ ይሁንልህ» በሚለው የአባቱ ቃል የተለማውን እፎይታ እያሰበ::

«እኛ ሰፈር አለገደች ተጠለፈች የሚል ወሬ መዛመቱን ስምቻለሁ:: ሠርግ እጠራለሁ ብሎ የሚጓጓ አይኖርም» አለች አለገደች እሷም እንዳቅሟ ቆጥ አሠር (ገሲ) መግባቷን እንዲሸፍንላት::

***

ዮሐንስ አላቻ ቢሆንም ጋብቻው የወላጆቹን ካንገት በላይ ይሁንታ በማግኘቱ እፎይ ብሎ ከርሟል፡፡ ይሁንና ጋብቻውን ከማስፈቀድ ያላነሰ ሌላ የቤት ሥራ ከፊቱ እንደተደቀነ ነው፡፡

«አሰገደች ከነ አባባ ጋር ተፈርቃ የምትቆየው እስከ መቼ ነው?» የሚል ሀሳብ የገባው ዮሐንስ ዘዴ በማፈላለግ ላይ ነው፡፡ ባውጠነጠነው ዘዴ አመርቂ ነገር ባለማግኘቱ ዓለሚቱና ተስፋዬን በጉዳዩ ላይ ለማማከር ወሰነና አንድ ቅዳሜ በቀጠሮ በተያዘ ሰዓት ዓለሚቱ ቤት ተገናኙ፡፡

«እንዴት ነው ጃል፣ የጫጉላ ሽርሽር የለም እንዴ?» አለ ተስፋዬ አግቦኛውን፡፡

«መቼም ሰው እንደ ሸንኩርት ካላጥክ አይሆንልህ፣ ደብተራ!» አለው ዮሐንስ ባልተናነሰ አግቦ፡፡

ዓለሚቱ ለወንድሟ ያላትን ክብርና ፍቅር የምትገልጽበት አንዱ መንገድ እቤቷ በመጣ ቁጥር በምታሰናዳው ለየት ያለ መስተንግዶ ነው፡፡

ዓለሚቱ ከወጥ ቤቷ ጋር ጉድ ጉድ ብላ ገበታ ሠርታ «ራት ቀርቧል» አለች በተለይ ወደ ዮሐንስ ቀረብ ብላ፣ እጇን በጀርባዋ ላይ አጣምራ፣ በዝርጋዳ ቁመቷ ወረድ ብላ፡፡

«ልዑል እምልዑላን ይቅደሙዋ!» አለ ተስፋዬ ዓለሚቱ ለወንድሟ ያሳየችው ከበሬታ ከሚገባው በላይ መሆኑን በማሽሟጠጥ፡፡

«ተስፋዬ መቼ ነው አንተ ለመልካም ነገር አፒታይት (ከሳቴ እይታ) የሚኖርህ!»



«አልገባህም እንጂ ምግቡን የሚያበላው አንዱ ከሳቴ እይታ ፣ እንድምታ ያለው ጭውውት ነው፣ የመንፈስ ምግብ፣ አይደለም እንዴ ዓለም!»

«ደግ ነው! እንዳላችሁት ይሁና!» አለች ዓለሚቱ ጎራዋን ሳትለይ፡፡

በዋዛ በፈዛዛ ራት ተበልቶ ገበታ ከፍ እንዳለ ዮሐንስ የተገናኙበትን የምሽቱን አጀንዳ ግልጽ አደረገ፡፡

- «አሰገደችን ከቤተሰብ ጋር እንዴት አድርጌ ላቀራርብ፡፡»
- «ለጫጉላ ሽርሽር ወደ አዋሳ ለመሔድ አስበናል፡፡ ይኸንን ለእነሱ ሳልነግር መሔዱ ከበደኝ፡፡ መንገሩ ደግሞ የባሰ ከበደኝ፡፡»

«ዮሐንስ አሁን ምንም ነገሩ ያለፈ ቢሆንም አንድ ነገር በቅድሚያ እንድተነፍስ ፍቀድልኝ - የምሬን ነው» አለ ተስፋዬ፡፡

«ቀጥል፣ ፈቅጃለሁ ምን ይሆን? መቸም አታመጣው የለህ!» አለ ዮሐንስ ፈገግ ብሎ፡፡

«እኔና ዓለሚቱ በራሳችን ተነሳሽነት በአንተና በአሰገደች መካከል የነበረው ግንኙነት አንተም፣ እኛም፣ የቅርብ ወዳጆችህ፣ በተለይም እኒያ ደግ ወላጆችህ ባላሰቡት ጡዘት መክረሩ አሳስቦን አነጋግረንህ ነበር፡፡ <ጊዜ ስጡኝና ላስብበት> ብለኸን በጎን የሆነው ሆነ፡፡ በቆረጣ ሆነ ነገሩ፡፡ ለምን?» አለና ተስፋዬ ሳያስበው በውስጡ በተፈጠረ ሽብር ንግግሩን አቆመ፡፡

የዮሐንስ ያልተጠበቀ ጥያቄ ሦስቱንም አንገት አስደፋ፡፡

«ተስፋዬ ይኸንን ጥያቄ ያነሳው ስለአንተ በመቆጨት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ወንድሜ ደግሞ በግልጽነት ስለምታምን

ጥያቄውን በፀጋ እንደምትቀበለው እርግጠኛ ነኝ» አለች ዓለሚቱ እሷም ብትሆን ጋብቻውን ያልተቀበለችው መሆኗን ለማሳየት::

«ተስፋዬ» አለ ዮሐንስ አእምሮውን በምክንያት ሞረድ ሳል ሳል አድርጎ እንደጨረሰ «ተስፋዬ! ጥያቄህ ትክክል ነው:: ከዚህም የባሰ ሊያናግርህ ሟናልባትም ሊያስቆጣህ ይገባል:: ይኸንን ስል ከቁጣህ ለማምለጭ ይቅርታ መጠየቄ አይደለም:: አንተም ሆንክ እህቴ እንደዚህ ያለውን ሽብ ረብ እንደማትሹ አውቃለሁ:: እኔና አሰገደች ግንኙነታችንን ወደጋብቻ ያሸጋገርነው ወድደን አይደለም::

«ወደን አይደለም» የሚለውን የዮሐንስን ምክንያት ለመስማት ተስፋዬና ዓለሚቱ ከተቀመጡበት ብድግ የማለት ያህል ተቁነጠነጡ::

«አዎ! ወድድን አይደለም፣ ተገድደን እንጂ» አለና ሳገ ተናንቆት ዝም አለ::

«ጆኒ ተረጋጋ! ተረጋጋ!» አለች ዓለሚቱ ሳጉ እሷንም እየተናነቃት::

«አሰገደች አረገዘች፣ ምን ሳድርጋት!» ዮሐንስ የአሰገደችን ማርገዝ ካረዳ በኋላ ጣምራ ጣምራ እየሆነ ከዓይኖቹ ዱብ ዱብ የሚለውን እንባውን ለመጥረግ መሐረብ አወጣ:: ተስፋዬ በአሰገደች ማርገዝ አዝኖ ሳይሆን በዮሐንስና በዓለሚቱ ማልቀስ ስሜቱ ተነክቶ እሱም አጀባቸው::

«በቃ የሆነው ለክፉም ሆነ ለበጎ አንድ ጊዜ ሆነ:: ይህን እዚህ ላይ ጋደም አድርገን ወደ ተገናኘንበት ጉዳይ እንመለስ» አለች ዓለሚቱ::

«ይሻላል» አለ ተስፋዬ::



«አጭር የቡና ጊዜ ቢኖረን!» አለ ዮሐንስ ወደ ዓለሚቱ ፊቱን ዞር አድርጎ::

«ጥሩ ብለሃል» በማለት ዓለሚቱ ደወል አንቃጨለች:: ሠራተኛዋ ከመቅጸበት መጥታ አፏን ባንድ እጇ ጥርቅም አድርጋ አፍና ጆሮዋን ከዓለሚቱ አፍ ስር ደቀነች::

«ቡና አባክሽ!» አለቻት::

«እሺ! እሺ!» እያለች ሠራተኛዋ ወደኋላዋ አንድ ሁለት ርምጃ ሔደት ብላ ወጥ ቤት ጥልቅ አለች::

«ዓለም እርግጠኛ ነኝ ይህች ልጅ ከገቢ የተሰጠችሽ መሆን አለባት» አለ ተስፋዬ የሠራተኛዋን ሥልጡንነት በማድነቅ::

«እናቷ የኮሶ ስንብት የሰጧት ነች» አለ ዮሐንስ ወደ ተስፋዬ ጆሮ ቀረብ ብሎ::

የዮሐንስን ሹክታ የሰማችው ዓለሚቱ ከጣራ በላይ መሳቅ የጀመረችው ተስፋዬ «የኮሶ ስንብት ሰው ይሰጣል እንዴ» የሚለውን በማውጣትና በማውረድ ላይ እንዳለ ነበር:: የኮሶ ስንብት ስጦታው ተስፋዬን ከማሳቅ ይልቅ ትዝብት ነበር የፈጠረበት:: እህትና ወንድም ግን እናታቸው እመቤት ጽዮን ሞገሳ «እንዳይከፋኝ» የተባለችውን ባሪያ ከአክስታቸው ለኮሶ ስንብት መስጠት አስታውሰው ነበር ሳቅ በሳቅ የሆኑት::

እንዳይከፋኝቷ ብለው ሲጠሯት «የእመቤቴን አያሰማኝ ሞቷን» ወይም «እንዳይከፋኝ» ተብላ ስትጠራ «የእመቤቴን ሞትሽን አያሰማኝ» በማለት ነበር እመቤቷ ወዳሉበት የምትቀርበው:: በኋላ በኋላ ጌቶች ስለከለከሉ ባሮቹና የባሮች ልጆች ሁሉ እንደ ማንኛውም የቤተሰብ አባል

«እሜት»

«አቤት»

ብቻ በማለት የተጠሩበትን ትዕዛዝ ተቀብለው ዞር እንዲሉ አዲስ ሥርዓት ተሠራ::

ሳቁ አባራና የእነ «እንዳይከፋኝ» ምንነት ተብራራ ሦስቱም ተዘፍቀው ከነበረበት ያልታሰበ ጨደድ ወጥተው ዘና ብለዋል::

«ዮሐንስ» አለች ዓለሚቱ አንድ በጎ ዐሳብ ብልጭ እንዳለላት በገጽታዋና በአካል እንቅስቃሴዋ እያመለከተች «ዮሐንስ እኔ በዚህ ጉዳይ ላይ መጀመሪያ እማማን ከዚያም አባባን ቀስ ብዬ ብቻ ለብቻ ልጠይቃቸው:: ልብ በል ጥያቄውን ከራሴ የመነጨ አድርጌ ነው የማቀርበው» አለች::

«ይኸማ ሲዋጥ በመረቅ!» አለ ተስፋዬ እሱም ስለአሰገደች በሚሰጠው አስተያየት ጓደኛው እንዳያስቀይም ከነበረው ሥጋት መገላገሉን እያሰበ:: ዮሐንስም በቀረበው ዐሳብ ተስማምቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ የምሥራቹን ወይም መርዶውን ለመስማት ወስነው ተለያዩ::

***

አሰገደች ሆዷ እየገፋ ሁሰመናዋ እየፋፋ ስለሔደ ባልና ሚስት አልጋ ለይተዋል:: በየዳንስ ወለሉ መውረግረግ፣ መሰበቅ፣ መሽክርከር ክቀረ ወራት ተቆጥረዋል:: ዮሐንስ በገባ በወጣ ቁጥር «ምን አማረሽ? ምን ላምጣልሽ?» ሲላት መቆላመጡ የበዛባት አሰገደች «ሁሉም አለ፣ ያማረኝ ሳይሆን የናፈቀኝ ናይት ክለብ ነው» በማለት የእሷንም የእሱንም የናይት ክለብ ትዝታ ትቀሰቅሳለች::



ዮሐንስ ያለሠርግ ካሰገደች ጋር ትዳር መመስረቱ ያደባባይ ሚስጢር ቢሆንም እንደቀድሞ ከአሰገደች ጋር በየናይት ክለቡና በየሆቴሉ መታየትን የቀነሰው ቀደም ብሎ ነው:: በተለይ ቅሪት መሆኗ ካስታወቀባት በኋላ:: አሰገደች በበኩሏ ይህን እፍን እፍን እንደ ከርቸሌ ነው የቆጠረችው:: ፒያሳ፣ መርካቶ፣ ሌላም ሌላም አካባቢ ሆዷን አንገፍጥጣ ከዮሐንስ ጋር መታየት ግዳይ የመጣል ያህል ያሸልላታል:: የቅሪት ልብስ፣ ልጥፍ ጫማ፣ የልጅ አልጋ፣ የልጅ ልብስ፣ የልጅ መታቀፊያ፣ የልጅ ማጠቢያ ገንዳ፣ የልጅ ሳሙናና ፓውደር፣ የልጅ መጫወቻና ማንሸራሸሪያ ጋሪ፣ የልጅ ብስክሌት ወዘተ እንግዛ በሚል ሰበብ ከቤት ከወጡ ቢያንስ እስከ ግማሽ ቀን ሲኳትኑ ይውላሉ::

«እንኳን ማርያም ማረችሽ» ለሚል ጠያቂ በየአራስ ቤት እንደተለመደው ገንፎ፣ ዳቦ፣ ቆሎ፣ ጭኮ፣ ቋንጣ፣ ደረቅ ብስኩት፣ ለስላሳ፣ አምቦ ውሃ ብቻ መቅረብ እንደሌለበት አሰገደች ዮሐንስን አሳምናለች:: ሁሉም ጠያቂ እንደየተዋረዱ ቀን ከሆነ ምሳ፣ ማታ ከሆነ ራት እንዲበላ፣ ከመጠጥም ጠጅ፣ ውስኪ፣ኮኛክ እንዲጋበዝ ተወስኗል:: አሰገደች ለመውለድ ወሯ እስኪገባ የእንግዳ ማስተናገጃ ዝግጅት ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል:: አሰገደችም ዮሐንስም የሚወለደው ወንድ ነው በሚል ጉጉት ስም ሲያማርጡ ነው የከረሙት::

አሰገደችን በአራስ ጥሪ ለማስደሰት ዮሐንስ ብዙ ነገር ሲያወጣ ሲያወርድ ከርሟል:: አንድ ቀን መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ባለው ጽ/ቤት አረፍ ብሎ ከወርቅ አንባር እስከ አውቶ ሞቢል ሊሸልማት አማራጮችን በጽሑፍ እየደረደረ ባለበት ጊዜ አንድ ነገር ትዝ አለውና ብድግ ብሎ አማተበ::

«እርግዝናዋን በነገረችኝ ምሽት በብስጭት ገብቼ መፍትሔ ይሆናሉ በማለት ከደረደርኩት ዝርዝር ውስጥ በመጨረሻ የፃፍኩት አስገደችን <መግደል> የሚል ነበር:: ያ ቀርቶ ነው አሁን ስለምትወልድልኝ ልጅ ያራስ ጥሪ መኪና እስከ መግዛት ላንበሸብሻት የማስበው፣ ይችን ምስኪን ባልገድልም ገድያታለሁ:: ምን እሷን ብቻ ልጄንም እንጂ» በማለት ብድግ ብሎ ጎርደድ ጎርደድ ማለት ጀመረ:: «ምን አይነት ጽንፈኝነት ነው? ካንዱ ጫፍ ወደ ሌላ ጫፍ» አለ ዮሐንስ ስሜታዊነቱን እየታዘበ::

ያን ከአንድ እስከ አስር የመፍትሔ ዐሳቦች ያስፈረበትን ወረቀት ከጠረጴዛው ኪስ ውስጥ ፈለግ ፈለግ አድርጎ በማውጣት ከላይ እስከታች አነበበ:: <አስገደች ይህን አውቃ ቢሆን ኖሮስ?> ቆም ብሎ አሰበ:: «አቅሙ የላትም እንጂ፣ ሳልቀድማት ለመቅደም መፍጨርጨሯ አይቀርም ነበር» አለና አንድ ኃይል ከቢሮው ገፍቶ ያስወጣው ያህል ከጽ/ቤት ውልቅ አለ:: መኝታ ቤት ገባ አስገደች የለችም::

«አስጉ!» አለ ድምጹን ከፍ አድርጎ

«እዚህ ነኝ ጆ! የመጥምቁን ኮተት እያስናዳሁ ነው» አለች ሁለተኛው መኝታ ቤት አልጋ ላይ ርፍቅ ብላ::

«ምነው ምነው! በነጠላው! በነጠላው ሲሆን ላፍ ይከብዳል፣ መጥምቁ ዮሐንስ ማለት ነበረብሽ» እያለ አስገደች ወዳለችበት ክፍል ዘው አለና «እንቺ አንብቢው» ብሎ ወረቀቱን ከርቀት ወረወረላትና የምትለውን ለመስማት ቆሞ ጠበቀ::

አስገደች ከመቸኮሏ የተነሳ መጀመሪያ በወረራ ከላይ እስከታች ሔደችውና «ጆኒ ምንድነው አልገባኝም» አለች «መግደል! መግደል» ከሚለው ቃል ላይ ዓይኗን እንደተከለች::



«ይህ መጥምቁ ዮሐንስን መፀነስሽን የነገርሽኝ ዕለት ምሽት በደመ - ነፍስ ካንቺና ከፅንሱ ጋር ያለኝን ግንኙነት ለማቋረጥ አማራጭ ይሆናሉ ብዬ የገመትኳቸው የመፍትሔ ሀሳቦች ነበሩ:: በመጨረሻ በ4ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተፃፈው ሃሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ይኸው ዛሬ ለዚህ በቃን» አለ ዮሐንስ ፍርሃትና ጭንቀት በተቀላቀሉበት ድምጽ አንገቱን ሰብር አድርጎ::

«ዮሐንስ! ልትገድለኝ! ምነው ምን አረኩና ዘርህን በተቀበልኩኝ?» ብላ ስቅስቅ አለች:: ዮሐንስ የሚለው ጠፍቶት አልጋው ላይ እንደተቀመጠች እቅፍ አረጋትና «የኔ እመቤት! የኔ ፍቅር! እርሸው፣ ቅዠት ነው» እያለ እሱም ባባና አብሯት አለቀሰ::

«በቃ በቃ አስጉ፣ በቃ ከእንግዲህ ውሸን ያነሳ ወሾ ይሁን» አለና ወረቀቱን በጫጭቆ ጣለው::

***

ሥሉስ የዘረላት አስገደች ገና ከጧቱ የባለቤቷን ፍቅር፣ እመቤታና ከበሬታ አትርፋለች:: ለሁሉም ነገር «እሷ እንዳለች» መባሉን አስገደችን በውጭም በቤትም አዛዥ ናዛዥ እያደረጋት ነው::

ጋብቻቸው የእሷን ቤተሰቦች ፈቃድ እንጂ የዮሐንስ ወላጆች ልባዊ ቡራኬ አለማግኘቱ አስገደችን እንዳሳሰባት ዮሐንስም ተገንዝቦታል:: በዐል ቀናት ግቢ ሔዳ እጅ መንሳቷ መልካም ጅምር ቢሆንም ፈጥኖ መጎልበት እንዳለበት ዮሐንስ ያስባል:: የእሷና የእነሱ ግንኙነት መጠናከር ልጆቹ ከእስ

ቤተሰብ ጋር ለሚኖራቸው የወደፊት ዘላቂ ግንኙነት ዋስትና እንደሚሆን ዮሐንስ ያምናል::

አንዳንድ ጊዜ ዮሐንስ መሰስ ያደርግና፣ «እንደ እነሱ ካለ ወግ - አጥባቂ ብዙም መጠበቅ የለበትም» ይላል::

የዮሐንስ ወላጆች፣ ሰምኖ ሳይሆን ተለምኖ መገባት የነበረበት ልጃቸው እነሱ ወፍ - ዘራሽ - ጎርፍ - አመጣሽ ፍናጅ የሚሏትን በማግባቱ መጸጸታቸውን የደበቁበት ጊዜ የለም:: ዛሬም ወልዳ ከብዳ ባሰሟልነቷ ከእልፍኝ እስከ ጓዳ በዘለቀበት ጊዜ ያንን ይላሉ::

ጋብቻው ገና በሰጋነቱ እንዲቀጭ እመቤት ጽዮን - ሞገስ መጽሐፍ አስገልጠው የአሰገደች ኮከብ ከዮሐንስ ኮከብ ጋር ግጥም አይደሰም መባሉን የሰሙት በመረረ ሐዘን ነበር:: ሐዘኑን ይበልጥ ያከበደባቸው የጥንቆላውን ውጤት ሰባሰቤታቸውና ሰልጆቻቸው ደፍሮ ለመናገር አለመቻላቸው ነበር:: እቶ ሁንዴ በምድር ላይ የሚጠሉት ነገር ቢኖር ጠንቋይ መሆኑን ባሰቤታቸው ያውቃሉ::

አሰገደች የሁለት ልጆች እናት ከሆነች በኋላም እንኳ፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ «ዮሐንስ! ካልጠፋ ሴት ምናለ የሚበቃትን ያህል ገንዘብና ንብረትም ረጥበህ ይህችን ዘር አጥፊ ወዲያ ብትገላገል» በማለት ልጃቸውን ያስጨንቁታል:: ዮሐንስ ግን የእናቱን ምክር የማይቀበልበትን ምክንያት አንገቱን እያቅሰለለሰ አንደበቱን እያለሰለሰ ስለሚነግራቸው አይጫኑትም:: በአንድ ወቅት በነገሩ ከመበሳጨታቸው የተነሳ እንጦጦ ማርያም ሔደው አልቅሰዋል:: አልያዘላቸውም እንጂ ጋብቻው እንዲፈርስ



ተስሰውም ነበር:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ከአብራካቸው የተከፈሉትን ሕፃናት ሲያዩ ረገብ ይላሉ::

«የሚገርመው <ፍየልና ክፉ ሰው ሲረግሙት ይረባል> እንደተባለው ነው የሆነላት፣ ይህች መናጢ» አሉ አንድ ቀን አሰገደችና ልጆቿ እጅ ነስተው እንደ ወጡ::

ይህም ሁሉ ሆኖ አሰገደች ፈተናውን ተቋቁማ ትዳሯን ቀጥ አድርጋ ይዛለች:: ፈራ ተባ ይል የነበረው አንደበቷ ርቱዕ ሆኗል:: ወዘናዋና ቅርጿም ኑሮዋን መስሎላታል::

የአሰገደች እንደ እንዝርት መሾር፣ መኳኳልና መሽቀርቀር ደስ ያሰኛቸው አባቷ አቶ ደምሴ «....... <መልካም ሚስት ለባሏ ዘውድ ናት> የሚለውን ቅዱስ ተግባር የእኔ ልጅ ፈጽማዋለች» ይላሉ:: እናቷም ወ/ሮ ዘምዘምም ከጉልት ኑሮ ተገላግለው ኪዎስካቸውን በከፈቱና በዘጉ ቁጥር «ብድርሽን በዘር ማንዘርሽ አግኚው:: ረዥም ዕድሜ ከሀብትና ከጤና ጋር ይስጥሽ» በማለት አሰገደችን ይመርቃሉ::

* * *

ዮሐንስ ድሮም የሴት ጓደኞችን ይሰስት ነበር:: አሁን ደግሞ ሚስቱን ከሁሉም በላይ ይሰስታታል:: ከዚህም የተነሳ አስገደች ተቀጥራ የሌላ ሰው ታዛዥ መሆኗ ሁልጊዜም ይቀፈዋል::

«አሰገደች የራሷን ድርጅት አቋቁማ ለመሥራት የዕውቀትም የልምድም ብቃት አካብታለች:: በዚህ ላይ የእኔ እገዛ ሲታከልበት አሰገደችን ባለድርጅት የማድረጉ ዕቅድ ሥሙር

እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ» አለ ዮሐንስ አንድ ቀን አስገደችን ሙሉ በሙሉ የራሱ የማድረግ ስስቱን እያሰበ::

ዮሐንስ ይኸንን ዐሳብ ለአስገደች ለመሸሸግ አልተቸገረም:: አንድ ግሩም ምሽት ባልና ሚስት አልጋዎቻቸውን አጠጋግተው በድሪያ ቀልድ ላይ እንዳሉ፣ ዮሐንስ አንገቱን ከትራሱ ላይ ቀና አድርጎ «አንድ ነገር - አንቺ እስከመቼ ነው የሰው ተቀጣሪ የምትሆኚው?» አለ ግራሞትም ቁጭትም በተቀላቀለበት ስሜት::

አስገደች ለጥያቄው ቅጽበታዊ መልስ የሌላት መሆኑን በሚገልጽ ፈገግታ «እኔ እንጃ!» አለች ማኳሸቷን ተወት አድርጋ::

«ደህና! ከትምህርትሽ፣ ከልምድሽ እንደዚሁም ከዝንባሌሽ አኳያ ራስሽን ችለሽ ወይም ከሌላ ሰው ጋር በሽርክና ምን ለመሥራት እንደምትፈልጊ አስቢበትና ንገሪኝ» አለ ዮሐንስ::

«በግሩም ምሽት፣ ግሩም ሀሳብ፣ በግሩም - አስተዋይ ባል» አለች አስገደች ከአልጋዋ ውስጥ ወጥታ ወደ ዮሐንስ አልጋ እየተጋባች::



# ምዕራፍ 10

## የፊታ/ቤኛ ሞት

ፊታውራሪ ቤኛ ገዳ «የህክምና ርዳታ አልሻም» በማለት የአልጋ ቁራኛ ከሆኑ አንድ ዓመት ተመንፈቅ ሆኗቸዋል:: ልጃቸው አቶ ሁንዴ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪና የፊታውራሪም የልብ ወዳጅ የሆኑትን ፀባቴ ገብረ ሥላሴን ይዘው የአባታቸውን ዐሳብ ለማስለወጥ ያደረጉት ሙከራ አልተሳካም::

«ፊታውራሪ ጠንቶባቸዋልና ከማረፋቸው በፊት ቢመጡ......» የሚል ደብዳቤ የፊታውራሪ ንብረት አስተዳዳሪ ከሆነው የእህታቸው ልጅ በደረሳቸው ማግሥት ቤተሰቡና የቅርብ ነኝ ያለ ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ከአዲስ አበባ ነቅሎ ወደ አቢቹ ለመሔድ ተነስቷል::

አስገደችም በዓለሚቱ አማካይነት እመቤት ጽዮን ፈቅደውላት አብራ ትሔዳለች:: «ዘሯ ተደባልቋል፣ ተንግዲህ ምን ማድረግ ይቻላል» ነበር ያሉት እመቤት ጽዮን አስገደችም እንድትሔድ ሲፈቅዱ::

እናትና አባታቸው ለአቢቹ ጉዞ በማድረግ ላይ ያሉትን ዝግጅት የተመለከቱ ደረጀና ጌታሁን «እኛስ ለምን አብረን እንሄድም» በማለት ጠይቀው ነበር::

«ሽርሽር መሰላችሁ የምንሄደው? ቅድመ አያታችሁ ታምመው ነው□ኮ» አለ ዮሐንስ እራሳቸውን በሁለት እጆቹ እያሻሸ

«ሊሞቱ!» አለ ጌታሁን ደንግጦ::

«ጠንቶባቸዋል እንጂ ገና አልሞቱም::»

«ታዲያ ለምን አይታከሙም እንዳይሞቱ» የደረጀ ጥያቄ ነበር::

«እኛ የምንሔደው ለዚህ ሁሉ ነው» አለ ዮሐንስ ለልጆቹ ጥያቄ የግድ አጥጋቢ መልስ መስጠት እንዳለበት በማሰብ::

«እንደሱ ከሆነ አንተ ሒድ እማዬ ለኛ ትቅር» አለ ጌታሁን በልምምጥ አባቱን ቀና ብሎ እያየ::

«እሺ ካለቻችሁ ጠይቋት» አለ ጥያቄና መልሱን ወደ እሷ ለመግፋት::

«እሔዳለሁ አልቀርም ካለችስ» የደረጀ ሌላው ፈታኝ ጥያቄ ነበር::

«እንደሱ ካለች በቃ እኛ እንሔዳለን......»

«እኛስ»

«ትቀራላችኋ!»

እነደረጀ ባባታቸው ውሳኔ አኩርፈው እናታቸው የምትለውን ለመስማት እየሮጡ ሔደው በጥያቄ አጣደፏት::

«እናንተ ትምህርት ቤት ሲዘጋ ሔዳችሁ እዚያ መክረም ትችላላችሁ፣ አሁን ለቅሶ ነው፣ ልጅ ደግሞ ለለቅሶ አይሔድም» አለች አሰገደች እንደማባባል ብላ::

እነ ደረጀ ነገሩ ስላልተዋጠላቸው ለንበጫቸውን እንደጣሉ ከእናታቸው አጠገብ ገለል አሉ::

ለአሰገደች እንጂ ለሌላው አቢቹ አዲስ አይደለም:: ለእሷ ግን አዲስ አካባቢና አዲስ የሕይወት አጋጣሚ ነው የሆነላት::

አቢቹ የከተተው ዘመድ አዝማድ በዕድሜ፣ በፆታና በማዕረግ ከፍና ዝቅ እንደ ማለቱ፣ በግብር ጊዜ በቅደም ተከተል



ለማስቀመጥ፣ እንዲሁም አንዳንድ የጋራ ምክክር ሲደረግ ተሳታፊ የሚሆኑትን ለመወሰን ዮሐንስ፣ ዓለሚቱና የፊታውራሪ የንብረት አስተዳዳሪ መክረዋል::

ፊታውራሪ ከቀን ወደ ቀን ሕመሙ እየፀናባቸው ስለሔደ ቤተሰብ ስለ ሥርዓተ ቀብሩ አፈጻጸምና ከቅርብም ከሩቅ ስለሚመጣው ለቀስተኛ መስተንግዶ በሰፊው ተወያይቶ ዕቅድና ፕሮግራም ወጥቷል:: የሥራ ድልድልም ተደርጓል::

በምክሩ ላይ የተገኙት የፊታውራሪ አበ ነፍስ እስኪቀበር ድረስ አስክሬኑ ኪዳነምህረት ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሲቀደስበትና ዳዊት ሲደገምበት እንዲያድር ሀሳብ አቅርበው ነበር::

«አባቴ ሥርዓተ ቀብሩ የሚፈጸመው ደብረ ሊባኖስ ስለሆነ እናንተና ሌሎችም የአካባቢው ካሕናት እዚሁ ተሰባስባችሁ አስክሬኑ እስኪሸኝ ድረስ ፍታተ፣ ፀሎቱን፣ በተገቢው ሥርዓት መሠረት ታከናውናላችሁ:: የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ስለሚመጡ ሥርዐተ ፍታቱን እሳቸው ይመሩታል:: እርሶን አደራ የምልዎት ካሕናቱና ለሥርዐተ ፍትሐቱ የሚያስፈልጉት ንዋየተ ቅድሳት ተሟልተው እንዲገኙ ነው:: ለዚህ እንዲሟላላችሁ የምትጠይቁት ሁሉ ካሁኑ ይታዘዝላችኋል» በማለት አቶ ሁንዴ ከፊል ትዕዛዝ የሆነ ውሳኔያቸውን አሳወቁ::

አቶ ሁንዴ ውሳኔያቸውን ያዳምጥ የነበረውን የፊታውራሪን የንብረት አስተዳዳሪ ጠቀስ አድርገው «ስማ የሚፈልጉትን ሁሉ ይንገሩህና አሟላላቸው፣ ገንዘብም ቢሆን ከጠየቁህ ስጣቸው» በማለት አዘዙት::

«እሺ! ምን ጠፍቶ ሞልቷል» አለ አስተዳዳሪው እጅ እየነሳ::

የፌታውራሪ ግቢ የተቆረቆረው ዙሪያ - ገባውን አገር በቀላሉ ለማየት ከሚያመች ከረብታማ ቦታ ላይ ነው:: ከግቢው በስተቀኝ በጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በጋ ከክረምት የማይደርቅ የዐባይ ገባር ወንዝ አለ:: የወንዙ ግራና ቀኝ በአግባቡ ሲጠበቅ የኖረ ደን ለብሷል:: ደኑን የዱር እንስሳት መኖሪያና መራቢያ እንዲሆን ለማድረግ መቻላቸውን ፊታውራሪ በኩራት ይናገሩታል::

ከግቢው በስተግራ ትይዩ ባለው ሌላ ጉብታ ቦታ ላይ ፊታውራሪ ያሳነፁት የቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ጉብ ብሏል:: የቤተክርስቲያኑ አፀድና የቀብር ሥፍራ ከሁለት ጋሻ መሬት በላይ ነው:: በፊታውራሪ ግቢ ዙሪያ በጠርብ በአጋምና በቀጋ የታጠሩ ሁለት ዕድሞች አሉ:: በዕድሞቹ ውስጥ ከ30 በላይ ቤቶች ሲኖሩ ቤቶቹ የጋሻ ጃግሬዎችና የአሽከሮች መኖሪያዎችን እንዲሁም የጥገቶችን፣ የበግ፣ የፍየል፣ የፈረስና የበቅሎ ጋጦችን ይጨምራሉ::

አስገደች የግቢው ስፋትና አደረጃጀት በጣም አስደንቋታል:: በአገኘችው አጋጣሚ ያገኘችውን ሰው ሁሉ በመጠየቅ ስለ ግቢውና ከግቢውም ውጭ ስላሉት አንዳንድ ነገሮች ስትረዳ ከርማለች:: አስገደች በተለይ የጥገቶቹንና ጥጆቻቸውን ጋጣ ስትጎበኝ አንድ ያልጠበቀችው ስሜት መጣባትና እንደ መረበሽ አለች:: ደግነቱ ዮሐንስና ዓለሚቱ በዚያ አካባቢ አልነበሩም::

የፊታውራሪን በጠና መታመም እየሰማ አንዳንዱም ዐርፈው ይሆናል በማለ ግምት እየመጣ ግቢው ሰው በሰው ሆኗል:: ሰው ቢጎርፍም በውጭ ጠይቆና ተስተናግዶ ከመሔድ



በስተቀር ፊታውራሪ ዘንድ ቀርቦ እግዜር ይማርዎት ለማለት አይችልም ነበር:: እቶ ሁንዴ ከመጡበት ቀን ጀምሮ ከፊታውራሪ አበ ነፍስና አንድ ዲያቆን ጋር ፊታውራሪ ከተኙበት ክፍል አጠገብ አንድ ሰፋ ያለ ክፍል ውስጥ ሆነው ሁኔታቸውን እየተከታተሉ ናቸው::

ፊታውራሪ ቤኛ አካላቸው ከበደኑ 48 ሰዓት ያስፈው ቢሆንም መሞታቸው ይፋ የሆነው እርብ ከሰዓት በኋላ ነው:: ማረፋቸው እንደተሰማ በዚያ የተገኘው ሁሉ እርሙን እንዲያወጣ ተፈቅዶ ለቅሶ ተጀመረ:: እንደርችት የሚቆጠር በእግረ መንገድ አካባቢውን ማንቂያ፣ የግባት ተኩስ ተስተጋባ::

አስገደች ግን ምን ብላ፣ እንዴት ብላ እንደምታስቅስ ግራ ስለተጋባች ወደ ክፍሏ ሔዳ ብቻዋን ኩርችም አለች:: ወላጆቿ ለለቅሶ የሚመጡበትን ሁኔታ ባለማመቻቸቷ አዘነች:: መሞታቸውን ተጠያይቀው ሌላው ሰው እንደሚመጣ መምጣት ይችሉ ነበር:: እኔ ነኝ ኃላፊነቴን ያልተወጣሁት ደደብ በማለት በራሷ ዐዘነች::

እስከ ማታ ለቅሶው ቀጥሎ ወደ ሁለት ሰዓት ላይ አጋፋሪ ከበደ «በቃ! ለዛሬው ይበቃል» በማለት ድምፁን አሰምቶ ለፈፈ::

በማግስቱ የፊታውራሪ የማዕረግ አልባሳት

– በብርና ወርቅ ሙካሽ የተሠራ ለምድ፣
– ባለሁለት የወርቅ ጥብጣብ ስጡ በወርቅ የተሠራ ቀሚስ፣
– ባለሁለት የወርቅ ነጠብጣብ ስጡ በሐር የተጠለፈ አብደላ ካኒ፣
– የመብሩቅ ሱሪ፣

- መናኛ ድርብ፣
- የሻሽ ድግፍ፣
- አጀታው አውራሪስ የሆነ ባለወርቅ ቅብ ሙጣና ጫሜ ያለው ጓራዴ፣
- ባለወርቅ ጋሻ ጣፋ፣
- በሐር ጥልፍ የተሠራ የበቅሎ ዕቃ፣
- ከብር ጌጣ ጌጥ የተሠራ የፈረስ ዕቃ፣

እንዲሁም

- የተሸለሟቸው ኒሻኖችና ሜዳልያዎች፣
- አዳኝነታቸውን የሚያረጋግጡ ሎቲዎችና በምስክርነት የቀረቡ የወግ እቃዎች፣
- ከጣምራ ጦር እስከ ዘመናዊ ጠመንጃዎቻቸው

በአልጋ መልክ ተሰርቶ በነጭ ጨርቅ በተሸፈነ ከፍ ያለ ቦታ እንደ ወግ ማዕረጋቸው ተሠትረው ሕዝብ እንዲያያቸው ተደርገዋል:: የተለያየ መጠን ያላቸው ፎቶ ግራፎቻቸው ዋናዎቹ ማስለቀሻዎች ናቸው:: ቀሚስ የለበሱ ፈረስና በቅሎም ማለፊያ በለበሱ ባልደራሶች እየተሳቡ መታየት ለቅሶውን ይበልጥ አድምቀውታል::

የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ከፊታውራሪ ጋር በነበራቸው የግል ወዳጅነት ጭምር ከአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት የተሰባሰቡትን ካሕናት ሥርዓተ ቅዳሴና ሥርዓተ ፀሎት እስከ ሣልስቱ መርተውታል::

ያገሬው ሕዝብ በፈረስ በፈረስ ሆኖ የጦር መሣሪያ ጭምር አንግቦ የፊታውራሪን ታላቅነት፣ ጀግንነት፣ አዳኝነትና ለጋስነት በቅብብሎሽ እያሰማ ይፎክራል::



ሁለት ቀን ሙሉ ከደብረ ብርሃንና ከሸዋ ጭምር በመጡ አልቃሾች ከጥፍር ውስጥ እምባ በሚያስወጣ ሙሾ ድርደራ ተለቅሶ፣ በሣልስቱ የቀብሩ ሥርዓት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈፀመ:: ፊታውራሪ የተቀበሩት ከ20 ዓመት በፊት ባለቤታቸው ወ/ሮ አበራሽ ቱፋ ከዚህ ዓለም በተለዩ ጊዜ ባሠሩላቸው መቃብር ቤት ነው::

አቶ ሁንዴና ቤተሰቡ እስከ ∀ሰባቱ∀ በዚያው አስተዛዛኙን ሲቀበሉ ከርመው በሳምንቱ መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ:: እንደ ተመለሱም ለቅሶ መቀመጣቸውን የሰማ ታላላቁ ሰው ሁሉ ግቢውን አጨናንቆት ከረመ::

አሰገደች በየአጋጣሚው አማቶቿን እጅ በመንሳትና «እንዴት አደርሽ?» ስትባል መሰንበቷን ወድዳዋለች:: የሁለት ልጆች እናት እስከሆነችበት በእስከዛሬ ቆይታዋ ከአማቶቿ ጋር ይህን ያህል መቀራረብ ኖሯት አያውቅም:: አሰገደች ግቢ የምትሔደው በአብዛኛው በታላላቅ ዓውዳመቶች «እንኳን አደረሳችሁ» በማለት እጅ ለመንሳት ነው::

# ምዕራፍ 11

## አሰገደችና ራሔል

አሰገደች ሦስተኛ ልጇን ቅሪት ነች:: በየወሩ ዶክተር ሶኮሎፍ የግል ክሊኒክ እየሔደች ትመረመራለች:: ክሊኒኩ በማኅፀን ሕክምና ከሌሎች ሁሉ የተሻለ ነው የሚል ስም አለው:: የልዕልታትም ደንበኞች አሉት::

የዶክተር ስኮሎፍ መደበኛ ሥራ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቤተ! ሳይዳ ሆስፒታል ሲሆን በግል ክሊኒካቸው የሚያክሙት በቀጠሮ የሚመጡ ደንበኞችን ነው:: አሰገደች ሁለቱን ልጆቿን የተገላገለችው በእሳቸው እጅ ነው::

አሰገደች እንደተለመደው ለፅንስ ምርመራ ዶክተር ሶኮሎፍ ክሊኒክ ሔዳ ወረፋ በመጠባበቅ ላይ ነች:: ነርሷ ታካሚን ወደ ምርመራ ክፍል ታስገባለች:: የጨረሱትን ሸኝታ ተረኛዋን ትጠራለች:: አሰገደች ተራዋ እስኪደርስ በያዘችው መጽሐፍ ላይ ዓይኗን ተክላለች:: በቃሬዛ የገባች አንድ ወላድ በአጭር ጊዜ ተገላግላ ስትወጣ በዚያ ያሰው ታካሚና አሳካሚ «እንኳን ማርያም ቀረበችሽ» እያሉ ደስታቸውን በመግለጽ ላይ እንዳሉ ነርሷ አንድ የታካሚ ካርድ ይዛ ብቅ አለችና «ስማችሁን አዳምጡ» አለች:: ሁሉም አንገቱን አቅንቶ ጆሮውን ሲቀስር ወ/ሮ ራሔል አበራ ብላ በዓይኗ ራሔልን ቃኘት ስታደርግ ከአሰገደች መደዳ ሦስተኛዋ ሴት ብድግ ብላ ወደ ማዋለጃው ክፍል አመራች አሰገደች ባለችበት ውሃ ሆና ቀረች:: ሳይታወቃት «ራሔል አበራ! ራሔል አበራ!» አለች አጠገቧ የተቀመጡት ሰዎች እስኪለሟት ድምፅ አውጥታ:: ድምጿ የቀሰቀሳቸው ሰዎች ትክ ብለው



እየተመለከቷት አሰገደች ደመ - ነፍሷን ብድግ ብላ ወጣች:: የራሔልን ስም መጥራቷ ትዝ አላትና «ምን ቀባጥሬ ይሆን?» በማለት በዐሳብ ወደ ኋላ አጠነጠነች::

አሰገደች እንደምንም እየተጎተተች መኪናዋ ጋ ደርሳ ከፍታ ገባችና ፊቷን ወደ ክሊኒኩ መልሳ ራሔልን ስትወጣ በማየት፣ እውነት ያች እርሷ የምታውቃት ራሔል አበራ መሆን አለመሆኗን ለማረጋገጥ በጉጉት ጠበቀች:: ጥቂት ቆየት ካለች በኋላ «ራሔል ሆነች አልሆነች ምን አስጨነቀኝ» በማለት መኪናዋን አስነስታ ለመሔድ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለች ራሔል ከክሊኒኩ ወጥታ በቀጥታ አሰገደች ወዳለችበት በቅሪት ርምጃ አዘገመች:: «ወደ እኔ ነው እንዴ የምትመጣው?» በማለት አሰገደች እንደገና ጭንቀት ውስጥ ገባች:: ራሔል ግን የአሰገደችን መኪና ታክካ አልፋ የራሷን መኪና ከፍታ ገባች::

«የግቢው ቅዱስ ገብርኤል አደራህን አንተ ጠብቀኝ ከዛሬው ምስቅልቅል ሁኔታ በመስቀልህ ከልለህ አውጣኝ» አለችና ከንብንቧን ዓይኗ ድረስ ዝቅ አድርጋ ራሔል እስክትሔድ ጠበቀች:: የተማፀነችው ቅዱስ ገብርኤል ለአሰገደች ዘብ ቆሞ ራሔል በሰላም ሔደችላት:: አሰገደችም እዚያው ከተቀመጠችበት ሦስት ጊዜ ሰውነቷን አማትባ ወደ ቤቷ በዝግታ ነዳች::

ግቢው ጭር ብሏል:: አሰገደች ከመኪናዋ ስትወርድ የተቀበሏት ድንክ ውሾቿ ናቸው:: ቦቢ፣ ኩርፎና (ፉንጊት) መቻል በእግሯ መሐል እየሾለኩ ዡራያዋን እየተሽከረከሩ ለእመቤታቸው በውሻ ፍቅር አቀባበል አደረጉላት:: የቤት ሠራተኛዋ የምድር ዓሰም ጫማዋን ለማውለቅና ትዕዛዝ ካለ ለመቀበል እጅ ነስታ እስከ መኝታ ክፍል ተከተለቻት:: አሰገደች

ያለ ወትሮዋ በዝምታ ተውጣ እግሯን እየጎተተች ገብታ አልጋው ግርጌ ካለው ፎቴ ላይ አረፍ አለች:: የምድር ዓለም ጫማዋን አውልቃ የቤት ጫማ አቅርባላት ወጣች::

«ያስቡት አይገድ» አለች ጥቂት እንደመሳቅ ብላ:: «መቼም የራሔልን እዚህ አገር መኖር ዮሐንስ አያውቅም ለማለት አይቻልም:: ታዲያ እንዴት አይነግረኝም? በስህተት እንኳ ስሟን አንስቶ አያውቅም:: ግን ምን ብሎ ሊነግረኝ ይችላል?» አለችና ራሔልንና ዮሐንስን በምናቧ መሳል ጀመረች:: ይኸንኑ ስታወጣ ስታወርድ ዮሐንስ ልጆቹን ከትምህርት ቤት ይዞ መጣ::

እነ ደረጀ እናታቸውን ስመው እንደወጡ ዮሐንስ ገባ::

«ዛሬስ ከብዶሻል» አለ ዮሐንስ ሊስማት እየቀረበ::

«መክበድ ብቻም አይደል፣ ጤናም የለኝ::»

«ዛሬ ክሊኒክ ቀጠሮ አለኝ ብለሽ አልነበር፣ እንዴት ሆነ?»

«ስላልተመቸኝ አልሄድኩም::»

«አሁን እንሂዳ!»

«አይ ነገ ይሻላል» አለችና አስገደች ከፎቴው ላይ ተነስታ አልጋው ላይ ጋደም አለች:: ዮሐንስም ወደ ጽሕፈት ቤት አመራ::

ራሔል ትምህርቷን ጨርሳ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሰች አንድ ዓመት ሆኗታል:: በፓሪስ ቆይታዋ በዮሐንስ እግር የተተካ ጓደኛ አፍርታለች:: እሷና ጓደኛዋ ወደ አዲስ አበባ የተመለሱት በእነሱና በየወላጆቻቸው መካከል ስምምነት የተደረሰበትን የጋብቻ በዓላቸውን ለማክበር ነበር:: አስገደች ጣውንቷን ያየቻት ራሔል የመጀመሪያ ልጇን የአምስት ወር ቅሪት ሆና ነው:: አስገደች



ይህንን መረጃ ለማግኘት የወሰደባት ጊዜ ከአንድ ሣምንት አይበልጥም - ዕድሜ ለገንዘቧ::

***

ዮሐንስ ሀሳቡ ሠምሮ ዕቅዱ ተግባራዊ ሆኖ አስገደች ዶ/ር ወልደ ሚካኤል ማዴቦ ጋር ካዛንቺዝ አካባቢ አንድ ክሊኒክ በሽርክና አቋቁመው መሥራት ከጀመሩ ዓመታትን አስቆጥረዋል:: ዶ/ር ወ/ሚካኤል በእናቷ በኩል የዓለሚቱ የሩቅ ዘመድ ናቸው:: አቶ ሁንዴ ደቅለዋት በእናቱ እመቤት ጽዮን-ሞገሳ መልካም ፈቃድ በአባቷ ቤት ያደገችውን ዓለሚቱን ዮሐንስ እንደ እህትም እንደ ወንድምም ነው የሚቆጥራት:: በርካታ ወንድምና እህት ባላቸው ጓደኞቹ ይቀና የነበረው ዮሐንስ ወልዷል - ከብዷል በዚህም ይኩራራል::

በሌላ ወገን፣ አንድ እህቱ የመጣላትን ባል ሁሉ መልሳ ቆማ በመቅረቷ ዮሐንስ ያዝናል:: «ዓለም እኔና አንቺ እንዳህያ ጡት ሁለት ነን:: ለቤት ሙሉ እህትና ወንድም አልታደልንም:: ሌላው ቢቀር ዘር ለማብዛት ብለሽ እንኳ ብታገቢ ምን ይመስልሻል?» ይህ የዮሐንስ የዘወትር ልመና ነው::

«ማን ባል ማን ሚስት ሊሆን? እኔ ባል ብሎ ነገር አይታየኝም:: በጋብቻ ስም ተፈጥሮ ያደለችኝን ነፃነቴን በብር ሣህን ላይ አድርጌ በገዛ ራሴ ለሌላ ሰው አሳልፌ የምሰጥ ደካማ ፍጡር አይደለሁም:: አስፈላጊ ከሆነ ሚስት ሳይኮን ዘር ማፍራት ይቻላል» በሚለው የዓለሚቱ አስተያየት ላይ ደፍሮ አስተያየት የሚሰጥ ሰው የለም:: የዓለሚቱ ዲቃላነት በአመለካከቷ ላይ ብርቱ ተፅዕኖ እንዳሳደረባት ስለሚገምቱ ክርክር የሚገጥም

የለም፡፡ አባቷም ቢሆኑ «ተዋት እንዳሰኛት ትሁን ጊዜ
የፈቀደው እስከሆነ ድረስ የግል ሕይወቷን በተመለከተ ጉ
ጣልቃ መግባት አያስፈልግም» በማለት ቆሞ ቀርነትን እንደነው
ላለመቁጠር ሽፍንፍን ያደርጓታል፡፡

አሰገደች በቤተሰቡ ውስጥ ያላት ተቀባይነት በድር
ስለሆነ በዚህ ዓይነቱ ውይይት፣ ክርክር፣ ጥያቄና መ
እምብዛም አትሳተፍም፡፡ የአሰገደች ዐቢይ ትኩረት ልጆ
መንከባከብና ሥራዋ ሆነዋል፡፡ ሥራ ከበዛባት አዳር - በቀረው
ማምሸት ትጨርሰዋለች፡፡

ዮሐንስም ብዙ ጊዜ እያመሸ ስለሚገባ ባልና ሚስት የ
ለምን እንዳመሹ አይጠያየቁም፡፡ አሰገደች አንዳንድ ጊዜ ወላጆ
ቤት ወይም ሌላ ቦታ በሌላ ምክንያት ብታመሽም ያው ሥ
በዝቶባት እንዳመሸች ነው የሚቆጠረው፡፡

ልጆቻቸው ግን አፍ አውጥተው ባይናገሩም በወላጆቻቸ
ማምሸት ቅሬታ አላቸው፡፡ «እናንተ ሌላ ቤት አላችሁ እን
ሁልጊዜ የምታመሹት?» አለች ማርያማዊት አንድ ቀ
አምሽተው የመጡትን ወላጆቿን ለመቀበል በረንዳ ላይ ቆማ፡፡

«በማምሸታችን አኩርፈሽ ነዋ! ሮጠሽ መጥተ
ያልሳምሽን?» አለ ዮሐንስ በሁለት እጁ ወገቧን ይዞ ጣ
እስከትነካ ጢል አደርጎ፡፡

«አምና!» ብላ እናቷን ለመሳም ተንደረደረች፡፡

«የሚሪ ጥያቄ ሁላችንንም ይወክላል» አለ ደረጀ የምሩ
ቀልድ አስመስሎ፡፡



«እኔ ልዳኛችሁ፣ በሉ ክሳችሁን........» በማለት ዮሐንስ ወቀሳውን ወደ እናታቸው ለመግፋት ሲሞክር መልኬ «ጆኒ አራዳ! አራዳ!» እያለ አባቱ ላይ ተጠመጠመ፡፡

«ማን ይዳኝ ታዲያ! እናንተው ከሳሽ፣ እናንተው ዳኛ ለመሆን አትችሉም» አለ ዮሐንስ እዚያው በረንዳ ላይ ከአሰገደች ጋር ቆሞ፡፡

«ጆኒ እኛ ከሳሽ ስለሆን መዳኘት ካልቻልን አንተና እሰጉም ተከሳሾች ስለሆናችሁ ዳኛ ልትሆኑ አትችሉም ማለት ነው፡፡»

«ደሬ ልክነህ በስምምነት ዳኛ እስክንሰይም ክሱን በይደር አቆይተን ወደ ቤት እንግባ!» በሚለው የዮሐንስ ዐሳብ አስታራቂነት ክርክሩ ቆመ፡፡

ልጆች ወደ ደብተራቸው ሲመለሱ ወላጆች ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ ልብስ ለመቀየር፡፡

«እነዚህ ልጆች□ኮ! እውነት አላቸው፡፡ ሥራው በፕሮግራም ታቅዶ ካልተመራ ለልጆቹ መስጠት ያለብሽን ጊዜ መሻማቱ ሲቀጥል ነው፡፡ እስከመቼ? በተለይ ሚሪ ያንቺን ትኩረት እየፈለገች መሰለኝ፡፡»

«ምን ጎደለባቸው? አጉል መሞላቀቅ» አለች አሰገደች የልጆቹን ቅሬታ ገሸሽ ለማድረግ፡፡

«ተይ! ተይ! በልጆቼ ቀልድ የለም፡፡»

«በልጆቼ!» አለች አሰገደች ድምፅዋን ናር አድርጋ፡፡ «ልጆችህ ያንተ የብቻ ከሆኑ አንተው.....»

«ጀመርሽ እንግዲህ ቁምነገሩን ወደጎን ገፍተሽ የነገር ጉጥ ለማውጣት» አለ ዮሐንስ አሰገደች ተናግራ ሳትጨርስ በመኻል አቋረጧት፡፡

# ምዕራፍ 12

## አክሊሉ ከጦር ሠፈር እስከ ጉራንጉር

አክሊሉ ሰለሞን፣ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በጂማ መንገድ፣ ቢያጆ በመባል የሚታወቀው የምድር ጦር ትራንስፖርትና ጽሕፈት ኮርስ ማሰልጠኛ ባልደረባ ነበር:: ወደ ቢያጆ የተዛወረው አንድ ዓመት ያህል በምድር ጦር ሙዚቀኛ ሻምበል ውስጥ በድምፃዊነት ካቀነቀነ በኋላ ነበር::

«ወታደር ከሆንኩ ወታደር እንጂ አዝማሪ መሆን የለብኝም፣ ወላጆቼስ ምን ይሉኛል?» በሚል በጎንደሬ ስምና ዝና ወዳድነት ተገፋፍቶ፣ አለቆቹን በመለማመጥ በሹፌርነት ለመሠልጠን ወደ ቢያጆ ተዛወረ::

ከስድስት ወር ሥልጠና በኋላ በ3ኛ ክፍለ ጦር፣ በአንደኛ ብርጌድ፣ ሁለተኛ ሻምበል አራተኛ የመቶ ተመድቦ ሥራውን ቀጠለ:: አክሊሉ ባገር ቤት ጎንደር የእስቴ መካነ ኢየሱስ ደብር ግልገል ድብትርናው፣ የበኋላውም ግልገል ሙዚቀኛነቱ ለውትድርናው ሥነ ምግባርና ሥምረት አስተዋጽኦ አድርገውለታል:: ያቅራራል፣ ይሸልላል፣ ይፎክራል:: ሲያሰኘውም ያንጎራጉራል:: አለቆቹም ይኸንን ስለሚወዱለት «እስቲ አንቆርቁረው!» ይሉታል:: ከመመስጣቸው የተነሳ አንዳንዶቹ ያጅቡታል::

የጎንደር ልጅና እሳት አንድ ናቸው፣
ሥጋን - ጥብስ - ቅቅል አርገው መብላታቸው::
ምን ያለው ወታደር ምን ያለው ጎንደሬ፣
ይበላ ጀመረ የሰው ሥጋ እንዳውሬ::



ደሜም ተመጠጠ፣
ሥጋዬም ቀለጠ፣
አጥንቴም ይኸው፣
እርሱ የበላው::
ጨረሰው!
ጨረሰው!
ጨርሶ በላው፣
ምንም አልቀረው::
ፍቅር ነው፣
ነፍስ ነው፣
የፍቅር መምሬ፣
ዝይኑ ጎንደሬ::

ይላል የመኪናውን መሪ በአንድ እጁ እያቃና በሌላው እጁ ራሱን እየደባበሰ::

ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ነሸጥ ሲያደርገው:-

እናንት ትላላችሁ ተኩሰን አንስትም፣
እኛም እንላለን ቃታ እናስከፍትም፣
ልቢቱ፣ ልቢቱ፣ ወይ ልቢቱ፣
በሳንጃ ተከፍተሽ የማትታይቱ::
ጦር ይምጣ! ጦር ይምጣ! ጦር ይምጣ አትበሉ፣
አሉብን ወንድሞች አጥር የማይዘሉ::
መዝለሉን ይዘላል እንሸሽ ካሉት፣
ወደኋላ ዞሮ መንገድ ከመሩት::
ፈሪ ዘረጥራጣ ፈሪ ዝርምቡጣ፣
ወደኋላ ሲሸሽ ዓይን አለው ከቂጡ::

በአየር ሲወረወር፣
አይገድበው አጥር።
እንቅፋት አይመታው፣
ዳገት አይበግረው።
መቼ ቂጡ ብቻ እግሩም ነው ዓይናማ፣
እንደ ቀን ብርሃን ነው ሲሸሽ በጨለማ።
የመንደር ፉደታ እጁ ደም አይነካም፣
መንካቱን ይነካል ሁለት አውራጣቱን፣
የወገቡን ቅማል የገደለበቱን።
በማለት ያቅራራና
የፋሲል ሎሌ የቴዎድሮስ፣
ጠላቱን ሳይጥል የማይመለስ፣
አገሩ ጎንደር መሐል ፎገራ፣
በኤም ዋኑ የሚያንጠራራ፣
በኤም ዋኑ ጠላትን አጭዶ፣
የጠላት ምሽግ ሰባብሮ ንዶ፣
የተበራየ አረገው ነዶ።

ግፋ ወደፊት ሆ! ብለህ ግባ
ውቃው!
ደባልቀው!
አርገው ገለባ።
ነፍሱን ለሴጣን ስጋውን ላውሬ
ቅዳው!
ደምብቀው!
የደሙን ኩሬ፣



ያገሬ ልጅ አይበገሬ፣
የወንዶቹ ወንድ እስቴው ጎንደሬ።
በማለት ይፎክራል

አክሊሉ ክሚወደው የውትድርና አገልግሎት የተለየው ያሽከረክረው የነበረ ትራኪርተር የሚባል መለስተኛ የሰውና የዕቃ ማጓጓዣ ወታደራዊ መኪና ከተቀበረ ፈንጂ ላይ ወጥቶ አደጋ ከደረሰበት በኋላ ነበር።

ሁለት ዓመት ያህል በሐኪም ቤትና በማገገሚያ ሲረዳ ቆይቶ በሕክምና ቦርድ ውሳኔ መሠረት ከሠራዊቱ ተሰናበተ።

ከስንብቱ በኋላ እስቴ መካነየሱስ ደብር ወላጆቹ ዘንድ አንድ ዓመት አዋዩን አሳርፎ፣ ሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ መጣ። አክሊሉ ለጥቂት ወራት ዘመድ ቤት በእንግድነት ከቆየ በኋላ፣ በአዲስ አበባ ኑሮ የሰው ሽክም መሆን ስለከበደው ቤት ተከራይቶ ወጣ።

አክሊሉ የተከራያት፣ ኖራ ሽው የተደረገባት፣ የካርቶን ኮርኒስ የገባላት፣ አንድ አልጋ የምታዘረጋ፣ አንድ ጠረጴዛ ከ4 ወንበሮች ጋር የምታዳብል የወ/ሮ ይፍቱ ሥራ ደመቀ ኩሽና ነች።

ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ የጋመረች ልጃገረድ እናት ናቸው። እርሳቸውም ቢሆኑ የባለቤታቸውን ሰባት ዓመት እስኪያስቆርቡ ተጠበቁ እንጂ፣ እጃቸውን ገና ለእድሜ ጫና ያልሰጡ አዛውንት ናቸው። ገላቸው የወንድ ጠረን መናፈቁን አላቋረጠም። «ያገር ባል» በመባል ይታሙ የነበሩት ባለቤታቸው አቶ ተሰማ ይመር በርካታ ኮማሪ ቁባቶች ነበሯቸው። መጠጥና ሴት ሲያሳድዱ

በመጨረሻ መንጠው ነው የሞቱት:: የሸዋዬ እናት ማዕድ ቤታቸውን ኳኩለው ያከራዩት ኑሮ ስለከበዳቸው ነው::

«ይሄ ደግሞ ምንድነው? ተከራይ ወይስ ቆጥ አስር?» የሚለውን የመንደሩን ሴት ሹምጥጫ እናትም ልጅም ሰምተውታል::

«እኔ ይፍቱ ሥራ ደ̃መቀ የረገጥኩት ድንጋይ ሲፈነቀል...ገና ምኑ ተያዘና!!» ʻበማለት ሲውረገረጉ ነው የሰነበቱት:: .... ለሽሙጥ ምላሽ መሆኑ ነው::

አክሊሉ ባይተዋርነቱ ሲጫነው እንደ ለመደው ያንጎራጉራል:: አልፎ አልፎም ክራሩን ይደረድራል:: ከመንደሩ ሴት ለአክሊሉ እንጉርጉሮና ሰንጎ መገን ጆሮ ያላዋሰች የለችም:: ወንዱ ግን እምብዛም አልወደደለትም::

«ይች አሮጊት፣ ካላጣችው ሰው አዝማሪ አምጥታ ሠፈሩን ፀጥታ ነሳችው□ኮ!» አለ በሚስቱ ቀልብ መሳብ ውስጥ ውስጡን የተከነው ባልቻ ገቢሣ ለቡና እድምተኞቹ::

«ለምን አገር ፍቅር አይገባም....አዝማሪ!» አለ በእነ ባልቻ ቤት የማምሻ ቡና ላይ ከነበሩት ጎረቤቶች አንዱ::

«ኦ! ኦ! ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ እንዳይሰሟችሁ» አለች የባልቻ ሚስት::

«አንቀልባ አውሻትና አዝላው ትዙር ጉዳያችን አይደለም» አለች ሌላዋ ቡና አጣጭ::

«እውነቷን ነው! እውነቷን ነው!» አሉ ወንዶቹ::

አዳሜ ያልበላውን ቢያክም፣ ወ/ሮ ይፍቱ ሥራና ልጃቸው የአክሊሉን ቁጥብነት፣ ጥርብርብነት፣ በተለይም በጊዜ



መሰብሰቡን ወደውለታል:: ለቤተሰብ አባልነትም እየፈቀዱት ናቸው::

ወጣትነቱና ወንዳወንድ ቁመናው ከሁሉም በላይ ጎንደሬነቱ፣ ድኽነቱን ይሸፍኑለት ይመስል አክሊሉ አንገቱን የደፋ ወጣት አይደለም:: አረማመዱ «ሆድ ወደ ውስጥ ደረት ወደ ውጭ» የተባለ ወታደር ይመስላል:: የደኻ ኩሩ ነው:: ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ «ቡና ጠጣ» ብለው ሁለት ጊዜ ካላኩበት በአንዴ ጥሪ ንክች አድርጎ እግሩን አያነሳም:: እርሳቸውም ይኽን ቁጥብነቱን በይፋ ባይናገሩለትም ወደውለታል::

ሸዋዬ ተሰማ ከአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ ከእናቷ ጋር የምትኖር የጋመረች ልጃገረድ ነች:: አጎጠጎጤዋ አበባ አውጥቶ ከዘረዘረ ከረምረም ብሏል:: ሸዋዬ የተቀጣላት የቀበሌ ኪነት አቀንቃኝና አስተዋዋቂ ሆና ማገልገሏን እናቷ ባይወዱትም አይቃወሙም::

አንድ የግል ታይፕ ት/ቤት ለስድስት ወር የተከታተለችው ኮርስ ሥራ ሊያስገኝላት ስላልቻለ፣ እንዳመቸ ቀንም ማታም ቀበሌ አካባቢ አንዳንዴም ከዚያ ራቅ በማለት ወጣ ገባ እያለች ኑሮን ተያይዛዋለች:: ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ «ገባሽ - ወጣሽ» የማለቱ ቁጥጥር ሰልችቷቸው እርግፍ አድርገው ከተውት አንድ ዓመት ሆኗቸዋል::

ሸዋዬ ከብሩህ ገጽታዋ ጋር ፍርጥም ያለ አካል ያላት ደመ-ግቡ ነች:: አካሄዷ ነጠቅ ነጠቅ ስለሆነ የዳሌዋና የጡቶቿ እንቅስቃሴ አረማመዷን ቁንጠኛ አድርገውታል:: «ከውሻ ክራንቻዋ መሾል በስተቀር የፊት ጥርሶቿ የወተት አረፋ ነው የሚመስሉት:: «ድኽነት ባይጫናት፣ ፀጉሯን ብትሠራ፣ ጥሩ

ጥሩ ለብሳ ሹል ጫማ ብትጫማ ሸዋዬ እኮ ልዕልት ሣራን ታሳስታለች» ይሏታል አንድ ጎረቤታቸው፣ የቀድሞ የክቡር ዘበኛ ባልደረባ፡፡ በድንቡሽቡሽነቷ አንቺ የሥጋ ከብት የሚሏት ሰዎችም አሉ፡፡

አንድ ቀን አክሊሉም ሸዋዬም በየበኩላቸው ሥራ ፍለጋ ሲዋትቱ ውለው ወደየቤታቸው በመመለስ ላይ እንዳሉ በረዶ የቀላቀለ ዝናብ ወቃቸው፡፡ ከዝናሙ ለማምለጥ ቸፍቸፍ ሲሉ ከአጥር ውጭ ተገናኙ «ወይ የዛሬ ዝናብ» አለች ሸዋዬ፡፡

«ደርሰናል በሩጫ እምልጠናል» አለ አክሊሉ፣ እንዲሁ እያሉ ተንደርድረው ሳይገባበዙ የአክሊሉን ቤት ከፍተው ገቡ፡፡

«ጥቁር እንግዳ» አለ አክሊሉ፡፡

«እብረን ከርመን የምን ጥቁር እንግዳ» እያለች ሹራቧን አውልቃ ማራገፍ ቀጠለች፡፡ በዝናብ የሾቀ ቀሚሷ ገላዋ ላይ ጥብቅ ብሎ መላ አካላዊ ቅርጽዋን አሳየባት -ጉያዋን ጭምር፡፡

ዝናሙ እያየለ የበረዶውና የቆርቆሮው ክዳን ጠብ (ቱማታ) ንግግርን ለመደማመጥ እስከ ማወክ ደረሰ፡፡

አክሊሉ የእሷን ውብ ትክለ - ሰውነት በእይታው እየቃኘ «...ዓይን ምን ይብላ! አሉ አያቴ? እውነታቸውን ነው□ኮ! ሰው በእህልና በውሃ ብቻ መኖር የለበትም» በማለት ሲያስላስል ተቀመጭ ብሎ መጋበዙን ዘነጋው፣ ሸዋዬ ለጊዜው ባገኘችው የእንጨት ወንበር ላይ አረፍ አለች፡፡

እንደ መባነን ባለ አነጋገር «ሻይ ላፍላልሽ?» አለ አክሊሉ፡፡

«ግድ የለም፣ ከሆነም እኔ ባፈላው ይሻላል» አለች፣ ወንዱ ልጅ ከሰል ምድጃ ዳር ሲርመጠመጥ የማየት ትግሥት የሌላት መሆኑን በሚገልጽ ፈገግታ፡፡



ምድጃውን ካልጋው ግርጌ ለማንሣት ጎንበስ ስትል ዳሌዋ የሰቀለው ቀሚሷን ቧቷን ተሰናብቶ ወደ ጭኗ ከፍ አለ፡፡ የአክሊሉ ርሁብ ዓይን፣ አያቱ እንዳሉትም ውብ አካሏን በስሜት አጣጥሞ ተመገበው፡፡

ሸዋዬ፣ እንቅስቃሴዋ የአክሊሉን ትኩረትና ስሜት መሳብና አለመሳቡን እንዳላስተዋለ ሆና ከሰል የማራገብ ሥራዋን ቀጠለች፡፡

ዝናቡ ተግ እያለ፣ ሻዩም እየደረሰ መጣ፣ ከሻዩ በስተጀርባ ያለው ስሜትና ፍላጎት ለአክሊሉም ሆነ ለሸዋዬ ሳይታወቅ የታወቀ መሆኑ ከሁለቱም ትኩስ ኃይሎች ልቦና የተሰወረ አይደለም፡፡ ከመስንበቻው ውስጥ ውስጡን ሲትመከመክ የነበረው የሁለቱም ትኩስ ኃይሎች መፈላለግ፣ ከሻዩ ጋር እየተፍለቀለቀ ነው፡፡ ፈልቷል፡፡ ሲገንፍል ከእሷ ወይም ከእሱ አንድ ምልክት እየጠበቀ ነው፡፡ ሁለቱም ደርተዋል፡፡

የሸዋዬ እናት በጓሮው በር ብቅ ብለው ጎርፉንና የበረዶውን ክምር አይተው «ጉድ! ጉድ! ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዕለተ ቀናቸው አጥለቀለቁን» ብለው ቀና ሲሉ የአክሊሉ ክፍል ገርበብ ብሎ ተመለከቱ፡፡

«አክሊሉ ምን ጊዜ መጣህ?» አሉ፡፡

«እኔም እዚህ ነኝ እማዬ፣ ዝናብ አባርሮኝ» አለች ሸዋዬ፣ ድምጽዋን ከፍ አድርጋ፣

<u>«ይሁን» ብለው ወደ ቤት መለስ አሉ የሸዋዬ እናት፡፡</u>

<u>«ለምን ሻይ አንጋብዛቸውም?» አለ አክሊሉ፡፡</u>

«እኔ ከተጋበዝኩ ይበቃል? አይመስልህም?» አለች ሸዋዬ ፈገግታ ባጀበው የአንገትና የትከሻ ውቂያ፡፡

«ሻይ ብቻ መሆኑ ከፋ» አለ አክሊሉ ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ ሊያሸጋግር በሚያግዝ ፈገግታ፣

«ሰው! ሰው! ይፈልግሻል» አሉ የሸዋዬ እናት፣ ከወደ ውጪ::

«እሺ እማዬ መጣሁ» ብላ ሻይዋን በፋት-ፋት ጥድፊያ ጨርሳ ልትሄድ ብድግ አለች::

አክሊሉ የሚናገረው ጠፍቶት እሷ ስትነሳ እሱም የሻይ ኩባያውን አስቀምጦ ብድግ አለ:: ዓይን ለዓይን ተያዩ «ለዛሬ ይህ ይበቃል፣ በል ቻዎ» ብላ እጇን ዘረጋችለት:: «አመስግናለሁ» አለና የጨበጠውን እጇን ጠበቅ አደረገው:: ከዚያም ቱር ብላ ከቤቱ ወጣች::

«ሞት ይጥራቸው፣ ደንቀራ አሮጊት፣ አሁን ሌሊቱ እንዴት ይነጋልኛል?» በማለት አጉተመተመ፣ ወደ ሄደችበት አቅጣጫ እያየ፣

አክሊሉ፣ ከአንድ ጎኑ ወደ ሌላው ሲገላበጥ፣ ትራስ ታቅፎ ሌሊቱ ነጋለት:: ማለዳው ላይ ግን እንቅልፍ ድብን አድርጎ ወስደውና ረሃብ የመተለገው አንጀቱ ተንጫጭቶ ከረፋዱ አምስት ሰዓት ግድም ቀሰቀሰው::

ለችግር ጊዜ ብሎ ለሞኑን ከሾላ ገበያ በሁለት ብር ከገዛቸው እንቁላሎች ሁለቱን ያለዘይት፣ ያለሽንኩርትና ቃሪያ ጠብሶ፣ ከዳቦ ጋር ቀማምሶ ከቤት ወጣ::

ከቤቱ እንደ ወጣ ሥራ አጦች «ድድ ማስጫ» ብለው ወደ ሚጠሩት የትንንሽ ደላሎችና ሥራ ፈላጊዎች መናኸሪያ ወደ ሆነው ካዛንቺስ አጂፕ አካባቢ አመራ:: «ድድ ማስጫ» መንግሥትን ከማማት አንስቶ ስለ ወሲብ፣ ስለመጠጥ፣



ስለሙዚቃ፣ ስለወንጀል ይህ ቀረው የማይባል ወሬ የሚለሰቅበት፣ አሉባልታና የፈጠራ ወሬ የሚበዛበት ግልጽ መድረክ ነው::

አክሊሉ «ድድ ማስጫ» ሲደርስ የመድረኩ ታዳሚዎች የወንድ ወሬ ጨርሰው ሴት አባላትን ለማቀፍ የሚያስችል ውይይት በግ አልም እያለ ነበር:: «ድድ ማስጫዎች» እንደ ፀጉረ ልውጥ የሚጠሉት ነገር የላቸውም:: በነባር አባል አማካይነት ማንነቱ ታውቆ ያልቀረበ ሰው ተቀባይነት የለውም:: የድስላውን ሥራ መሻማቱ፣ ሥራም ሲገኝ የውድድሩን ዕድል ማጣበቡ ጥቅማቸውን ስለሚነካ በተቻለ መጠን የአባላቱ ቁጥር እንዳይንዛዛ ይፈልጋሉ:: «የድድ ማስጫ» አባላት ጆሮ ጠቢ ነው ብለው የጠረጠሩትን ሰው አባል ከሆነም በኋላ ይሰርዙታል::

«የፈለግነውን አምተንና ተሳድበን መኖራችን ሥራ ፈትነቱ የሚያሳድርብንን ጫና የሚያቃልልልን ስለሆነ ጆሮ ጠቢን እንጠየፋለን» ይላሉ::

***

አክሊሉ ከሽዋዬ ጋር የጀመረውን ግንኙነት ቀጥሎ ወደተራከቦተ ከንፈር አሸጋግሮታል:: አክሊሉ ስለወሲባዊ ግንኙነት መሥጋት እንደሌለባት፣ ከ «ድድ ማስጫ» ያካበተው የወር አበባ የጊዜ ስሌት ጆሮ ጠገብ መረጃ ማግባባት ይዟል::

«ያንድ ቀን መዘዝ፣ ያለዘጠኝ ወር አይመዘዝ» በማለት እናቷ እንደ ዘይቤ የሚያዘወትሩትን ማስጠንቀቂያ በፈገግታ አጅባ ስትነግረው፣ አክሊሉ ድኽነቱ የልጅ አባት እንዳይሆን ካላገደው በስተቀር፣ ልጅ ቢኖረው የቱን ያህል ደስ እንደሚለው ልቧን በሚረታ አነጋገር ለሽዋዬ ደጋግሞ ነግሯታል:: የማታ ማታ ሽዋዬ ተረታችለት:: በመጨረሻም አወቃት:: በሥርቆት በጣም ተላመዱ:: ጓደኝነታቸው በእናቷና በጎረቤቶቻቸው በጥርጣሬ ከመታየት አልፎ የቡና መጠጫ ወሬ ከሆነ ሰንበትበት ብሏል::

ከወሲባዊ ግንኙነት ሌላ አማራጭ የደስታ ምንጭ እምብዛም የሌላቸው አክሊሉና ሽዋዬ በወጣትነት ፍቅር፣ በስርቆት ፍቅር ከነፉ:: የፍቅራቸው ብርታትና መተማመናቸው የወሊድ ቁጥጥር ለማድረግ ፋታ ሲሰጣቸው አልቻለም:: የወር አበባና የጊዜ ስሌትም በዝንጋታ ቀኑና ሰዓቱ ይፋለስባቸው ጀመር፣ ልቅ ሆኑ:: ካንተ ሌላ፣ ካንቺ ሌላ ተባባሉ:: ከአንድ ነፍስ የተሠሩ ሁለት አካላት ወደመሆን ተቃረቡ::

ዲቁናንና ሙዚቃን መተዳደሪያ ለማድረግ ሞክሮ የነበረው አክሊሉ ሲያዜም ድምፁ መረዋ ነው:: ሲያንጎራጉር የሰው - ወፍ ያወርዳል:: አሁን ደግሞ ከሽዋዬ ጋር በፍቅር መጦፉ ዘፋኝነቱን ይበልጥ አወጣው:: ፈላበት::



በወገቧ ሰብቃ፣
በጭኖቿ አሙቃ፣
ስታደርገው ደቃ! ደቃ! ደቃ!
ያ ነበር መግባቢያው የፍቅራችን ቋንቋ::
ድምፅ - አልባ ውይይት፣
በጊዜ ጀምሮ እስከ እኩለ - ሌሊት፣
የማይጠገበው ቢሰሙት! ቢሰሙት::
ውይይቱ ሲግል፣
ግለቱ ሲያናፍል፣
ዝልፍልፍ ዝንፍልፍል፣
ሙክክ አልን ብስል!
ድብን አልን ክስል::

***

ቅጠል ሳትበጥሽ፣
ሥራሥር ሳትምሽ፣
መድኃኒቱን ሠርተሽ፣
በክናድ እቅፍሽ፣
በከናፍር ቅምሻሽ፣
አቅምሰሽኝ ነበር፣
ማር-የፍቅር ማር::

በዳሌ ንዝር ሰብቀሽ፣
በጭንሽ አሙቀሽ፣
በግለቱ አቅልጠሽ፣

አጣፍጠሽ ቀምመሽ፣
አቅምሰሽኝ ነበር፣
ማር-የፍቅር ማር።

በማለት እያሞጋገሰ ያች ጠባብ አልጋው ሦስተኛ ሰው ማዳበል የሚችል ሥፍራ እስከሚተርፋት ድረስ ተቃቅፈው የፍቅር ወለላቸውን አጣጣሙት። እሷም በበኩሏ የፍቅር እርካታዋን አልሸሸገችም።

ትናንትናም አልኩት ዛሬንም ደገምኩ፣
ሚዛኑ እስኪመጣ የፍቅራችን ልኩ።
ከቴ መቼ አልኩና አልጋ ይንካ ጎኔ፣
መላው አካላትህ ፍራሼ ነው ለኔ፣
አንገትህ ላንገቴ ደረትህ ለጡቴ፣
አካሌ ላካልህ ለግዷል ሰውነቴ።

ቀስ በቀስ ከርራ፣
የፍቅራችን ሐድራ።

ኃይል እየተሰማኝ ሲጨምር ጉልበቴ፣
በፍቅርህ ዝማሬ ይረካል ስሜቴ።

በባቲ፣ ባምባሰል ቅኝቱን አክርረው፣
ዳግም በትዝታ ባንቺ ሆዬ በሰው።

ቅኝቴን ሲቃኘው፣



ቅኙቱን ስቃኘው፣
እሱ የኔን ሲለው፣
እኔም የሱን ስለው፣
መልሰን ቀልሰን ስንደጋግመው፣

ያኔ ነው!
ያኔ ነው!
ሐድራ የሚገባው።

እያለች ልቡን ስታግለው፣ አካሉን ስታግመው፣ ሳይጠግባት ስትመግበው፣ ጊዜው ነጎደ። ልቧ ፍቅሩን የተቀበለውን ያህል ማሕፀኗም ዘሩን ተቀበለ። በፍቅር መኻል አስደንጋጭ ነገር ተከሰተ። ተደናገጡ። ሆኖም ፍቅር ሁሉን ቀሰል አድርጎ በማሳየት ባህሪው አዘናጋቸው።

ቅሪት ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ የሸዋዬን ሆድ እንደ መዳበስ አክሊሉን የሚያስደስተው ነገር አልነበረም። ሸዋዬ ግን ከፀነሰች በኋላ ያ ፍልቅልቅነቷ በአዲስ የቅብጥብጥነት ባሕሪ እየተሰወጠ መምጣት፣ አክሊሉን ከሥራ አጥነቱ ጋር በመተጋገዝ አንገቱን አስደፋት።

# ምዕራፍ 13

## አክሊሉና አሰገደች

ሆሳዕና ክሊኒክ «ከድድ ማስጫ» በድንጋይ ውርወራ ርቀት ላይ ይገኛል:: የክሊኒኩ ባለንብረቶች ዶ/ር ወልደ ሚካኤል ማዴቦና የክሊኒኩ የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ ወ/ሮ አሰገደች ከድድ ማስጫዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ከሕክምና ደንበኝነት በላይ ነው::

በአንዳንድ ዓመት በዓል ሰሞን ክሊኒኩ የ«ድድ ማስጫ» አንጋፋዎችን በድጎማ ይፈቅዳቸዋል:: አልፎ አልፎም ነፃ የህክምና አገልግሎት ስለሚሰጣቸው ክሊኒኩን የደኻ አለኝታ ነው ይሉታል:: የሚረዳቸውን ክሊኒክ እንዳቅማቸው ለመርዳት «አይ ክሊኒክ፣ ሆሣዕና□ኮ ክሊኒክ ብሎ ዝም ነው:: ሌላው ሬሣ ያመርታል፣ ሆሳዕና ክሊኒክ ግን የሞተ ያስነሳል» በማለት ሰመደለል ይቃጣቸዋል::

የክሊኒኩን ንብረት:- መድኃኒት፣ አልኮል ሲሪንጅ፣ ዕቃ የመጣበትን ካርቶን የሽንት ቤት ወረቀት፣ አንሶላና ብርድ ልብስ፣ ሌላም ሌላም ቁሳቁስ በጉያቸው ሸጎጥ አድርገው የሚወጡትን፣ ወይንም በአጥር ላይ የሚሸኙትን ሠራተኞች በማጋለጥ «ድድ ማስጫዎች» ለአሰገደች የሚሰጡት መረጃ ግንኙነታቸውን ወደ ቤተሰብነት ደረጃ እያሸጋገረው መጥቷል::

አሰገደች አንዳንድ ጊዜ ከአነ አባ መላ ጋር ቢሮ ዘግተው ስለሚያወሩ፣ የክሊኒኩ ሠራተኞች አሰገደችን በሥነ ምግባር



ብልሹነት ያሚታል:: በአንድ ወቅት ዶክተሮችና አነ አሰገደች ከሚጠቀሙበት መፀዳጃ ቤት ግድግዳ ላይ:-

«አመሰ ልክስክስ አመሰ ውዳቂ፣
ሰንጋ ፈረስ አስሮ አህያ ናፋቂ::»

የሚል ጽሑፍ ተቦጫጭሮ በመታየቱ ክሊኒኩ ከላይ እስከታች ክፉኛ ታምሶ ነበር::

ትርምሱ ጋብ ያለው፣ አንዲት ነርስ፣ አንድ የመድኃኒት ክፍል ሠራተኛና አንድ ዶክተር በሠራተኛ ቅነሳ ሰበብ ከክሊኒኩ ከተባረሩ በኋላ ነበር::

ሽዋዬ የወር አበባዋ ከቀረበት ዕለት ጀምሮ መቅበጥበጥና የባሕሪ ለውጥ በማምጣቷ፣ ግራ የተጋባው አክሊሉ፣ በሆሳዕና ክሊኒክ በግማሽ ዋጋ የጤና ምርመራ እንድታደርግ የአባ መላን ትብብር ይጠይቃል:: ጥያቄውን ያለማመንታት የተቀበለው አባ መላ ወዲያውኑ አክሊሉን አሰገደች ቢሮ ይዞት ይገባል::

«ምን እግር ጣለህ አባ መላ?»

«እመቤትዬ ስለናፈቁኝ እጅ ለመንሳት ነው» የሚለውን መልስ በመስጠት ላይ እንዳለ አክሊሉ በዚያ ሶታ ቁመናው፣ ድግድጋት ሲቀረው፣ ቀልብን በሰረቀ እጅ አነሳስ ዝንጥፍ አለ::

«አረፍ በሉ»

«ሥራ ፈተን ሥራ እንዳናስፈታ ነዋ!»

«ግድ የለም አባመላ» አሰች እንደማለዳ ፀሐይ ከሚሞቅ ፈገግታ ጋር::

እነ አባ መላ በመቀመጥ ላይ እንዳሉ ዶ/ር ወልደ ሚካኤል ሳያንኳኩ በር በርግደው ዘው አሉ::

እነ አባ መላ ብድግ ብለው ኖር አሏቸው:: ዶክተሩ ወደ አሰገደች እየቀረቡና የሰላምታ እጃቸውን እየዘረጉ «ጤናም የለኝ፣ በዚህ ላይ ደግሞ ደክሞኛል፣ በእኔ ምትክ ዶ/ር ደምሴ የሌሊት ተረኛ ይሁን፣ አንቺ ትፈልጊኛለሽ? ወደ ቤት መሄዴ ነው» አሉ::

«የሚያስቸኩል ጉዳይ የለኝም» አለች አሰገደች::

«በሉ እንግዲያው ሄድኩ» ብለው ወጡ::

«እኛ□ኮ ከዶክተር ጋር ጉዳይ ነበረን፣ መቸ ነው የሚመጡት?» አለ አባ መላ ሲፈራ ሲቸር::

«ምንድነው ጉዳዩ ሚስጢር ካልሆነ...? አለች አሰገደች::

«አይ እሜትዬ የምን ምስጢር አመጡ - ልመና ነው - ያው እንደ ተለመደው አለ አባ መላ::

«ምን ነበር ልመናው?»

«ይኸ ሥራ - አጥ ጓደኞችን ባለቤቱ ቅሪት ሆናበት ተቸግሯል::»

«እና ታዲያ ምን ፈለገ?»

«እንድትመረመርለት ነበራ!»

«እሱ ከሆነ እዳው ገብስ ነው፣ እኔ እንድታስወርድ ..... ልትል እንደሆን ብዬ ድንግጥ አልኩ» አለች አሰገደች::

አክሊሉ ቀበል አድርጎ ከተቀመጠበት ብድግ እንደማለት እያለ «አያደለም እመቤትዬ <ታጣፋው የላት ትከናነበው አማራት> እንዲሉ ሆነና ሳይታሰብ ቋጠረችብኝ፣ ታዲያ ሆዷ ባዶ በነበረበት ጊዜ ያልነበረ፣ አዲስ ባሕሪ አመጣች:: ጤናዋ እየታወከ...»

የጀመረውን አቋርጣ «ነገ ይዘሃት ና ትታያለች፣ ለነገሩ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት እንደዚሁ ናቸው፣ ያቅበጠብጣሉ»



በማለት አሰገደች መልስ ሰጥታ እነ አክሊሉ አመስግነው በመውጣት ላይ እንዳሉ፣ «አባ መላ አንድ ጊዜ» በማለት ጠራችውና «ይህ ልጅ ሥራ ፈላጊ ከሆነ ለምን እዚህ ለጥበቃ አንቀጥረውም፣ ሲያዩት ደህና ይመስላል» አለች::

«እኔማ በቂ ሰው አላችሁ ብዬ እንጂ ልጁ ንቁ ነው:: ደግሞም ገጠር አደግና ወታደር ቀመስ ስለሆነ ታማኝ ሃይማኖተኛ ይመስላል» አለ አባ መላ::

«ግድ የለህም በጥበቃ እንቀጥረውና ሥራ እንዲለማመድ ማድረግ ይቻላል» በሚለው የአሰገደች አስተያየት ተስማምተው ተለያዩ::

«ወታደርነቱ፣ ወጣትነቱ፣ ባላገርነቱ፣ ሶታ ተክለ ሰውነቱ፣ ከሁሉም ከሁሉም ድኽነቱ ዋጋ አላቸው፣ ለእሱም ለእኔም አስተማማኝ መሣሪያ ይሆናሉ:: ዛሬ የመጀመሪያው መጀመሪያ ሆኖአል» አለች እሰገደች::

***

የአክሊሉን መቀጠር ጓደኞቹ «የሥራ ሎተሪ ወጣልህ» ይሉታል:: አክሊሉ የሌሊት ቋረኛ ሲሆን፣ ቀን እቤቱ ገብቶ ያርፋል፣ ይተኛል:: በምትተርፈው ጊዜ ከሽዋዬ ጋር ይዳሩበታል፣ የባጡን የቆጡን ያወሩበታል:: ከቢሮ አካባቢ ብዙ እንዳይርቅ ከአሰገደች የተሰጠውን ትእዛዝ በማክበር ወደ ቢሮም ብቅ ይላል:: ቢሮ አካባቢ ይላላካል፣ አትክልት ይኮተኩታል፣ ውሃ ያጠጣል፣ ግቢ ያፀዳል:: ጉልበቱንና ጊዜውን እንደ ሌሎቹ የጥበቃ ሠራተኞች አለመሰሰቱ በአስተዳደሩ አካባቢ ሞገስን አትርፎለታል:: አድናቂዎቹ «ጅንኑ» ይሉታል:: አክሊሉ

በእንጉርጉሮ ወይም በቀረርቶ ስለሚያጅበው ሥራው አይሰለቻቸውም:: እስካሁን አክሊሉ በውል ያልተረዳው ነገር ቢኖር፣ አሰገደች ስለትዳሯ እሱ ሊያውቅ ከሚገባው በላይ እንዲያውቅ ያደረገችበትን ምክንያት ነው:: በአንጻሩ በአቻ የሥራ ጓደኞቹ ዘንድ «በኋላ የመጣ ዓይን አወጣ» እንዳስባባለው አክሊሉም ቢሆን ተረድቶታል::

«ከአንደበቱ ባይወጣም «ዘበኛ ወደደም-ጠላ ምን ያመጣል ምድረ ሰካራም-ሌባ የራሱ ጉዳይ» የሚል ንቀት ማሳየቱ አልቀረም::

አንዳንድ ጊዜ አክሊሉ አሰገደች ቢሮ ገብቶ ቆየት እያለ መውጣቱ፣ የአክሊሉ ሥራ ከጥበቃ በላይ እንደሆነ የሚገምቱ አሉ:: የዚህ ዓይነት ግምት መኖሩን እርሱም አውቆታል:: «ይህን የጭን - አሽከር ያመጣብን ያ አባ መላ ነው» መባሉንም ሰምቷል::

«ነገር አንሺውን - እሾህ አጣሪውን» (ይወጋል) እንደተባለው አንድ ቀን ይጠየቁበታል:: ያን ጊዜ ምን እንደሚውጣቸው አያለሁ:: አጅሪት እንደሆነች ባላጋራዋን ከገደል ላይ ገፍትራ እንጦሮጦስ ወርዶ ሲንኮታኮት ካላየች (በቀር) በበቀሏ እንደማትረካ፣ ከእኔ በተሻለ እነርሱ ያውቋታል:: አዎ! በቀል እኮ የማር ወለላ ነው:: ይጣፍጣል:: አንዳንድ ጊዜ ጥፍጠቱ ከማርም ይጥማል» ፎጋሪዎቹ የሚደርስባቸውን ቅጣትና ውርደት ቶሎ ለማየት ያለወን ጉጉት፣

«መስተዋት ይገዛል ሞኙ የሰው ልጅ፣

ሁሉን የሚያሳየው መስንበት ነው እንጅ!»

በማለት ያንጎራጉራል::



ሸዋዬ ወረ ግቡ ሆናለች:: ስምንተኛው አልቆ ዘጠነኛው ወር ከገባ ሦስት፣ አራት ቀን ሆኗል:: አክሊሉ ሸዋዬን ለማማማጥ ከትናንት ጀምሮ እቤት ውሏል:: እጁን ሸዋዬ ሆድ ላይ እያሳረፈ «ምን ይሰማሻል?» ይላታል ደግሞ ደጋግሞ::

«ምን ይሰማኛል? ፍርሃት ነዋ! አታድርቀኝ» ትላለች እጁን ከሆዷ ላይ እየገፋች::

«ልብ አርጊ ወደ ሀኪም ቤት መሔድ ያሰብሽ ምጡ ሳይጠናብሽ ነው:: ገና ሲጀምርሽ ትነግሪኛለሽ»::

«እሺ አልኩህ! ስንት ጊዜ እሺ ልበልህ! እኔ□ኮ አሁንም ቁልቁል እየተጫነኝ ነው:: እንዲያውም አሁን እያራጠበኝ ነው፣ ብንሔድ ይሻላል» አለች ሸዋዬ በጭንቀት::

«ደህና! እንሔዳለን፣ መጣሁ» ብሎ አክሊሉ ከቤት ውልቅ አለ::

«አክሊሉ የሽንት ውሃ እየፈሰሰኝ ነው ጥለኸኝ የምትሔደው?» ብላ ሸዋዬ ተበሳጨች::

አክሊሉ ጥያቄዋን እንዳልሰማ ዝም ብሎ ሔደ:: የሆነ ቦታ ስልክ ደውሎ ወዲያው ተመለሰና ሸዋዬን እያባበለ ይዞ ወጣ::

፮ —

# ምዕራፍ 14

## የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተውኔት

ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ በጧት አንድ እድርተኛቸው ለማስተዛዘን የሣልስት ለቅሶ ሔደዋል:: አክሊሉ፣ ሸዋዬን ፊል ጃኬቱን አልብሶና ደጋግፎ ወደጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለመውሰ ኮረኮንቹን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጨርሰው አስፋል ወጥተዋል:: ወደ ኋላ ገልመጥ እያለ የታክሲን መምጣ ሲጠባበቅ አንድ ባለ አውቶሞቢል አልፏቸው ሲሄድ ሲል አክሊሉ እጁን አውለበለበ:: መኪናው ቆሞ ጠበቃቸው:: እህቱ ባለቤቷ በሌለበት በድንገት ምጥ ይዟት ሐኪም ቤት ለማድረስ ታክሲ በማጣቱ መንገድ ላይ ልትጥለው መቃረቧን በማስተዛዘን ተናግሮ ሳይጨርስ፣

«ግቡ! ግቡ! በሞትኩት!» አለች ከሹፌሩ ጎ የተቀመጠችው ሴት::

«ምን ሰዓት ጀመራት?» አለ የመኪናው አሽከርካሪ፣

«ትንሽ ቆይቷል» አለ አክሊሉ::

«ሠፈራችሁ እዚህ ነው?» አለች ሴትዬዋ::

«አዎ በዚህ በኮረኮንቹ መንገድ ገባ ብሎ ነው» አለ አክሊሉ::

«ጌታዬ እግዚአብሔር ብድርዎን ከፋይ ያድርገኝ» አለ አክሊሉ በአክብሮት አንቱ ብሎ::

«ግድ የለም፣ ይህ ምን ቁም ነገር ሆነና ነው» አለ አሽከርካሪው::



ሸዋዬ ተረኛው ሐኪም ወዳለበት ምርመራ ክፍል በድጋፍ ተራምዳ መድረስ ስላልቻለች በተንቀሳቃሽ ቃሬዛ (ስትሬቸር) ላይ ተንጋልላ ተወሰደች::

«አንተ ሒድና ካርድ አውጣላት፣ እስከዚያ እኔ ረዳታለሁ» አለ አንድ ቅን የሆስፒታሉ የሕክምና ረዳት ሠራተኛ:: አክሊሉ ሠራተኛውን ስለትብብሩ አመስግኖ ወደ ካርድ ክፍል ርምጃውን አፋጠነ::

«እንዴት ሆነች፣ ማዋለጃ ክፍል ገባች?» የባለ መኪናው ሚስት ጠየቀች::

«ልትገባ ነው፣ ካርድ አውጣላት ተብዬ ነው.....» አለ አክሊሉ::

«ስሟንና አድራሻዋን ንገረን እኛ እናስወጣላታለን አንተ ሂድላት» አለች ሴትዬዋ::

«እሺ» አለ አክሊሉ ስሟንና አድራሻዋን ከኪሱ ዳብሶ ባገኛት ወረቀት ላይ ለመጻፍ በመዘጋጀት ላይ ወዳለው ባለመኪናው እየተጠጋ::

«ስሟ ሸዋዬ ነው::»

«የአባቷስ ስም?»

«ተሰማ::»

«እድሜዋ ስንት ይሆናል?»

«23 ዓመቷ ነው::»

«ከፍተኛ፣ ቀበሌ የቤት ቁጥር?» አለች ሚስቲቱ ጣልቃ ገብታ::

«ከፍተኛ 15፣ ቀበሌ 27፣ የቤት ቁጥር 009 መሰለኝ» አለ አክሊሉ እያመነታ::

«በቃ አንተ ሒድ፣ ካርዱን እኛ እናወጣላታለን» አለች ሴትዮዋ ቁራጯን ወረቀት ከባለቤቷ እጅ ተቀብላ ካርድ ወደ ሚሞላው ሠራተኛ እየተመለከተች::

«ለካርድ ማውጫኛ ለአልጋ ማስያዣ» አለና አክሊሉ የተወለኑ የአሥር ብር ኖቶች አውጥቶ ብር መቁጠር ሲጀምር «ግድ የለም፣ እሱን ያዘው» ብላ ሴትዮዋ ፊቷን ወደ ባለቤቷ መለስ አደረገች::

የባለቤቱ ሀሳብ የገባው ባል «ለጊዜው ያዘውና በኋላ እንተሳሰባለን፣ አሁን ካርዱን ቶሎ አድርስላት ለአልጋ መያዣ የሚከፈለው ከተገላገለች በኋላ የምትተኛ ከሆነ ይመስለኛል» አለ ባለመኪናው የዳበረ ልምዱን በማካፈል::

ሌላ ምጥ የተያዘች ሴት በማዋለድ ላይ የነበረው ተረኛ ሐኪም ሥራውን ጨርሶ ወደ ምርመራ ክፍል ሲመጣ ሁለት ምጥ የተያዙ ወላዶች «ሞትኩ፣ እናቴ ወይ አላየሽኝ፣ ጥሩልኝ፣ ኸረ ባካችሁ እርዱኝ! ወይኔ! አይ የቀን ጎዶሎ.....!» እያሉ የባጥ የቆጡን ይለፈልፋሉ::

«የጠናባትን» አለና ሐኪሙ ወደ ማዋለጃው ክፍል ተመለሰ::

የባለ መኪናው ሚስት «በል እንግዲህ ማርያም ትቅረባት» ብላ ካርዱንና ገንዘብ የተከፈለበትን ደረሰኝ ለአክሊሉ ለጥታው መለስ አለች::

አክሊሉ ካርዱን ለነርሷ ሰጥቶ ሴትዬዋን ተከትሎ ወጣ:: «ጌታዬ ብድርዎን እግዜር ይከፈልዎ፣ በጣም አመሰግናለሁ:: የእህቴ ባለቤት ሌላው ቢቀር <እግዜር ይስጥልኝ> እንዲልዎ



ራሻዎን ቢሰጡኝ፣ ድፍረት ካልሆነብኝ» አለ አክሊሉ መሬት ሬት እያየ::

«ምን ችግር አለ! እንዲያውም ሕፃኑ ወንድ ከሆነ ለኔ፣ ት ከሆነች ለባለቤቴ ክርስትናውን ይሰጠን ይሆናል» አለና ለመኪናው ፈገግ ብሎ ካርድ ከቦርሳው አውጥቶ ሰጠው::

ሸዋዬ አልጋ የተያዘላት ሦስተኛ ማዕረግ ነበር:: ሆኖም እርሷ ቀደም ብለው በተገላገሉትና ከመገላገላቸው በፊት ስፒታል ተኝተው ክትትል እንዲደረግላቸው በገቡ እናቶች ሦስተኛ ማዕረግ ወላድ ክፍል አልጋ በሙሉ ስለተያዘ በሐኪሙ ዕዛዝ ሸዋዬ ሁለተኛ ማዕረግ ነው የተኛችው:: የማዕረግ ለውጡ ጨማሪ ማስያዣ ገንዘብ እንደሚያስጠይቅ ለአክሊሉ ተነግሮት «እሺ እጨምራለሁ» ብሏል::

***

ሸዋዬ በሣልስቱ ወንድ ልጅ በቀዶ ሕክምና ተገላገለች:: ምጡ ከባድ ነበር:: እሷም ትተርፋለች ያለ ሰው አልነበረም::

«እመብርሃን የጭንቅ አማላጇ፣ ወለላዋ፣ ከጉድ አወጣችኝ» አሉ ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ::

«በእግዚአብሔር ፈቃድ እሷስ ተርፋለች፣ አሁን የክፍያው ነገር ነው አሳሳቢው» አለ አክሊሉ::

«እሱን እናንተ በርቱበት የማረሉን ነገር ለእኔ ተውት» አሉ ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ በማያሻማ አነጋገር::

አክሊሉ ኮሪደሩ ላይ ለመንጎራደድ ወጣ ሲል «ከድድ ማስጫ» ጓደኞቹ መካከል ሦስቱ ሙዝና ብርቱካን በኅብረት

ገዝተው መጡ:: «ታዲያስ ጻል እንኳን ደስ ያለህ» በማለ
ተሳሳሙ::

«በቡሃ ላይ ቆረቆር፣
በቂጥኝ ላይ ቁምጥና፣
በድኽነት ላይ ስንፍና::
ነው የሆነው ነገሩ» አሉ አክሊሉ::

«ተው ባክህ! ልጅ መወለዱ እንጂ በድሉ ያድጋል» አለ
እንደኛው:: ከዚያም ወደ ክፍል ገብተው «እንኳን ማርያ
ማረችሽ» እያሉ ጥግ ይዘው ቆሙ:: ጥቂት አጫውተዋት «ድ
ማስጫዎች» «ማርያም በሽልም ታውጣሽ» በማለት ሲወጡ
«አክሊሉ እንዴት ቢመቸው ነው ልጅቱን ሁለተኛ ማዕረግ
ያስተኛት» በማለት እየተገረሙ ሄዱ::

ሸዋዬ እየበረታች ቁስሉም እየጠገገ መጣ:: በሣልስቱ
ረፋዱ ላይ ጉብኝት ያደረገው ሐኪም «የተለየ ነገር ካላጋጠመ ነገ
መውጣት ትችያለሽ» አላት::

ይኽንን የሰማው አክሊሉ የሕክምናው፣ የአልጋውና
የመድኃኒቱ አገልግሎት ሂሣብ እንዲሠራለት ጠየቀ::

«ትውጣ የተባለው ነገ ስለሆነ ዛሬ ሂሳቡን ማሳወቅ
አይቻልም» ብላ ነርሷ ነገረችው:: እሱ ግን አቅራቢያውን ግምት
እንኳ ቢያውቅ ክፍያውን ለማሰናዳት እንደሚያግዘው በመግለጽ
እንድትተባበረው ነርሷን ተማፀናት:: «እሺ ከሰዓት በኋላ»
አለችው::

የክፍያው ነገር ያሳሰባቸው አክሊሉና ሸዋዬ ወዲያው
ምክክር ያዙ:: ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ እንደሆነ «የኔ ድርሻ ማረስ
ብቻ ነው» በማለት አስቀድመው ተናግረዋል:: ስለዚህ ዕዳው



የሁለቱ ብቻ ሆኗል:: ከተቻለ ገንዘቡ የሚከፈልበትን፣ ካልሆነም ጥቁር አንበሳ የሚሸወድበትን በርካታ አማራጮች አውጥተው አወረዱ:: አንዱ አማራጭ ሕፃኑን በተኛበት ትታው ደንገዝገዝ ሲል ሕመምተኛ ጠያቂ መስላ ወጥታ እንድታመልጥ የሚገፋፋ ሐሳብ ነበር:: በጉዳዩ ላይ ረዥም ጊዜ የወሰደ ምክክር ቢያደርጉም ሸዋዬ መቁረጥ አቃታት::

«ለምን ያንን ሲፍት የሰጠንን ሰውዬ አናስቸግርም?» አሉ አክሊሉ አዲስ ሐሳብ የተከሰተለት መሆኑን በሚያንፀባርቅ ስሜት፣

«እንዴት አክሊሉ! አላበዛነውም? ዓይናውጣነት እንዳይሆንብን!»

«ስንሰነባበት ሴትዬዋ <ድንገት ባለቤቷ ካልመጡ ከሆስፒታል ስትወጣ ሊፍት ብንሰጣት ውለታችንን የተሟላ ያደርገዋል> ማለቷን ሰምተሻል፣ እንዳየሁት ባልና ሚስት የእግዜር ሰዎች ናቸው» አሉ አክሊሉ የሸዋዬን ስምምነት በሚጠይቅ ቅላፄ::

«አክሊሉ ምንድነው የምታወራው? የኛ ችግር□ኮ ከሊፍት በላይ ነው:: በሰውየው ሊፍት ለመገልገል በቅድሚያ የሆስፒታሉን ክፍያ መፈጸም እንዳለብን ዘነጋህ እንዴ? ወይስ ሰውየው የሆስፒታሉንም ክፍያ ሸፍነው የሊፍቱንም አገልግሎት ይሰጡናል ነው የምትለኝ፣ አልገባኝም?»

«ልክ ነሽ ሸዋዬ፣ ሳይታወቅሽ ወደ ነገሩ እምብርት እየተጠጋሽ ነው» አሉ አክሊሉ::

«በእናትህ አትቀልድ አክሊሉ» አለች ሸዋዬ የአክሊሉ ፍላጎት ያልገባት መሆኑን በገጽታዋና በአካል እንቅስቃሴ እየገለጸች::

«ሰውየውን በሊፍቱ ለበብ እጠራዋለሁ፣ ችግር የለም፣ ግን እሱ ከመምጣቱ በፊት ከሆስፒታሉ ሠራተኞች ጋር የምንቋጥረው ትንሽ ቁም ነገር ይኖራል::»

«አንተ ሰው!» አለች እንደ መበርገግ ብላ::

«ቆይ! ቆይ! አትበርግጊ፣ አንቺ ያለብሽ አርጊ - ተናገሪ የምልሽን ማድረግ ብቻ ነው::»

«በል ጨርሰው እሺ::»

«እንዳልኩሽ አሁን ሄጄ ከሆስፒታሉ ሰዎች ጋር ቅድመ - ዝግጅቱን ልሥራ::»

«ለምን አትነግረኝም፣ እኔም ቅድመ - ዝግጅታችሁን ማወቅ አለብኝ፣ አይደለም እንዴ?» የሸዋዬ ጥያቄ ስጋት ያጀበው ነበር::

«ሰውየው ተጠርቶ እንደመጣ ሚስትህን ያዋለድንበትንና አስተኝተን ያከምንበትን ሒሳብ ክፈል ብለው እንዲይዙት - መያዝ ብቻ አይደለም እንዲያዋክቡት ይደረጋል:: አንቺም <አዎ ከሱ ነው የወለድኩት፣ እዚህ ሆስፒታል አምጥቶ ገንዘብ ከፍሎ ያስገባኝ እሱ ነው> ብለሽ ድርቅ ስትይበት ሰውየው ይደነግጣል:: ይፈዛል፣ ወይም እብደት ይቃጣዋል:: ብቻ በዚህም በዚያም ብለን ተጋግዘን የሆስፒታሉን ገንዘብ እንዲከፍል እናደርገዋለን::»

«ሰውየው አላውቃትም ብሎ ቡራከረዩ ቢልስ?»

«እሱማ ማለቱ መች ይቀራል! <እኔን እዚህ ወርውሮ ከሌሎቹ ቅምጦቹ ጋር ሲዳለቅ ከርሞ ዛሬ ገና ብቅ ማለቱ ነው>



ትያለሽ:: እስከዚያው በነገሩ አስቢበት፣ በዚህ ዐሳብ የምትስማሚ ከሆነ ዝርዝር ሴራውን ሳላስጨብጥ ከሆስፒታሉ ሠራተኞች ጋር ልነጋገር፣ ካስፈለገም የሻይ ብዬ ጉርሻ እሰጣቸዋለሁ:: ከቀናኝ ስልኩን ለሰውየው ደውዬ እመጣለሁ» በማለት ወጥቶ ከሔደ በኋላ እንደገና ወደ ክፍሉ ተመልሶ «እረስቸው ያላሳየሁሽ!» አለና አንድ ትንሽ ፎቶግራፍ ሰጣት::

«የማነው!»

«የባለመኪናው::»

አክሊሉ ይህን ፎቶግራፍ እንዴት እንዳገኘው፣ አሁን ለእሷ ለምን እንደሰጣት፣ ሸዋዬ ከመጠየቋ በፊት «ባለመኪናው አድራሻው ያለበትን ካርድ ሲሰጠኝ የገንዘብ ቦርሳውን አውጥቶ ሲዳብስ ወድቃ ነው ያነሳኋት» አለ::

«ለምን ታዲያ ወዲያው አልሰጠኸውም ነበር?»

«እኔ እንጃ!»

«አሁን እኔ ምን ላድርገው?»

«እየሽ! ከሱ ነው የወለድኩት ስትይ፣ በአንቺና በሱ መካከል የቆየ ትውውቅ ለመኖሩ፣ ማለት ቁባቱ ለመሆንሽ ማስረጃ ይሆናል - አይመስልሽም?»

«ሠመረ፣ ሴራው ሠመረ በለው!» አለች ሸዋዬ በፍንጠዛ::

«በነገራችን ላይ» አለ አክሊሉ ወደሸዋዬ ጠጋ ብሎ፣ «ልብ አርጊ ይኸንን ሚስጢር እናትሽ እንኳ መስማት የለባቸውም» አለ አክሊሉ::

«አይ አክሊሉ፣ ምን ብዬ፣ ለምን ብዬ ነው የምነግራት? ምንም እናቴ ብትሆን በማጭበርበራችን መታዘቧ□ኮ አይቀርም» አለች ሸዋዬ ተከዝ ብላ::

«ማጭበርበር አልሸው? ተሳስተሻል፣ ይህ መላችን ከተሳካ ወደር የማይገኝለት ጥበብ ነው የሚሆነው» አለ አክሊሉ ወኔ እየተሰማው::

«ሳይነቃብን ዳር ካደረስነው ትልቅ ድል ሊሆን ይችላል:: በሌላ በኩል ሳስበው ደግሞ፣ በቅን መንፈስ እኛን ለመርዳት ያን ያህል የደከሙትን ሰዎች ውለታ በልተን በምንፈጽመው ድርጊት መኮነናችን አይቀርም» አለች ሸዋዬ ፍርሃቷን እያሳየች::

«ሸዋዬ አትሞኚ፣ እኛ ምስኪኖች ወደ ሰማይ የምንሄደው አበሳችንንና ኩነኔያችንን በምድር ዓለም ጨርሰን ነው:: ስለዚህ ከሞትን በኋላ የሚኖረው ኩነኔ ሊያሳስበን አይገባም....» አክሊሉን አቋርጣ «ስማ አክሊሉ አንተ በእግዚአብሔር አታምንም እንዴ? እንዴት ኩነኔ የለም ትላለህ - ደፋር» አለች ሸዋዬ የአክሊሉን ክህደት በመታዘብ

«ታውቂያለሽ እኔ□ኮ ዲያቆን ነበርኩ:: ስለሃይማኖት ብዙ አውቃለሁ ባልል፣ አንዳንድ ነገር ይገባኛል:: አሥርቱን ቃላት፣ የኦሪትን ሕግጋት ጠብቆ፣ እንደገና እንደ ወንጌሉ ቃል ለመኖር የተመቻቸ ኑሮን ይጠይቃል:: እንደ እኔ ያጣ የነጣ ምስኪን ደኻ፣ በሀብት ባሕር ውስጥ ከሚዋኝ ባለፀጋ፣ <ለዕለት ጉርስ ላመት ልብስ> ማማረያ ጥቂት ነገር ብወስድ የሚያስኮንን አይመስለኝም» በማለት የሸዋዬን ሥጋት ለመቅረፍ ሞከረ::

«በል! በል! በቃህ፣ የዛሬው ያንተ ስብከት የቁጣ መዓት እንዳያመጣብን እጸልያለሁ» ብላ ሸፍንፍን አለች::



# ምዕራፍ 15

## ሸዋዬና ዮሐንስ

ባለመኪናው የስልክ ጥሪ ሲደርሰው እንዴት እንደተገላገለች ሳይጠይቃት በመቅረቱ ማፈሩን ገልጸ «ደህና! ደህና! ነገ አራት ሰዓት ገደማ እመጣለሁ፣ ለመሆኑ ለመግባት ችግር አይኖርም?» በማለት ጠየቀ::

«በተመላላሽ ታካሚ መግቢያ በር በኩል እኔ እጠብቅዎታለሁ፣ ምናልባት በር ላይ ዘበኞች ካስቸገሩዎት በሽተኛ ለማውጣት ነው ይሏቸዋል» አለ አክሊሉ::

«ደህና! ደህና! እስከዚያው እግዚያብሔር ያበርታሽ በልልኝ እህትህን» በማለት ተሰነባበቱ::

ሸዋዬና አክሊሉ ቀኑን ሙሉ በየበኩላቸው ሲያለዝቡ በዋሉት ሴራ ላይ ስለሚተባበሯቸው ሰዎች እንደገና አንስተው መነጋገር ጀመሩ::

«የሆስፒታሉን ሠራኞች እኔም አነጋግራለሁ፣ ሲስተሯ በጣም ተግባቢ ነች:: ሚስጢሩን ሳልነግራት የልጇ አባት በጣም እንደሚጨቁነኝ፣ ከከተማው ሴቶች ግማሽ ያህሉ የእሱ ቅምጦች መሆናቸውን አንጀት በሚበላ እሮሮ አስረዳታለሁ:: ከኔ የተረፈውን ሲስተር ካላት ልምድ ታሟላዋለች» በሚለው የሸዋዬ ዘዴ አክሊሉ ተስማማ::

ባለመኪናው በማግስቱ ጠዋት አራት ሰዓት ተሩብ ላይ አውቶሞቢሉን እያሽከረከረ የመጀመሪውን በር ያለፍተሻ ስተት ብሎ ገባ:: በሆስፒታሉ ተመላላሽ መታከሚያ መግቢያ በር ላይ ቆሞ የጠበቀው አክሊሉ ማደግደግ ሲቀረው በጎንደርኛ እጅ አነሳስ

ተቀበለው:: ሞቅ ባለ ሠላምታ ተጨባብጠው ወደ 6ኛ ፎቅ ወላድ ክፍል ለመሄድ የመጀመሪያውን ኬላ «በሽተኛ ለማውጣት ነው» ስላለ ያለችግር አለፉ:: ሽዋዬ የተኛችበትን ክፍል ገርበብ ያለ በር ገፋ አድርገው ዘው ሲሉ፣ ሽዋዬ ከትራስ ላይ ራሷን ቀና አድርጋ እንደማቃለት ባለ ስሜት፣ ቅጭም ባለ ገጽታ ተቀበለቻቸው:: አክሊሉ እንግዳውን አስገብቶ ሹልክ ብሎ ወጣ::

«ምነው! ምነው!» አለ እንግዳው በአዘኔታ::

«አላውቅም አሞኝ ነው ያደርኩት» አለች ሽዋዬ በቀዘቀዘ ስሜት::

ጥግ ይዘው ሲጠባበቁ የነበሩት የሆስፒታሉ ሠራተኞች ገቡና «ተዘጋጂሽ! ጨርሰሽ ከሆነ ከአምስት ሰዓት በፊት አልጋውን መልቀቅ አለብሽ» አለ አንዱ::

«ገንዘቡን ከፍሎ ደረሰኝ የሚያመጣልሽ ሰው ከሌለ እኔ ልተባበርሽ እችላለሁ» አለ ሌላው የሆስፒታል ባልደረባ::

«አዝናለሁ መለስ ብለን ሳንጠይቅሽ፣ ባለቤትሽስ?» አለ እንግዳው የአልጋውን ብረት በሁለት እጆቹ እንደያዘ::

«የምን ባል! እዚህ እንደ ዕቃ ወርውረኸኝ የትም ከርመህ አሁን መጥተህ.....» በማለት ሽዋዬ የጀመረችውን ወቀሳ ሳትጨርስ «እሳቸው ነበሩ እንዴ አምጥተው ያስተኙሽ?» የእንግዳውን ዓይን በትዝብት እየተመለከተ ጠየቀ ከሆስፒታሉ ሠራተኞች አንዱ::

«ታዲያስ!» ብላ ሽዋዬ በቪክስ በታጀሉ ጣቶቿ የዓይኗን አካባቢ ዳለለችው::

ዮሐንስ የሚሰማውን ሁሉ ማመን አቅቶት «የጨው ዓምድ» ሆኖ ቀረ::



«ጌታዬ ሰዓት እየደረሰ ነው፣ አምስት ሰዓት ካለፈ ክፍያው የአንድ ሙሉ ቀን ሒሳብ ስለሚያስጨምርዎ ፈጠን ቢሉ ይሻላል» አለ ሌላው የሆስፒታሉ ባልደረባ::

«የእንግዳው ዓይን በንዴት ፈጠጠ፣ ራሱን መቆጣጠር ተስኖት ሽዋዬ ወደ ተጋደመችበት አልጋ ተወረወረ:: በመጫቷ ላይ አደጋ ከማድረሱ ፊት ተጯጩኸው ዮሐንስን ከክፍል አስወጡት:: በሁኔታው የተደናገጡት የሆስፒታሉ ሠራተኞች በሚያረጋጋ መንፈስ የተቆጣበትን ምክንያት ጠይቀው ለመረዳት ሞከሩ::

«ወይኔ ዮሐንስ! ይህች የመንገድ ዳር ሸርሙጣ እንደዚህ ትቀልድብኝ፣ ባትገድለኝም ሞቻለሁ፣ ተዋርጃለሁ፣ እኔ□ኮ የሕግ ሚስት ያለኝ የአራት ልጆች አባት ነኝ:: የት አባቷንስ አውቃታለሁና ነው <እንደ ዕቃ እዚህ ወርውረኸኝ ጠፋህ> የምትለኝ» አለ እጆቹን እያወራጨ::

ይህንን የድንፋታ ንግግር የሰማችው ሽዋዬ «ሰውየው ያፍዝ ያደንግዝ አለው አታሏችሁ ሳይከፍል እንዳይሄድ» አለች ድምጽዋን ከፍ አድርጋ::

«አንቺ ሸርሙጣ! እኔ ዮሐንስ ሁንዬ የምታሠር ከሆነ በአንቺ የዕዳ ክፍያ ሳይሆን አንቺን ገድዬ ነው» በማለት ወደ ክፍል ለመግባት ሲሞክር በግርግር ተሰቦ የከበበው ወሬ አዳናቂ ይዞ አስቀረው::

«እሽ አሁን ምን አድርግ፣ ምን ይሁን ነው የምትሉኝ?» አለ ዮሐንስ ወደ ሆስፒታሉ ሠራተኞች ፊቱን በማዞር::

«ለማንኛውም ወደ አስተዳደር ቢሮ እንሂድና እንነጋገር» አለ የጥበቃ ኃላፊው::

«የአስተዳደር ቢሮ የምሄድበት አንዳች ምክንያት የለኝም» በማለት ዮሐንስ ለወሬ ያስፈሰፈውን የሰው ጫካ መጣስ ጀመረ::

«ጌታዬ ክብርዎን ቢጠብቁ ይሻላል፣ ቅድም መግባት አይቻልም ብለን በር ላይ ልንመልስዎ ስንል <በሽተኛ ለማውጣት ነው> አላሉም ነበር?» አለው የቅበቃው ኃላፊ::

«አንተ ደግሞ የማነህ ደደብ» አለ ዮሐንስ ለመማታት እየቃጣ::

«ጌታዬ፣ ጠባይ ያድርጉ» አለ ሌላው ካርባይን የወደረ የጥበቃ ሠራተኛ:: ከዚህም ከዚያም ሆይ ሆይ ተባለና ዮሐንስ በጥቂት የሆስፒታሉ ሠራተኞች ታጅቦ ወደ አስተዳደር ቢሮ 3ኛ ፎቅ ወረደ:: ባጋጣሚ አስተዳዳሪው ለጊዜው ከቢሮአቸው አልተገኙም::

ዮሐንስ በብስጭት የደነዘዘ አካሉን ከአስተዳዳሪው ቢሮ የእንግዳ ወንበር ላይ ዘፍ አደረገው:: የሚናገረው ሁሉ ያለቀበት ይመስል ዓይኑን ግድግዳው ላይ ሰክቶ ዝም አለ::

«ወይኔ ሰውየው፣ ይህን ጉድ ቤተሰቤ በተለይ ባለቤቱ ብትሰማ ምን ይባላል» አለ ሲቃ በተናነቀው አንደበት:: በዚያ እንደ ጉድ ይመለከተው ከነበረ ሰው አንዳንዱ ከንፈሩን ሲመጥለት ሌላው የማነው አጭበርባሪ እያለ አንሾካሾከ::

«አንድ ጊዜ ስልክ ብደውል» አለ ዮሐንስ የአስተዳዳሪውን ጸሐፊ ልመና በተቀላቀለበት ጥያቄ::

«ይችላሉ» አለች ጸሐፊዋ::

«ሀሎ! ተስፋዬ ነህ! ለብርቱ ጉዳይ ስለምፈልግህ ጥቁር አንበሣ ሆስፒታል አስተዳዳሪው ቢሮ እንድትመጣልኝ፣ እባክህ ፈጠን በል» አለ::



«የአሳካሚ ካርድ ያልያዘ ሰው በዚህ ሰዓት አያስገቡም ክ!»

«ተስፋዬ እንደምንም ብለህ ድረስልኝ:: በየትና እንዴት እንደምትገባ አላውቅም፣ ብቻ ድረስልኝ» ካለ በኋላ ስልኩን ዘጋ::

«እስቲ ለማንኛውም ጊዜ ስጡኝ» አለ ዮሐንስ ገና ከወዲሁ የተረታ በሚመስል አንደበት::

«አንድ ሺህ ብር ለማይሞላ ገንዘብ ይህን ያህል ከሚጨነቁ ለምን ወዲያ ከፍለው አይገላገሉም?» አለ የሂሣብ ሠራተኛው በሽሙጥ አንቱታ::

«የተጠየቅሁት ርዳታ ቢሆን ኖሮ ሁለትም ሦስትም ሺህ ብር መክፈል የምችል ሰው ነኝ፣ ነገር ግን ይህን በአጭበርባሪዎች ሴራ የተወሰነብኝን ዕዳ ብከፍል ራሴን ማለቂያና መቆሚያ ወደሌለው አዘቅት መጣሌ ነው» አለ ዮሐንስ የሆስፒታሉ ዕዳ ክፍያ የሚያመጣውን መዘዝ በሚያስገነዝብ አነጋገር::

በስልክ የተጠራው ተስፋዬ ከሩብ ሰዓት በኋላ ተንደርድሮ ሲገባ በቁም እስር ላይ የቆየው ዮሐንስ ቀና ብሎ ተመለከተው::

«አንድ ጊዜ እሱን ላነጋግረው» በማለት አስፈቅዶ ወደ ኮሪደሩ ገለል አሉ:: ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ለጥቂት ደቂቃዎች ከተነጋገሩ በኋላ የዮሐንስ ባለቤት አሰገደች ይህን ወሬ ከሌላ ሰው ከመስማቷ በፊት እየተፈጸመ ያለውን ተንኮል በቀጥታ ከተስፋዬ አንደበት ብትሰማው እንደሚሻል ተስማሙ::

«ለክፉም ለደጉም አሰገደች አንድ ሺህ ብር ይዛልህ ብትመጣ አይከፋም» አለ ተስፋዬ:: ዮሐንስም በዚሁ ተስማምቶ ተለያዩ::

ሰባት ሰዓት ተኩል ሲሆን አስተዳዳሪው መጡ:: ጸሐፊዋ የደረሰውን ሁሉ ባጭሩ አስረዳቻቸው:: ከተበደልኩ ባዩ አንደበት መስማት የፈለጉት አስተዳዳሪ ዮሐንስን አስጠሩ::

ዮሐንስ ነገሩን ከመነሻ እስከ መድረሻ ረጋ ብሎ አስረዳ:: አስተዳዳሪው ማመን እስኪያቅታቸው እየተገረሙ «ታዲያ አሁን ምን ቢደረግ ይሻላል ነው የምትለው አንተ?» ብለው ጠየቁት፣

«እኔ በምንም ዓይነት የዚች ዱር አዳሪ ሴት የልጅ አባት የምሆንበት ሁኔታ የለም» በማለት ንግግሩን ሳይጨርስ፣

«አዎ! ጌታዬ አዎ!» አሉ አስተዳዳሪው:: ወዲያውም ቀጠል አድርገው:: «እርሷ የልጅ አባት ነው ብላለች:: አንተ ደግሞ አላውቃትም ነው የምትለው፡ ይሁንና ከየትም ይሁን ከየት በመኪናህ አሳፍረህ አምጥተህ አስተኝተሃት መሄድህን አልካድከም:: አይደለም እንዴ?»

«የለም! የለም! ጌታዬ አይሳሳቱ! ነገሩ እንደርሱ አይደለም! ምነው? ምነው?» አለ ዮሐንስ የአስተዳዳሪውን ንግግር አቋርጦ::

«ታዲያ እንዴት ነው? ቅድም የነገርኸኝ ይኸንኑ አልነበረም?» አሉ አስተዳዳሪው የዮሐንስ ማስተባበያ በሚያጣጥል መልክ::

«እኔና ባለቤቴ ከመንገድ ላይ አግኝተን ለነፍስ ብለን ሆስፒታል አደረስናት እንጂ እኔ አላስተኛኋትም ነው የምለው» አለ ዮሐንስ::

አስተዳዳሪው በሽሙጥ ፈገግታ «ባል አይደለሁም ግን ሆስፒታል ማድረሴን እርግጥ ነው ካልክ አስተኝተንና አዋልደን ያከምንበትን ሂሣብ ክፈልና ሌላውን ክርክር በፍ/ቤት መሟገት ትችላለህ:: በበኩሌ ጨርሻለሁ:: ማንም ከየሸርንቁላው የዲቃላውን



እናት እያመጣ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ እየጣለ ሂሣቡን አልከፍልም ማለት አይችልም:: ኃይለ ሚካኤል የተጠየቀውን ገንዘብ ሲከፍል እራሷን ይዞ እንዲወጣ አድርጉ» በማለት ለጥበቃ ኃላፊው ትዕዛዝ ሰጥተው ዮሐንስ እንደ ተቀመጠ እየተጎሻመጡ ጥለውት ወጡ::

«ወይ የቀን ጎዶሎ! ምነው ፈጣሪዬ ምን አልኩህ? በዚህ ዓይነት ውርደት ትቀጣኛለህ፣ ከቶ ምን በደልኩህ» በማለት ቀና ብሎ ከጣራው ሥር ተደብቆ ጉዱ ያልሆነውን ጉድ የሚታዘብ ለመሰለው እግዚአብሔር ስሞታውን አሰማ::

«ዮሐንስ፣ እኔ አላምንም፣ ምንድነው ነገሩ? የምሰማው ታሪክ እውነት ነው?» አለች አሰገደች ከጸሐፊዋ ቢሮ ወደ አስተዳዳሪው ቢሮ ግማሽ አካሏን አስገብታ፣ ተስፋዬ ከኋላዋ ተከትሏታል::

ከአሰገደች መንታ ጥያቄ ለየትኛው መልስ መስጠት እንዳለበት እስኪወስን ድረስ ግራ ገብቶት ዝም አለ ዮሐንስ::

«አሁን የሚያዋጣው የታከመችበትን ዕዳ ከፍሎ የወ/ሮ ሸዋዬ ባልም ወይም የልጅ አባት አለመሆኑን በሕክምና ምርመራና በፍርድ ቤት ተሟግቶ ራስን ነፃ ማውጣት ነው:: ከዚህ ሌላ አማራጭ መንገድ ያለ አይመስለኝም» አለ የሂሣብ ሠራተኛው::

«ለመሆኑ ስንት ብር ነው?» አለ ተስፋዬ

«ዘጠኝ መቶ አሥራ አምስት ብር ከሰባ ሳንቲም ብቻ ነው» አለ ሂሣብ ሠራተኛው::

«ባለቤቴ ይሉኝታ ፈርቶ የሌለበትን ወንጀል አምኖ ገንዘብ ከሚከፍል መታሠሩን እመርጣለሁ፣ ቢታሰር አይሟሟ፣ ሕግ

ካለ በሕግ ነፃነቱን ያገኛል» አለች አስገደች አንገትና ትከሻዋን እያዋቃች::

«ገንዘቡን ከፍሎ ሙግቱንና የሕክምና ምርመራውን መቀጠል ሲቻል ለምን ይታሠር?» አለ ሌላው የሆስፒታሉ ሠራተኛ::

በዚህ ውዝግብ መካከል ተስፋዬ ሂሣብ ሹሙን በዓይን ጠቀስ አደረገውና ገለል አሉ «የእኔ ወንድም እነርሱን ተዋቸው፣ ያውልህ 1000.00 ብር፣ ዮሐንስ ከባለቤቱ ጋር ወደ ቤቱ ይሂድ፣ ለእኔ መልሱና ደረሰኙ ይሰጠኝ» በማለት ውጥረቱን ለማርገብ ተስፋዬ የራሱን እርምጃ ወሰደ::

«የሂሳብ ሹሙ ወደ እነ ዮሐንስ ተመልሶ ግድ የለም፣ ለአሁኑ በእኔ ዋስትና ወደ ቤትህ ሂድ፣ ነገ ተነገወዲያ ተመለስና እንነጋገር» አለው ከአዘኔታ የመነጨ በሚመስል ውሳኔ::

«ይኸ እንኳን ይሻላል» አለች አስገደች::

ዮሐንስ ግን የሕፃኑ ደምና የእሱ ደም ተመርምሮ አባትና ልጅ አለመሆናቸው እንዲረጋገጥ ስለፈለገ ሸዋዬ ከሆስፒታል ከመሰናበቷ በፊት በተፈለገች ጊዜ ሕፃኑን ይዛ እንድትቀርብ ዐሳብ አቀረበ::

ተስፋዬ «ይኸንን እኔ ተከታትዬ ላስፈፅም፣ አሁን አንተ ወደ ቤትህ ሂድ» በማለት ያቀረበውን ዐሳብ አስገደች ስለደገፈችው እነ ዮሐንስ ወደ ቤታቸው አመሩ::

«አሬ አያርፍ፣ ዓይኔ አያርፍ፣ ታስታውሳለህ በቀደምለት እኔ ነበርኩ እባክህ እነዚህን ሰዎች እንርዳቸው ብዬ መኪና ያስቆምኩህ:: ምነው ልሣኔን በዘጋው» አለች አስገደች::



«.....ዛሬ ግን እንዴትና ለምን ወደዚህ መጣህ» በማለት ጥያቄ ያስከተለች እንደሆነ ዮሐንስን መልስ ስለሚቸግረው በሥጋት ተወጠረ:: ነገሩን ለማረሳሳት ወይም መልሱን ለማዘጋጀት የሚረዳውን ጊዜ ለመግዛት፣ ብድግ ብሎ ወደ መጸዳጃ ቤት ሔደ:: «እኔ ሌላ ምክንያት ብደረድር ውሎ አድሮ ሐቁ መውጣቱ ስለማይቀር መዋሸት የለብኝም፣ እንዴት እንዳታለለችኝ እውነቱን መናገር ነው ያለብኝ» በማለት ወስኖ ወደ ሳሎን ተመለሰ:: ቀልዱ፣ ሽሙጡና ተረቡ የነገው ውሎ ምክክር ራት ላይ እንደማባያ ተኮመኮመና ገበታ ከፍ እንዳለ ዮሐንስ ወደ መኝታ ቤት ገባ::

«ዛሬ ሥዕል ቤት ነው የማድረው» አለች አስገደች

«ይሁን» አለ ዮሐንስ፣ ትንሽም ሳያቅማማ፣

# ምዕራፍ 16

## አስገደች በሥዕል ቤት

ሥዕል ቤት አስገደች ዕለት በዕለት ከፈጣሪዋና ከአማላጆቿ ጋር የምትገናኝበት የቪላው 4ኛው መኝታ ክፍል ነው:: የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ የመላዕክት፣ የጻድቃንና ሰማዕታት ምስሎችና መንፈሳዊ ጥቅሶች ግድግዳውን ሞልተውታል::

በአንደኛው ግድግዳ ጥግ ከመጽሐፍ ቅዱስ እስከ መንፈሳዊ መጽሔት የያዘ መደርደሪያ አለ:: በሌላው ግድግዳ ጥግ መለስተኛ ጠረጴዛና አራት ወንበሮች ተሰይመዋል::

በስተምሥራቁ ግድግዳ ወለል ላይ እንድ ዳጎስ ያለ የጥጥ ፍራሽ አምሮ ተነጥፏል:: ይህ ቦታ አስገደች ጧትና ማታ ተንበርክካ የምትፀልይበት ስለሆነ አማላጆቿ ጭምር የሚስተናገዱበት መቅደስ ነው ብላ ታስባለች::

ሥዕል ቤት፣ አስገደች አንዳንድ ጊዜ ነገር ሲገባት የምትቆዝምበት፣ ከዚያም አለፍ ሲል የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ትልሟን የምትቀይስበት ክፍል ነው::

አስገደች ቀን በኀሊናዋ መዝግባ ከመደበኛ ሥራዋ ጋር ስትገረድፍ የዋለችውን የግልና የቤተሰብ ጉዳዮች በጥንቃቄ የምታሰዝበው (ከክታ አቡክታ የምትጋግረው) ሥዕል ቤት ውስጥ ነው::

የአስገደች ሥዕል ቤት፣ ከሚመስሏት ጠያቂ - ጓደኛ ዘመድ አዝማድ ጋር ቆይታ ያደርጉበታል:: ሲያስኛቸውም ቡናና ሻይ ከልዩ መክሰስ ጋር ይቋደሱበታል:: ሥዕል ቤት የአስገደች ሁለ - ገብ ቢጢሌ አዳራሽ ናት::



ዛሬ አስገደች ሥዕል ቤት የገባችው ራሱን የቻለ የቤት ሥራ (አጀንዳ) ይዛ ነው:: «ዛሬ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በአክሊሉ፣ በሽዋዬ፣ በሆስፒታሉ ባልደረቦች በአንድ ወገን፣ ዮሐንስ፣ ተስፋዬና እኔ በሌላ ወገን የተወነው ትያትር የቱን ያህል ተዋጥቶልናል? የሚቀጥለውን ክፍል ሁለት በተሻለ ጥራት እንዴት መተወን እንችላለን?» የሚሉት መጠይቆች በየፈርጃቸው መልስ መልሳቸውን በዚህ የአስገደች ሥዕል ቤት አዳር ያገኛሉ::

«እኔ ያለፈቃዱ ከሱ በማርገዜ፣ በመካከላችን የነበረውን ግንኙነት ለማቋረጥ <አስገደች ደምሴን መግደል> እንዱ ዘዴ እንዲሆን ታስቦ ነበር:: አዎ! ባልሞትም ሞቻለሁ:: ከተደገሠልኝ ግድያ የተረፍኩት በጥበቤ እንጂ በእሱ አዘኔታ አይደለም::

«በዳንስና በፍቅር ዮሐንስን ማርካት አይቻልም እንዳልተባለለት ሁሉ <የዳንስ ወለል ኮከብ፣ ያልጋ ንግሥት ልትባይ ይገባሻል> አስኝቼ ነው ከግድያ ያመለጥኩት::

«ዮሐንስ ሴት የቀመሰው ገና የ13 ዓመት ልጅ ሳለ እንደነበር ነግሮኛል:: ሦስት ልጃገረዶችን አበላሽቷል:: ቋሚና ጊዜያዊ የሴት ጓደኞቹን ብዛት እሱም የሚያውቅ አይመስለኝም:: ዛሬም እንኳ በየሆቴሉ የሚያገላብጣቸውን ሴቶች እነ እገሊት ማለት ባልችልም፣ ይታዩኛል:: ዮሐንስን ከአስገደች መዳፍ ውስጥ ፈልቅቆ ለማውጣት ያቾ አቃጣሪ እህቱ ቆማ ነው የምታድረው:: ዛሬም ቢሆን እንቅልፍ የላትም፣ ከንቱ ልፋት፣ አስገደች ደምሴ ቀድማለች» አለች አስገደች የራሷን ሴስኝነት በእውን የዮሐንስን አመንዝራነት በምናብ እያሰላሰለች::

ወዲያው ባጠገቧ ካለው ጠርሙስ በብርጭቆ የቀዳችውን ውሃ ጭልጥ በማድረግ ዘና አለች:: የጠጣችው ውሃ ተጨማሪ

ብርታት የሰጣት ይመስል ከተቀመጠችበት አፈፍ ብላ ተነሳች፡፡ ጥቂት ከተንጎራደደች በኋላ፣ «ዮሐንስ ሁንዬን ውድ ባለቤቴን አሁን <ልጡ የተራሰ፣ ጉድጓዱ የተማሰ> ያለቀሰት ምስኪን ፍጡር አድርጌዋለሁ፡፡ ጆኒ በክብር ከነሕይወቱ ወደ መከራ እንጦርጦስ ይወርዳል፡፡ ፊት ይነጭለታል፣ ደረት ይመታለታል፡፡

«ይህ በዮሐንስ ላይ የተወሰደ ርምጃ፣ በተለይ ወላጆቹ በእጠቃላይ ዘመዶቹ ድኽነቴን እንደ ነውር - ኃጢአት በመቁጠር ሰነሱኝ - ቤተሰባዊ ፍቅር አፀፋዊ ብቀላ ነው፡፡

«በክፍል አንድ ተውኔት ድንቅ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ አንዳች ነገር አልተዛነፈም፡፡ ጆኒ ተቀድሟል፡፡ በተዘረጋለት ወጥመድ ውስጥ ገብቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ቢንፈራገጥ ይላላጣል እንጂ ምንም አያመጣም፡፡

«አዎ! ወንድ ጨካኝ ነው፣

ዮሐንስ ወንድ ነው፣

ስለዚህ ዮሐንስ ጨካኝ ነው፣ አረመኔ ነው፡፡ ዮሐንስ ከሌላው ወንድ ተለይቶ ሊታዘንለት አይገባም፡፡

«በስለት አንገቴን እስኪቀላ ልጠብቀው አልችልም፡፡ ጠርጥር ተብሏል፡፡ የማይጠረጥር ወንድ ከሴት አንድ ነው የሚለው የአባቴ አነጋገር ዛሬ ዛሬ ለእኔም ለሴቲቱ መሥራት አለበት፡፡ ጠርጣሪ ወንድ ብቻ እንዲሆን የፈቀደውን የተበላሸ የወንድ ሥርዓት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መታገል የግድ ይሆናል፡፡

«ጠርጥር፡- እዚያ ውስጥ የተደበቀ አይጠፋም መርዛም ሥንጥር፣ የሚለው መላ ምት፣ እኛን ሴቶችንም ሊያነቃን ይገባል፡፡ ከመጠርጠር በፊት፣ ሁሉንም ነገር መጠርጠር ክፋት



የለውም፡፡ ምንጊዜም በማንኛውም ሁኔታ መቀደም አያስፈልግም፡፡ ተመራምሮ ውጤት ላይ መድረስ መነሻው መጠራጠር ነው፡፡ አለመጠራጠር ማለት ደካማነት ነው፡፡ ለዚህም ነው ተጠራጣሪ ወንድ ብርቱ፣ የማትጠራጠረዋ ሴት ደካማ መሆንን ለማግለጽ፣ ተጠራጣሪነት የወንድነት ዓይነተኛ ባሕሪ ተደርጎ ሲሾፍ ነው የተኖረው፡፡

«እኔ ልጅት በዮሐንስ ላይ የወሰድኩት ርምጃ ዝንተ ዓለም ወንድ የኃይልና የጥንካሬ ጣዖት ተደርጎ የሚመሰክበትን የወንድ ሥርዓት ባፍጢሙ ለመድፋት ፋና ወጊ ይሆናል፡፡

«ስለሆነም ፈጣሪ እምላክ ለእኔ የሰለሞንን ጥበብ፣ ለዮሐንስ ደግሞ የኢዮብን ትግሥት እንዲሰጠን እማፀነዋለሁ አደራውን፡፡

«አክሊሉና ሽዋዬ ነፍስ ናቸው፡፡ ይህች መናጢ መታረሻዋን አገኘች፡፡ አክሊሉ ያመት ፈቃዱን ወስዶ አርፎ ከጓዳው መወሸቅ አለበት፡፡ ይኽን ትዕዛዝ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ በዘበኝነት ስቀጥረው ግንኙነታችን ወደደም ጠላም የአሽከርና እመቤት ጭምር መሆኑን ይገነዘባል፡፡ የሚያስፈልገውን ያህል ገንዘብ ይሰጠዋል፡፡ በማስታቅፈው ገንዘብ እሱም ቤተሰቡም ከድኽነት ይፋታሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ፍቅርም አቀምሰዋለሁ - በቃ አለቀ እክሊሉ ከዚህ በላይ ምን ይፈልጋል? አመዳም የደኻ ልጅ፡፡ ከዚህ ሴራ መረብ ውጭ ለመሆን ካፈነገጠ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡ እኔ አሰጉ እንኳንስ ስራሴ............

«እዎ ገንዘብ ኃይል ነው፡፡ ገንዘብ ሥልጣን ነው፡፡ ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ የተባለው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ይህ አባባል እንድ ጊዜ እንደገና በተግባር መፈተን አለበት፡፡

«ዓለምን የሚያሽከረክሯት (እስከዛሬ የወንድ ብቸኛ መሣሪያ በመሆን) ገንዘብ፣ ሥልጣን፣ ኃይል፣ ወሲብና ፍቅር ናቸው:: ዛሬ እነዚህ ሁሉ በእኔ - አሰገደች ደምሴ እጅ ይገኛሉ::

«የማዴቦ ልጅ (ዶ/ር ወልደ ሚካኤል) እሞት-አልጋው ላይ ሆኖ የካንሰሩን ሥቃይ ያዳምጥ፣ የክሊኒኩ ሥራ ለእኔም አልበቃ::

«በመጨረሻ እኔና ልጆቼ በተለይም ማርያማዊት ወ/ሚካኤል ሚሊየነሮች ሆነን በሀብት ባሕር አይደለም! አይደለም! በሀብት ውቅያኖስ ውስጥ የምንዋኝበት አዲስ ዓለም ሕይወት ይፈጠራል::

«እዚህ ላይ የእምነት፣ የስብዕና፣ የሞራል፣ የሥነ ምግባር፣ የሀቀኝነት ጥያቄዎች ለጊዜው ገለል ማለት ይኖርባቸዋል:: አንድ ባሪያ ለሁለት ጌታ በአንድ ጊዜ ሊገዛ አይችልምና::

«ዓላማዬ በትክክል ግቡን ከመታ በኋላ ለጊዜው የተገለሉት እነዚህ ኅብረተሰቡ የሚነብኝ የሰው-ሰውነት መስፈርቶች ወደነበሩት እንዲመለሱ ይሆናል:: ያንጊዜ ደግሞ ለሌላ አዲስ ጌታ ታደረ ማለት ነው--- ለሰማዩ ጌታ፣ ተራ በተራ::

«ንስሐ ይገባል፣
ምፅዋት ይሰጣል፣
በጎ በጎ ተግባር ይፈፀማል::

«ዓለም እንደዚህ ናት:: የማነስና የመብዛት ጉዳይ ካልሆነ በቀር፣ ሰው የተባለው ፍጡር ሕልውና ከዚህ ወጣ-ገባ ውጭ አይደለም:: ዓለም-ሕይወት የተቃርኖና አንድነት ውሕደት ክስተት



ነው:: ዓለም በዚህ የተፈጥሮ ሕግ ሲገዛ ኖሯል:: ዛሬም እየተገዛ ነው:: ርኅራኄና ጭካኔ፣ ጽድቅና ኩነኔ፣ ደግነትና ክፋት፣ ብልጽግናና ድኽነት ነበሩ፣ አሉ፣ ወደፊትም ይኖራሉ::

«እግዚአብሔር ቁጣው የዘገየ፣ ምሕረቱ የበዛ አምላክ ነው የተባለው፣ እንደ ኃጢያታችን ብዛት እንደ ሰውነታችን ክፋት ፈጥኖ ስለ ማይቀስፈንና የንስሐ ጊዜ ስለ ሚሰጠን አይደል? ነው! ነው! ነው!!!

«አዎ! ይኽንን ውጥን ሥራ እንዲሳካልኝ፣ እንዲባርክልኝ እማፀነዋለሁ» በማለት አሰገደች በቁሟ ሦስት ጊዜ አማትባ በጉልበቷ ተንበርክካ ዓይኗን ከጨፈነች በኋላ በግንባሯ ተደፋች--- ለመጸለይ::

«የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም የፈጠርክ፣ ሥርዓቱንም የመሠረትክ፣ በሰማየ ሰማያት የምትኖር የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ --- የዳዊት፣ የእስራኤል አምላክ፣ ኃያሉ እግዚያብሔር ሆይ! አንተን አመለክሁ ሰይጣን ዲያብሎስን ካድሁ::

«አንተ ቸር ይቅር ባይና የፍቅር አምላክ ነህ:: አንተ ቁጣህ የዘገየ ምህረትህ የበዛ አምላክ ነህ፣ እንደ ሰውነቴ ክፋት እንደ ኃጢአቴ ብዛት አልቀሰፍከኝም::

«ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ በባሕሪያችን ያደረው ኃጢአት ይሰረይ ዘንድ አንድ ልጅህን ወደዚህ ዓለም ላክኸው:: እርሱም ስለእኛ መዳን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በመስቀል ላይ ሰጥቶ ሞተ:: ተቀበረ፣ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በመቃብር ቆይቶ ተነሳ፣ ሞታችንን በሞቱ ድል ነሳ:: ስለዚህ አዳኜን ጌታ እየሱስ ክርስቶስን አመንሁ፣ ሰይጣን ዲያብሎስን ካድሁ::

«መንፈስ ቅዱስ አንተ ከአብ የሰረፅህ፣ ከአብ ከወልድ ጋር በአንድነት አመልክሃለሁ፣ እሰግድልሃለሁ። አንተ በነብያት አድረህ የተናገርክ ነህ፣ እኔንም ከእርኩስ መንፈስ ያፀዳህ ነህ፣ ከአብ ከወልድ ጋር በአንድነት እሰግድልሃለሁ። ሰይጣን ዲያብሎስን ክጃለሁ።

«ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቀኑንም ሌሊቱንም ባርከህ፣ እኔንም ቤተሰቤንም ከአልታሰበ የሰይጣን ሽመቃና አደጋ ሰውረህ እዚህ ስላደረስከኝ አመሰግንሃለሁ።

«ክብር ምሥጋና ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ዛሬም ነገም፣ ለዘወትርም አሜን»

«ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይኸን ልመናዬን፣ ይኸን ምሥጋናዬን፣ ይኸን አድናቆቴን በእመቤቴ ቅድስት ድንግል ማርያም፣ በቅዱስ ዑራኤል፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በቅዱስ ጊዮርጊስ፣ በቅዱስ ተክለ ሃይማኖት አማላጅነት ወደ ገናናው ዙፋንህ ቀርቤና ራሴን ዝቅ አድርጌ አቀርባለሁ» በማለት የተለመደ ጸሎቷን አደረገች።



# ምዕራፍ 17

## የዮሐንስ ውጥረት

ጧት በቁርስ ገበታ ላይ ሲሰየሙ ሁለቱም ዓይናቸው ቀልቶና አብጦ፣ አንዱ የሌላውን ችግርና ጭንቀት የተገነዘቡ ቢመስሉም ስለችግሩ ማንሳት ሳይፈልጉ ቁርሳቸውን ቀማምሰው ተነሱ።

ዘበኛው የውጭውን በር ወለል አድርጎ ሲከፍት የተስፋዬ አውቶሞቢል ስተት ብላ ቪላው በር አካባቢ ስትቆም፣ ዮሐንስ እስከ በረንዳ ብቅ ብሎ ተስፋዬንና ባለቤቱን በእጅ ሰላምታ ተቀበለ።

«እንቺ ግቢ» አለና ተስፋዬ የዮሐንስን እጅ እንደ ጨበጠ ወደ አትክልቱ ውስጥ ዞር አሉ።

«ምን አሰብክ» አለ ተስፋዬ የዮሐንስን ዓይን ዓይን እየተመለከተ።

«ምን አስባለሁ፣ እኔ በዓይኔ እንቅልፍ ሳይዞር አፍጥጬ ነው ያደርኩት። እሷም ሥዕል ቤት ነው ያደረችው»

«ምን ትቀልዳለህ» አለ ተስፋዬ የዮሐንስን ንግግር አቋርጦ፣ ቀጠል አድርጎም «ነገሩ ምን ይመስልሃል፣ የጤና ነው?» አለ ተስፋዬ በአስገደች ዝምታና ገለል ብሎ ማደር ያደረበትን ሥጋት ለመግለጽ።

«ከአስገደች ጋር ቁርስ ገበታ ላይ ስንገናኝ ዘልላ የምታንቀኝ መስሎኝ ነበር፣ እሁንም ቢሆን ጠባ በማንኛውም ደቂቃ ሊፈነዳ ይችላል ብዬ እሰጋለሁ» አለ ዮሐንስ ጭንቅ በቀሰፈው አንደበት።

«እቤት አይሻላችሁም? ከብርድ ላይ ግቡ» አለች አስገደች ድምጿን ከፍ አድርጋ::

ዮሐንስ ልብሱን ለባብሶ በተስፋዬ አውቶሞቢል ሲወጡ ሲሉ የተስፋዬ ባለቤት እኔን ፏሮ ጣል አድርጋችሁኝ እለፉ በማለት የኋላ በር ከፍታ ገባች:: ፏዛንቼስ ሱፐር ማርኬት አካባቢ ሚስቱን አውርዶ ተስፋዬ ጉዞውን ወደፊት ቀጠለ::

«የት ነው የምንሔደው፣ ጥቁር አንበሳ ነው እንዳትለኝ?» አለ ዮሐንስ::

«ወደዚያም እንሔዳለን፣ ግን ከዚያ በፊት በፍንጃል ቡና ላይ የውሎአችንን ሥልት መቀየስ ይኖርብናል:: ከየት እንጀምር? ስለ አስገደች ቁጣ ማብረጃ መነጋገር ያለብን ይመስለኛል» አለ ተስፋዬ::

«ካልክስ አሁን በይበልጥ ያሳሰበኝ የዚያች ሴተኛ አዳሪ ጉዳይ ሳይሆን የአስገደች የጠብ ዝግጅት ነው:: እንደምታውቀው አስገደች ደግ ነች፣ የደግነቷን ያህል ደግሞ እልኸኛ ነች:: ተጠራጣሪ ነች:: በሆነ ባልሆነ ትርኪ ምርኪ ነገር ማንንም አትጣላም:: ከተጣላችህ ግን የምር ነው የምታደርገው:: በጣም ታምነኛለች፣ እኔ ደግሞ እሷ ከምታምነኝ የበለጠ እምናታለሁ:: ጨዋ ነች:: ራሷን አክብራ ባሏንም የምታስከብር ልዩ ሚስት ነች፣ ጠቧን የምፈራውም ስለዚህ ነው» በማለት ዮሐንስ ንክኪ በሌለው ዱብ ዕዳ ጸንቶ የቆየው ትዳሩ ሲበጠበጥ፣ ምናልባትም ሲፈርስ ታየውና «አበስኩ ገበርኩ» አለ ፊቱን በሁለቱም እጆቹ እየሸፈነ::

«አንተ ይህችን ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሃት መቼ ነበር? እውነቱን ንገረኝ» አለ ተስፋዬ::



«ተስፋዬ ትቀልዳለህ መሰለኝ፣ እንዴት ትጠረጥረኛለህ፣ ደግሞስ ከአንተ የምደብቀው ምን ምድራዊ ምስጢር ይኖራል?» አለ ዮሐንስ በተስፋዬ ጥያቄ ተገርሞ::

«እንደማትዋሸኝ አምናለሁ፣ ይህ ከሆነ አሁን ሁለት ከባድ ሥራዎች ከፊታችን ተደቅነዋል:: ሁለቱም ጊዜ አይሰጡም:: ለነገ የሚያስኝ ነገር ስለ ሌለ ሁለቱንም ጎን ለጎን ተከታትለን መፍትሄ ማምጣት ይኖርብናል» አለ ተስፋዬ::

«የሸርሙጣዋ ዕዳው ገብስ ነው፣ የአስገደች ጠብ እንዳይፈነዳ ምናልባትም ገንፍሎ ከፈነዳ ፈጥኖ የሚበርድበትን ዘዴ በቅድሚያ መሻት አለብን:: ለእኔ ከትዳሬ የሚበልጥ ምንም ነገር የለም» አለ ዮሐንስ::

«አትሞኝ! የሸርሙጣዋ ሴራ ተጋልጦ ከሸፈ ማለት፣ ዮሐንስ ንፅሕናው ተረጋገጠ ማለት መሆኑን መዘንጋት የለብህም:: እንዲያውም ሁለት ወፍ በአንድ ድንጋይ እንደተባለው ይሆናል» አለ ተስፋዬ::

«እሱስ እውነት ነው» አለ ዮሐንስ::

ይህንኑ ሲያወጡ ሲያወርዱ ወደ አራት ሰዓት ገደማ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ደርሰው መኪናቸውን አቁመው ወደ አስተዳዳሪው ቢሮ አቀኑ::

ጸሐፊዋ «እንግዳ ስላላቸው አረፍ በሉ» አለቻቸውና ከመቀመጣቸው በፊት እንግዳው ስለ ወጡ ግቡ ተባሉና ገቡ::

«ከምን ደረሳችሁ?» አሉ አስተዳዳሪው ጠቡ መብረድ አለመብረዱን ለማወቅ ያደረባቸውን ጉጉት በሚገልጽ ምልከታ::

«ለጊዜው የትም አልደረስን:: በዚህ አጭር ጊዜ የት ይደረሳል ብለው ነው!! ቁም ነገሩ እሱ አይደለም:: ጌታዬ እኔ አንድ ጥያቄ እንድጠይቅዎት ይፈቀድልኝ?»

«ይቻላል::»

«ለመሆኑ ይህ ሆስፒታል ከሣሽም፣ ዳኛም፣ አስፈጻሚም የመሆን ሥልጣን እንዴት ነው ሊያገኝ የቻለው?» የተስፋዬ ጥያቄ ነበር::

«የዚህ መልስ አጭር ነው» አሉና አስተዳዳሪው «ለመሆኑ ሰው ሁሉ ሚስቱን ወይም ቁባቱን እያስረገዘ እኛ ግቢ አምጥቶ ጥሎ የሚሄድና እኛም በነጻ አዋልደንና አክመን፣ በነጻ የምንለቅ ከሆነ፣ ሆስፒታሉ ይህን ችግር ተሸክሞ መዝለቅ የሚችል ይመስላችኋል?» በማለት አስተዳዳሪው መልሰው ተስፋዬን ጠየቁ::

«የዚህ ዓይነት ችግር ከዚህ በፊት ገጥሟችሁ ያውቃል፣ ወይስ ገና ለገና ይመጣብናል ከሚል ሥጋት የመነጨ ነው?» ተስፋዬ መልሶ ጠየቀ::

«የሚገርመው፣ በእውነት በጣም የሚገርመው፣ ይህን ዓይነቱን ወራዳ ድርጊት የሚፈጽሙት ያጡ የነጡ ድሆች ቢሆኑ ምንም አልነበር፣ በዚህ ዓይነቱ ቅሌት ከተጋለጡት አብዛኞቹ በሥልጣንም በሀብትም አንቱ የተባሉት መሆናቸው ነው» አሉ አስተዳዳሪው ዓይናቸውን ከዮሐንስ ላይ ሳይነቅሉ::

እነ ዮሐንስ የሚሉትን አጥተውና እፍረትም ስለተሰማቸው እርስ በርስ እየተያዩ ዝም አሉ::

«እኔ ከተፈቀደልኝ አንድ ትንሽ ምክር ቢጤ ልለግሥ» አሉ አስተዳዳሪው ኮስተር ብለው::



«ጌታዬ ይቀጥሉ! ይቀጥሉ!» አለ ተስፋዬ::

ዮሐንስ የገባበትን ቀውስ እያሰላሰለ የተስፋዬና የአስተዳዳሪው ቃለ ምልልስ ታዳሚ ሆነ::

«ይህችን ሴት በእርግጥ የማታውቋት ከሆነ፣ እንዳላችሁትም ርኅራኄያችሁ ያመጣባችሁ መዘዝ ከሆነ፣ በብልጠቷ እንደ በለጠቻችሁ ሳታመነቱ ማመን አለባችሁ:: ተውኔቱ በእሷ አሸናፊነት፣ በእናንተ ተሸናፊነት መደምደሙን ከመቀበል ሌላ አማራጭ ያላችሁ አይመስለኝም:: ይልቁንም የልጅ ማሳደጊያውን ጥያቄ እንዳታስከትል ከወዲሁ ነገሩን በሽምግልና የምትገላገሉበትን ዘዴ መሻቱ ነው የሚሻላችሁ» በማለት አስተዳዳሪው ምክር ቢጤ ከለነዘሩ በኋላ «ጌታዬ ባልሳሳት እርስዎ ትዳር አለዎት?» ብለው ዮሐንስን ጠየቁት::

«አዎ ትዳር አለኝ፣ ያውም የደረጀ» አለ ዮሐንስ እንዲያዝኑለት ትከሻውን እየጨመቀ::

«ከዚች ሴት ጋር ሲነታረኩ ባለቤትዎ ምንም ያህል ቢያምኑዎ ስሜታቸውን መጎዳቱ የማይቀር ነው:: ንትርኩ በቀጠለ መጠን የባለቤትዎም ጥርጣሬ ያንኑ ያህል ይጨምራል:: ትዳራችሁም ወደባሰ እክል ያመራል:: ስለዚህ በተቻለ መጠን ውሾን ያነሳ ውሻ ይሁን በሚል አካሄድ ድፍንፍን ማድረጉ ይበጅ ይመስለኛል:: ነገሩ አንድ ጊዜ አደባባይ ከወጣ ማጣፊያው እንዳያጥር.... ይቅርታ በግል ኑሮዎ ላይ ብዙ አወራሁ» አሉ አስተዳዳሪው::

«ነገሩ□ኮ <ወደሽ ከተደፋሽ፣ ቢረግጡሽ አይክፋሽ> እንደተባለው መሆኑ ነው» አለ ዮሐንስ በስላቅ ፈገግታ::

«አልከውና፣ አልከውና» አለ ተስፋዬም ስቆ በሚያስቅ ምልከታ ወደ ዮሐንስ ዞር ብሎ::

«የሆነስ ሆነና ድል አድራጊዋ አራስ አልጋዋን ለቃለች?» አስተዳዳሪው ጸሐፊያቸውን ጠሩተው ጠየቋት::

«አዎ መውጣቷን ሰምቻለሁ» አለች ወደ አስተዳዳሪው ቢሮ ግማሽ አካሏን በማስገባት:: አድራሻዋም አለን፣ በተፈለገች ጊዜ ሁሉ ለመቅረብ ትችላለች» አለች ፀሐፊዋ::

«ከእኛ የምትፈልጉት ነገር ካለ እንተባበራለን» በማለት አሰናበቷቸው::

«እኒህ ሰው□ኮ ሙግቱ አብቅቷል ነው የሚሉት፣ ገና ፋይሉ ሳይከፈት! አይመስልህም!» የዮሐንስ ጭንቀት የተሞላበት ጥያቄ ነበር::

«አልተሳሳትክም ዮሐንስ!» አለ ተስፋዬ::

ተስፋዬና ዮሐንስ የአስተዳዳሪውን ምክር አዘል አስተያየት በየራሣቸው እያፍተለተሉ እንደ ተኮራረፈ ሰው ሳይነጋገሩ መኪናቸው ውስጥ ገብተው ከሆስፒታሉ ግቢ ወጡ::

***

ሸዋዬ ልጇን ታቅፋ፣ በኮንትራት ታክሲ ከመኖሪያ ግቢዋ ደርሳ እግሯ መሬት ከመንካቱ፣ በታክሲዋ የሞተር ድምጽ የተቀሰቀሰ ጎረቤት በነቂስ ወጥቶ በእልልታ ተቀበላት:: የሠላሳ ብር ዱርዬ በግ ታርዶላት ደም ተራምዳ፣ ወደ እናቷ ቤት ገባች::

ፈገግታዋና አረማመዷ ከአራስነት ይልቅ ከጦር ግንባር በድል አድራጊነት የተመለሰ ጀግና ይመስል ነበር:: የሸዋዬ መፍነክነክ፣ የጎረቤቶቿ አቀባበል ሲታከልበት፣ ከዚህ ሁሉ ጀርባ



በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ያስብዙ ታዳሚ የተተወነው ትያትር ሥምረት፣ ለሸዋዬ የጀግና አቀባበል ተደረገላት የሚያስኝ ነበር:: አክሊሉ የሒሳብ ሠራተኛውን በማግባባት የደረሰኙን ፎቶኮፒ ይዞ መጥቷል:: ሌላ ትልቅ ድል::

«የገንዘቡ ከፋይ ዮሐንስ ሁንዴ ተብሎ በደረሰኙ ላይ መጻፉን አክሊሉና ሸዋዬ ማመን ተስኗቸው አራስ ቤት እንደገና ፊደሉን እየቆጠሩ አነበቡት:: ልክ ነው:: ቀና ብለው ተያዩና ፊታቸው በሙሉ ጥርስ እስኪሆን ድረስ ሳቁ:: በተለይ ሸዋዬ ሳቅ ከጣራ በላይ ነበር:: «አንበሲት ነሽ» አለና አክሊሉ ከናፍሩን ሞጥሞጥ ሲያደርግ፣ ሸዋዬ ዋ! እንዳልነክስህ አክንባሎ ሰበራው እስኪደርስ ታገሥ» ብላ ፊቷን ወደ ግድግዳው አዞረች::

«ትልቁን ማርክ የያዘው፣ ዋናው የቤት ሥራ ተሠርቷል:: አሁን ውጤቱን መቶ በመቶ ለማድረግ በቀሪው የቤት ሥራ ላይ ማታ ለብቻችን ቆይታ እንይዝበታለን» አለ አክሊሉ::

«ልክ ነው ዳገቱን ጨርሰናል፣ የቁልቁለቱ ጉዞ አያቅተንም» ብላው አክሊሉ አለባበሱን አሳምሮ ሌላ ሰው መስሎ፣ ኮፍያ አድርጎ ወደ «ድድ ማስጫ» ወጣ::

# ምዕራፍ 18

## ያላቻ ጋብቻ መዘዝ

በአባቱ ከራስ ጎበና ዳጬው፣ በእናቱ ከአፄ ዮሐንስ (ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ) የዘር ሐረጉ የሚመዘዘው ዮሐንስ፣ አያት ቅደመ አያቶቹ አገራቸው ከእነርሱ የምትጠብቀውን ዜጋዊ ግዳጅ በሚያኮራ ድል ተወጥተው አልፈዋል ብሎ ያምናል::

ይኽን እምነቱን እንደ አብዛኞቹ የጨዋ ልጆች በየደረሰበት እንደ ውዳሴ ማርያም የመድገም ፍላጎት የለውም:: የመደብ ጀርባውን በተመለከተ ሌላም ሰው ቢሆን ሲያወራ መስማት አይፈልግም::

በዚህ ጉዳይ ላይ አባባ ጌቶችና ዮሐንስ ያላቸው አቋም ለየት ያለ ነው:: በታላላቅ ዓውዳመቶች «እንኳን አደረሰዎ» ለማለት የሚመጣ ወዳጅ ዘመድ ጠጁን እያንደቀደቀ፣ ቁርጡን እያወራረደ በእግረ-መንገድ ስለ እሳቸውና አባቶቻቸው ባላባትነት፣ ገዥነት፣ ዐዳኝነት፣ ጀግንነትና ለጋሥነት ይተረከለታል:: ይህ ሁልጊዜም የመስተንግዷቸው አንዱ አካል ነው:: ከዚህ ቀደም የሰማው ሰው ቢሆንም ደግሞ መስማቱ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም ብለው ያምናሉ:: እሳቸው ገድሎቻቸውን ሲናገሩ ሁሉም ሰው ሕፃናት ጭምር ትንፍሽ ሳይሉ ማዳመጥ አለባቸው::

በእመቤት ጽዮን ሞገሳ በኩል ያለው የደም ጥራት---- የአጥንት ክብደት የሚነሳው ዋቢነቱ ለአባባ ጌቶች ታላቅ ለውነት ተጠቃሽ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው::

ጌታ ሁንዴ ቤኛ ነወር ባይላችሁ፣
አጥንቱ ከብዶት ነው ኮርቶ አይምሰላችሁ::



ለአባዱላ ሁንዴ መሶብ እስፋለሁ፣
በጋሻው እንጀራ ሲበላ አይቻለሁ::

በማለት ተቀባብለው ላሞገሷቸው ባልና ሚስት አዝማሪዎች አሩሲ ጠቅላይ ግዛት፣ በጭላሎ አውራጃ፣ ኮፌሌ ወረዳ ሽሬ ም/ወረዳ፣ ከሚገኝ ርስታቸው ግማሽ ጋሻ መሬት መሸለማቸውን ዘወትር በኩራት ያነሱታል::

አንድ ጊዜ ደግሞ ከሸኖ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው ርስታቸው ላይ ባሠሩት የገጠር መኖሪያ ቤታቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ለመዘከር በተጣለ ስፊ ግብር ላይ ደጉ የተባለ አሽከራቸው፣

ቡከን ልጅ ከመውለድ፣
ይሻላል ማስወረድ፣
ደግሞም ከማስወረድ፣
ይሻላል ሴት መውለድ፣
ፀጉሯ የሐር ጎፍላ የመሰለ እንደሆን፣
አባ ዱላ ሁንዴን፣
ታመጣለች ዝሆን::

ይምጡ ባይ ይሰብሰቡ ባይ፣
ሲሰበሰቡ እንፍጃቸው ባይ፣
አሽከሩ ነብር ጌታው ግስላ፣
ኩፍ ኩፍ ይላል እንደ ጉሽ ጠላ፣
ያንተ አሽከር ያንተ ቡችላ፣

በማለት አቅራርቶ ከጌቶችና አመቤት ጽዮን ሞገሳ ፊት ለፊት በርከክ ብሎ ፋከራውን ስላንደቀደቀው ጌቶች አንድ አጭር ምንሽር ከሃያ ጥይት ጋር፣ ባለቤታቸው ደግሞ ኩታ ሸልመውታል:: ይኸንን የአባቱን ጀግንነት ባሕሪ ዮሐንስ በእጅጉ ያደንቀዋል::

## *አዳኙ ጥዱ*

ዮሐንስና አስገደች በታላላቅ ዐመት በዐል ወላጆቻቸውን «እንኳን አደረሳችሁ» ማለት የማይታጎል ተግባራቸው ነው:: ካመች ባልና ሚስት በልጆቻቸው ታጅበው፣ ካላመች ዮሐንስ ወደ ግቢ፣ አስገደች ብቻዋን ወይም ከልጆች ጋር ወላጆቿ ቤት ይሔዳሉ:: ይህ ልማድ ከውጥረቱም በኋላ አልተቋረጠም::

የልጆቹ ምርጫ ከግቢ ይልቅ የአስገደች ወላጆች ቤት መሆኑን በግልጽ ይናገራሉ:: የግቢው ሥነ ሥርዐት ያሸማቅቃቸዋል:: አያቶቻቸውን እጅ ነስተውና ጫማ ስመው አንዳንድ ጊዜ ገለል ይላሉ:: ሌላ ጊዜ ከላሎኑ አንድ ጥግ አረፍ ብለው የሚቀርብላቸውን እየቀማመሱ ወግ ያዳምጣሉ::

የልጆቹ ሳሎን መቆየት በዚያ ያለውን ሥነ ሥርዓት ለመልመድ ዕድል ስለሚሰጣቸው ዮሐንስ ይወድደዋል:: አስገደችም ብትሆን ልጆቿን ከአያቶቻቸው ጋር የሚያቀራርበውን አጋጣሚ ትፈልገዋለች::

በአንፃሩ በበዐልም ሆነ ባዘቦት ቀናት ልጆቹ አስገደች ወላጆች ቤት ሲሔዱ «ከዚህ ተመለስ» የለባቸውም፣ እንደልባቸው ተናግረው፣ እንዳሻቸው ወጥተው ገብተው፣ የፈለጉትን በልተውና ጠጥተው፣ ያልፈለጉትን ትተው



ይቦርቃሉ:: ከአቶ ደምሴ ጋር እንደ ጓደኛ ነው የሚያወሩት:: ይህ ደግሞ ከልጆቹ የበለጠ እሳቸውን ደስ ያሰኛቸዋል::

አንድ ጊዜ አቶ ደምሴ ለልጅ ልጆቻቸው አጣፍጠው የነገሯቸውን የወንድማቸውን የአዳኝ ጥዱ ተሰማን ታሪክ፣ ደረጀ የበለጠ አጣፍጦ በመጻፍ ተደንቆበታል:: ደረጀ ታሪኩን የጻፈው፣ ት/ቤቶች በክረምት ተዘግተው በመስከረም እንደ ተከፈቱ፣ የ12ኛ ክፍል መምህራቸው በእረፍታችሁ ጊዜ ስላነበባችሁት ምርጥ መጽሐፍ ወይም ስላያችሁትና ስለሰማችሁት ገጠመኝ ከ500 ባላነሱ ቃላት ድርሰት ጻፉ ብለው ለሰጡአቸው የቤት ሥራ ነው::

## *የደረጀ ድርሰት*

ፋሺስት ኢጣሊያ በዓለም አቀፍ ሕግ በተከለከለ የጋዝ መርዝ ጭምር ተዋግታ የኢትዮጵያን ከተሞች በ1929 ሚያዝያ ብትቆጣጠርም፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ በዱር በገደሉ መውለብለቧን አላቋረጠችም::

ስለ ሀገራቸው አንድነትና ሉዓላዊነት ደማቸውን ያፈሰሱ፣ መራራ ሞትን የታገሱ ሰማዕት አርበኞች፣ ጣሊያንን ፋታ በማይሰጥ ጥቃት ለቅዘው ስለ ያዙት፣ አርበኛውን ∀በፈሪ ዱላ∀ ለማንበርከክ በመሞከር ላይ ነው::

አዳኝ ጥዱ ከአርበኞች አንዱ ነበሩ:: ዓይነ ጥሩ ተኳሽ ጥዱ በተለያዩ ዐውደ ግንባሮች ጣሊያንን ገጥመው ግዳይ ጥለዋል፣ ምርኮም አስቆጥረዋል:: የአርበኝነት ሥራታቸው በደጃች አበራ ካሳ ውስጥ ነበር:: ደጃዝማች በአርበኝነቱ ሥራ

ብዙም ሳይቆዩ ከጣሊያን መንግሥት ጋር ተደራድረው እጅ እንደሰጡ ወዲያውኑ በግፍ ተገደሉ::

የደጃች አበራ ጦር ሲፈታ አዳኝ ጥዱ ∀ውሃ ስንቁ∀ ዓይነት ቡድን (መደበኛ ክልል የሌለው ጭፍራ) መሥርተው በቀላሉ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ጣሊያንን ተግትገውታል:: አንድ ሁለት ጊዜ ፍቼ ከተማ ውስጥ ሠርገው በመግባት በሰነዘሩት ጥቃት በርካታ ሶልዳቶዎችንና ባንዶችን ገድለው አምልጠዋል::

አንድ ቀን፣ አዳኝ ጥዱ ጠመንጃቸውን ደብቀው፣ ከሁለት ጓደኞቻቸው ጋር አሳቻ የባላገር ልብስ ለብሰው የጠላትን ሁኔታ በመሰለል ላይ እንዳሉ በአፈሳ ተያዙ::

ቀደም ባለው ሰሞን በጠላትና በአርበኞች መካከል በተደረገ ውጊያ የተማረኩ አርበኞችና በአፈሳ የተያዙትን ተጠርጣሪዎች ከፍቼ ወደ አዲስ አበባ ለመላክ ዝግጅት በመደረግ ላይ መሆኑን የአካባቢው አርበኞች መረጃ ደረሳቸው:: ከዚያ በፊት ወደ አዲስ አበባ የተላከ ምርኮኛ ወይም ተጠርጣሪ በሠላም ወደ ቤቱ ተመልሶ አያውቅም::

ያንን የጠላት ዝግጅት ለማክሸፍ ከቀረቡ በርካታ አማራጭ እርምጃዎች የሚከተለው ተመረጠ:: ፍቼ ከተማ ውስጥ ካሉ የአርበኞች ደጋፊዎች ጋር መላላክ ተደርጎ ሃያ አምስት ብርቱ አርበኞች በቂ ጉርሻ ካላቸው 25 ማስፊያ ጠመንጃዎች ጋር ፍቼ ከተማ እንዲገቡ ተደረገ:: መውጫ መግቢያውን ሁለት ቀን ካጠኑ በኋላ በሣልስቱ ጎኅ ከመቅደዱ በፊት አርበኞች በዘብጥያው ላይ ጥቃት ሰነዘሩ:: በአፈሳና በምርኮ ከተያዙት እሥረኞች መካከል በተኩስ ልውውጥ ጊዜ አሥራ አንዱ ሞተው ከሙቶ በላይ የሚሆኑት አመለጡ:: ከጠላት ወገን አምስት ጣሊያኖች፣ 16



የሐማሴን ባንዳዎች ተገደሉ:: ጥቃቱን ከሰነዘሩት አርበኞች መካከል ሦስት ሞቱ::

አዳኝ ጥዱ ግን ሳያመልጡ ቀሩና እዚያው በእሥረኛነት ቀጠሉ:: እሳቸው ከማምለጥ ወደ ኋላ የቀሩት ሌሎችን እንዲያመልጡ በማድረግ ላይ ስለነበሩ ነው::

በደረሰው ጥቃት ክፉኛ የተናደደው የአካባቢው አስተዳዳሪና የጦሩ የበላይ አዛዥ ኮሎኔል ሮቤርቶ ጋሲና ሳያመልጡ የቀሩ አርበኞችን እግር - ተወርች አስሮ ሜዳ ላይ አሰጣቸው:: በእነሱ ላይ ሊወስድ የታሰበውን የመቀጣጫ እርምጃ ያይ ዘንድ ሕዝብ ታዝዞ ወጣ:: ሁሉም የተመደበለትን ቦታ ከያዘ በኋላ ሦስት የተማረኩ አርበኞች እጃቸው በካቴና እግራቸው በእግረ ሙቅ ታስሮ ከሕዝቡ ፊት ለፊት እንዲቆሙ ተደረገ::

በአፈሳ ከተያዙት መካከል አርበኞቹን ለመግደል ሦስት ሰዎች ተመርጠው ከሙሉ ጉርሻ ጋር ጠመንጃ ተሰጣቸው:: የተመረጡት ሰዎች ትዕዛዙን ለመፈጸም አመነቱ::

«በታዘዛችሁት መሠረት እነዚህን ሽፍቶች ከገደላችሁ በነፃ እለቅቃችኋለሁና አይዟችሁ» በማለት ኮሎኔል ጋሲና በቱርጁማን አግባባቸው::

በወገኖቻቸው ላይ ያን የመሰለ የግድያ ወንጀል መፈጸም የከበዳቸው ሦስቱ ሰዎች እርስ በርስ ተመካከሩና «እኛ መታሰሩ ይሻለናል፣ ሰዎቹን መግደል አይሆንልንም» በማለት ለኮሎኔሉ ገለጡለት:: ጣሊያኑ በጣም ተናድዶ «እናንተ ፈሪዎች ናችሁ:: ጣሊያን ፈሪ አይወድም:: ዓለም ደግሞ የፈሪዎች አይደለችም:: ስለዚህ እናንተ ከነዚያ ከሚገደሉት ሰዎች ጋር መሞት ነው

ያሰባችሁ» አለና እጅና እግራቸው እንደ አርበኞቹ ታስሮ ለሞት እንዲዘጋጁ አስደረጋቸው::

ከዚያ በኋላ ኮሎኔሉ በአፈሳ ወደ ተያዙት በርካታ ሰላማዊ (ተጠርጣሪ) ሰዎች ቀረብ ብሎ «ማነው ወንድ፣ ጥሩ ተኳሽ? ከእናንተ መካከል አምስት ጀግና ሰዎች እፈልጋለሁ:: በነፃ ለመለቀቅ የምትፈልጉ ካላችሁ ብድግ በሉና ቁሙ» በማለት ጠየቀ::

አዳኝ ጥዱና ጓደኞቻቸው ብድግ ብለው ቆሙ::

«ብራቮ! ብራቮ» አለና ጣሊያኑ ሌሎችም የእነሱን አርአያ እንዲከተሉ በቱርጁማን ሰበከ:: የተነሳ ሰው አልነበረም::

«ሁለታችሁ አምስቱንም ሽፍቶች መግደል ትችላላችሁ?» ብሎ አዳኝ ጥዱን ጠየቃቸው::

«እሺ እንገድላቸዋለን በቂ ጥይትና ጠመንጃ ስጡን» አሉ

«ጠመንጃና ጥይት ብቻ አይደለም፣ እነሱን ከገደላችሁ በኋላ ሌላም የምሸልማችሁ ነገር አለ» በማለት አደፋፈራቸው::

አዳኝ ጥዱና ጓደኞቻቸው ከኮሎኔል ጋሊና እጅ ጠመንጃና ጥይት ተቀበሉ::

«ካርታውን ከጠመንጃው ጋር ማዋደድ ትችላላችሁ?»

«አዎን እችላለሁ» አሉና አዳኝ ጥዱ ጠመንጃቸውን አጉርሰውና አቀባብለው ጓደኛቸው እስኪዘጋጁ ጠበቁ:: ጣሊያኑ የእጅ ሰላምታ ሰጥቶ አሰናበታቸው::

አዳኝ ጥዱ አንድ ሁለት ርምጃ እንደ ተራመዱ በመብረቃዊ ቅጽበት ዞር ብለው ኮሎኔል ጋሊናን ግንባሩን ብለው ጣሉት:: ጓደኛቸውም ሌላውን የጣሊያን ባለሥልጣን ተኩሰው ከገደሉ በኋላ እዚያ በጥበቃ ላይ በነበሩት ባንዶች ላይ ተኩስ



ከፈቱ:: በፈረንጆቹ መገደል የተደናገጡት ባንዶችም በእነ አዳኝ ጥዱ ላይ ተኩሱባቸው::

በአፈሳ የተያዘው ሕዝብ ባንዶቹን በድንጋይና ባገኘው ነገር ሁሉ ወገራቸው:: ከባንዶቹ መካከል የተወሰኑት ከሀገሬው ውስጥ ተመልምለው የሰለጠኑ ስለ ነበሩ የጠመንጃቻቸውን አፈሙዝ ከሰሜን በመጡት ነባር ባንዳዎች ላይ አዞሩ:: አዳኝ ጥዱ በተኩሱ ውስጥ ቢቆስሉም አምልጠው ሔዱ:: ጓደኛቸው ቆስለው ወደቁ:: አምስቱም ሰዎች ለጊዜው ሳይገደሉ ወደ ዘብጥያ ተወሰዱ:: ሌላው በመቶ የሚቆጠር በአፈሳ የተያዘው ሰላማዊ ሕዝብ ወደ ቤቱ ሳይመለስ በዚያው ለአርበኝነት ሥራ ዱር ገባ::

## *እጅግ በጣም ጥሩ*

የት/ቤቱ ቤተሰብ ያነባበው
ዘንድ በምርጥ ድርሰትነት
ሠሌዳ ላይ ይለጠፍ::

ደረጀ፣ ይህ ድርሰት ሠሌዳ ላይ ከተለጠፈበት ጊዜ ጀምሮ የት/ቤት ቅጽል ስሙ አዳኝ ጥዱ ሆነ::

***

ዮሐንስና ቤተሰቡ ግቢ ሔደው እናትና አባቱን እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ በማለት እጅ ነስተው ወደ ቤታቸው ተመልሰዋል:: እነሱም በደረጃቸው በስልክና በግንባር እየመጡ እንኳን አደረሳችሁ የሚሏቸውን ዘመድ ወዳጅ ማስተናገድ ይዘዋል:: በዮሐንስና በአሰገደች መካከል መሰንበቻውን ጎሽት ብሎ የነበረው ሁኔታ ያሳሰባት ዓለሚቱም መጥታለች:: ጨዋታ ደርቷል::

«አንተስ እንደ አባባ ጌቶች ለምን ተረት አታጫውተንም፣ አትችልበትም መሰለኝ» አለች ማርያማዊት አባቷ ጭን ላይ ተቀምጣ ለስላሳ ጉንጬን እየዳበሰች::

ቀና ብሎ ዓይን ዓይኗን እየተመለከተ ዮሐንስ ፈገግ አለ:: በሕፃኗ አነጋገር ቤቱን ሳቅ ሞላው:: ዓለሚቱ ግን አልሳቀችም፣ ኮስተር ብላ «ማነው ተረት ነው ያለሽ?» በማለት ለሰነዘረችው ጥያቄ መልስ ከመስጠቷ በፊት ዮሐንስ ማርያማዊትን አቅፎ ወደ ሌላ ክፍል ሸኝቷት ተመለሰ::

ገና እንደ ተቀመጠ ነገሩ የከነከናት አስገደች «አንተንና ቤተሰብህን የሚጠቅስ ነገር ሲነሳ ሁልጊዜ ጆርባህን ትሰጣለህ፣ ለምን?» አለች አስገደች ጥያቄውን ረገጥ አድርጋ::

«ለምን አልሽ? አንቺስ ብትሆኚ ይህን ጥያቄ እስከዛሬ ለምን አቆየሽው?» አለ በሚገረምም እይታ::

«አመቺ ሁኔታና ጊዜ ስጠብቅ» አለች ፈርጠም ብላ::

«መልካም፣ እኔ ራሴ ስለራሴና ቤተሰቤ ተረት ተረት እንዳወራ የምጠበቅ አይመስለኝም:: ሌላ ሰው ግን የመሰለውን ሊያወራ ይችላል -- ካስፈለገ ማለቴ ነው::»

«ጆኒ» አለች ዓለሚቱ ድምጽዋን ከፍ አድርጋ «የማንነት እውክታ (IDENTITY CRISIS) ያለባቸው ይጨነቁ እንጂ፣ አንተ ራስህን መደበቅ የለብህም:: ወንዝ የሚያሻግር የእናትና አባት ስም አለህ:: እንደ ወርቅ የነጠረ ዝርያ አለህ» በማለት ፊቷን አስገደች ወዳለችበት በመመለስ አንገራበደች::

«አዎ! ዓለም ልክነሽ ቢሆንም ለሁሉም ጊዜና ቦታ አለው ኮ!»



«እሱስ ልክ ነህ....» ብላ ዓለሚቱ ልትቀጥል ስትል፣ ጆሮአቸውን ጣል አድርገው ሲያዳምጡ የቆዩት የአስገደች ቤተሰብ አባል የሆኑት እንግዳ፣ ዓለሚቱን አቋርጠው የጎሪጥ እየገረመሙ «ጨዋታችሁ መልካም ነው፣ ድካውን ሳያልፍ በመደማመጥና በመከባበር ከሆነ» አሉ::

የእንግዳው ተግሳጽ አዘል መልዕክት የተላለፈው ለእሷ መሆኑን የጠረጠረችው ዓለሚቱ «ነገሩ አልገባኝም፣ ተግሳፅ ነው ወይስ ምክር» በማለት ደስም አደረገቻቸው::

«እረ! እረ! ምን ቢያገድ! በቤተሰብ ጭውውት መካከል ተግሳፅን ምን አመጣው?» አሉ እንግዳው እንደማሌጥ ብለው::

«አገር ያወቀውን፣ ፀሐይ የሞቀውን፣ የወላጆቻችንን ማንነት እንደዚህ ባለ መድረክ ላይ ማንሳት «በእግራቸው እንዳይረግጡት፣ ተመልሰውም እንዳይነክሷችሁ፣ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ:: ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ» የሚለውን የታላቁን ቅዱስ መጽሐፍ ትዕዛዝ እንደማፍረስ ይቆጠራል:: ተግባባን!» የሚለው የዓለሚቱን አፍ እልፊት አስገደች ልትቋቋመው አልቻለችም::

«ምን አልሽ አንቺ ቅርሻታም...» ብላ ብድግ ስትል፣

ዮሐንስና ሌሎቹም ተጋግዘው እሷን ወደጓዳ ዓለሚቱን ወደ በረንዳ ገፋፏቸው::

አስገደች ገላጋዮቿን ጥሳ እንደገና ወደ ሳሎን ተመለሰች:: ዓለሚቱም ወደሳሎን ተመልሳ ለመግባት ተገሰለች:: ሁለቱም ከየገላጋዮቻቸው እጅ ለመውጣት ቢፍጨረጨሩም አልሆነላቸውም::

«የድፍን ቡልጋ፣ የድፍን ወሎ ልጅ አስገደች ደምሴ በዘሯ አፍራም አታውቅ:: ንገሩኝ ባይ! ስመሆኑ አንቺ ማነሽ? አናውቅሽም እንዴ?» በማለት አስገደች ከገላጋዩ እጅ እጇን መንጭቃ ዓለሚቱ ወደ አለችበት አቅጣጫ ቸርር! ስትል ዮሐንስ ያዛት::

«እንዴ! ምነው አለ፟ን በቃ! በቃ!» አሉ እኒያ ሳይቸግራቸው ነገር የደነቀሉ እንግዳ::

«ምን ይበቃል አባባ! ማንነቷን ካላወቀች ሲነገራት ይገባል፣ ሆ! ሆ! አይገርማችሁም? ዓለሚቱ ሁንዴ ብሎ ሌላውን ዘር አንኳሳሽ! ኧረ ተይ ስወሬም አይመች፣ ነገሩን ገልብጠሽ በፊርሱ ነው ያየሽው፣ እኛ ላይ ከመንጠልጠልሽ በፊት በቅድሚያ ራስሽን መርምሪና እወቂ» ብላ አስገደች ወደ መኝታ ክፍል ስመግባት መንገድ ስትጀምር፣

«ስሚ አስገደች! ካንቺ ጋር አፍ ላፍ መካፈት አንቺኑ መሆን ነው፣ ግን ግን አንድ ነገር ልጠይቅሽ፣ አንቺ ላይማ እንዴት መንጠልጠል ይቻላል? ገና ትናንት አንገትሽን ያቀናሽ ምስኪን አስገደች! እኔ□ኮ ገና ከት/ቤት ጀምሮ የማውቅሽ ሰው ነኝ፣ <ስጽድቅ ተብሎ ታዝላ፣ ቀረች ተንጠልጥላ> የተባለውን ረሳሽ እንዴ? ብላ መልስ ሳትጠብቅ ወደ መኪናዋ ስመሄድ ደረጃውን ወረደች::

የእናታቸውንና የአክስታቸውን አጥንት የሚሰብር ስድብ፣ ገርበብ ካለው የመኝታ ቤታቸው በር ሥር ተለጥፈው ሲያዳምጡ የቆዩት ማርያማዊትና ወንድሞቿ ትልቁ መኝታ ቤት ገብተው አስገደች ፊት ተደረደሩ:: አገባባቸው እናታቸውን ለማጽናናት



ነበር:: ነገር ግን ምን ብለው እንደሚናገሩ ግራ ስለገባቸው በየአልጋው ጫፍ ላይ አረፍ አሉ::

«ዓለምን አወዳትም፣ ሁለተኛ አክስቴም አልላትም» አለች ማርያማዊት ዓይኖቿ እንባ እንዳቀረሩ::

«ማሚ አይዞሽ፣ እኛ አለንልሽ:: እኛ□ኮ! ብዙ ነን:: ጆኒም አለ» አለና መልኬ እናቱን ደባበሳት::

«ሰድቦ ለሰዳቢ የሰጠኝ ማን ሆነና አባታችሁ አይደለም!» አለች አስገደች ሳግ እየተናነቃት::

«አሰግዬ በቃ ተይው፣ አሁን የሆነው ሆኗል፣ ትረፍበት፣ ኑ እንውጣ» አለና ደረጀ እህቱንና ወንድሞቹን ይዞ ሲወጣ ዮሐንስ ተካቸው:: ባልታሰበ ሁኔታ የተፈጠረውን ያልታሰበ ግጭት ማራገብ ያልፈለገው ዮሐንስ ምንም ሳይናገር ከቁምሳጥኑ ውስጥ ካፖርቱን አውጥቶ ለብሶ ወጣ::

***

በማግስቱ ጧት «ጆኒ ማታ በጊዜ ልትመጣ ትችላለህ? እኔ እቤት ነኝ» የአስገደች ጥያቄ ነበር::

«ምነው፣ ደህና ፈለግሽኝ? ስለትናንት ማታው ከዓለሚቱ ጋር ስተያያዘ ጉዳይ ከሆነ...» ብሎ የጀመረውን ሳይጨርስ አቋርጣ፣

«አዎ! ሌላም ሌላም መነጋገር ያለብን ጉዳይ አለ» አለች ፈርጠም ብላ::

«ፈቃድሽ ከሆነ፣ በእኔ በኩል አሁን መነጋገር እንችላለን» አለ ዮሐንስ ውይይቱን እሱም ሲፈልገው እንደነበር በሚጠቁም የአካል እንቅስቃሴ::

«ጥሩ! ጥሩ!» ብላ አሰገደች ወደ ሳሎን ስታመራ ዮሐንስም ተከተላት::

«ዮሐንስ አንተና እኔ የተጋባነው የማንነትን ምንነት ገደል ንደን ነው:: ከአብራካችን የተከፈሉት ልጆቻችን የዚህ ገደል መናድ ዓይነተኛ ማስረጃዎች ይመስሉኛል::

«አሁን አሁን ግን ከድኻ ቤተሰብ መምጣቴ ስብእናዬን ወደ ውሻነት ደረጃ ዝቅ እያደረገው ነው:: ጠባሳው መቸውንም የማይሽር፣ አጥንት የሚሰብር ስደብ ሲወርድብኝ አንድም ቃል አልተነፈስክም:: ለኔ! ያ ዝምታህ፣ የእህትህን የዓለሚቱን ተሳዳቢነት እንደ መጋራት ሆኖ ነው የታየኝ::

«ጋብቻችን የወላጆችህን ሙሉ ቡራኬ እንዳላገኘ አውቃለሁ:: ዓለሚቱም በማያገባት ገብታ ስታለቀልቅ እንደነበር አውቃለሁ...» በማለት አሰገደች ብሶቷን በገጽታዋና በአካል እንቅስቃሴዋ እያጀበች ልትቀጥል ስትል፣ «አሰገደች! አሁን የምትፈልጊውን ንገሪኝ፣ ላይና ታች ሳትረግጭ » አለና ዮሐንስ ከተቀመጠበት ብድግ አለ::

«የምትፈልጊውን ንገሪኝ አልክ! ምን እንድነግርህ ትጠብቃለህ? ከዚህ በላይ! አንገሸገሸህ እንዴ!»

«እውነቱን ልንገርሽ፣ እስካሁን አንድም የነገርሺኝ ነገር የለም:: የነገርሽኝ መስሎሽ ከሆነ፣ ነገረሽኝ እንዳልነገርሽኝ መሆኑን ላረጋግጥልሽ»

የዮሐንስ አባባል አሰገደችን አዲስ ብግነት ለቀቀባት:: ብግነቱ ታፍኖ የቆየውን እንባ ፈነቀለው፣ መንታ መንታው እየወረደ ፊቷን አቃጠለ፣ ለጊዜው የምትናገረው የጠፋባት



ይመስል ዝም አለችና ቀና ብላ ዮሐንስን በእንባዋ ጭጋግ ውስጥ አጨንቁራ ተመለከተች::

ዮሐንስ ቀጣዩን ርምጃ በትግሥት አድፍጦ ይጠብቅ ገባ::

አሰገደች እንደ መርግ አክብዳ ለማሳየት የጀመረችው ብሶቷን ዮሐንስ ባዶውን ስላስቀረባት የንትርኩን አቅጣጫ መቀየር እንዳለባት በመረዳት፣ «ትዳራችን አደጋ ላይ ነው:: ያለፈው ውርደቴ ሳያንሰኝ ለምን በላይ በላዩ ይጨመርበታል:: ጥቃቱ ከምሸከመው በላይ ሆኖብኛል:: በዚህ ጉዳይ ላይ ያለህን አቋም ማወቅ እፈልጋለሁ» በማለት የዮሐንስን መልስ ለመስማት አቆበቆበች::

«አሰገደች በከንቱ ባጀሽ:: የትናንቱን የእንቺንና የዓለሚቱን ድንገተኛ ግጭት ፍፁም ግንኙነት ከሌለው የእነ ሸዋዬ ከንቱ ሴራ ጋር ልታገናኚው እየሞከርሽ ይመስለኛል:: ፍላጎቴን፣ ብሶቴን፣ ንትርኬን፣ ሙግቴን ለማስተጋባት ያገለግሉኛል ብለሽ፣ ሁለት የማይገናኙ ጉዳዮችን አንድ ልታደርጊያቸው ትፈልጊያለሽ:: አይጠቅምሽም፣ ደግሞም አያዋጣሽም::» የዮሐንስ አነጋገር እንደማስጠንቀቂያ የሚቆጠር ነበር::

«እሺ ቆይ! ዓለሚቱ የትዳራችን ጠንቅ አይደለችም ነው የምትለው አንተ?»

«ስለዚህ ምን ይሁን?» አለ ዮሐንስ እንገቱን ወደ እሷ አስግጎ::

«ዮሐንስ ድርሻህን ተናገር! ሁሉንም ነገር ወደኔ አትግፋ:: ነገሬን ታቃልላለህ፣ ደግሞም ታለምጣለህ» አለች አሰገደች እየተበሳጨች::

«አሰገደች መቼም እንድዋሽ አትፈልጊም፣ ካልዋሽሁ በስተቀር ስለ ዓለሚቱ የተናገርሽውን ማስተባበል ያቅተኛል፣ ግልጽ ነኝ?» አለ ዮሐንስ አሰገደች በራሷ ሙግት እየተረታች መሆኗን ከወዲሁ እንድትገነዘብ በሚያደርግ ፋከራ::

የባሏን የመሟገቻ ጭብጦች ማስተባበል ተስኗት አሰገደች እንደገና ዝም አለች::

«ዓለሚቱ የእኔና የአንቺን መጋባት እንደማትቀበለው ያወቅሽው ዛሬ ወይም ትናንት አይመስለኝም:: ዓለሚቱ ጋብቻችንን የማትደግፍበት ለራሷ የራሷ የሆነ በቂ ምክንያት ሊኖራት ይችላል:: ግን ለእኔና ለአንቺ ጋብቻ የዓለሚቱ አቋም ወሳኝ ባለመሆኑ ተጋብተን ኖረናል:: አራት ልጆችም አፍርተናል::

«ከዚህ እውነት ፊት ለመቆም ብርታቱ ሊኖረን ይገባል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ፣ ያለፉ ውጥንቅጥ ችግሮችን እያልመዘመዝን፣ ቁስል ለቁስል የምንቧጠጥ ከሆነ ትዳራችን ይፈርሳል:: ጥቃቅን ችግሮችን እያገዘፍንና በስሜታዊነት እየተገፋፋን ትዳራችንን ባናፈርሰው ይሻለናል:: እኔና አንቺ...» ብሎ የጀመረውን ሃሣብ ሳይቋጭ ተወራጭቶ ከቤት ወጥቶ ሔደ::

***

ዮሐንስ ከቤት ወጥቶ መኪናው ተጋብቶ ወዴት እንደሚሔድ ሳያውቀው ነዳ:: ሰሞኑን የተፈጠረው ችግር ቀደም ሲል ከነበረው ጋር ተጋግዞ፣ ዮሐንስን የልጆቹ ጉዳይ ከመቸውም ይልቅ አሳሰበው::



የልጆቹ ከእናትና ካባቱ ማግኘት የሚገባቸውን አያታዊ ፍቅር ሙሉ ለሙሉ አለማግኘት ዮሐንስ ባይናገረውም ይከነክነዋል:: «በተለይ ወንዶቹ ልጆች ነፍስ እያወቁ መጥተዋል፣ አንድ ቀን ይኸንን ጥያቄ ቢያነሱብኝ ምን እመልስላቸዋለሁ?» አለና መልኬ ገና የአሥር ዓመት ሕፃን ሳለ የጠየቀውን ጥያቄ አምታትቶ እንዴት እንደ መለሰለት አስታወሰ::

አንድ ቀን ከት/ቤት ወደ ቤት ሲመለሱ መልኬ እንዲህ ሲል ነበር የጠየቀው:- «ጆኒ! የእነ አባባ ጌቶች ቤት ለምንድነው ግቢ የሚባለው? የእነ አቡሌስ ቤት (አቡሌ ለአሰገደች አባት የልጅ ልጆቻቸው ያወጡላቸው ቁልምጫ ነው) ለምን ግቢ አይባልም?»

ዮሐንስ ለዚህ ጥያቄ የልጁን ስሜት የማይነካ መልስ መስጠት ተስኖት «መልክዬ ይህን እስከ ዛሬ አለማወቅህ ገርሞኛል፣ ማርያማዊትን ጠይቃት እራሷ ትነግርሃለች» በማለት ጥያቄውን ስላከሸሰበት፣ «እሺ» አለ መልኬ ታናሹ ማርያማዊት ያወቀችውን ባለማወቁ እየከነከነው:: የአባቱንና የወንድሙን ባልታሰበ ጥያቄ መፋጠጥና የታዘበው ደረጀ «ጆኒ አራዳ! ዋና ነህ!» ሲለው፣ «ደረጀ-አራጋቢ ወደ ውጭ!» በማለት ዝም አሰኘው::

«ወደፊት ከዚህ ጠንከር ያለ ጥያቄ ሊወረውሩ ይችላሉ:: የእኔና የአሰገደች ወላጆች መደባዊ ርቀት በልጆቹ ማንነት ላይ እውክታ እንዲፈጥር አልፈልግም» አለ ዮሐንስ በእጽንኦት::

# ምዕራፍ 19

## አዲስ የጥቃት ግንባር

እንደ ዮሐንስ ባይሆንም፤ አሰገደች ዛሬ ዛሬ እንዳቅሟ ዘመደ ብዙ ሆናለች:: ዮሐንስ በእሷ ላይ አደረሰ የተባለውን በደል ከሰሙበት ጊዜ ጀምሮ እየተጠራሩ ምክክር ይዘዋል::

«እኔ እስካሁንም ማመን ተስኖኛል:: በሌላ በኩል ደግሞ በፈጸመብኝ ክሕደት የግፍ አምላክ በእጁ ላይ ጥሎልኛል» በማለት አሰገደች በምታሰማው ሮሮ የተገፋፋው ወዳጅ ዘመድ ዮሐንስን ለመበቀል እያሸመቀ ነው::

በዚህና በሌላውም የተመቻቸ ሁኔታ የልብ ልብ የተሰማት አሰገደች አዲስ የጥቃት ግንባር ለመክፈት የሚያስችላትን ቅድመ ዝግጅት በመንደፍ ላይ ነች::

«ለምን ዮሐንስ ብቻ! የግፍና የጥላቻ የመርዝ ብልቃጥ የሆኑት ወላጆቹስ! እነሱም በእኔና በልጆቼ ላይ ለሚያሳዩት ንቀትና ጥላቻ ብድራቸውን መክፈል አለባቸው:: አብዮቱ ድጧቸዋል:: እኔ ደግሞ አንድ ጊዜ እንደገና እጨፈላልቃቸዋለሁ:: ከነዘርማንዘራቸው መደምሰስ አለባቸው» ለሚለው አዲስ የጥቃት ግንባር፣ የዮሐንስንና የወላጆቹን ስስ ጎን በማጥናት ላይ እንዳለች፣ አክሊሉ ከጎንደር የመጡ የአባቱ ባልንጀራ ስለ ታሰሩበት እሳቸውን ለማስፈታት ወዲያ ወዲህ የሚልበት 100 ብር እንድታበድረው አሰገደችን ይጠይቃታል::

«እንግዳህ ለምን ታሰሩ?»

«ፀጉረ ልውጥ ተብለው ነዋ!»



«የት - ማነው ያሰራቸው?» የአሰገደች አጠያየቅ ግራ ያጋባው አክሊሉ «ልደታ ሠፈር ያለ ቀበሌ ነው፣ የቀበሌውን ቁጥር ወይም ስም ገና ልጠይቅ ነው» አለ አክሊሉ በዝግታ::

«በማታውቀው ቀበሌ እንዴት ልትረዳቸው ትችላለህ? ሠፈርህ አይደል?»

«ልደታ□ኮ የጎንደሮች ሠፈር ነው፣ ቀበሌዎቹን የሚያውቅ ዘመድ አዝማድ አይጠፋም::

«ለምን አጠንክሬ እንደጠየቅሁ ገብቶሃል?»

«ኧረ አልገባኝም::»

«የዮሐንስ ወላጆች የሚኖሩት እዚያ ከፍተኛ ውስጥ ነው::»

«እነሱ እንዲረዱኝ ነው?»

«አይ አንተ! እነሱ ምን ይረዱሃል፣ አደኃሪዎች::»

«እንግዲያሳ?»

«ያባትክን ጓደኛ ለማስፈታት ወዲያ ወዲህ ስትል፣ በእግረ መንገድ በቀደም ፔንሲዮን ሳለን ላነሳነው ጉዳይ መሣሪያ ወይም ተባባሪ የሚሆኑ የቀበሌ ተመራጮችን እንድታፈላልግ ብዬ ነው::»

«አዲስ የፍልሚያ ግንባር መክፈት በመፋፋም ላይ ላለው ዘመቻችን የምንሰጠውን ትኩረት እንዳይሻማ- - -» ብሎ ዐረፍተ ነገሩን ሳይጨርስ፣ «አክሊሉ!» አለች አሰገደች ጮክ ብላ:: «አንተ ያልበላህን አትከክ» የአሰገደች አነጋገር፣ አክሊሉ የሚነገረውን መስማት፣ አድርግ የተባለውን ሳያመነታ መፈፀም ያለበት ቶፋ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነበር::

እንደፍላጎቷ ካልተነዳላት፣ በእሱም ላይ ቢሆን ልታሴርበት እንደምትችል የተገነዘበው አክሊሉ፣ «እሺ! እሺ! እንዲያውም የአኢሴማዋ ሊቀመንበር ያገራችን ልጅ ነች ብለውኛል» አለ::

«ብራቮ አክሊሉ! የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል ይባል የለ! እሷ ላይ ጥብቅ በልባት፣ ካሼፈለገም ያው እንደልማድህ - -» ብላ አሰገደች ተንከተከተች::

አሰገደችና አክሊሉ ጠጠር ያለ ጉዳይ ሲገጥማቸው፣ በቂ ጊዜ ወስዶ ለመነጋገር ከከተማ ወደ ዳር ወጣ ይላሉ:: በደብ ረዘይት መንገድ ቃሊቲ ከመደረሱ በፊት፣ ከዋናው መንገድ በስተቀኝ፣ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ገባ ብሎ የሚገኘው ዘመናዊ ፔንሲዮን (የእንግዳ ማረፊያ) የአሰገደች ምርጫ ነው:: በፔንሲዮኑ ጥንድ ሆነው በመኪና የሚመጡ ደንበኞች 24 ሰዓት ይስተናገዱበታል:: ለአዳር 100 ብር፣ ለደርሶ መልስ 50 ብር ያስከፍላል::

ሞራልና ሥነ-ምግባር በጎደለው በፔንሲዮኑ አገልግሎት በተበሳጩ የቀበሌ አመራር አባላት ግብታዊ ርምጃ ሁለት ጊዜ ተዘግቶ ነበር:: ባለቤቱ ባለው ሰፊ ማህበራዊ ግንኙነት እየመለሰ ከማስከፈቱም በላይ ቀበሌዎቹን እንዲገሰፁ አስደርጓል::

አሰገደች ወደዚህ ፔንሲዮን የምትመጣው በክሊኒኩ የሰርቪስ መኪና ነው:: ከአክሊሉ ጋር የሚገናኙት ቀደም ሲል በተያዘ ቀጠሮ መሠረት ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ዓውደ ምሕረት አካባቢ ነው:: አሰገደች ተሳላሚ መስላ ትገባለች:: መኪናውን ሳትቆልፍ ወጥታ በፅርዱ ባንደኛው ጥግ ቆም ብላ ሰውነቷን አማትባ ትሳለማለች:: ክፍት በተወችው መኪና ውስጥ የአክሊሉን መግባት እንዳረጋገጠች ክንብንቧን አስተካክላ ወደ መኪናዋ ታመራለች:: ከዚያ በኋላ ወደ ቃሊቲ ትረግጣለች::



የፔንሲዮኑ ጥበቃ ከወህኒ ቤት ጥበቃ ቢጠብቅ እንጂ አይላላም:: በ24 ሰዓት ፈረቃ የሚለዋወጡ ስምንት በስውር የታተቁ ወጠምሻ ዘበኞች አሉት::

ልዩ የጭቅናና የበግ ጥብስ የፔንሲዮኑ ዕውቅ የምግብ ዓይነቶች ሲሆኑ፣ ከመጠጥ ብላክ ሌብል፣ ሺቫስ፣ ኮኛክና ጎርደን ጂን ያቀርባሉ:: ለስላሳና ቢራ ግቢው ውስጥ ገብተው አያውቁም ነው የሚባለው::

***

በዮሐንስ ወላጆች ላይ ከውስጥና ከውጪ የተተከሉት ሰዎች ለአኢሴማዋ ሊቀመንበር መረጃ ማቀበል ጀምረዋል:: አቶ ሁንዴ ቤኛ የወደቀው አድኃሪ ሥርዓት አቀንቃኝ እንዳልነበሩ ቢታወቅም፣ ብር እንዳፈር ይዝቁበት የነበረውን የገጠር መሬት የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ለወረሰባቸው አብዮት የሚደማ ልብ እንደማይኖራቸው የአኢሴማዋ ሊቀመንበር ሌሎቹን፣ የከነማና አኢወማ አመራር አባላት የማሳመን የሕቡዕ ዘመቻ ይዛለች:: ለዚህ አገልግሎቷ ያስፈልገኛል ያለችውን ብር ተችሯታል::

***

ብሩ ኤጀርሳ፣ አቶ ሁንዴ ገና በሕፃንነቱ ካገር ቤት አምጥተው ያሳደጉት ወጣት ነው:: ጮሌና ተፊ ስለሆነ አቶ ሁንዴ በጣም ያቀርቡታል:: ብሩ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምሮ አቋርጧል:: ጌቶችን መከተልና መላላክ ከትምህርቱ ይልቅ ዋና ሥራው ስለሆነ በፈተና ቀን እንኳ ከት/ቤት የሚቀርበት ጊዜ

አለ:: የአንደኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተናን የወደቀውም በዚህ ምክንያት ነው:: ይህ ደግሞ ብሩን አበሳጭቶታል::

በቀበሌ ለወጣቶች የሚሰጠውን የአብዮታዊ ንቃት ትምህርት አልፎ አልፎ መከታተሉና በኢህአፓም መመልመሉ የብሩን ልብ ወደ ውጭ እያሸፈተው ነው:: ይኸንን የብሩን ሁኔታ የተረዳችው የቀበሌው ኢሊሰማ ሊቀመንበር ወጣቱን በገንዘብም በአብዮታዊ ጓድነትም ቀርባዋለች:: መጨቆኑና የጉልበቱ መበዝበዝ እንደሚያስቆጫት በምትሰጠው አስተያየት ብሩ ልቡ ተነክቷል::

የአቶ ሁንዴንና የቤተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መረጃዎችን ልቅም እያደረገ ለኢሴማዋ ሊቀመንበር የሚያቀብለው ብሩ የልብ ልብ ተሰምቶታል:: የብሩ ክትትል ያተኮረው በይበልጥ በአቶ ሁንዴ፣ በደረጀና ባባቱ በአቶ ጉልቴ ላይ ነው::

አቶ ሁንዴ በእንግድነት ካስጠጓቸው ከአቶ ጉልቴ ጋር አፍ ላፍ ገጥመው የሚያወሩትን መስማት ባይችልም፣ ሁለቱ የአደኃሪው ሥርዐት ሰዎች ከሰው ነጠል ብለው ቆይታ እንደሚይዙ፣ አንዳንድ ጊዜም ደረጀ (በቁጥጥር ሥር ከመዋሉ በፊት) ያጅባቸው እንደነበር ብሩ የ24 ሰዓት ሪፖርት ያቀርብባቸው ነበር::

ብሩ የመሠረተ ትምህርት ኮሚቴ አባል በመሆን መመረጡ ወደ ቀበሌ ለመሔድ ደህና ሰበብ ሆኖለታል:: ብሩን በመሣሪያነት እስከ ወዲያኛው ለመጠቀም ያላትን ፍላጎት ለማሳካት «በውነት በጣም ጎበዝ ወጣት ነህ በርታ:: ብቻ አንድ ነገር ላሳስብህ እወዳለሁ:: ይኸውም አቶ ሁንዴ ወይም ሌላ



የቤተሰቡ አባል የሆነ ሰው ከእኔ ጋር ስላለህ ግንኙነት እንዳችም ፍንጭ እንዳያገኙ ተጠንቀቅ:: እንደ ዱሮህ ሲጠሩህ አቤት፣ ሲልኩህ ወዴት በማለት ትሁት ሁንላቸው - ገባህ!» በማለት አስጠነቀቀችው::

ብሩ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ መቀበሉንና ተግባራዊም ለማድረግ እንደሚጥር ቃል ገባላት::

«ጎበዝ! ሌላ የምትጠነቀቀው በምስጥህ ገንዘብ በአለባበስህ፣ በአመጋገብህ ወይም በሌላ መልክ ለውጥ እንዳታሳይ ነው:: ለውጥ ካሳየህ ጥርጣሬ ያድርባቸውና ባንተ ላይ ክትትል ማድረግ ይጀምራሉ - ግልጽ ነው!»

«እሺ ጓድ፣ ይኸንን እንኳ አላሰብኩትም ነበር:: አሁን ግን እንዳልሽኝ አደርጋለሁ» በማለት ለጊዜው የሰጠችውን 100 ብር ተቀብሎ እጅ ነስቶ ሔደ ብሩ::

***

ሸዋዬ የልጅ ማሳደጊያ አበል ለማግኘት በዮሐንስ ላይ የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት የሚያስችላትን ዝግጅት ጀምራለች:: ሚስጥሩ እንደተጠበቀ ሙግቱን ለመርታት የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ አክሊሉና አስገደች ከቢሮ ውጭ እየተገናኙ ምክር ይዘዋል::

«አክሊሉ አደራህን፣ የዚህ ውጥን መሳካት የሚመጣው ከሚስጥርነቱ መጠበቅ ነው:: አካሔዳችን ሁሉ ውስጥ ለውስጥ መሆን አለበት:: የእኔንና የአንተን ግንኙነት ባለቤትህ እንኳ ማወቅ የለባትም:: የምን ማወቅ፣ መጠርጠር፣ አዎ በትንሹ

እንኳ መጠርጠር የለባትም:: አባባሌ ግልጽ ይመስለኛል» አለች አስገደች አክሊሉ የሚለውን ለመስማት! እየተዘጋጀች::

«ይህ□ኮ እርሶ አደራ የሚሉበት፣ እኔ አደራ የምቀበልበት ጉዳይ አይደለም:: የጋራችን ነው:: ሸዋዬ የምታቀርበውን ክስ በተመለከተ ማመልከቻ ለመጻፍም ሆነ ስለሙግቱ ከአንዳንድ የሕግ ባለሙያዎች ዐሳብ የምጠይቀው ሚስጥሩን አፍኜ ይገፍ ነው:: በየቀኑ የቃረምኳትን የመሟገቻ ዐሳብ ፊደል እንደሚቆጥር ተማሪ ነው ሸዋዬን የማስጠናት:: በዚህ በኩል ዐሳብ አይግባዎት» አለ አክሊሉ::

«ትንሽ ፍራንክ ያስፈልግህ ይመስለኛል?» ለሚለው የአስገደች ጥያቄ መልስ ሳይሰጥ አክሊሉ አንገቱን ዘለስ አደረገ::

«አይ ያንተ ነገር ላልጋ ትሽከረመማለህ፣ የሚያስፈልግህን ገንዘብ ለመጠየቅ ትግደረደራለህ፣ ሲጠይቁህ መልስ ለመስጠት ትፈራለህ:: ያንተ ወታደርነት እምኑ ላይ ነው?» አለችና 200 ብር ከቦርሳዋ አውጥታ ሰጠችው::

አክሊሉ ለአስገደች አስተያየት መልስ ሳይሰጥ ብሩን ተቀብሎ ኪሱ ከተተ::

«በል እንግዲህ ወደ ቢሮ ብቅ የምትል ከሆነ አስቀድመህ ስልክ ደውልልኝ መጥተህ እንዳታጣኝ::»

«እሽ የጥበቃው ኃላፊ እስካሁን ምንም አላለዎት?»

«እንዴት! ምን ሊለኝ ይችላል?»

«በእኔ አለመገኘት ጥበቃው ላላ........»

«ተወው እባክህ ያለውን ሰው አብቃቅቶ ይሠራል:: ካስፈለገም ይቀጠርለታል» አለች ኮምጨጭ ብላ::



አክሊሉ፣ አስገደች አፍሳ በምታሸከመው ብር ያላሰበው ሲሳይ ቢሆንለትም፣ ከአስገደች ጋር በፈጸመው ድርጊት፣ በተለይ አስገደች ባሏን በሐሰት ወንጀላ ለመጣል ለወጠነችው ሴራ መሣሪያ መሆኑ እየዘገነነው ነው::

«የምድሩን በዘዴም በገንዘብም ኃይል እንደተወጣነው፣ ወ/ሮ አስገደች እንደሚሉት የሰማዩንም ንስሐ በመግባት እናረግበዋለን» ይላል አክሊሉ ራሱ ለራሱ:: አክሊሉ ካደረበት ሥጋት የተነሳ ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት ከምን ጊዜውም የተቆጠበ ሆኗል::

***

ዮሐንስ በትዳሩ ላይ ማግጦ የደቀለ ስለሆነ፣ ከንብረቱ ሙልጭ ወጥቶ፣ አስገደች በጋራ ያፈሩትን በሙሉ መጠቅለል አለባት በማለት የአስገደች ዘመዶች በመሸረብ ላይ ያሉትን ሴራ ዮሐንስ ከሰማበት ቀን ጀምሮ የአእምሮ ሠላም የለውም:: ለዚህ ሁሉ ሴራ መክሸፍ ዋናውና ዓይነተኛ መፍትሄ የሸዋዬ ሐሰተኛ ነት በአደባባይ መጋለጥ ስለሆነ፣ ዮሐንስ በሕግ ብቻ ሳይሆን በገንዘብ ጭምር ፍትሕን ለማግዛት ቆርጦ ተነስቷል::

# ምዕራፍ 20

## የዓለሚቱ መረጃ ዕደና - 1

❖

በአሜሪካ አገር የአንጀት ካንሰር በሽታቸውን በሕክምና ሲረዱ ቆይተው የሞቱት የዶ/ር ወ/ሚካኤል ማዴቦ ኑዛዜ በአርባቸው ዕለት ይፈስሳል ተብሎ ሲጠበቅ ባለመፍሰሱ በቤተሰቡ መካከል ሁከት ተፈጥሯል:: በእናቷ በኩል ቤተሰባዊ ግንኙነት ያላት የዮሐንስ እህት ዓለሚቱ ከኑዛዜው አለመፍሰስ ጋር ተያይዞ የደረሳትን ግርድፍ፣ ነገር ግን በጣም ጠቃሚ ወሬ በማለዘብ ላይ ነች:: ወሬው ያልተጣራ ነው፣ ቢሆንም «ትንሽ እሳት በሌለበት ጭስ አይኖርም» እንደተባለው ስለሆነ ጭራውን ጨምድዳ ይዛለች::

ኑዛዜው በጋዜጣ መውጣቱ ስለማይቀር ለጊዜው የክትትል አቅጣጫዋን በዚያ በኩል አደረገችው:: ውላ አድራ፣ የተፈጠረው ቤተሰባዊ ሁከት በቤተ ዘመድ ጉባኤ እየታየ መሆኑን ደረሰችበት:: የቤተሰብ ጉባኤው በየሣምንቱ ስድስት ኪሎ ቶታልን አለፍ ብሎ በምትገኝ አንዲት አነስተኛ ሆቴል ቤት ውስጥ የሚሰበሰብ መሆኑን አረጋግጣለች:: አካባቢውን ገና ተማሪ በነበረችበት ጊዜ ደህና አድርጋ ስለምታውቀው ሆቴል ቤቷን ለማግኘት አልተቸገረችም:: የቤተሰብ ጉባኤ አባላትና የዶ/ር ወ/ሚካኤል ቤተሰብን ወክለው የሚገኙት ግለሰቦች እነማን መሆናቸውን ማወቅ የመጀመሪያ የቤት ሥራዋ አደረገችው::

አንድ ጊዜ ከወንድ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከሴት ጓደኞቿ ጋር ሆቴል ቤቷን አዘወተረች:: ሆኖም ለአንዳቸውም ምስጢሯን አላጋራችም:: የዓለሚቱ ክትትል ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት



ነበር:: ሳይነቃባት መረጃውን ለማግኘት እንቅስቃሴዋን ሁሉ በሽፋን ነበር ያደረገችው::

ለጥርጣሬዋ ምንም ዓይነት አጥጋቢ መረጃ ሳታገኝ ሁለት ወር ያህል ደከመች:: አንድ ቀን ዕድል ቀንቷት ከስብሰባ ሲወጡ፣ በቅርብ ርቀት ካየቻቸው የጉባኤው ተሳታፊዎች መካከል የአንዳቸውንም እንኳ ስምና አድራሻ ለማወቅ አለመቻሏ ዓለሚቱን ክፉኛ አናደዳት::

ስብሰባው የሚደረገው ሆቴል ቤቱ ለመኝታ ከሚያከራያቸው በአንደኛው ለፊ ክፍል ውስጥ መሆኑን የኋላ ኋላ ደረሰችበት:: ውይይታቸውን ለማዳመጥ የተሳታፊዎቹንም ስም ለማወቅ ከመሰብሰቢያቸው ግራና ቀኝ ካሉት ክፍሎች አንዱን ተከራይታ ጆሮዋን ለመቀሰር ወሰነች::

***

አንድ ቅዳሜ ጧት፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ የመጣች ሥራ ፈላጊ የሚያስመስላትን አልባሳት ለብሳ፣ አነስ ያለ ሻንጣ አንጠልጥላ የሆቴሉ እንግዳ ሆነች::

«አልጋ አለ?» የመጀመሪያ የዓለሚቱ ጥያቄ ነበር::

«ሳይኖር አይቀርም፣ ወደ ውስጥ ገባ በይና አልጋ የሚያከራየውን ልጅ ጠይቂ» አላት ካዳሚው (ባሬስታው)::

ዓለሚቱ ሻንጣዋን ቡና ቤት ውስጥ ትታ፣ ወደ ውስጥ እንደ ገባች አንድ ያላጠናቀቀችው የቤት ሥራ መኖሩ ትዝ አላት:: መሰብሰቢያ ሊሆን ይችላል ብላ ከጠረጠረችው ክፍል ግራና ቀኝ ያሉት መኝታ ክፍሎችን ቁጥሮች አውቃ «እዚህ ወይም እዚያ ክፍል ይሁንልኝ» ማለት ነበረባት::

በዚህ መካከል አልጋ አከራዩ ልጅ «ምን ፈለግሽ አልጋ ነው?» አላት::

«አዎ! እዚህ ቢሆንልኝ ከዳር» አለችው ክፍሉን በጣቷ እያመለከተች::

«እሱ ለጊዜው ሰው አለበት፣ ለአዳር ከሆነ ግን ይቻላል» አላት::

«ግድ የለም እጠብቃለሁ፣ በዘጠኝ ሰዓት ይለቀቅ ይመስልሃል? የዓለሚቱ ሥጋት የተሞላበት ጥያቄ ነበር::

«ካፈጠናቸው አንድ ሰዓት፣ ከዘገዩ እስከ 8 ሰዓት ሊቆዩ ይችላሉ» አለ ልጁ በፈገግታ::

«እኔ ለአዳር ነው የምፈልገው፣ ይህንኑ ክፍል ያዝልኝ» በማለት 10 ብር የአንድ ሌሊት ኪራይ ከፍላው ወደ ቡና ቤቱ ተመለሰች:: የክፍሉ እስከ ቀኑ 8 ሰዓት ያለመለቀቅ ዓለሚቱን ከፉኛ አሳሰባት::

«መቼም ሰውየው አውሬ መሆን አለበት፣ የዚህ የዚህ ለምን አዳር አላደረጉትም? የሥርቆት ግንኙነትም ሊሆን ይችላል:: ሥርቆት ቢሆንማ ኖሮ ቶሎ ጉድጉድ ብለው ይለያዩ ነበር እንጂ ይህን ያህል ጊዜ አይሟዘዙም:: ወይ አምላኬ እንቅልፍ ድብን አድርጎ ወስዷቸው ይሆን? እንደሱ ከሆነ ቀለጥኩ» በማለት ራሷ እየጠየቀች ለራሷ መልስ በመስጠት ላይ እንዳለች፣ ሰዎች ከመኪናው ወርደው ግቢ ገቡና በቡና ቤቱና በአጥሩ መካከል ባለው መንገድ ወደ መኝታ ክፍሎቹ አመሩ:: እነማን እንደሆኑ ለማወቅ የቡና ቤቱን የምግብ አዳራሽ ከለላ በማድረግ ዓለሚቱ ሁለት ወንዶችና አንድ ሴት ላይ ዓይኗን ጣለች:: የሴትዬዋ ክንብንብ እስከ አፍንጫዋ መውረድ ማንነቷን



ለመደበቅ የመፈለጓን ምልክት ስለሰጣት ዓለሚቱ ጊዜ ሳታጠፋ ወደ ተከራየችው ክፍል ለመግባት የሚያስችላትን ጥረት ቀጠለች::

አልጋ አከራዩን ጠርታ «ምን ይሻላል እባክህ አሁን□ኮ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት እየሆነ ነው:: ክፍሉን አስለቅቅልኝ እንጂ» አለችው::

«እውነትሽን ነው፣ ያለዚያ የሁለት ደርሶ መልስ ኪራይ አስከፍላቸዋለሁ» አለና የስድስት ቁጥርን በር አንኳኳ:: ብዙም ሳይቆዩ የተከራዩት ሰዎች ክፍሉን ለቀቀው ወጡና አንሶላ ተቀይሮላት ዓለሚቱ ገባች::

የስብሰባው ቃለ ጉባዔ ጸሐፊ ሆና የተመደበች ይመስል ዓለሚቱ አንዲት ትንሽ ቴፕ-ሪኮርደር ጠምዳ፣ በተጨማሪም ወረቀትና እስክሪቢቶዋን አዘጋጅታ፣ የምታዳምጠውን ሁሉ ለመቅረጽና ለመመዝገብ ተሰናዳች:: ዓለሚቱ ደስታና ሐዘን በተቀላቀለበት ቆይታዋ ሳትረታ የውይይቱን ጭማቂ ከሞላ ጎደል መዝግባ ያዘች:: ቴፕ - ሪኮርደሩም ሹክሹክታ ሲቀረው ሌላውን በሙሉ ቀርጿል::

ስብሰባው በመመራረቅ ተዘጋና ሁሉም ተከታትለው ወጡ:: ዓለሚቱም ድምጿን አጥፍታ ቆይታ ወደ ቡና ቤቱ ብቅ አለች::በተረጋጋ መንፈስ ቡና አዛ ከጠጣች በኋላ ወደ መኝታ ክፍሷ ተመልሳ፣ አልጋ አከራዩን ተሰናብታ ሻንጣዋን ይዛ ወጣች::

የማንንም ትብብር ሳትጠይቅ ይህን እንደ ወርቅ የነጠረ መረጃ በማግኘቷ ዓለሚቱ «ወንድነት» ተሰማት:: «ይህች አላቲ ሸርሙጣ ሠራሁላት፣ አሁን በእጄ ላይ ወድቃለች:: ለየዋሁና

ለደገ ወንድሜ በደሉን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተበቀለለት» አለች ራሷ ለራሷ፡፡

*ዓለሚቱ በዚያኑ ዕለት የድል ምሽት ማረፍ ወይም መዝናናት ሳትፈልግ በማስታወሻና በቴፕ የያዘችውን መረጃ አጠናቀረች፡፡*

*ወ/ሮ ትግሥት ሙሉጌታ የሕግ የሰማንያ ሚስታቸው፣ ከእርሳቸው የተወለዱት ሦስት ልጆች አስቴር፣ አሰግድና አባቡ ሕጋዊ የአባታቸው የዶ/ር ወ/ሚካኤል ወራሾች መሆናቸውን በፍ/ቤት ፋይል ከፍተው በጋዜጣ ለማሳወጅ መስማማታቸውን፣*

*ከጋብቻ ውጭ የተወለደችውንና ዶ/ር ወ/ሚካኤል በኑዛዜ ያቀፏትን ማርያማዊትን በተመለከተ በእናቷ በወ/ሮ አሰገደች ደምሴ ጥያቄ መሠረት የዶ/ር ወ/ሚካኤል ልጅ መሆኗ በቤተሰብ ዘንድ ዕውቅና ማግኘቷ ብቻ በቂ እንዲሆን፡፡ ይህንኑ ዐሣብ ቤተሰቡ በአድናቆት በመቀበል ለማርያማዊት እንደ ጉርሻ የሚቆጠር 50,000 ብር ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን፣*

*የዚህ የቤተዘመድ ጉባኤ ሰነዶች በሙሉ በከፍተኛ ምስጢርነት እንዲጠበቁላቸው ወ/ሮ አሰገደች ያቀረቡትን አደራ ሁሉም ወገን የተቀበለው መሆኑን ዓለሚቱ አረጋገጠች፡፡*



***

እነሽዋዬ ከአውራጃ ፍ/ቤት ያወጡትን የፍትሐ ብሔር ክስ መጥሪያ ለዮሐንስ በእጁ መስጠት ስለፈሩ በወረዳ ፖሊስ ጣቢያ አማካይነት እንዲደርሰው አድርገዋል፡፡ ሽዋዬ እንደተመከረችው በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ሕፃኑን ታቅፋ ችሎት ቀርባ ተቆራጭ ለማሳዘዝ ብታለቅስም አልቀናትም፡፡

በችሎቱ ላይ በእንባ አጅባ ያሰማችውን እንጀት የሚያላውስ ንግግር ከቤት ሆኖ ይጠብቃት ለነበረው አክሊሉ መልሳ ተረከችለት፡፡ የሽዋየን ትረካ በጥሞና ያዳመጠው ጓደኛዋ አክሊሉ በመገረም «ይህች ሰው የቱን ያህል ችሎታ ቢኖራት ነው ያልተፈጸመባትን በደል የተፈጸመባት ለማስመሰል እንባዋን እንደ ጎርፍ ያወረደችው? አቤት ያባይ እንባ!

«ዮሐንስን በሐሰት እንባ የልጇ አባት አደረገችው፡፡ ዳኛ ውም በሐሰት እንባዋ ልቡ መነካቱን በገሃድ አሳይቷል፡፡ ሕጉ የማያወላዳ ሆኖበት ነው እንጂ ያለ ተጨማሪ ቀጠሮ በወሰነላት ነበር፡፡ ሽዋዬ እኔንስ ብሆን እስካሁን ላለመሸወዷ ምን ማረጋገጫ አለኝ፡፡ በሬ ታራጁ እንደሚውለው ሆኖ እንደሆነስ፡፡ ማን ያውቃል? ሽዋዬ□ኮ የማታለል ንግሥት ብትባል አይበዛባትም» በማለት አክሊሉ ውስጥ ውስጡን እየተብሰከሰከ «ወደ ሥራ መሄዴ ነው» ብሎ ከቤት ወጣ፡፡

***

ከውጭ ሽዋዬ፣ ከቤት ደግሞ አሰገደች እንደ ብራና ወጥረው ዮሐንስን የተወለደበትን ቀን እያስረገሙት ናቸው፡፡

ዙሪያው ገደል በሆነ ጠባብ መስክ ላይ «አዙረኝ አታዙረኝ» ሽክርክሪት ተጫውቶ እንደ ወደቀ ልጅ ነሁልሏል:: ማንንም የቅርብ ጓደኞቹን እንኳ ስለጉዳዩ ተናግሮ ማሳመን ተስኖታል:: የአስገደችን መንታ ምላስ የፈሩ አንዳንድ ወዳጆቹ ገና ከወዲሁ ጆሮአቸውን ከልክለውታል:: ከጊዜ ወደ ጊዜ የኃዘኔታው ሚዛን ወደ አስገደች እየደፋ መምጣት ዮሐንስን ይበልጥ ገለልተኛና ቆዛሚ አደረገው::



# ምዕራፍ 21

## ሌላው የመረጃ ዕደናና የአብዮት ፈተና

ዓለሚቱ ማንንም ሳትይዝ፣ ማንንም ሳታማክር ሁለተኛውን የመረጃ ዕደና ዕቅደ ነደፈች:: የዕደናውን:-

-ቅደም ተከተል ሒደትና ስልት፣

-ታሳቢ የመረጃ ምንጮች፣

-በመሣሪያነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ግለሰቦችና ተቋማት፣

-የዕቅድ ማስፈፀሚያ ወጪ፣

በሚገባ ታሽተውና ተሰልቀው ለትግበራ ተመቻቹ::

ዓለሚቱ ለወጠነችው ዕቅድ መሳካት በአሥሩ የአዲስ አበባ አውራጃ የቤተሰብ ችሎቶችና ቤተ መዛግብት አካባቢ በማንዣበብ የቅድመ-ትግበራ ቅኝት አደረገች:: የዓለሚቱ ትኩረት ዳኞችና የቤተ መዛግብት ሹሞች ላይ አነጣጠረ::

አንድ የተባረከ ቀን፣ ዓለሚቱ ከቤት ማለድ ብላ በመውጣት የአራዳውን ገነተ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተሳልማ ወደ አውራጃው ፍርድ ቤት ችሎትና ጽሕፈት ቤቶች ግቢ ለመግባት መንታውን መንገድ በማቋረጥ ላይ እንዳለች የሚች ዶ/ር ወ/ሚካኤል ማዴቦ ባለቤት ወ/ሮ ትግሥት ሙሉጌታ መኪናዋን አቁማ ስትቆላልፍ አሻግራ አየቻት:: ዓለሚቱ ወደ ኋላ መለስ ብላ የሴትዮዋን እንቅስቃሴ ጠበቀች::

«ቅዱስ ጊዮርጊስ! ሰማዕተ ልዳው፣ በዚህ የመረጃ ዕደና ዘመቻ አንተም ገባህበት? ፍጡነ ረድኤት እስከ መጨረሻው አትለየኝ አደራህን» አለች መንፈሷ በሐሴት ተሞልቶ::

ወ/ሮ ትግሥት ሦስተኛ የቤተሰብ ችሎት መዝገብ ቤት መግባቷን ዓለሚቱ ካረጋገጠች በኋላ ደባቃ ጥግ ይዛ አደፈጠች::

የሴትዮዋን መውጣት በዓይነ ቁራኛ እየጠበቀች «ዛሬ ዕቅዴ ግማሽ በግማሽ እንደ ተፈጸመ እቆጥረዋለሁ:: አዎ ወጥመዴ ይዘልኛል! አስገደች ‹ደምሴ ያቺ ልዝብ ሰይጣን! ከእንግዲህ አበቃላት:: አስገደች ሰይጣን ነች:: እሷና ሰይጣን የሚበላለጡ ከሆነ እሱ (ሰይጣን) ቀደም ብሎ በመፈጠሩ ብቻ ነው» አለች የአስገደችን እኩይ ድርጊት እያሰበች::

ዓለሚቱ አሁንም ዓይኗን ከመዝገብ ቤቱ በር ላይ እንደ ተከለች ነች:: ወደ መዝገብ ቤቱ የሚገባ ሰው ብዙ ነው፣ የሚወጣው የገባውን አለማከሉ ዓለሚቱን ግራ አጋባት::

«ዓለሚቱ ሁንዴ ትግሥት! ርጋታ!» አለች ራሷን በራሷ ለመምከር:: ዓለሚቱ አላስችላት ስላለ እያደባች ወደ መዝገብ ቤቱ ተንቀሳቀሰች:: በሩ በባለ ጉዳይ ስለተጨናነቀ ወደ ውስጥ ለመግባት አልተቻለም:: ከውጭ ሆና ወደ ውስጥ አጮለቀች::

«በሩን ለቀቅ አድርጉት እባካችሁ» አለ ተላላኪው እንደ ቁጣ ባለ ድምፅ::

«እሽ! እሽ!» አሉና ጥቂት ሰዎች ወደ ኋላ አፈገፈጉ::

ዓለሚቱ ወደ ተላላኪው ጠጋ ብላ «እባክህ እርዳኝ» አለች ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ::

«ምን ነበር?» አለ ተላላኪው::

«አብራኝ የመጣች እህቴ ከገባች ቆየች:: ድንገት ሳላያት ወጥታ እንደሆን ለማረጋገጥ ፈልጌ ነው::»

«ያንቺ ቀላል ነው፣ ግቢና እይ» ብሎ ፈቀደላት::



ዓለሚቱ ወደ መዝገብ ቤቱ ዘልቃ ግራ ቀኙን መልከት ስትል፣ ወ/ሮ ትግሥት ከመዝገብ ቤቱ ሹም ጠረጴዛ ቀረብ ባለ ወንበር ላይ ዘና ብላ ተቀምጣ አየቻት::

ፊቷን ወደ ግድግዳው ዞር አድርጋ ቦርሳዋን በመክፈት እጇ የገባውን ብር ጨብጣ ተላላኪውን በዓይኗ ጠቀስ አደረገችውና «እህቴ ወጥታለች መሰለኝ የለችም፣ አንተ ግን ጥሩ ሰው ነህ፣ እግዚያብሔር ይስጠልኝ» ብላ በብር እጇ ጨበጠችውና ወጣች::

«ለዛሬ የእስካሁኑ በቂ ነው፣ ለቀሪው ነገ ተነገ ወዲያ እመለስበታለሁ» ብላ ከግቢው ወጥታ ሄደች::

ዓለሚቱ አላስችላት ስላለ፣ ደግሞም ውሎ ሲያድር ተላላኪው ሊዘነጋት እንደሚችል በማሰብ፣ ከሰዓት በኋላ ተመልሳ መጣች::

ተላላኪው ገና ሲያያት «እህ መጣሽ! ግቢ! ግቢ!» አለ የሲጃራ ጪስ ደጅ ያደረ ማጭድ ያስመሰለውን ጥርሱን ከከንፈሩ እያላቀቀ::

«የከናፈሩ መላቀቅ ጆሮዎቹ ገደቧቸው እንጂ ዞረው ይጋጠሙ ነበር» አለች ዓለሚቱ በተላላኪው አፍ ስፋት እየተገረመች::

ዓለሚቱ ጥግ ይዛ በመቆም ተላላኪውን ጠቀስ አደረገችውና መጣ «ሹሙን ለማነጋገር ነበር» አለችው::

«ምን ችግር አለ፣ እነዚያ የተቀመጡ ሰዎች ሲወጡ ያንቺ ተራ ስለሆነ ማነጋገር ትችያለሽ» አላት::

«ስማቸው ማን ነበር?»

«ዘኪሮስ ከበደ ይባላሉ፣ አዲስ ናቸው፣ በጣም ጥሩ ሰው ናቸው» በማለት ሲያወራ፣ የመዝገብ ቤቱ ሹም እያነጋገራቸው ከነበሩት ባለ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው ወደ ችሎቱ ጽ/ቤት ገቡ::

ብዙም ሳትቆይ ዓለሚቱ ነገ ጧት ለመመለስ ወስና ከግቢው ወጣች::

***

ዓለሚቱ አደባባይ ስትወጣ የመጀመሪያ ጊዜዋ አይደለም:: ከአምስት ዓመት በፊት እናቷ ወ/ሮ ታደለች ላጺሶ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውንና እሷ የእናቷ ብቸኛ ወራሽ መሆኗን ያረጋገጠችው በአዲስ አበባ አውራጃ ፍ/ቤት የቤተሰብ ችሎት ነበር:: ያን ጊዜ ዓለሚቱ እንዲህ እንደ ዛሬ ከተራ ሰው ጋር መጋፋት አልገጠማትም:: ጥላዋ ከለላዋ አባቷ ያጅቧት ነበር:: የሁንዴ ቤኛ አውቶሞቢል ችሎቱ በር ድረስ ተሽከርክሮ ሲቆም ዳኛው ራሱ እጅ ነስቶ የተቀበላቸው ጊዜ ነበር:: ዛሬ ያ ሁሉ የለም -- ጊዜው የአብዮት ነው::

አደባባዩ ክብርና ሞገሱ ተገፍፏል:: የቀድሞው ሥርዓት አገዛዝ መልክ በፈርሉ ተገልብጧል --የመደብ ሹም ሽር::

ደርጉ ሥልጣኑን ያሟሸው መሳፍንቱን፣ መኳንንቱንና ባለሥልጣናቱን ክብራቸውን ገፍፎ፣ በሶሻሊዝም ዕወጃ ንብረታቸውን ዘርፎ ወደ የማጎሪያ ቤቱ በመወርወር ነው::

አፈሳው፣ ግድያውና ስደቱ በቀድሞው ሥርዓት ተጠቃሚዎች ላይ ብቻ አልቆመም:: በከፈለው የደም መስዋዕት አብዮቱን ያቀጣጠለው ተማሪውና ምሁሩ ደርግን ገና ከምሥረታው ስለተቃወመ፣ የሥልጣን ጥያቄው ወደ እርስ በርስ



ግድያ ተሸጋገሯል:: የተቃዋሚዎችን ነጭ ሽብር ለመደምሰስ፣ ብሎም አብዮቱን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ለማሸጋገር በሚል ምክንያት ደርግ ቀይ ሽብርን አውጇል::

የእርስ በርስ ፍጅቱ ከከተማ እስከ ገጠር፣ ከአደባባይ እስከ ጦር ሠፈር ተዛምቷል::

«እኔ አላማረኝም ዓይን እገላለጡ፣

ወንድ የወለዳችሁ መልሳችሁ ዋጡ»

የተባለለት ቀይ ሽብር የአብዮቱንም ወገኖች አልማረ:: በሥልጣን ጥያቄ ድርድር የለም:: አስፈላጊ ሆኖ ካገኘችው አብዮት ልጇን መብላት ትችላለች በሚል ርምጃ የደርግ አባላት፣ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና ካድሬዎች ጭምር ወደ ወህኒ እየተጣሉ ናቸው:: የተመቱም አሉ::

አቶ ሁንዴ የቀድሞውን ሥርዓት ተጋፊና አገር ወዳድ ዲሞክራት ናቸው በመባል ከእስራት ተርፈዋል:: በመንጥር ዘመቻም ቤታቸው አልተፈተሸም::

የቀድሞው ሥርዓት ታላላቅ ሰዎች ሚስቶች በመብራት እየታሰሱ ለሚሊሺያ ስንቅ ዝግጅት የግዳጅ ተሳትፎ በአውቶብስ አንዳንዴም በከባድ የጭነት መኪና (ኤንትሬ) ወደ ታጠቅ ጦር ሠፈር ሲወሰዱ፣ እመቤት ጽዮን ሞገሳ ግን የቤት ሠራተኞቻቸውን እንዲልኩ ተፈቅዶላቸዋል::

አቶ ሁንዴና ቤተሰቡ በአብዮቱ የጎሪጥ ባለመታየታቸው ቢፅናኑም፣ በአንዳንድ የአብዮቱ ጨካኝ ርምጃ ከማጉረምረም አልተቆጠቡም::

አንድ ቀን አቶ ሁንዴ «ሁሉም መንገዶች ወደ ዓለም በቃኝ ያመራሉ» በማለት በአብዮቱ ላይ ተሳልቀዋል የሚልና

ሌላም ጥቆማ ለቀበሌ ይደርሳል:: ጥቆማውን ለማጣራት የቀበሌው ጥምር ኮሚቴ በደብዳቤ ጠርቷቸው ቀበሌ ይሄዳሉ:: አቶ ሁንዴ ለምን እንደተጠሩ ባያውቁም የጥሪውን ቀንና ሰዓት አክብረው ተገኙ::

«ምነው ደህና መጡ?» አለ በሊቀ መንበሩ ቢሮ በር ላይ ቆሞ ባለ ጉዳይ የሚያጋፍረው የአብዮት ጥበቃ ጓድ::

«ተጠርቼ ነዋ!» አሉ አቶ ሁንዴ::

«ከተጠሩማ ይግቡ» ብሎ አስገባቸው::

«እንዴት ዋላችሁ ጓዶች» አሉ አቶ ሁንዴ ገብተው እንደቆሙ::

«እግዚአብሔር ይመስገን ይቀመጡ» አለ የቀበሌው ሊቀ መንበር ከወንበሩ ሳይነሳ::

«ዛሬ ነገር አለ» አሉ አቶ ሁንዴ ሲገቡ ኖር አለመባላቸውን እያሰቡ::

«ሥራችንን መጀመር እንችላለን» አለ የአብዮት ጥበቃው ኮሚቴ ሊቀ መንበር::

«አቶ ሁንዴ» አለ የቀበሌው ሊቀ መንበር ኮስተር ባለ መልከታ::

«አቤት» አሉ አቶ ሁንዴ በቀዘቀዘ ድምፅ::

«እርሶ የቀድሞው ሥርዓት ተጠቃሚ፣ የበርካታ ጋሻ መሬትና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ባለንብረት ነበሩ:: ለቤተ መንግሥቱም ቅርብ እንደነበሩ እናውቃለን:: ሆኖም የሥርዓቱ ተጠቃሚ እንደመሆንዎ፣ እንደ ጓደኞችዎ በግል በሕዝብ ላይ የፈጸሙት በደል አለመኖሩን ሁላችንም ስለምናውቅና በአብዮቱም



ላይ ጥላቻ ስላላሳዩ፣ ማንም ሳይነካዎ በሰላም ነው የሚኖሩት:: አይደለም እንዴ!» አለ የኮሚቴው ሰብሳቢ ድምፁን ናር አደርጎ::

«ነው! እውነት ነው!»

«ታዲያ <ሁሉም መንገዶች ወደ ዓለም በቃኝ ያመራሉ> የሚለውን በአብዮት ላይ መሳለቅ ምን አመጣው? ከርሶ ይጠበቃል? ምን ለማለት ፈልገው ነው እስቲ ይንገሩን?» አለና ወደኋላው ለጠጥ አለ::

«ይኸንን ቁምነገር ብለው አመጡላችሁ?»

«አዎ አመጡልን፣ የአብዮቱ ተቆርቋሪዎች» አለች የአኢሴማዋ ሊቀ መንበር በጣም ተከሳትራ::

«ጓዶች እኔ እንኳን ከሰው ጆሮ የገባውን ንግግሬን ቀርቶ፣ በልቤ ውስጥ ያለውን እንኳ የምክድ ሰው አይደለሁም:: እውነት መናገሬ የሚያስቀጣኝ ከሆነ፣ ቅጣቱን በጸጋ የምቀበል አባታችሁ ነኝ:: እናንተ ልጆቻችን ከእኛ ከአረጋውያን መማር ያለባችሁ ቁምነገር ቢኖር፣ እውነትን ተናግሮ እመሸበት ማደርን ነው:: አልክ የተባልኩትን ያልኩበትን ምክንያት ላስረዳ፣ በጥሞና አድምጡኝ:-

- ደርግ ያስራል፣
- መንግሥት ያስራል፣
- ደኅንነት ያስራል፣
- ጦሩ በየጦር ሠፈሩ ያስራል፣
- ፖሊስ ያስራል፣
- አጠቃላይ ም/ቤት ያስራል፣
- ከፍተኛ ያስራል፣
- ቀበሌ ያስራል፣

- ክፍለ ሀገር ያስራል፣
- አውራጃ ያስራል፣
- ወረዳ ያስራል፣
- የገበሬ ማህበር ያስራል፣
- አኢወማ ያስራል፣
- አኢሴማ ያስራል፣
- የፋብሪካ ወዝአደር አብዮት ጥበቃም ያስራል::

«ማነው የማያስር? የእኔ አባባል ከዚህ ገደብ የለሽ እስራት ጋር እንዲገናዘብ እፈልጋለሁ:: መግደልና ማስር በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ያሰምረዋል? ደም መቃባት ለማንም አይበጅም:: <መካሪ የሌለው ንጉሥ ያለ አንድ ዓመት አይነግሥ> የተባለውን አልሰማችሁም? መንግሥት□ኮ አባት ነው:: አባት ደግሞ ሩኅሩኅ ነው:: ታጋሽ ነው:: መሐሪም ነው:: ይህ መንግሥት ሕዝብን ቆም ብሎ ማዳመጥ ከማንም ይልቅ ለራሱ ይበጀዋል:: የጥንቱ መሪዎች ሕዝብን የማዳመጥ ፍላጎት □እረኛ ምን አለ?□ እስከሚለው ይወርድ እንደነበር ታውቃላችሁ? ኢትዮጵያ ሦስት ሺ ዘመን ያስቆጠረ መንግሥት ባለቤት የሆነችው ያለ ብልሃት አይደለም::

«እኔ መታሰር አይደለም፣ ብሞትም ግድ የለኝም:: አገሬንና ወገኔን ከጦር ሜዳ እስከ ቤተ መንግሥት ጓዳ በቅንነትና በታማኝነት አገልግዬ የዜግነት ግዴታዬን ተወጥቻለሁ::

«ይብላኝ ለእናንተ ለውጥኖቹ» አሉና ድንገት ዝም ብለው በከዘራቸው መሬት መቆርቆር ያዙ::



የቀበሌው ጥምር ኮሚቴ አባላት ተጠቃቅሰው ወጣ ብለው ከተመካከሩ በኋላ ተመለሱ::

«አባባ ስለ ምክርዎ በጣም እናመሰግናለን:: ለወደፊቱ ከእንደዚህ ያለ አነጋገር ቆጠብ ማለቱ ይበጃል:: ስንፈልግዎ ይመጣሉ:: ለዛሬ በእኛ ዋስትና ወይም በራስዎ ዋስትና ሊሔዱ ይችላሉ» በማለት ከተቀመጠበት ብድግ አሉ::

«ልጆቼ እኔን ባያችሁበት ዓይን ሁሉንም እዩ:: ይህም ቀን ያልፍ ይሆናል:: ቅንነት፣ ደግነትና አስተዋይነት መቸም ቢሆን፣ ማንንም ጎድቶ አያውቅም:: በሉ እናንተንም እኛንም እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ይሰውረን» በማለት ተሰናብተው ወጡ::

የጥምር ኮሚቴው አባላት በአቶ ሁንዴ ድፍረት እየተደነቁ በየእጃቸው ላይ ያለውን የእስረኞች ዝርዝር የያዘ ወረቀት በመመልከት ላይ እንዳሉ

«ጓዶች ይቅርታ!» አለች የአኢሴማዋ ሊቀ መንበር::

ሦስቱም ድምጽ ሳያሰሙ ባንድ ጊዜ፣ በአንድ አይነት ምልከታ ወደሷ አፈጠጡ::

«አቶ ሁንዴ ላይ ሌላም ጥቆማ ነበር□ኮ! ጓድ ሊቀ መንበር ለምን እንዳላነሳኸው አልገባኝም?» አለች ሊቀ መንበሯ::

«ጥቆማውን ጓዶች ሊሰሙት ይገባል ካልተባለ በስተቀር፣ እሳቸው ባሉበት አንስቶ ለምን እንደዚህ በማለት ጸለዩ ወይም ለምን ስለደርግ አይጸልዩም? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ስላልመሰለኝ ነው» አለ ሊቀ መንበሩ::

ለማንኛውም የአቶ ሁንዴን ጸሎት እንስማው ተባለና በአኢሴማዋ ሊቀ መንበር አማካይነት የደረሰውን ጽሑፍ ከጠረጴዛ ኪስ ውስጥ አውጥቶ ሊቀመንበሩ አነበበ::

«.....የአብርሃሙ ሥላሴዎችን፣ ሦስት አካል አንድ ባሕርይ ብዬ አምናለሁ:: ሰይጣን ዲያብሎስን ክጃለሁ:: ጌታ ሆይ ይህን ባገርና በወገን ላይ የመጣ ውርደትና ፍጅት እያየህ ዝም አትበል:: ኢትዮጵያን ከጥፋት፣ ሕዝቧን ከስደት፣ ትታደግ ዘንድ እማጸንሃለሁ:: እንዲሁም ያለ ምርጫችንና ያለፈቃዳችን በላያችን ላይ የተጫኑትን መንግሥትና መሪ በኃያሉ ክንድህ አስወግደህ፣ ያንተን ሕግጋትና ሥርዓታት አክብሮ የሚያስከብር፣ አገርንና ሕዝብን በእኩልነት፣ በነፃነት፣ በአንድነት፣ በፍቅር፣ በትግሥት፣ በጥበብ የሚያስተዳድር መንግሥትና መሪ ትተካልን ዘንድ ከታላቁና ከገናናው ዙፋንህ ስር ወድቄ እለምንሃለሁ» የሚል ነው አለና አጀንዳ ሆኖ እንነጋገርበት ካላችሁ አቶ ሁንዴ ይጠሩ በማለት ጠየቀ::

«እኔ በበኩሌ» አለ የአብዮት ጥበቃው ሊቀ መንበር «እኔ በበኩሌ እኚህን ሰው ለምን እንደዚህ ብለው ይጸልያሉ ብሎ መጠየቅ ያገር መሳቂያ መሆን ነው:: ይህም ብቻ አይደለም፣ በሆነው ባልሆነው፣ በትንሹም በትልቁም ሰውን መነካካቱ ለአብዮቱ አላስፈላጊ ጠላት መፍጠር እንዳይሆን ስጋት አለኝ» በማለት የሰነዘረውን አስተያየት በመደገፍ «ተጨማሪ» አለ የአኢወማው ሊቀመንበር::

«ቀጥል» አለው ሰብሳቢው::

«ለምንም ለማንም የማይበገረው ሕዝባዊ አብዮታችን በአድኃሪያን ጸሎት ይከሽፋል የሚል ስጋት የለኝም:: እነዚህ የባሪያ አሳዳሪውና የፊውዳሉ ሥርዓት ካድሬዎች ባነጠሱ ቁጥር መሸበር የለብንም:: ሃይማኖት የተባለው የሰፊው ሕዝብ ማደንዘዣ (እፅ) ኦፒየም ጊዜው አልፎበታል:: የተደራጀውና



የታጠቀው ሕዝባዊ አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት በተሸጋገረበት በአሁኑ ጊዜ፣ የእነ አቶ ሁንዴ ጸሎት ያከሽፈዋል ብሎ መስጋት በራስ አለመተማመን ነው:: በበኩሉ፣ በግለሰቦች ጸሎት ላይ ውይይት መክፈት ጨርሶ አይታየኝም» በማለት የሰነዘረው አስተያየት አባላቱን በሙሉ ስላሳመነ የአቶ ሁንዴ ጉዳይ ተዘጋና የጥምር ኮሚቴው አባላት ለሻይ ወጡ::

አቶ ሁንዴ ለጥያቄ ይፈለጋሉ የሚል ጥሪ ደርሷቸው ወደ ቀበሌ ሲሄዱ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አይደለም:: በልማት ሥራ እንዲያማክሩ፣ ለእናት አገር ጥሪ፣ ለሌላም ለሌላም ሕዝባዊ ጉዳይ ቀበሌ፣ አልፎ አልፎ ከፍተኛም ይጠሯቸዋል:: የአቶ ሁንዴን መጠራት ቤተሰቡ ሁልጊዜም በስጋት ነው የሚቀበለው:: ንግግራቸው ፊት ለፊት ስለሆነ ከቀበሌዎቹ ጋር አላስፈላጊ ንትርክ ውስጥ እንዳይገቡ ባለቤታቸው ይመክሯቸዋል:: ዮሐንስና ዓለሚቱ ግን ከምክርም በላይ የሆነ ማስጠንቀቂያ እስከ መስጠት ይደርሳሉ::

የአባታቸውን ወደ ቀበሌ መጠራት እናታቸው በስልክ ስላሳወቋቸው ዮሐንስና ዓለሚቱ ግቢ መጥተዋል:: በጣም ቢዘገዩም፣ በአባታቸው በሠላም መመለስ ደስ የተሰኘው ቤተሰብ አቶ ሁንዴን በረንዳ ወጥቶ ነው የተቀበላቸው::

«ደህና መጡ!» አሉ እመቤት ጽዮን ለክብራቸው ተገቢ በሆነ እጅ አነሳስ::

«ደህና ነው፣ ደህናም አይደለ፣ ለጊዜው በዋስ ተለቅቄ ነው የመጣሁት» አሉ::

«ምን ተፈጠረ ደሞ!» አለ ዮሐንስ ተቻኩሎ::

ዓለሚቱ ዕጧ ዱብ ስላለ ፈዝዛ ዓይን ዓይናቸውን ተመለከተች::

«ለማንኛውም እንግባ» እሉና ጌቶች ወደሳሉን እመሩ:: ሚስትና ልጆች ባጠገባቸው ሰፋዎች ላይ ተኮለኮሉ:: አቶ ሁንዴ የሆነውን ሁሉ አንድ ባንድ ረጋ ብለው ነገሯቸው:: የእመቤት ጽዮን ዓይኖች እንባ ማፍለቅ የጀመሩት የባለቤታቸው ትረካ እንደ ተጀመረ ነው::

«አባባ ወቅቱ በጣም ፈታኝ ነው:: እንደዚህ ባለ ጊዜ ከማንኛውም ነገር ቀጠብ ማለት ያስፈልጋል:: ይህንን የምለው እርሶ የወቅቱን አደገኛነት አይገነዘቡም ብዬ አይደለም» አለ ዮሐንስ ሲፈራ ሲቸር፣ አባቱ በደርግ ላይ የሚያሳዩትን ጣላቻ ረገብ እንዲያደርጉ ተማፃኝ ዓይኖቹን እያስለመለመ::

«ሥጋትህ፣ ጭንቀትህ ይገባኛል ግን!» አሉ አቶ ሁንዴ በገነፈለ ስሜት «ዝም በል፣ አትናገር ወይም የአብዮቱ ሕግ ነው እየተባለ በንፁሐን ዜጎች ላይ አፈና፣ ስደት ከዚያ በላይ ጭፍጨፋ ሲካሔድ እያየህ እንዳላየህ፣ እየሰማህ እንዳልሰማህ ሁን ነው የምትለኝ - አይደለም? እንደዚህ ያለውን ዝምታ እንኳን ዛሬ በጃንሆይም ጊዜ አላደረግሁት፣ ታፍኜ አልሞትም» አሉ አባቱ ወደ ዮሐንስ እንደገና አንገታቸውን መዝዘው ዓይናቸውን አፍጥጠው::

«ጃንሆይ በጊዜው ቀልጠፍ ማለት ሲገባቸው፣ ልጡ የትራሰ፣ ስሌት የተደገሰ፣ ጉድጓዱ የተማሰ ገፍገፍ እስኪሆኑ አልጋውን የሙጥኝ በማለታቸው ዙፋኑን አዋርደው፣ እሳቸውም ተዋርደው፣ አገርንም አዋርደው ሞቱ:: ንጉሡ እሺ ቢሉ በውድ፣ እምቢ ካሉ በግድ አልጋውን ለማስለቀቅ ተደጋግሞ ቢሞከርም



ሳይሳካ ቀረ» በማለት የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመገልበጥ ተሞክረው ስለ ከሸፉት አድማዎች መናገር ሲጀምሩ፣

«አባባ ስለከሸፉት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች- - » ብሎ አባቱ በየትኛው አድማ ውስጥ እንደነበሩ ለማወቅ የነበረውን ጉጉት ሳይናገር እናቱ አቋርጠው «ምናለ ሌላ ሌላውን ብናወራ! እሳቸውም ደክሟቸዋል ይረፉበት» አሉና ብድግ አሉ::

«አይዞሽ! ቁጭ በይ! እየፈራን አንሞትም:: የታደለ መሣሪያ አንስቶ ዱር ቤቱ ይላል:: ይገድላል፣ ይሞታል፣ እኛ ደርግን ተፋልመን የክብር ሞት ለመሞት ባንታደልም፣ ስለ ንጉሡም ሆነ ስለ ደርግ እኩይ ድርጊት መናገር ሊሳነን አይገባም:: አንቺም ልጆቼም አንድ ነገር ልብ እንድትሉ እሻለሁ:: መከራና ሞት ስለ ፈሩት፣ ስለ ሸሹት፣ አይቀርም:: ከመሞቴ በፊት በቁሜ እንድሞት አንቺም እናንተም ልጆቼም አትጠብቁ::» ብለው ዝም አሉ::

«ከመጀመሪያው እንኳ ቢሆን ይሻል ነበር፣ አሁን ኮ ደርግ ሥር ሰዷል፣ ጭፍራም አብዝቷል» አሉ እመቤት ጽዮን በለሰለሰ አንደበት::

«ባንድ በኩል እውነትሽን ነው፣ ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ፣ እጅ ስጡ፣ መሣሪያ አስቀምጡ ሲል ቆም ብለን ማሰብ ነበረብን፣ ነገር ግን:-

ያለምንም ደም፣

ኢትዮጵያ ትቅደም

በሚል አሳሳች መፈክሩ እኛን ካደነዘዘ በኋላ፣ በኢትዮጵያ ምትክ ደርግ ራሱን አስቀደመ:: ስህተቱ እዚያ ላይ ነው::

«በደርግ አሳሳች መፈክር መዘናጋታቸው ያንገበገባቸው ጎጃሞች:- <ዐባይ በጣና ላይ ደልሎ ደልሎ፣

ቤቱን ሠርቶ ቀረ ጊዜያዊ ነኝ ብሎ>

በማለት ቁጭታቸውን መግለጣቸውን ሰማሁ:: ቢያንስ ደርግ ከሐዲ፣ አጭበርባሪ መሆኑን እንደዚህ ባለ ሥልት የመግለጽ ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል» ብለው ዘና አሉ::

«ጃንሆይ እስኪጃጁ አልጋውን አለቅም ማለታቸው አንዱና ከባዱ ስህተት እንደ ነበር አባባ በትክክል ተናግረውታል:: እኔ ደግሞ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሌላ ስህተት ታይቶኛል:: በዚያን ጊዜ ወደ ፖለቲካ ድርጅትነት ሊያድጉ የሚችሉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች መታፈንና በእንጭጭነት በመቀጨት ሌላው የሥርዓቱ ዐቢይ ስህተት ይመስለኛል:: የአፈናው መሣሪያ ለነበረው መለዮ ለባሽ-ደርግ መንገዱን ጨርቅ እንዲሆን ያደረጉለት ጃንሆይ ራሳቸው ናቸው:: □ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን□ እንዲሉ፣ ፍፁማዊ የዘውድ አገዛዝ ይከተለው የነበረው የራስ ፀረ-ዲሞክራሲ ፖሊሲ ሰለባ ነው የሆነው» አለች ዓለሚቱ በጃንሆይ ላይ በሰነዘረችው አስተያየት አባቷ የሚሉትን ለመስማት ቸኩላ::

«ደግ አስተውለሻል። አንዳንዶቻችን ያ አፈና አገር እንደሚጎዳ እንገነዘብ ነበር:: ታዲያ አፈናውን ፀጥ ለጥ ብለን ባለመቀበላችን ከሹመት አገራችን ተሸረናል:: በንጉሡ ፊት የሹመት ሽልማት ሞገስ ተነፍገናል::

«በነገራችን ላይ» አሉ ጌቶች በንጉሡ ላይ የነበረው ተቃውሞ ትዝ ብሏቸው:: «የንጉሡን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መቃወም የተጀመረው ገና ባንዲራችን እንደተመለሰች በ1934



ዓ.ም ነበር - - -» በማለት አቶ ሁንዴ የታመቀ ብሶታቸውን ለመግለጽ ሲመቻቹ፣

«እንዴት አባባ! ያን ጊዜ ምን ዓይነት ንቃትና ድርጅት ኖሮ መፈንቅለ መንግሥት ታሰበ?» ዮሐንስ ይህን ጥያቄ የሰነዘረው የአባቱን መረጃ በመጠራጠር ሳይሆን ታሪኩን እንዲያብራሩለት መሆኑ ገብቷቸዋል::

«ጃንሆይ፣ ከ1933 እስከ 66 ዓ.ም ባለው የግዛት ዘመናቸው ከዘጠኝ ጊዜ በላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች ተደርገውባቸዋል:: ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የነበላይ ዘለቀ አመጽ፣ የነብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ፣ የነደጃች ታዬ ጉልላቴ፣ የነቢትወደድ ነጋሽ፣ የነመንግሥቱ ነዋይ፣ የነደጃች ታከለ ወልደ ሐዋርያት፣ የነጀኔራል ታደሰ ብሩ፣ የነኮማንደር እምሩ ወንዴ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች ከከሸፉ በኋላ የመጨረሻውና ዘጠነኛው የደርግ የመንግሥት ግልበጣ ሴራ ባልተፈለገና ባልተጠበቀ አቅጣጫ ሔደ:: አልጋውን ያነቃነቀው የሕዝብ አመጽ ቢሆንም፣ ሥልጣኑን በአቋራጭ የያዘው የመለዮ ለባሽ ክፍል ሆነ::

«አብዛኞቹ የመንግሥት ግልበጣ አድማዎች ያነጣጠሩት በጃንሆይ ላይ ነበር:: ያም ትክክል ነበር» አሉ አቶ ሁንዴ በንጉሡ ላይ የነበራቸውን ተቃውሞ በማስረገጥ:: «ጃንሆይ ወደ እንግሊዝ ተሰድደው በነበረበት ጊዜ ዘወዱ እንዳለ ሆኖ፣ ለመንግሥታቸው ፓርላማ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ አካላት ሙሉ ሥልጣን ለመስጠት ቃል ገብተው እንደነበር አብረዋቸው ተሰደው የነበሩት እነ ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ አጫውተውናል:: ንጉሡ የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰው

የአገዛዙን ሥልጣን በዘውዱ ሥር እንዲማከል አደረጉ:: በዚያ ድርጊታቸው ቅያሜ ማትረፋቸውን እሳቸውም አውቀውታል» አሉ አቶ ሁንዴ::

«እርሶ የሥርዓቱ ተጋፊ ነበሩ:: ከየትኛው ቡድን ጋር ነበር ያበሩት?- - -» በማለት አባቱን በሚኮረኩር ፈገግታ የጀመረውን ጥያቄ እናቱ ጣልቃ ገብተው አቋረጡት::

«ዮሐንስ!» አሉ እናቱ ፊታቸውንም አካላቸውንም ወደሱ ዞር አድርገው፣ «የምን ነገር መቆስቆስ ነው? እንኳን እንደዚህ ነካክተሃቸው አባትህ - - - »

አይዞሽ ዐሳብ አይግባሽ፣ በተደጋጋሚ የጣሉት ወጥመድ አንዱም አልያዘላቸውም:: በተለይ በ1943 ዓ.ም እነቢትወደድ ነጋሽ፣ እነ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ እነሻለቃ በቀለ አትናቲዎስ የሞከሩትን አልጋ ግልበጣ ቀደም ብዬ እውቅ ነበር:: በአድማው እንድሳተፍ ተጠይቁ <ጊዜ ስጡኝ ላስብበት> በሚል ሰበብ ማመንታቴን ተረድተው እነሱም ቸል አሉኝ»

«እርሶ ተራማጅ ሆነው በግልፅ ሲቃወሙ የነበረውን የዘውድ ሥርዓት ተጋግዘን እናስወግድ ሲባሉ እንዴት አመነቱ» አለች ዓለሚቱ አባቷ የጀመሩትን ታሪክ ተርከው እስኪጨርሱ አላስችል ብሏት::

«ሰማሽ ልጄ! እኔ ኮ ዘውዱን አልነበረም ስቃወም የቆየሁት:: ዘውዳዊውን የአፈናና የጭቆና አገዛዝ እንጂ!» በማለት ጉሮሯቸውን ጠራረጉ::

«ቅድም፣ ጃንሆይ በስደት ዘመናቸው ገብተውት ስለነበረው ቃል ኪዳን አለመከበር ያልኩትን ታስታውሳላችሁ:: ጃንሆይ ለፓርላማ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትርና ለፍትሕ አስተዳደር ተገቢው



የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ባለመስጠት እሳቸው ሁሉንም ነገር ሆኑ:: የእኔና የሌሎችም አገር ወዳዶች ተቃውሞ የመነጨው ከዚህ ነው:: ዘውዱን እንቃወምም:: በዘውዱ ስም፣ በዘውዱ ሽፋን በሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን ግፍና በደል እንጂ! ዘውዱን በዘውድነቱ አልተቃወምንም:: ዘውዱ የዘላለማዊት ኢትዮጵያ:-

የነፃነት፣

የሉአላዊነት፣

የአንድነት፣

የጥንታዊነት፣

የታሪካዊነት፣

የእነዚህ ሁሉ ስብስብ የሆነው ኢትዮጵያዊነታችን ምልክት ነው:: በእግዚአብሔር ተመርጠው፣ ሕዝብን በአባትነትና በእኩልነት እንዲመሩ የተቀበሉትን አደራ ሲበሉና ቃል ኪዳናቸውን ሲያፈርሱ፣ በከሐዲ ነገሥታት ላይ ማመፅ ለእኔ ወንጀል አይደለም::

«የእነ ቢትወደድ ነጋሽ አድማ ግን ንጉሡን ገድለው ኢትዮጵን ሪፐብሊክ ማድረግ ነበር:: ሪፑብሊክ ሲኮን ዘውዱ ቀረ ማለት ነው:: የኢትዮጵያዊነት ውርስና ቅርስ የሆነው ዘውድ እንዲወገድ አልፈልግም:: ለዚህ ነበር ከነሱ ጋር ያላበርኩት::»

«ከዚህስ ሌላ?» አለ ዮሐንስ አባቱ ስንት ጊዜ በመንግሥት ግልበጣ አድማ እንደተሳተፉ ለማወቅ ያለውን ጉጉት እያሳየ::

«እነ ደጃዝማች ታየ ጉልላቴ፣ እነ ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ፣ እነ ፊታውራሪ እምባው ጉልላቴ፣ ሌሎችም በርካታ መሣፍንትና መኳንንት ወጥነውት የነበረው የመንግሥት ግልበጣ ሴራ ውስጥ ለመሳተፍ ዳር ዳር ብዬ ነበር:: ሆኖም

የእነሱም ዓላማ ዘውድን አስቀርተው ሪፑብሊክ ኢትዮጵያን ለመመሥረት መሆኑን ስረዳ፣ ቀስ ብዬ አፈነገጥኩ:: በዘውድ ላይ ማመፅ በኢትዮጵያዊነት ላይ ማመፅ ነው:: ዘውድ የነፃነት፣ የዕድገትና የሥልጣኔ እንቅፋት አለመሆኑን በእንግሊዝና በጃፓን ያለውን የዘውድ አስተዳደር መመልከት ይቻላል::

«አሁንም ቢሆን» አሉ አቶ ሁንዴ ወደ ተነሱበት ጉዳይ ለመመለስ «አሁንም ቢሆን የጃንሆይ ካልጋ መውረድ ተገቢ ነው:: ባይሳካልን እንጂ እኛም ደጋግመን ሞክረነው ነበር:: ነገር ግን በሳቸው ዳፋ ዘውድን ያህል ክቡር ንዑድ ቅርስና ውርስ ኢትዮጵያ ማጣቷ በእጅጉ ያሳዝናል:: እኔን ይበልጥ የሚያቃጥለኝና የሚንገበገበኝ ደግሞ ካልጠፋ ሰው:-

ጉርባ መኮንኖች፣

ሃምሣ አለቆች፣

አሥር አለቆች፣

ተራ ወታደሮች፣

ንጉሠ ነገሥታቱን ተክተው ያገር መሪ፣ የሕዝብ አስተዳዳሪ እንሁን ማለት ነው::»

«አባባ ሁለት ወደ አይሆንም:: መለዮ ለባሹ ፈጥኖ በትረ ሥልጣኑን ባይዝ ኖሮ፣ የጃንሆይ መንግሥት ከወደቀ በኋላ በተፈጠረው ክፍተት እስከፊ ደም መፍሰስ ሊከሰት ይችል ነበር» አለ ዮሐንስ::

«ዮሐንስ!» አሉ አባቱ ድምጻቸውን ለዘግ አድርገው «ዮሐንስ! የእኔ ተቃውሞ□ኮ ለምን መለዮ ለባሹ ሥልጣን ያዘ አይደለም:: ሲሆን ሲሆን የዘውዱ ሥርዓት እንዲቀጥል የተቀባ ንጉሣዊ ርዕሰ ብሔር ቢኖረን፣ ያም ካልሆነ ከመለዮ ለባሹ



መካከል በትምህርት፣ በልምድ፣ በሥነ-ምግባር ብቁ ከሆኑት ጄኔራሎች መካከል አንዱ መንበረ ሥልጣኑን በመያዝ፣ የደርግ አሻንጉሊት ሳይሆን፣ ልብ በል፣ የደርግ አሻንጉሊት ሳይሆን፣ አገሪቱን መምራት በተገባው ነበር::

«ትናንት የከፍተኛ መኮንኖች ሹፌር፣ የሚስቶቻቸው ዘንቢል ተሸካሚ፣ የጦር ሠፈር ጽዳት ሠራተኛ የነበሩ ቀረንጠሎዎች እንዴት ይግዙን? እንዴት ይግዙን? ትምህርት የላቸው፣ ልምድ የላቸው፣ አባቶቻቸውን ጠርተው አያቶቻቸውን አይደግሙ፣ እነዚህ ናቸው አገርን የመምራት ኃላፊነት የሚሸከሙ? ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘር የወረዱትና የተቀቡት ንጉሥ መሸከም ያቃታቸውን የሕዝብ እረኝነት እነዚህ ወላጅ ፍናጅ ምናምንቴዎች እንዴት ይችሉታል?

«ኢትዮጵያ! ይህን የቁም ሞትሽን ሳያዩ የሞቱት ልጆችሽ ምንኛ ታደሉ!» በማለት የተናነቃቸውን ሳግ አፍነው ወደ መኝታ ክፍላቸው ገቡ::

***

የጥምር ኮሚቴው አባላት በየእጃቸው ላይ ያለውን የእስረኞች ዝርዝር የያዘ ወረቀት እንደገና መመልከት ጀመሩ::

«ያን ቀንደኛ አናርኪስት ደረጀ ጉልቴን እናነጋግር:: ከፍተኛም የእሱ ጉዳይ ከምን ደረሰ? በማለት ጠይቆኛል» አለ ሰብሳቢው:: በቀረበው ሃሳብ ሁሉም ስለተስማሙ ደረጀ የፊጥኝ እንደታሰረ መጣ::

ደረጀ ቀን የጣለው ደኻ ቤተሰብ አባል ነው:: አባቱ ጉልቴ ማንተጋፍቶት በውስጥ አርበኝነት ውለታቸው በአሩሲ ጠቅላይ

ግዛት፣ ጢቾ አውራጃ፣ ጠና ወረዳ አንድ ጋሻ መሬት ካገኙ በኋላ «ርስቴን አቀናለሁ» በሚል ሰበብ ገጠር ገብተው ቀጭን ጌታ ሆነው ነበር:: ያለመታደል ሆነና፣ ባልጠበቁት ጊዜና ሁኔታ፣ በገጠር መሬት አዋጅ ተፈናቅለው አዲስ አበባ ተመልሰዋል:: አቶ ጉልቴ ከአሥር ዓመት በፊት ወደ አሩሲ የኮበለሉት የደረጀን እናት ሰማኒያ ሳያወርዱ ሌላ ሚስት አግብተው ስለነበር መመለሳቸውን ቤተሰቡ አልተቀበለም:: ቀድሞም ቢሆን፣ ደረጀ አልፎ አልፎ ካባቱ ዘንድ ከርሞ ሲመለስ ከሚያመጣው ቀለብ በስተቀር፣ በአባቱና በእናቱ መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋርጧል:: ከዚህም የተነሳ አቶ ጉልቴ ለጊዜው ካረፉበት የአቶ ሁንዴ ቤት ጥገኛ እንደሆኑ ቀርተዋል:: ባላምባራስ ማንተጋፍቶት የወንበር ቤኛ ገዳ የፍርድ ጸሐፊ ስለነበሩ ልጆቻቸውን /ሁንዴንና ጉልቴን/ አብሮ አደግነታቸው ያስተሳስባቸዋል::

አቶ ሁንዴና ደረጀ የተለያየ ጎራ ተሰላፊ ቢሆኑም፣ በየአንፃራቸው ሲያመች በግልጥ ሳያመች በስውር አብዮቱን እየታገሉ ናቸው:: መረጃም ይለዋወጣሉ:: አንዳንድ ጊዜ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚከፈቱት ውይይት፣ አቶ ሁንዴ ስለ አብዮቱ ከባልንጀሮቻቸው ሻል ያለ ግንዛቤ አስጨብጧቸዋል:: ደረጀንም ትግሉን በጽናት እንዲጋፈጥ አግዞታል::

«ደረጀ» አለ የጥምር ኮሚቴው ሰብሳቢው «አንተ አብዮት አልመጣብህም፣ መጣልህ እንጂ! እንጀራ ጋግረው ያሳደጉህን እናትህን.....»

«ተው ባክህ!» አለ ደረጀ የሲቀ መንበሩን ንግግር አቋርጦ እዚያው በተቀመጠበት እየተቁነጠነጠ «ይህን የአባ መሸ በከንቱ ስብከትህን ልደታ ቤተ ክርስቲያን አድርገው» አለና «ለምን



እንደዚህ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ትፈጽሙብኛላችሁ? ሌላ ቢቀር እናንተ ዘንድ ስቀርብ እንኳ የተጠፈርኩበት ካቴና አይወልቅልኝም?» ሲል ጠየቀ::

«ደረጀ አትቸኩል፣ አይዞህ! ስለሱም ስለ ሌላውም እንነጋገራለን፣ የተጠራኸውም ለዚህ ጉዳይ ነው አለ» የአብዮት ጥበቃው ሊቀ መንበር::

«ታዲያ የምን ቀጠሮ ነው ፍቱኝና፣ ተዝናንተን እንነጋገራ!» አለ ደረጀ::

«በመጀመሪያ ረጋ በል» አለ የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴው ሊቀ መንበር::

«እሺ! ምንድነው ከኔ የምትፈልጉት?»

«ካንተ የምንፈልገው፣ በኢሕአፓ ውስጥ የትኛው ቡድን አባል እንደሆንክ እንድትነግረን ነው» አለችው የአኢሴማዋ ሲቀ መንበር::

«ለምንድ ነው የምነግራችሁ? እሱን ተናግሬ ከናንተ ምሕረት ለማግኘት?» አለና ደረጀ በዋዘኛ ጠየቀ::

«ደግሞስ» አለ ደረጀ «እኔ ምን መሆኔን አታውቁምና ነው የምትጠይቁኝ?»

«ለምንድነው የኢሕአፓ መሣሪያ አፈሙዝ በእኛ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ያነጣጠረው? በእኛ መገደል አብዮቱን ከግሥጋሴው መግታት የምትችሉ ይመስልሃል?» በማለት ሰብሳቢው ክፉኛ ደነፋ::

«አዎ! እንዴታ! እናንተ ምን እንደሆናችሁ ታውቃላችሁ? አታውቁም:: እኔ እነግራችኋለሁ፣ በጥሞና አድምጡኝ አለና «ጓድ የቀበሌ ሲቀ መንበር አንድ ጥያቄ፣ የድፍረት ቢመስልም

ልጠይቅህ፣ ለመሆኑ ኮሲና ሙጃ ታውቃለህ::» አለና ንግግሩን ቆም አደረገ::

«አዎ አውቃታለሁ»

«መልካም እንግዲያውስ እናንተ ኮሲ፣ ደርግ ደግሞ በኮሲው ላይ የበቀለ ሙጃ ነው:: ሙጃ ሣር ቢሆንም ለእንስሳ መኖነት አያገለግልም» በማለት የኮሲንና የሙጃን ምሳሌ በውል አጢነው እንደሆን ለማረጋገጥ የኮሚቴውን አባላት ዓይን እየተመለከተ ዝም አለ::

«ታዲያስ» አለ የኮሚቴው ሰብሳቢ::

«ገበሬው፣ ኮሲውን አስወግዶ ሙጃው እንዳይበቅል በማድረግ፣ ኮሲ አፈር ደግሞ ለጪንጫ ዕዳሪ መሬት እንደ ማዳበሪያ በመጠቀም ጠቃሚ አገልግሎት ላይ ማዋል አለበት» አለ ደረጀ ፈርጠም ብሎ::

«አላበዛኸውም!» አለ የአኢወማው ሊቀ መንበር በዛቻ መልክ::

«አንቺ ደግሞ ማነሽ! አብዮተኛ! የጥጃ ቀንዳም!» አለ ደረጀም በፋንታው እያሽሟጠጠ::

«ታዲያ ያንተ የሥራ ድርሻ ምን መሆኑ ነው?» አለው የአብዮት ጥበቃው ኮሚቴ ሊቀ መንበር::

«የእኔን የሥራ ድርሻ በግልጽ ልንገራችሁ፣ ኮሲውን አፈር ማስወገድ ነው እንደ ብልሁ አስተዋዩ ገበሬ» አለ አሁንም በድፍረት::

«በቃ! ረቃ! ከዚህ በላይ ምን እንዲነግረን እንፈልጋለን?» ተባብለው ደረጀን ወደ ማጎሪያው እንዲወስድ ከበር ላይ የቆመውን የአብዮት ጥበቃ ጓድ ጠሩት::



«አንድ ጊዜ የመጨረሻ ነች፣ አትስልቹ» አለ ደረጀ «ደርግ እንኳን ለናንተ ለራሱም ስለማይሆን በተጭበረበረ አዋጅና በጊዜያዊ ድል አትታለሉ:: ሕዝባዊውን አብዮት ለማዳን ከእውነተኛው ሕዝባዊ አብዮታዊ ድርጅት ኢሕአፓ ጋር ተደባለቁ:: ለፀረ-ሕዝብ ድርጊታችሁ ንስሐ ግቡ:: ደርግ በምንም ኃይል ቢጠናከር የኢትዮጵያን ሕዝብ እውነተኛው የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ሊያደርግ አይችልም:: ከእባብ እንቁላል እርግብ አይፈለፈልምና» ብሏቸው ደረጀ ወደማጎሪያው ተመለሰ:: ሊያመልጥ ሲል ተባለና በዚው ሰሞን ተደመሰሰ::

***

ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ በርካታ የጎንደር፣ በተለይም የሰሜን ጎንደር አብያተ ክርስቲያናት ተዳፍነዋል:: ለእነዚህ ችግረኛ አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ ለማሰባሰብ የአክሊሉ አባት አበ ነፍስና የቅርብ ወዳጅ መምህር ኃይለ መለኮት አዛገ አበ ነፍስና ልደታ ቤተክርስቲያን አካባቢ ሲዘዋወሩ፣ ፀጉረ ልውጥ ተብለው በቁጥጥር ሥር ከዋሉ ሰንበት ብለዋል:: እኒህን መንፈሳዊ አባት ለማስፈታት አክሊሉ ያደረገው ሙከራ ባይሳካም፣ ዕድሜ ለአሰገደች ብር ከልዩ ምርመራ (ሥቃይ) ድነዋል:: የጥምር ኮሚቴ ሥራ ስለበዛበት በጊዜ ሳላነጋገራቸውም:: ቃላቸውንም አልሰጡም ነበርና ይምጡ ተብለው ገቡ::

መምህር በእጃቸው ላይ የተገኘው ገንዘብና መስቀላቸውም ጭምር ተመዝግቦ መጋዘን ስለገባ፣ ወደ ጥምር ኮሚቴው ቢሮ እንደገቡ «እንዴት ዋላችሁ» በማለት እጃቸውን አሳለሟቸው::

የኮሚቴው አባላት ሳይወዱና ሳይፈቅዱ በይሉኝታ የቁሉን እጅ ከተሳለሙ በኋላ በትዝብት እርስ በርስ ተያይተው ተቀመጡ።

«አባ ስምዎን ቢነግሩን?»

«መምህር ኃይለ መለኮት አዛገ እባላለሁ»

«አገርዎ የት ነው?»

«ጎንደር።»

«ኢዲዩ ነዎት?»

«አይደለሁም።»

«ኢህአፓ ነዎት?»

«አይደለሁም።»

«ገንጣይ ወንበዴ ነዎት?»

«አይደለሁም።»

«ታዲያ ምንድንዎት?»

«እኔ! እኔ! እኔማ! የጠራሁ ጎንደሬ!»

«አሁን እውነት ጥያቄው ሳይገባዎት ቀርቶ ነው ጎንደሬ ነኝ ያሉት?» አለ የኮሚቴው ሰብሳቢ ቆጣ ብሎ።

«ታዲያ ምን ልበል? ምንድነህ? ብለህ ስትጠይቀኝ «ሰው ነኝ» ብል ይሻል ነበር? ያን ያላልኩት ማሌጥ እንዳይሆንብኝ ብዬ ነው» አሉ ለሙግት ዝግጁ መሆናቸውን በማሳየት።

«ጥያቄው የየትኛው ፀረ-አብዮት ድርጅት አባል ነዎት? ነው» አለ የአብዮት ጥበቃው ኮሚቴ ሊቀ መንበር።

«ፀረ-አብዮት ማለት በጎንደር ውርጋጡን እያስጨፈጨፈ ያለው ጉግ ማንጉግ መሆኑ ነው?» አሉ አባ አንገታቸውን ወደፊት ወርወር አድርገው።

«አዎ» አለ የኢወማው ሊቀ መንበር።



«ምን አዎ ትላለህ! በጎንደር ማነው የወጣቱ ጨፍጫፊ! ነገሩ የገባህ አልመሰለኝም! ማነው ጨፍጫፊ ማነው? አስጨፍጫፊውስ? አባ ይለዩ።»

«እኔ እነማን እንደሆኑ የአጥፊና ጠፊን ስም ለይቼ አላወቅሁ። እንዲያው ተላለቁ ሲባል ነው የምሰማ» አሉ አባ ከሙግቱ በፊት ለፊት ሳይሆን በስርቆሽ በር ወጥቶ ለማምለጥ።

«አባት! አያምታቱ፤ የላክዎትን ድርጅት በይፋ አጋልጠው፤ ግለ ሒስ በራስዎ ላይ አካሒደው፤ የበደሏትን አገር፤ የበረበሩትን አብዮት ለመካስና ለመገንባት ቃል ከገቡ ብቻ ነው፤ የንቃት ትምህርት ወስደው የሚፈቱት» አለ የኮሚቴው ሰብሳቢ።

«ምነው ልጄ! ምን አረኩህ! እኔ የበደልኩትም አገር! የበረበርኩትም አብዮት የለም። እንዴት! እንዴት ማን ወልዶ ማን ቢያሳድግ! ስማህ! እኔ ኮ ከፍ ሲል ከፋሲል፤ ዝቅ ሲል ከቴዎድሮስ አረግ የምመዝ የጠራሁ ጎንደሬ ነኝ። አገሪቱ የማን ሆና ነው እኔ በዳይ የምሆነው?»

«በቃ! በቃ! ያ እንደ አባላዘር በሽታ በዘር የሚተላለፍ ትልቅነት አብቅቷል። ጊዜው ያለፈበት ተረት ተረትዎን ትተው ለሚጠየቁት ብቻ መልስ ይስጡ» አለ የአብዮት ጥበቃው ኮሚቴ ሊቀ መንበር በግሳፄ።

አባ መልሳቸው ጠያቂዎቻቸውን እንዳልጣመ ስለተገነዘቡ ዝም አሉ።

«ግድ የለም ማታ ያወጧታል። እንዲህ እንዳሸፉ አይቀሩም» ተብለው ወደ ማጎሪያ ተመለሱ።

«ጊዜያችንን በከንቱ አቃጠልን፣ የዋኽ ጎንደሬ.......» አለች የአኢሴማዋ ሊቀ መንበር::

«ውጤቱ ባያመረቃም ለዛሬ እዚህ ላይ ቢበቃን» አለ የአኢወማው ሊቀ መንበር::

«አይቻልም በዚህ ደብተኙ ላይ አንድ ውሳኔ መድረስ አለብን:: እዚሁ የንቃት ትምህርት ይወሰድ ወይም በዋስ እንልቀቀው?» በማለት ሰብሳቢው አማራጭ ሀሳቦችን አስቀመጠ::

ከአጭር ጊዜ የሀሳብ ልውውጥ በኋላ እዚሁ ንቃት ይውሰድ በሚለው ተስማሙ:: ሪፖርት ለከፍተኛው እንዲተላለፍ፣ የከፍተኛው ካድሬ ለተወሰኑ እስረኞች የንቃት ትምህርት እንዲሰጥ በተጨማሪ ተወሰነ:: በውሳኔው መሠረት:-

- አብዮትና አብዮታዊ ሁኔታ፣
- አብዮታዊ ሽግግር፣
- አብዮታዊ ዲሞክራሲ፣
- አናርኮ ሲንዲካሊዝም፣
- ዲያሌክቲካዊ ቁስ አካልነት፣
- ታሪካዊ ቁስ አካልነት፣

በሚሉ ስድስት አርእስት በቁጥጥር ሥር ለዋሉት የተወሰኑ እሥረኞች በከፍተኛው ካድሬ ለአንድ ወር ያህል የንቃት ትምህርት ተሰጣቸው::

እሥረኞች ከመለቀቃቸው በፊት ካድሬው ካስተማራቸው ርዕስ ባንዱ ላይ ያዘጋጁት ጽሑፍና የቃል ማብራሪያ እሥረኞች፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች አመራር አባላትና የእሥረኞች ቤተሰቦች በተገኙበት ፕሮግራም ላይ ያቀርባሉ::




መምህር ኃይለ መለኮት የደረሳቸው ርዕስ «የሰው ዘር አመጣጥ» የሚል ሆነና ተቀበሉ:: እሳቸው ስለዝግጅቱ እምብዛም አልተጨነቁ:: በዝግጅት ላይ መዋል የነበረው ጊዜ ለጸሎት አደረጉት:: ቀኑ ደረሰ:: መምህር ኃይለ መለኮት ተራቸውን ጠብቀው አትሮኖሱ ኋላ ቆሙ:: የፕሮግራሙ መሪ ካድሬ፣ «አባ <ስለ ሰው ዘር አመጣጥ> ያዘጋጁትን ጽሑፍ ያቀርባሉ:: ገለፃውን እንዲያጠናክሩልዎት የተሰጡዎትን ከዝንጀሮነት ወደ ሰውነት የተደረገውን የበርካታ ሚሊዮን ዓመታት ጉዞዎች የሚያሳዩትን ሥዕሎች አንድ ባንድ ይተነትናሉ:: ለትንተናው እንዲያመች ሥዕሎቹን ጥቁር ሠሌዳው ላይ ይለጥፏቸው» በማለት አዘዛቸው::

«የስዕሎቹን ልጠፋ ጓድ ካድሬ አንተ ወይም አንድ ሌላ ሰው ቢረዳኝ» አሉ መምህር ኃይለ መለኮት እንደመለመን ባለ ትህትና

«እሺ! እኔ ለጥፋቸዋለሁ:: እርሶ ገለፃዎን ይቀጥሉ» በማለት ካድሬው ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ተጋግዞ ልጠፋውን ጨረሰና «በሉ እንግዲህ አባን ቤቱ በጥሞና ያዳምጣቸው» በማለት ወደ ፕሪዚዲየሙ አመራ::





1



2





«በዚህ ርዕስ ይህን ዝግጅት እንዳቀርብ ዕድል ስለተሰጠኝ ጓድ ካድሬን አመሰግናለሁ:: ጓዶች፣ እንዲሁም ሌሎቻችን፣ እሥረኞች ማለቴ ነው፣ የሰው ዘር ከየትና መች እንደመጣ በግልጽ የምናውቀው ነገር ነው:: ሰው ሰውን ሲወልድ፣ ሰው ሰውን ሲወልድ፣ ሲወልድ ሲዋልድ፣ ሲወልድ ሲዋለድ - - - »

«አባ ያቁሙ! ያቁሙ! የሰው ዘር ከብናኝ በትናአኮት ሒደት፣ ከዚያም ከነጠላ ኅዋስ እስከ ዝንጀሮ ያለውን አዝጋሚ እድገት፣ በመጨረሻም ዝንጀሮ እንዴት ወደ ሰውነት እንደተለወጠ የተማሩትን ያስተምሩ:: እቀልዳለሁ ካሉ እዚችው ይከርሚታል» አለ ካድሬው በተግሳጽና በዛቻ::

አባ ወደ ካድሬው ትክ ብለው ተመለከቱ:: ጥቁረቱን፣ የአፍንጫውን ቀዳዳ መስፋትና የሰርኑን መደፍጠጥ እያስተዋሉ ጥቂት ሴኮንዶች ዝም አሉ:: «ጓድ ካድሬ አንተ ደግ አባትህን አውቀሃል» ልበለው አሉና አሰቡ፣ ይኸንኑ ሲያወጡ ሲያወርዱ---

«ይበሉ እንጂ አባ!» አለ ካድሬው::

«አዎ መቼም ያ ያለፈ ጨቋኝ አደኃሪ ሥርዓት በእኛ በጎንደሮች ላይ ያልፈፀመው በደል የለም:: አልጋው ከጎንደር ወደ ሸዋ ከተዛወረ በኋላ፣ ከእኛ ከሰዎቹ አልፎ ተርፎ፣ የሰሜን ጭላዳ ዝንጀሮም ሳይቀር የጭቆናው ሰለባ ነበር ማለት ይቻላል:: ይህ ሁሉ የሸዋ ዝንጀሮ ሰው ሲሆን፣ አንድ እንኳ የጎንደር ዝንጀሮ ሰው አልሆነም:: አብዮታችን ከዚህ ጭቆና ስላወጣን ክብር ምሥጋና ይግባው:: ነጻ የወጡት ያገሬ የጎንደር ዝንጀሮች በቅርቡ ሰው እንደሚሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ» ብለው ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ::



ታዳሚው ሁሉ ትንፋሽ እስኪያጥረው፣ አንዳንዱም ከተቀመጠበት ወንበር ላይ እስኪወድቅ ሳቅ በሳቅ ሆነ::

መምህር ኃይለ መለኮትም እዚያ በተገኘው ታዳሚ ተማጽኖ በነፃ ተለቀቁ::

# ምዕራፍ 22

## ዓለሚቱና የመዝገብ ቤቱ ሹም

ዓለሚቱ ለመዝገብ ቤቱ ሹም ምስጢሯን አካፍላ ሠነዶችን በእጇ የምታስገባበትን ድርድር አገባዳለች:: ሹሙ፣ የእነ ወ/ሮ ትግሥት ሙሉጌታን መዝገብ አንድ ባንድ አገላብጦ ተመልክቷል:: ፎቶ ኮፒ መደረግ የሚገባቸው ሠነዶች መርጦ ምልክት አድርጎባቸዋል:: ዓለሚቱ ሠነዶቹን ለማግኘት የተጠየቀችውን ገንዘብ ለመክፈል ወደ ኋላ እንደማትል የመዝገብ ቤት ሹም ግምት ወስዷል:: ዓለሚቱ ወደ አውራጃው ፍ/ቤት መሔድ አቁማ ግንኙነታቸው በስልክና በተያዘ ቀጠሮ በግንባር እየሆነ ነው::

«በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ ጊዜ የወሰድን ይመስለኛል፣ ወደ መጨረሻው ምዕራፍ ብናሸጋግረው ምን ይመስልሃል?» አለች ዓለሚቱ በላይ ዘለቀ መንገድ ቀስተ ዳመና ምግብ ቤት እሷ መኪና ውስጥ ራት በልተው ሲሸኛኙ::

«አዎ! በእኔ በኩል የቀረ ነገር ያለ አይመስለኝም::»

«ገንዘቡን ልስጥህና ፎቶ ኮፒ አስደርገዋ!» አለች ዓለሚቱ::

«ፎቶ ኮፒ ማስደረጊያ ካንቺም ባልወሰድ....» ብሎ ፊቱን ወደ እሷ መለስ አደረገ::

«አንድ ነገር ላረጋግጥልህ እወዳለሁ፣ ከሰው ነፍስ ወዲህ የጠየቅኸውን ሁሉ ታገኛለህ፣ አንተ ያለብህ መጠየቅ ነው:: ባንተ ጥያቄ ላይ ድርድር አይኖርም:: ተግባባን!» በሚለው ቁርጥ ያለ ግልጽ አነጋገሯ ዓለሚቱ ልቡን ሰረቀችው::



«ለክፉም ለደጉም ነገ አምስት መቶ ብር ይዘሽ ትመጪለሽ:: የቀረውን ስንገናኝ እንነጋገርበታለን» ተባብለው ለመለነባበት ሲጨባበጡ ሲፈራ ሲቸር እጆዋን ሳም አደረገ::

«ከንፈርና ሌላው የማን ሊሆን ነው አንተ እጄን የምትስመው» ብላ ግጥም አድርጋ ሳመችው::

«ጥንቅሽ» አለ እርካታውን በሚገልጽ ምልከታ::

«አገዳው ብቻ አይደለም ፍሬውም፣ የሁል ጊዜ ጥንቅሽ እንዲኖርህ ያንተ ሲሆን ይችላል» ብላ እንደገና ከለከሰችው::

«ቢይ ነገ ወደ ማታ አንድ ሰዓት ላይ እዚሁ እንገናኝ::»

«ለምን አልሸኘህም?»

«ግድ የለም፣ እዚሁ አካባቢ ጓደኞቼ ይጠብቁኛል» ስላለ ተሰነባብተው ተለያዩ::

«አንድ ምዕራፍ!» አለች ዓለሚቱ የምሽቱን ተልዕኮ መሳካት እያሰበች::

«እግዜር ካለ ነገ ጉሮ ወሸባዬ የምዘፍንበት፣ የዕደናውን ግዳይ የምጥልበት የመጨረሻው መጨረሻ ምዕራፍ ይሆናል» እያለች የድሉን ዋዜማ ግቢ ወላጆችዋ ጋር ለማሳለፍ ወስና አውቶሞቢሏን ወደ ሚክሲኮ አደባባይ ነዳች::

ይህንንስ የድል ዋዜማ ምሽት ከዳዊት አሰግደው ጋር በየዝጉብኝ እየዞሩ ነበር ማንጋት የሚል ሃሳብ መጣባትና አውቶሞቢሏን ወደ ዳር አቁማ አቅጣጫዋን ወደ ዳዊት ቤት ለመቀየር አሰበች:: ዳዊት የዓለሚቱ መደበኛ ጓደኛ ነው:: እሱ የሚወዳትን ያህል ዓለሚቱም ትወደዋለች:: ዓለሚቱ ወንድ ጓደኞቿን በጥንቃቄ የመያዝ ብቃት አላት:: አትበለጥም:: ማንም ሰው የሰጠውን ያህል ብቻ መቀበል አለበት ባይ ናት::

«ዳዊት ሰሞኑን ጉንፋን ይዞኛል ብሎ ብቅ አላለም:: ከአልጋ አስነስቼ በየዝጉብኝ (በየሴክሬቶ) እንዙር ስለው <ለምን> ቢለኝ ምን እለዋለሁኝ» የሚል ጥያቄ ለራሷ አቀረበች:: የጥያቄውን መልስ ማግኘት ስላቃታት እንደገና ዐሳቧን ለውጣ ወደ ቤቷ ለመሔድ ወሰነች::

ዓለሚቱ ዳዊትን ለማግኘት የሻቀለ ስሜቷን ገታ አድርጋ፣ ነገ ከመዝገብ ቤቱ ሹም ጋር ስለምታሳልፈው ሌሊት አሰበች::

«ነገ ማታ ሁሉ ነገር አልቆ ሰነዶቹን ከተቀበልኩ በኋላ ዳዊት በድንገት ከተፍ ብሎ ለምን አይገላግለኝም» የሚል አዲስ ሴራ ከዳዊት ጋር ለመሸረብ ዳዳት:: ይህን ሴራ ተግባብቶ ለመዶለት ዓለሚቱ ምስጢሯን ለዳዊት ማካፈል ግድ ሊሆንባት ነው:: ይህንኑ ስታወጣ ስታወርድ ቤቷ ደረሰች:: እንደገባችም ስልክ ወደ ዳዊት ደውላ ነገ ጧት በጥብቅ እንደምትፈልገው ነገረችው::

***

*<u>ዝጉብኝ</u>፡- አንዳንድ የቀድሞ መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሚስቶችና ቁባቶች መሶብ ቤት በማለት፣ ዓይነቱ የበዛ፣ ጣት በሚያስቆረጥም መዘያ (ወጣ ወጥ) የሀገር ባሕል ምግብ የሚነግዱበት፣ የምሽት አዝማሪ እያዘፈኑ የአልኮል መጠጦችን በውድ ዋጋ የሚቸበችቡበት፣ ለተራ ሰው ዝግ የሆነ፣ መኪና እንደ ልብ የሚያስቆም ግቢ ያለው ቪላ ነው:: አንዳንድ ጉዳይ አስፈፃሚዎች የደርግ አባላትን፣ ከፍተኛ ካድሬዎችን፣ የመንግሥት ታላላቅ ባለሥልጣኖችን በቀጠሮ የሚያስተናግዱባቸው ልዩ ዝጉብኞችም አሉ:: እነዚህ ቪላዎች ሴክሬቶም በመባል ይታወቃሉ::*



***

በማግስቱ፣ ዓለሚቱ ሱሪ ታጥቃ፣ በነጭ ሸሚዝ (ብሉዝ) ላይ ቴሬኳር (ጉርድ ካፖርት) ደርባ፣ ጠቆር ያለ መነፅር ሰክታ፣ ዱቤ ከልል ዓይነት ኮፍያ ደፍታ፣ እጅግ ውድ ከሆኑት ሽቶዎቿ ሁለቱን ጡት መያዣዋ ላይ፣ አንገቷ ሥር፣ ኮቷ ኮሌታ አካባቢ እርከፍክፋ፣ ጥርሷን በኮልጌት አሳምራ ቦርሻ፣ ዓይንና ቅንድቧን ባልደመቀ ኩል ነካ ነካ አድርጋ፣ ተረከዙ እጠር ያለ ልጥፍ ጫማ ተጫምታ፣ ፎርድ ታወነስ አውቶሞቢሏን ነዳጅ ሞልታ በጊዜ ወጣች:: ለጊዜው መድረሻዋ አራዳ ጊዮርጊስ እንዲሆን ወስናለች::

የቀስተዳመናው ምግብ ቤት ቀጠሮ ሰዓት እስኪቃረብ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ቆየች:: ደንገዝገዝ ሲል ሞቢል ነዳጅ ማደያ አጠገብ ካለው አደባባይ እስከ አፄ ምኒልክ ሐውልት ባሉት መንታ መንገዶች ላይ እየነዳች የመዝገብ ቤት ሹሙን ፍለጋ ያዘች:: በዚያ አጭር ርቀት አምስት ጊዜ ያህል በሙሽራ ጉዞ ዝግ በማለት ከነዳች በኋላ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከአሥር ደቂቃ ሲሆን፣ የመዝገብ ቤት ሹሙ ሻንጣ-አከል የቆዳ ቦርሳ ይዞ ከፍ/ቤቱ ግቢ ሲወጣ አየችው::

ሴይቼንቶዎች (ታክሲዎች) መንገደኛ ከሚያሳፍሩበት ኬላ ቀረት ባለ የመንገዱ ጠርዝ ላይ ቆማ ጠበቀችው:: እርሱም ዓይቷት ኖሮ፣ ጊዜ ሳያጠፋ የመኪናውን በር ከፍቶ ጥልቅ አለ::

ዓለሚቱ ሽቅብ በበላይ ዘለቀ መንገድ መኪናዋን ረገጠች:: ለእጅ እንኳ ሰላምታ ጊዜ አልነበራቸውም:: ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ እስኪደርሱ «እንዴት ዋልክ! እንዴት ዋልሽ» ከማለት ያለፈ ቃል አልተነፈሱም:: ከኋላ አባራሪ የተከተላቸው ይመስል ተንደርድረው ቀስተዳመና ምግብ ቤት ግቢ ጥልቅ አሉ:: ጨለም

ካለው የግቢው ግራ ክንፍ አካባቢ ታምነሷን ከገረገደች በኋላ ፊቷን ወደ እንግዳዋ አዙራ ድምፅ ሳይወጣት መነጽሯን አንስታ ፈገግ አለች:: እሱም ምንም ሳይናገር ፈገግ እያለ አንገቱን ወደ እሷ አዝምሞ ግራ እጁን በትከሻዋ ላይ አሳለፈ:: የተነፋፈቁ፣ ፍቅር የተራቡ ከናፍር የላይታች ፊታቸውን በዝግታ ያዙ:: እሱ ወደ እሷ፣ እሷም ወደ እሱ ዘመሙ! ከመኪናው መሪ የተረፈውን ቦታ በእቅፍቅፍ ተጨማምቀው ያዙት:: ሁለቱም ትንፋሽ ሲያጥራቸው አየር ስበው ወደ የወንበሮቻቸው ቀና አሉ::

«ታዲያስ ደህና ውለሻል?»

«እኔስ ደህና ውዬ ነበር፣ ባንድ ምት አሁን ነፍሴን ሰማየ ሰማያት ላካት እንጂ» አለች ዓለሚቱ በሰዛ ለሆነው ሁሉ መርካቷን በሚገልጽ ፈገግታ::

«እኔ ምን ልበል! የታኘኩት?»

«ገና ትዋጣለህ፣ ምኑን አይተኸው!»

«ማ ማንን እንደሚውጥ እናያለን::»

«ዓለሚቱ ሁንዴ ሴት ነች□ኮ! በሴትነቷ የምትመካ! በእንብርክክ የምታስኬድ ሴት!» ብላ ለፉከራዋ በሚስማማ ትህትና ጀርባውን ቸብ ቸብ አደረገችው:: የምግብ ቤቱ አሳላፊ (ቦይ) ትዕዛዝ ለመቀበል አሰፍስፎ መቆሙን ያዩት ዘግይተው ነው::

«አንድ በያይነቱ፣ አንድ ጥብስና አንድ ክትፎ ለብለብ ከሁለት ሜታ ቢራ ጋር» ዓለሚቱ አዘዘች::

«ዛሬ የኔ ግብዣ ነው»

«አይሆንም ይህ የኔ ግብዣ ነው፣ የአንተን ማታ ትጋብዘኛለህ» አለች ጭኑ አካባቢ በቀኝ እጅዋ መታ አድርጋ::



የዓለሚቱ አነጋገር በደምስሮች ውስጥ ትኩስ፣ በፍቅር ስሜት የተንተከተከ ደም ለቀቀበት:: ትክነቱን መቋቋም ስላቃተው ግራ እጁን በትከሻዋ ላይ አሳልፎ የመጎተትና የመጭመቅ ያህል አቅፎ፣ አምስቱን ጣቶቹን በጡት መያዣዋ ላይ አሳርፎ ዝም አለ::

ዓለሚቱ አንገቷን ቀና አድርጋ ወደ ከናፍሩ ጉዞ ስትጀምር በዩ መጣባቸውና ወደ ነበረችበት መለስ አለች::

«ደንቃራ» አለና እሱም እጁን ሰበሰበ:: እራታቸውን እሱ በእሷ እጅ፣ እሷ በእሱ እጅ በልተው፣ ቢራቸውን ደግመው ሒሳቡን ዓለሚቱ ሸፈነች::

«ለሰጪ እግዜር ይስጠው፣ ለንፉግ ልብ ይሰጠው ነው! የሚባለው?» አለ::

«በንፉግነት ለመታማት ገና ነህ፣ ክዚህ በኋላ ያለው ግብዣ ያንተ፣ የቦታውም ምርጫ ያንተ እንዲሆን እፈቅዳለሁ::»

«እንዳልሽውም ግብዣው የእኔ ይሁን፣ ቦታውን ግን አንቺ ብትመርጪ!»

«በእኔ ምርጫ ትስማማለህ?»

«መቶ በመቶ ነዋ!»

«ታዲያ ለምን እንደልባችን እንድንሆን እቤት አንሔድም?»

«አንቺ ካልሽ ይሁን ግን - - - »አለና ዝም አለ::

«አታስብ፣ ሥጋትህ ገብቶኛል:: ባለፈው ያጫወተኩህን ምስጢር ታስታውሳለህ፣ ጓደኛ አለኝ:: ለሥራ ራቅ ወዳለ ቦታ ሔዷል:: ምናልባት ቶሎ መጣ ቢባል የሚቀጥለው ሳምንት ይሆናል:: እንዳጋጣሚ ቢመጣ እንኳ <የለችም፣ ግቢ ሔዳለች>

ከተባለ ከአጥር ውጭ ነው የሚመለሰው፣ የራሱ መኖሪያ ቤት አለው» በማለት አሳመነችውና ጉዞ ወደ ዓለሚቱ ቤት ሆነ።

ዘበኛው የዓለሚቱን መኪና ጡሩንባ አጥርቶ ያውቃል። ገና የመጀመሪያውን ድምፅ ሲሰማ በር መክፈት ይጀምራል። ወደ ግቢ የምትገባው በመጣችበት ፍጥነት ተንደርድራ ነው።

ቤቱን እንዲመጥን ረዘም ብሎ በተገነባው አጥርና በአትክልት ሥፍራው አለፍ አለፍ ተብለው የተተከሉት መብራቶች በጊዜ በርተው ግቢውን አድምቀውታል። ዓለሚቱ ውጭ አምሽታ ከሆነ እስክትመጣ፣ ወይም ከእሷ ጋር የሚያመሽ እንግዳ እቤት ካለ እስኪሔድ የግቢውና የበረንዳ መብራቶች በሙሉ ፏ እንዳሉ ያመሻሉ። ዓለሚቱ የኢትዮጵያ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ባልደረባ እንደመሆኗ የወርሃዊ ፍጆታ ክፍያ አያሳስባትም። (የባለሥልጣኑ ባልደረቦች በወር እስከ ሃምሣ አንድ ብር ድረስ በነፃ የመገልገል ድጎማ ይደረግላቸዋል።)

የዓለሚቱ መለስተኛ ቪላ፣ ስፊ ግቢ ለማስተረፍ ሲባል፣ ወደኋላ በጣም ጠጋ ተደርጎ ነው የተገነባው። ለማብሰያ፣ ለመጋዘን፣ ለሠራተኛ ማደሪያና የውጭ መጸዳጃ ቤት (ሰርቪስ) በ «L» ቅርፅ በምሕንድስና ሙያዊ የቦታ አጠቃቀም ዘዴ መገንባት ግቢውን ተጨማሪ ውበት አጎናፅፈውታል። የግቢው ስፋት 3000 ካ/ሜትር ገደማ ነው።

በዚህ ስፊ ግቢ ውስጥ ዓለሚቱ «ቤሳ» ደን የምትለው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ አለ። የባሕር ዛፍ፣ የኮሶ፣ የዝግባ፣ የወይራ፣ የጥድ፣ የአጣጥ፣ የውልክፋ፣ የግራር ዛፎች የግቢውን ቀኝ ክንፍ ይዘዋል። በነዚህ ዛፎች ውስጥና ዳር ዳር ድግጣ፣ ኮሽም፣ ጡንጅት፣ አጋም፣ ቀጨሞ፣ ምስርች፣ እንጆሪ፣ ቀጋ የመሳሰሉት



ቦታ ተሰጥቷቸዋል። እነዚህና ለሎቹም የአበባ፣ የሣርና የቅጠላ ቅጠል፣ የዛፍ ችግኞች፣ በየተመደበላቸው ቦታ የሚተከሉት፣ ከላይ በዳስ ከታች በጆንያ ተተግነው፣ ከጉርድ በርሜል እስከ ላስቲክ ከረጢት ባለ ዕቃ ውስጥ ከፀደቁ በኋላ ነው።

ሁሉም የዛፍና የቅጠላ ቅጠል ችግኖች በቁመትና በውፍረት ረዝመውና ፋፍተው ለደን የተመደበውን ቦታ እንዳይሸሙ በጉንደላ፣ በምልመላ፣ በግርዛትና በመታረቅ ይገራሉ።

ዓለሚቱ ከብሔረ ጽጌ ድርጅት ጋር የመሠረተችው የቅርብ ግንኙነት የራሷን ሚጢጢ ብሔረ ጽጌ ለመፍጠር ረድቷታል።

ከዛፍ እስከ ሣር ያለው የዓለሚቱ ግቢ ተክል ዓይነቱ፣ ዘርያው፣ ዕድሜው፣ ጥቅሙና አገልግሎቱ፣ ባሕሪው፣ ሌላውም መለያው በባሕር መዝገብ ሠፍሯል። ተክሎቹ የሚለሙት በተፈጥሮ ማዳበሪያ የዶሮ ኩስ፣ በጠጥ፣ ፋንዲያ፣ ፍግ ነው።

በስድሳ ሜትር ጥልቀት ጊቢዋ ውስጥ ተቆፍሮ የተገኘው የጉድጓድ ውሃ ተገቢው ምርመራ ተደርጎለት ለመጠጥ ጭምር ጥቅም ላይ የሚውል ለመሆኑ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል።

ሁለቱ አትክልተኞች ከዘበኛው ጋር በመተጋገዝ የሚያከናውኑትን ተግባር ዓለሚቱ በሳምንት ሁለት ቀን ሐሙስና እሁድ ትከታተላለች፣ ትቆጣጠራለች።

ለባልና ለልጅ ቤተሰባዊ ፍቅር ለጥቶ ለመቀበል ባትታደልም፣ ዓለሚቱ እምብዛም ካልተለመደ ሌላ ምንጭ አስርጸዋለች። በዚህም ለየት ባለ ተግባሯ ትሁት ኩራት እንዳላት ታሳያለች።

ከታዛ እስከ መኝታ ክፍል ያሉት የቪላው አገልግሎቶች የዓለሚቱን ወግ አጥባቂነት እንዲገልጹ ታስቦ የተደራጁ ይመስላሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ በሳሎንና በምግብ ቤት የሚታዩት የሞዝቦልድ የምግብ ጠረጴዛና ወንበሮች፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ውብ ምንጣፎች ዓለሚቱ አክራሪ ወግ አጥባቂ ላለመሆኗ አውራ ምስክሮች ናቸው::

ዓለሚቱና እንግዳዋ ግቢ እንደገቡ የድመት አውራ የሚያካክሉ ሁለት ደንክ ውሾች ተቀበሏቸው:: እንግዳው በመብራቱ ድምቀት፣ በአትክልቱ ሥፍራ ውበት ቀልቡ ተሳበ:: ግራ ቀኝ፣ ፊትና ኋላ እየተሽከረከረ «መለስተኛ ቤተ መንግሥት» አለ ዓለሚቱ እንድትሰማው ወደ እሷ ቀረብ ብሎ::

«ግባ! ሌላ ጊዜ በቀን በደንብ ታየዋለህ» አለች ለግቢዋ የተቸረውን አድናቆት በትህትና በመቀበል::

ዘበኛው ከእንግዳው እጅ የቆዳ ቦርሳውን እንዲቀበል ካንገት በላይ ባለ የዓይንና የግንባር የፊት ምልክቶች ዓለሚቱ ትዕዛዝ ሰጠች:: ሮንዳስ እጅ እንደሚነሳ ሰው ከወገቡ አጥፍ፣ ከአንገቱ ዝንጥፍ ብሎ ወደ እንግዳው ተቻኮለ:: የዘበኛውና የእንግዳውን ቦርሳ ልቀቅ አለቅም ግብግብ ያየችው ዓለሚቱ «እንዴ ኧረ ባክህ ልቀቅለት» አለች ሽክሙ እንዳይከብደው ያዘነችለት ይመስል::

«ግድ የለም?» አለ እንግዳው የመመንጨቅ ያህል ቦርሳውን ከሮንዳስ እጅ አላቅቆ::

ወደ ሳሎን ገብተው ቁጭ ከማለታቸው በፊት «ትንሽዋን ቤተ መንግሥት ላስጎብኝህ!» አለች ዓለሚቱ ቀደም ሲል እንግዳው የሰጠውን አስተያየት በሚያስታውስ ለዛ::



እንግዳው ቦርሳውን እንደተሸከመ ዓለሚቱን ተከተለ:: መጀመሪያ ስተት ብለው ወደ ዋናው መኝታ ክፍል ገቡ:: የመታጠቢያ ቤቱን በር ከፍታ «ግባ-መጣሁ» ብላ መለስ አለች::

«እውነትሽን ነው፣ ይህ የተበላ ቧንቧ ውሃ ይዞ መጥቷል መሰለኝ» በማለት የሱሪውን ቁልፍ ለመፍታት ቦርሳውን አልጋው ግርጌ ካለው ጠረጴዛ ላይ አኑሮ ገባ::

ዓለሚቱም ሌላውን መታጠቢያ ቤት ጎብኝታ ተመለሰች:: ክፍሎቹን ጎብኝተው እንዳበቁ «ቀጣዩ ምን ይሁን? መዝናናት! የመኝታ ቤት ቆይታ! ምረጥ! አለች ዓለሚቱ እንግዳዋ የልብልብ እንዲሰማው በሚጋብዝ ፈገግታ::

«ዋናውን፣ የመጣንበትን የቤት ሥራ ብናስቀድም ምን ይመስልሻል!» አለ እንግዳው ዓለሚቱ ስትጨነቅለት የስነበተችለት ጉዳይ የእሱም ጭንቀት ሆኖ መቆየቱን ለማመልከት::

«የጨዋ ልጅ እጁን ይጠማዋል! አይደለም እንዴ!» አለች ዓለሚቱ በርካታ የመጠጥ ዓይነቶች ወደ ተጫነው ጋሪ እያመራች::

ጋሪውን ገፍታ ወደ እንግዳው በማቅረብ «ኮኛክ፣ ውስኪ፣ ጂን፣ ባዙቃ፣ የግሪክ ኡዞ፣ ቮድካ፣ ከፈለክ ደግሞ ካማት የሚያዳሪ፣ በድግፍ የሚሔድ ጠጅ አለ» አለች ዓለሚቱ እንግዳዋን መጠጥም ፈገግታም እየጋበዘች::

አሰብ አደረገና «ቢራ ካለ በጀመርነው ብንቀጥልስ!» አለ እንግዳው::

እሷ ናቅ አድርጋ ዝርዝር ውስጥ ያልጠቀሰችውን ቢራ በመጠየቁ ደንገጥ አለችና ወዲያው «አምቦ ውሃም አለ ለውሃ

ጥም ከሆነ» አለች ዓለሚቱ እንደ ፍላጎቱ፣ እንደ ስሜቱ ልታስተናግደው ዝግጁ መሆኗን በማሳየት::

«መልካም! መልካም! ሌላውን ቀስ ብለን እንደርስበታለን» አለ እንግዳው::

አምቦ ውሃቸውን ይዘው ጎን ለጎን በመቀመጥ ከቦርሳው ውስጥ አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ ካስቀመጠው ፋይል ውስጥ ሠነዶቹን መረጡ:: የተመረጡትን ሠነዶች ከፎቶ ኮፒዎቻቸው ጋር አመሳክረውና ቅደም ተከተል አስይዘው በሌላ ፋይል አጋቡና ተረካከቡ::

ዓለሚቱም አጠገቧ ካኖረችው ቦርሳዋ ውስጥ አምስት መቶ ብር አውጥታ «ብድርክን፣ ውለታህን እግዚያብሔር ይክፈልህ:: ያንተ ውለታ በገንዘብ የሚለካ አይደለም» በማለት ሰጠችውና ይህ ደግሞ «ትንሽ ልጅ አለችኝ እናቷ ጥላት ስለጠፋች እናቴ እያሳደገቻት ነው ላልከኝ ሕፃን የወተት መግዣ ይሁን» በማለት ሦስት መቶ ብር እጁ ላይ ቁጭ አደረገችለትና ተሳሳሙ::

«ከሙሉ ጠርሙስ ነው የምንጠጣው» አለችና አንድ ብላክ ሌብል ውስኪ ከጋሪው ላይ አንስታ እንዲከፍተው ሰጠችው::

እንግዳው አልተግደረደረም:: ውስኪውን ከፍቶ በሁለት ብርጭቆዎች በመቅዳት አንዱን በሁለት እጆቹ ካንገቱ ሰገደድ ብሎ ሰጣትና ሌላውን አንስቶ «ለጤናችን» በማለት ብርጭቆዎቻቸውን አጋጩ::

ከዚህ በኋላ የቀረው የምሽቱ ፕሮግራም መኝታ ቤት ውስጥ እንዲሆን የቀረበውን ሀሳብ እንግዳው ሳያቅማማ ተቀብሎ ወደዚያው አመሩ::



ወደ መኝታ ቤት ከመግባታቸው በፊት ዓለሚቱ ሦስት የስልክ ጥሪዎች ነበሯት:: ለጥሪዎቹ መልስ የሰጠችው መኝታ ቤት ባለው ስልክ ነበር::

አራተኛው የስልክ ጥሪ ጭርር አለ:: ዓለሚቱ እንግዳዋን መኝታ ቤት አስቀምጣ የመኝታ ቤቱን በር በመዝጋት ወደ ሳሎን ገባች:: ከአጭር ቆይታ በኋላ ወደ መኝታ ቤት ተመልሳ «ጠጣ እንጂ!» ብላ ብርጭቆውን ወገቡ ድረስ ሞልታ በረዶ አጨቀችበት::

«ይገፍ! ይቻለሁ□ከ! እየሞቀኝ ነው» አለና ኮቱን አውልቆ ወንበር መደገፊያ ላይ ሰቀለው::

«ምናባቱ! በጣም ከሞቀህ ሸሚዙንስ፣ ሱሪውንስ፣ ሌላውንስ ለምን አታወልቀውም» አለች ዓለሚቱ ጀርባውን ቸብ አድርጋ እየሳቀች::

«እውነትሽን ነው! ጊዜው ሔዷል» አለና ሰዓቱን ገልመጥ አደረገ::

«ቢጃማ እንዴት ነው፣ ትወዳለህ?» አለች ዓለሚቱ ቁም ሣጥን እየከፈተች::

«ቢጃማ ለብሼ ተኝቼ አላውቅም:: ቢጃማ የምለብሰው እሁድና ቅዳሜ እቤት የምውል ከሆነ ብቻ ነው» አለ::

«እንደሱ ከሆነ ለዛሬ እኔም ይቅርብኝ» ብላ ዓለሚቱ ከመታጠቢያ ቤቱ ጋር ወደ ተያያዘው መልበሻ ክፍል በመግባት ልብሷን አወላልቃ በሙታንታና በጡት በያዣ ብቻ ብቅ አለች::

እሱም ተራውን ወደ መታጠቢያ ቤት በመግባት ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በሙታንታ ብቅ አለ::

«እንዴት ነው! መብራት?»

«ቢጠፋም ባይጠፋም በበኩሌ ግድ የለኝም» አለ እንግዳው::

«በቃ እንዳለ ይሁን» ብላ አልጋውን ገለጥለጥ አድርጋ በመግባት «ብትፈልግ በቀኝ፣ ብትፈልግ በግራ ያውልህ ተኛ» አለችው ሁለት ሜትር ስፋት አልጋዋ መኻል ተጋድማ::

እንግዳው ለዓለሚቱ ግብዣ መልስ ለመስጠት ግራ ቀኙን እየተመለከተ ከአልጋው ግርጌ ቆም አለ፣ ጆሮውን ጣል አድርጎ::

«አልጋው ካላስኘህ አማራጭ መጠቀም ትችላለህ» አለችው::

የመኪና ጡሩንባ አካባቢውን ሲሰነጥቀው ዓለሚቱ በመብረቃዊ ፍጥነት ከአልጋው ላይ ተወርውራ በመነሳት ቢጃማዋን አጠለቀች::

መስኮት ከፍታ «ስንዱ! ስንዱ!» በማለት ሠራተኛዋን ተጣራች::

ሮንዳሣ «እትዬ! እትዬ!» የሚል የጭንቀት ድምፅ አሰማ::

ዓለሚቱ ቁም ሳጥኑን ከፍታ እንግዳውን «ለጊዜው እዚህ ቆይ» በማለት ከቆለፈችበት በኋላ ወጣች::

ሮንዳሳን «በሩን ክፈት» ብላ ወደ መኝታ ቤት መለስ አለች::

የእንግዳውን ኮት፣ ጫማ፣ ሸሚዝና ሱሪ በየቦታው ተበታትነው ከተቀመጡበት ለቃቅማ ቁምሳጥኑ አናት ላይ ካለው የሻንጣ ማስቀመጫ ኪስ ውስጥ ከተተቻቸው:: የመጠጡን ጋሪና ብርጭቆዎቻቸውን ወደ ሳሎን ሸኝታ ወደ ታዛ (በረንዳ) ብቅ አለች::



ዳዊት መኪናውን ጋራዥ አቁሞ ሮንዳሳን «ለምን ቶሎ አልከፈትክም» በማለት እየገሰፀ ወደ ዓለሚቱ ቀረበ::

«ምነው እንደዚህ መሸብህ?» አለች ዓለሚቱ በተዘረጋው የዳዊት እቅፍ ውስጥ ለመግባት ጎደድ ጎደድ እያለች::

«ጤናም የለኝ፣ ብቻሽን በመከረምሽ ትናፍቂ እንደሆን ብዬ እንጂ፣ ከአልጋም መነሳት አልነበረብኝም» አለ ዳዊት ለከናፍር ስላምታ እያሞጠሞጠ፣ እሷም ወደ እሱ አስገገች:: እንደተቃቀፉ ሳሎን ገቡ:: አረፍ ብለው ዳዊት ስለ ክራሞቱ እሷም ስለ ናፍቆቷ ጭውውት ላይ እንዳሉ የቤት ሠራተኛዋ ሥንዱ ወደ ዓለሚቱ ቀረብ ብላ «ራት» አለች::

«እውነትሽን ነው ዳዊት ራት ብላ» አለች ዓለሚቱ::

«የለም ቢቀርብኝ ይሻላል፣ ገላዬን ተለቃልቄ ዘፍ ማለት ነው ያለኘኝ ደክሞኛል» አለ ዳዊት ወደ መኝታ ቤት ለመግባት እየተነሳ::

ተከታትለው መኝታ ቤት እንደገቡ ዳዊት ከአልጋው ግርጌ ባለው ጠረጴዛ ላይ ተጣጥፎ የተቀመጠውን የሌሊት ልብስ አንስቶ «ቢጃማ አዘጋጅተሽ ነው የጠበቅሽኝ» ብሎ ቢጃማውን ይዞ ወደ መልበሻ ክፍል ገባ::

«ብርድ እንዳይመታህ» ብላ ዓለሚቱ የመልበሻውን ክፍል በር ዘጋችበት::

ዳዊት ተለቃልቆ እስኪወጣ ምን ማድረግ እንዳለባት ቆም ብላ ባይዷ ታስብ ይመስል ጣራው፣ ግድግዳው፣ ወለሉና አልጋው ላይ አፈጠጠችባቸው:: የዓይኗን መንከራተት የእንግዳው ቦርሳ ሲያደናቅፈው «ወይ!» የሚል ድምፅ አሰማች::

ድንጋጤዋ ፈንቅሎ ያወጣውን ድምፅ የዳዊት ጆሮ ተቀብሎ ኖሮ «ምንድነው ዓለም?» አለ::

«ምንም አይደል ዕቃ አነሳለሁ ስል ከእጄ አምልጦኝ ነው» አለችው::

በርሳውን እንግዳ መኝታ ቤት ወስዳ ከጠረጴዛ ሥር ወርወር አድርጋ ወደ መኝታ ቤት ተመለሰችና አልጋው ጠርዝ ላይ ኩርምት ብላ በረዥሙ ተነፈሰች::

«ዓለም ምነው ድምፅሽ ጠፋ፣ አለሽ እንዴ? መጣሁ!» አለ ዳዊት ለዘግ ባለ ድምፅ::

«የት እሄዳለሁ! አለሁ» አለች ሳይታወቃት ድምጽዋን አድክማ::

«የአባቴ የሁንዴ ዓምላክ የሰው ሰው........ ወይኔ ዛሬ አየር አጥቶ ድብን ቢል ምን ይደረጋል?» ብላ ቀጥሎ የምትለው ጠፍቶባት ዝም አለች::

«ዓለም ለኔም ላንቺም ማርቲኒ ቀድተሽ ጠብቂኝ»

«ማርቲኒ ነው የራብህ?»

«ምን ያልራበኝ ነገር አለ! ሁሉም ነገር ነው የራበኝ::»

«አይዞህ አትቸኩል ትደርስበታለህ::»

«አዎ እውነትሽን ነው አሁኑኑ ደረስኩበት፣ ጨርሻለሁ መጣሁ» አለና ቁኝር ካለችበት ዓለሚቱን አቅፎ አነሳና ከእርጥብ ገላው ጋር በቁሙ አዋደዳት:: በመጠኑ የዓለሚቱ ጥማቱን ቸስ አደረገና አልጋው ላይ ወረወራት::

«እሽ የራስጌውን መብራት አብርተህ ይህንን አጥፋው» አለች ወደ ኮርኒሱ እያመለከተች::



«ከፈለግሽ አንቺ አጥፊ አብሪ፣ እኔ አሁን ለሌላ ትዕዛዝ ጊዜ የለኝም» ብሎ ቢጃማውንና የቤት ጫማውን ሲያወላልቅ ዓለሚቱ ተንጠራርታ መብራቱን አጠፋች::

ከዚያ በኋላ ያለው ጊዜ ከትንፋሽ በቀር ድምፅ የማይሰማበት ሌሊት ሆነ:: አይነጋ የለ እንደምንም ጎህ ቀደደ:: ዳዊት ቢ. ቢ. ሲ ራዲዮ ጣቢያን ለማዳመጥ መስመር ሲፈልግ ዓለሚቱ መታጠቢያ ቤት ገባች::

ተጠናቅቃ ወጥታ ከአልጋው ጠርዝ ገባ ብላ እንዳረፈች «ቁርስ ምን ይሠራልህ» እያለች በአንድ እጇ የውስጥ ገላ ጭጉኝ የመሰለውን የደረቱን ላይ ፀጉር ደባበሰችው::

«አንቺ የመረጥሽው::»

«የአልጋ መውረጃ የወንድ ምርጫ ቢሆን ነው የሚሻለው» አለች ዓለሚቱ ፊቷን ደረቱ ላይ ሽቅብ ቁልቁል እየፈተገች::

«ቁርስ እስኪበስል ሌላ ቁርስ» አለ በደረቱ ላይ ፊቷን ወደ ፊቱ እያቀና::

«ቶሎ ቁርስ አድርገን እነ አባባ ግቢ ትጥለኛለህ፣ መኪናዬ ድምፅ ስለምታሰማ ተመልሼ ጋራዥ እወስዳታለሁ::»

«ተነስ ነው የምትይኝ::»

«አዎ! በጧት ልሒድ::»

«ለምን የእኔን መኪና ይዘሽ አትሔጂም፣ እኔ ስልክ ደውዬ ከቢሮ ሌላ መኪና እንዲመጣልኝ ማድረግ እችላለሁ» አለ ዳዊት::

«የእነ አባባ ትርፍ መኪና ስላለ ከዚያ እወስዳለሁ ወይም ሾፌር ያደርሰኛል፣ ለማንኛውም አንተ ተነስ ለባብስ አለች» መቸኮሏን እያሳየች::

ዳዊት የዓለሚቱን መቸኮል በመረዳት ተለቃልቆ ጢሙንም ሳይላጭ ለባብሶ ምግብ ቤት ሔዶ ተሰየመ።

ስንዱ ገበታውን ሙሉ አድርጋ ተጨማሪ ትዕዛዝ ለመቀበል ጥግ ይዛለች።

«አሬ ክፍቱን ያደረ ዕቃ ዕቃ እንዳይል ነው እንጂ፣ እኔ□ኮ ሁልጊዜም ቁርስ ባልበላ ነው የምመርጠው» አለ ዳዊት።

«የአካል ቅርጽህን ለመጠበቅ እንደምትጨነቅ አውቃለሁ» አለች ዓለሚቱ ገበታው ላይ እየተሰየመች።

«አልተሳሳትሽም ዓለም» አለ ዳዊት።

ዓለሚቱም እሱም እንደነገሩ ይኸንንም ያንንም ለካከፈው የቁርሱ ገበታ ተነሳ።

ለመሔድ መኪናው ውስጥ ገብተው ከተንቀሳቀሱ በኋላ «አንድ ጊዜ ዕቃ ረስቼ እስክታዞር መጣሁ» ብላ ወደ ቤት ጣደፍ ጣደፍ አለች።

ወደ ቤት እንደገባች እንግዳው የተደበቀበትን ቁምሳጥን መክፈቻ ቁልፍ ለስንዱ ሰጥታ «በዚህ ቁምሳጥኑን ክፈችና እንግዳው ይውጣ። እኔ በአሥራ አምስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ እመለሳሁ። አልጠብቃትም እሄዳለሁ ካለ ቦርሳው ይኸውልሽ፣ ልብሱም ይኸው» ብላት ወደ ዳዊት ኩብ ኩብ አለች።

የዳዊት መኪና ከግቢ እንደወጣች ስንዱ ወደ ቁምሳጥኑ ተጠጋች። ቆም ብላ አዳመጠች። ድምፅ የለም፣ መክፈቱን ፈራችና እጇ ተንቀጠቀጠ። «ጋሼ የትኛው ቁምሳጥን ውስጥ ነዎት?» አለች በተሰባበረ ድምፅ።

እንግዳው መልስ ሳይሰጥ በማኮሻኮሽ ያለበትን ቁምሳጥን ጠቆማት። ስንዱ እንደምንም ብላ ቁምሳጥኑን ከፈት ስታደርግ



እንግዳው ተበለሻሽቶ ኖሮ ቤቱ በመጥፎ ሽታ ተመታ። በከፊል ጎሲናውን የሳተው እንግዳ ከቁም ሳጥኑ ውስጥ ግማሽ ራቁቱን ዝርግፍ አለና ወለሉ ላይ ተዘረረ።

ስንዱ በድንጋጤ የምትይዘውን አጣች። ወዲያ ወዲህ ተራወጠች። ከእልፍኙ በር ቆማ ሮንዳሰን ጠራችና የሆነውን ነገረችው።

«ታዲያ እኔ ምን ልርዳሽ?» አለ ሮንዳሳ።

«ተረዳድተን በሸክምም ቢሆን መታጠቢያ ቤት አስገብተን እናለቅልቀው። ቶሎም ነፍስ ከዘራና መሔድ ከፈለገ ሸኙት ብላለች እትዬ።»

በዚሁ ተስማምተው እንግዳውን መታጠቢያ ቤት አግብተው በቀዝቃዛ ውሃ ሲያጥቡት እንደመባነን ባለ ድምፅ «ሰውየው ሔዷል?» ብሎ ጠየቀ።

«አዎ ሔዷል! አንተ እንዴት ነህ?.... አይዞህ!» አለች ስንዱ ደገፍ አድርጋው።

ሮንዳሳ ምንም ሳይናገር አጣጥቦ በሸክም አወጣውና አልጋው ላይ በጀርባው ከአጋደመው በኋላ የዓለሚቱን ቡሉኮ አከል ጋቢ አለበሱት።

«እባካችሁ አድኑኝ፣ ከዚህ ቤት እንደምንም ብላችሁ አውጡኝ» በማለት ተማፀነ።

ስንዱና ሮንዳሳ ተያዩና ገለል ብለው ተንሾካሾኩ። ሮንዳሳ ሲይቼንቶ በኮንትራት እንዲ መጣ ሃያ ብር ሰጠችው። እስከዚያው እሷ ልብሱን አለባብሳ ደግፋ ወደ በረንዳ አወጣችው። ገና ከአውራ መንገድ እንደ ደረሰ የቀናው ሮንዳሳ ሲይቼንቶ ይዞ

ከተፍ አሉ፡፡ እንግዳው በድግፍግፍ ሲይንቼንቶ ውስጥ ገብቶ እንደተቀመጠ «የትኛው ሆስፒታል ነው?» አለ ሹፌሩ፡፡

«ቀረብ ካለው የትኛውም ሆስፒታል ብታደርሰኝ ይበቃኛል» አለ እንግዳው፡፡

ሮንዳሳና ስንዱ ታክሲዋን ሸኝተው «ጉድ! ጉድ!» እያሉ ወደ መኝታ ቤት ገቡ፡፡

«በይ እንግዲህ ይሄ ያንቺ ድርሻ ነው» አለ ሮንዳሳ ዳሌዋ አካባቢ በያዘው ቆመጥ ነካ አድርጎ፡፡

«በእናትህ እርዳኝና አብረን እናጽዳ» አለች ስንዱ በዓይኗ ጭምር እየለመነች

«ምን ታደርጊልኛለሽ?»

«የፈለግኸውን፡፡»

ሮንዳሳና ስንዱ በመተጋገዝ በመኝታ ቤቱ ጽዳት ላይ ተፍ ተፍ ሲሉ አለሚቱ ከተፍ አለች፡፡

ሮንዳሳ የመኪና ጥሩምባ ሲሰማ ከቤት እንደ ጥይት ተወርውሮ ወጣ፡፡



# ምዕራፍ 23

## የሴራው ጡዘት

ዓለሚቱ ባንድ በኩል መረጃዋን እያደነች በሌላ በኩል ውድ ወንድሟ ያለበትን ሁኔታ ዕለት በዕለት ትከታተላለች፡፡ በስልክ፣ በአካልና በግንባርም እየተገኘች ታጽናናዋለች፡፡ አንድ መልካም ቧት ከቢሮው ስልክ በመደወል ሠላምታ ከተለዋወጡ በኋላ «.....አባይና ስንቅ እያደር ይቀላል፣ እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል» የሚለውን የአባባ ጌቶችን አባባል ታስታውሳለህ? ስለዚህ ኀሊናህን የሚያቆስል በደል እስካልፈጸምክ ድረስ መጨነቅ የለብህም፡፡ ለማንኛውም ቅዳሜና እሁድ ሰፋ አድርገን የምንነጋገርበት ብርቱ ጉዳይ ስላለ ወደ ቤት ብቅ በል» በማለት በክትትል የደረሰችበትን መረጃ ብልጭ በማድረግ በመጠኑም ቢሆን ከጭንቀቱ ልታሳርፈው ሞከረች፡፡

ዓለሚቱና አሰገደች አይትና ምራት ብቻ አልነበሩም፡፡ ---- «አባብ ለአባብ ይተያያል ካብ ለካብ እንዲሉ፣ አንዷ የሌላዋን አፍ አልፌት ሲጠባበቁና በጥርጣሬ ሲተያዩ ነው የኖሩት፡፡ ባለፈው ጊዜ ክፉኛ ተጋጭተውበት በነበረው የአፍ ሳቻ «ይቅር ለእግዚአብሔር» ተባብለዋል፡፡

***

«ዓለሚቱ ከሣሎኗ አረፍ ብላ ከዚህ በኋላስ ክትትሉ በምን አቅጣጫና እንዴትስ ይቀጥል? ለመሆኑ! እንደ ማርያማዊት

የተቀሩትስ ሦስቱ የአስገደች ልጆች ከወንድሜ አብራክ የተከፈሉ ለመሆናቸው ምን ማረጋገጫ ይኖራል?» በማለት አሰላሰለች::

መሰስ አድርጋ ደግሞ «ወንድሜ ይህን ያለቀለት፣ እሸት የሆነ ማስረጃ እጁ ላይ ዱብ ሳደርግለት ተናድዶ የኃይል ርምጃ ቢወስድስ?» የሚል ሥጋት ሹጣባት፣ ሥጋቷ ነፍስ እየዘራ እየገዘፈ ሄደ «በዚህ መኻል የሰው ሕይወት ቢጠፋስ? እም! እም! ነገሩ አሁን ከእኔ አቅምና ችሎታ በላይ የሆነ ይመስለኛል:: በልምድም፣ በሙያም ከእኔ ላቅ ያሉ ሰዎችን ማማከሩ ተገቢ ስለሆነ ቅዳሜ ከዮሐንስ ጋር ከመገናኘታችን በፊት፣ ይህን የቤት ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርብኛል» ወደሚል ውሳኔ ላይ አደረሳት::

የምስጢር ሰነዶቿን በቁም ሳጥን ውስጥ በሚቀመጡ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ጌጣጌጦች ማስቀመጫ ልዩ ሣጥኗ ውስጥ ቆልፋ አኑራለች:: የቁም ሳጥኑን ቁልፍ በሌላ አዲስ ቁልፍ የሰወጠችው መረጃዎች በእጇ በገቡ ማግሥት ነበር::

***

ቀኑ ማክሰኞ ከሰዓት በኋላ ነው:: ስልክ ጭርር ሲል ዓለሚቱ እጀታውን አንስታ «አስተዳደር አገልግሎት» አለች:: ከ2-3 ሴኮንዶች ማዳመጥ በኋላ «ሶስና እኔ አላምንም፣ አዲስ አበባ ነው ያለሁት እንዳትይኝ ብቻ!» ብላ ከወዲያኛው የስልኩ ጫፍ የሚነገረውን ስታዳምጥ ከቆየች በኋላ «ደህና! ደህና መጣሁ! መጣሁ!» ብላ ቦርሳዋን አንጠልጥላ ወደ መኪናዋ ጡብ ጡብ አለች::



ሶስና የዓለሚቱ «ሀደ-መላ» (የመላ እናት) ነች:: እሷ የቋጠረችው አይፈታም፣ ሌላው የቋጠረውን ለመፍታት ግን ጊዜ አይወስድባትም::

ሶስና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባልደረባ ስትሆን በሥራ አሥመራ ተመድባ በማገልገል ላይ ነች:: ወደ አዲስ አበባ የመጣችው የተጠራቀመ የእረፍት ጊዜዋን ወስዳ ከቤተሰቦቿ ጋር ለመቆየት ነው::

***

አንዳንድ የአስገደች ዘመዶች እራሷ ያልጠየቀችውን ምክርና አስተያየት መለገስ የጀመሩት ገና ከጧቱ ቢሆንም እምብዛም ቦታ አልሰጠቻቸውም:: የዮሐንስና የአስገደች የግል ገንዘቦች ስለሆኑ ውስጣዊ ባሕሪያት አንዳችም ነገር ሳያውቁ፣ እሷን ቅድስተ ቅዱሳን፣ እሱን እርኩሳተ እርኩሳን፣ ለማስመሰል የሞከሩትን ሁሉ አስ ገደች «የደናቁርት መላ ምት» በማለት ታዝባለች::

የማሪያማዊትን ከጋብቻ ውጭ መወለድ በማንም፣ በተለይ በዮሐንስ ዘመዶች ሳይነቃባት ሽፍን ክድን አድርጋ በፈፀመችውና ባስፈፀመችው ቁምነገር ከፍተኛ ርካታ ብታገኝም፣ ገና ባልተረጋገጠው የዮሐንስ ወንጀል ላይ መረባረቡ ኅሊናዋን እያስጨነቀው መጥቷል:: የዮሐንስ ከሚችለው በላይ መጫን፣ የሌላውን ገመና ለማየት ሲያንነብሱ የራስ ገመና ይጋለጣል እንደተባለው እንዳይሆን ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረጉ ይመረጣል:: ያለዚያ በምቆፍረው ጥልቅ ጉድጓድ እኔው ራሴ.........» ብላ ዓይኗን ጭፍን አደረገች::

ዮሐንስ በጋብቻው ላይ ደቀሰ በሚል ክስ እሱን ከንብረቱ ሙልጭ አስወጣለሁ ብዬ ስዋትት፣ እኔው እራሴ ሙልጭ ወጥቼ እንዳልቀር የሚሰውን ሥጋቷን እያፍተለተለች ከሥዕል ቤት ወደ ሳሎን ወጣች::

* * *

«ጆ! ቡና ይፈላልህ?» አለች አስገደች በሳሎን አንደኛው ጠርዝ ላይ ገና የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ባካበታቸው መጻሕፍት መደርደሪያ አጠገብ ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ወደሚያገላብጠው ባለቤቷ እየቀረበች::

«ይሁና» አለ ዮሐንስ ቀዝቀዝ ባለ የአካልና የድምጽ ኅብር::

«ድንቅ የስለላ ፊልም ተውሼ አምጥቻለሁ፣ ለምን አሁን አብረን አናየውም?» አለች አስገደች አለወትሮዋ ወደ ዮሐንስ በጣም ቀረብ ብላ::

«ፕሮጀክተሩን ተስፋዬ አልወሰደውም እንዴ?» ዮሐንስ ዓይኑን ከሚያነበው መጽሐፍ ላይ ሳይነቅል ነበር ይህን ጥያቄ የሰነዘረው::

«ነገ ነው የሚወስደው» አለች ፈጠን ብላ::

«ልጆቹ በሌሉበት?» ዮሐንስ ቀና ብሎ ጠየቀና አስገደችን እንደ እንግዳ ከላይ እስከታች ተመለከታት::

«ልጆቹ የስለላ ፊልም ምን ያደርግላቸዋል? ካሰኛቸውም ባመቻቸው ጊዜ ሊያዩት ይችላሉ» ለሚለው የአስገደች መልስ አፀፋ መስጠቱ አስፈላጊ ስላልመሰለው እንደመጎተት ባለ ቀስታ ወደ ሶፋው አመራ::



«የስለላ ፊልም ለእኛስ ቢሆን ምን ያደርግልናል? ከስለላ ሥራ ጋር ምን ጉዳይ አለን?» አለ ዮሐንስ ግብዣውን በተፅዕኖ መቀበሉን በሚገልጽ አነጋገር::

«ስለስለላ ፊልም ዲስኩር እንድሰጥ መጠየቅህ እንዳልሆነ ተስፋ አለኝ» አለች አስገደች ረጋ ብላ::

ባልና ሚስት የፊልሙን አስደናቂ ትዕይንት በመከታተል ላይ እንዳሉ ዓለሚቱ ስልክ ትደውላለች:: አስገደች የስልኩን እጀታ ብድግ አድርጋ - «ሀሎ» አለች::

«አስገደች እንዴት ነሽ፣ ዓለሚቱ ነኝ»::

«አ ደህና ነሽ! ምነው ጠፋሽ?» የአስገደች አፀፋ ሰላምታ ነበር::

«ሥራ በዝቶብኝ ነው:: ጆኒ አለ?»

«አዎ አለ!» አለችና ለዓለሚቱ ጥያቄ መልስ ከሰጠች በኋላ ወደ ዮሐንስ መለስ ብላ ዓለሚቱ ትፈልግሃለች» በማለት የስልኩን እጀታ ለዮሐንስ አቀበለችው::

«ታዲያስ ቀሮ! ባገር አለሽ እንዴ» አላት (ቀሮ የዓለሚቱ የቤት ስሟ ሲሆን ብልጥ እንደማለት ነው::)

«ማንን ለማስደሰት ነው ቀሮ የምትለኝ? እኔ ዓለሚቱ ሁንዴ ነኝ:: የደወልኩት የበቀደሙን ቀጠሮ ለማስታወስ ነው:: ነገ ምሳ አብረን በልተን! የከሰዓት በኋላ ጊዜህን በሙሉ እፈልገዋለሁ፣ እኔ እቤት እንገናኝ እስከዚያው ደህና ሁን!» ብላ መልስ ሳትጠብቅ ስልኩን ዘጋች::

ዓለሚቱ፣ ታላቋን ዮሐንስን ከፍቅሯ የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ብኩርናውን አታከብርለትም::

ጋሼ ዮሐንስ ማሰት ሲገባት ጆ! ጆኒ! የሚሉትን ቁልምጫዎች እንዳሰኛት እያቀያየረች ነው የምትጠራው::

«የቆሎ ጓደኛሽ አደረግሽኝ□ከ!» ይላል እሱም ቁልምጫዋ፣ የእህቱ የፍቅሯ መግለጫ መሆኑን «ተገንዝቤልሻለሁ በሚል ፈገግታ::

አሰገደች የወንድምና እህት መሞካሸት በሰማች ቁጥር ፊቷ በተለይም ግንባሯ መስመሮችን ይዘረጋሉ:: «የምን ጋጠ-ወጥነት ነው?» ትላለች ባለቤቷ የሚገባውን ከበሬታ መነፈጉ ያስቆጫት ይመስል::



# ምዕራፍ 24

## ዓለሚቱ ቤት-አጸፋ ሴራ

«ጥቂት እንግዶች ትልቅ ግሩም ምሳ» አለ ተስፋዬ የዓይነቱን ብዛት ጣት ከሚያስቆረጥመው ጣዕሙ ጋር እያገናዘበ::

«ባለቤትን ቢጨምር ኖሮ የበለጠ ድንቅ ይሆን ነበር» አለ ዮሐንስ እህቱን እንድትናገር በሚቀሰቅስ ስላቅ::

«ለእንጀራ እናቴ ያልኩትን እናቴ ብትበላው ደስ አይለኝም፣ ተግባባን! ወንድም ዓለም» አለች ዓለሚቱ በተለመደ ጠረባዋ::

«ወ/ሮ ሶስና የሚያክሉት ካለ?» አለ ተስፋዬ ወደ ሶስና ማይክሮፎን ይዞ የቀረበ ይመስል፣ ጭብጡን ወደ አፏ ጠጋ አድርጎ:: ቀልዱ የገባት ሶስና «በዓለሚቱ ግብዣ..... ጋባዧ ከለጠችው ሌላ አስተያየት ሊኖረኝ አይችልም» አለች በትህትና::

«የሆነ ሆነና የምሳው ምክንያት ምንድነው?» የዮሐንስ ጥያቄ ነበር::

«ምሳው ምሳ ነው፣ ቁምነገሩ ሌላ ነው» አትቸኩል፣ አይዞህ ትደርስበታለህ አይቴ አሰገደች እንዳትቆጣ በጊዜ እንለቅሃለን» አለች ዓለሚቱ እንደ ጂሌት ምላጭ በሚሞለጭ የሥላች አነጋገሯ::

«ነገሩ ምንድነው-------?» ዮሐንስ ተናግሮ ሳይጨርስ፣ «ነገሩ እንዲህ ነው? አሁን ወደ ቁምነገሩ እንመለስ» አለች ዓለሚቱ ወደመኝታ ቤቷ ገባ ብላ አንድ ተለቅ ያለ ካኪ ፖስታ ይዛ በመምጣት::

«እዚህ ፖስታ ውስጥ ያሉትን ሠነዶች በጋራ እናነብባቸዋለን፣ ከዚያም እንመረምራቸዋለን፣ ግን በቅድሚያ ከቅርብ ቀናት ወዲህ በወንድሜ ቤት ድንገት የገባውን ቀንዳም ሰይጣን ቀንዱን ለመስበር የመጀመሪያውን ስንዘራ እኔ ብቃጣም ሌሎቻችሁም ድርሻ እንደሚኖራችሁ ላሳስባችሁ እወዳለሁ» ብላ ማብራራቷን ቀጠለች....

«ባንድ በኩል ሽዋዬ፣ በሌላ በኩል ውድ ባለቤትህ ወ/ሮ አለገደች ባልሠራኸው ወንጀል ኃጢአተኛ ሊያደርጉህ እየተፍጨረጨሩ ናቸው:: ይኸን ጉዳይ ባላሰለስ ጥረት ተከታታዬ ከአንተ ይልቅ ወንጀለኞቹ እነርሱ ሁለቱ ሴቶች መሆናቸውን የሚያረጋግጠውን መረጃ በእጄ አስገብቻለሁ:: ቀሪዎች ካሉ አብረን ዕናድናቸዋለን» በማለት ተናግራ ስታበቃ ፖስታው ውስጥ ያሉትን ሠነዶች አውጥታ ቅደም ተከተል ከአስያዘች በኋላ እንድታነባቸው ለሶስና ሰጠቻት::

ሶስና ሁሉም ሊያዳምጣት በሚያስችል ድምፅ አንብባ ስትጨርስ፣ ዮሐንስ ድንጋጤው በግልጽ እስኪታወቀበት ድረስ የሚሆነውን አጣ:: ብድግ ለማለት ሞክሮ አቅሙ ከዳውና ተመልሶ ተቀመጠ::

«ዮሐንስ» አለች ዓለሚቱ ናር ባለ ድምፅ «ዮሐንስ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ኋላ የምታፈገፍግበት ጥግ የለህም:: የመንቀሳቀሻው ክፍት ቦታ አልቋል:: የመሸሺያ ሥፍራ አታገኝም:: ከዚህ በኋላ የሚጠብቅህ የሞት ሽረት ትግል ነው:: ሁለቱ ሴቶች አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ባጋጣሚ ቅሌታቸውን፣ ወንጀላቸውን፣ ውርደታቸውን እፍረታቸውን በሙሉ ያንተ አድርገውታል:: ከአራታችን ሌላ አንድም ተጨማሪ ረዳትና



አማካሪ ሳያስፈልገን አስገደችና ሽዋዬ ለጊዜው ያሸከሙህን ወንጀል እንደየድርሻቸው መልሰው ራሳቸው አጋሰሶቹ እንዲሸከሙት ማድረግ አለብን:: አማራጭ የለንም፣ በሕግ አደባባይ የአንተ ነፃነት ታውጆ የእነሱ ወንጀል መጋለጥ አለበት:: ይህ ደግሞ ለነገ የሚባል ርምጃ አይደለም:: ነገ በጣም ነው የሚዘገየው:: ዛሬ ከዚች ደቂቃ ጀምሮ ቀጣዩን ርምጃ እንወስዳለን» በማለት ወንበሯን አስተካክላ ተቀመጠች::

የቁጭት እሳት በላያቸው እየነደደ ዓለሚቱን ላለማቋረት ፀጥ ብለው የነበሩት ሦስቱ እድምተኞች (ሶስና፣ዮሐንስና ተስፋዬ) ዓይናቸውን አፍጥጠው በአንድ ጊዜ መናገር ጀመሩ::

«ግድ የለም እንደማመጥ ረጋ በሉ» አለችና የመናገር ቅድሚያውን ዮሐንስ እንዲያገኝ ባንገቷ ንቅናቄ ቀጥል አለችው::

«አስገደች፣ ማርያማዊትን ከዶ/ር ወ/ሚካኤል ማዴቦ ነው የደቀለቻት፣ ከአንተ አብራክ የተከፈለች አይደለችም፣ የእንጀራ ልጅህ ናት ነው የምትይኝ?» አለ ዮሐንስ የሰማውን ሁሉ እንደ ቅዠት በመቁጠርና ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ለመንቆራጠጥ እየቃጣው::

እንደ መሳቅም እንደ መናደድም እየዳዳው «ግን እንዴት ይኸን መርዶ ልታረዱኝ ደፈራችሁ:: የሰው ሞት ነው ሰው የሚያረዳው:: እናንተ ግን የራሴን ሞት ነው□ኮ! ያረዳችሁኝ:: እኔ ዮሐንስ እያለሁ የለሁም! የለሁም! የታለሁ?» አየር እንዳነሰውና ራሱንም መቆጣጠር እንዳቃተው ሆኖ ከቤት ለመውጣት ወደ በሩ አመራ::

ሦስቱም አስቀድመው በሩን ይዘው ለአንድ አፍታ አረፍ እንዲል ለመኑት:: ለጥቂት ደቂቃዎች ክፍሉ በዝምታ ተዋጠ::

ዮሐንስ ግንባሩን ጠረጴዛው ላይ ደፍቶ በክናዱ ሸፍኖ ካደፈጠበት ባነነ:: «ምን ነበር ያላችሁት? እንዳብድ ነው ይህን አስቃቂ መርዶ የነገራችሁኝ አይደለም? ዓለሚቱ ንገሪኝ፣ አለገደች በኃይል፣ በጉልበት ተደፍራ ካልሆነ በቀር ሕይወቷ እያለ ሌላ ወንድ ጭኗ ውስጥ ይገባል ˜ብዬ አላምንም:: ሚስቴን፣ ሞግዚቴን፣ ማጣት አልፈልግም፣ ቅዱስ ዑሩኤል እባክህ የሰማሁትን ሁሉ ሐሰት አደርገው! ሐሰት ይወራ! ያም ሆነ ይህ ወደቤቴ ልሂድ» ብሎ ዮሐንስ እንደ ገና ሲነሳ ተሰማምጠው አስቀመጡት::

«በረንዳ ወጣ ብለን ቡና እንጠጣ» አለች ዓለሚቱ::

ተስፋዬ፣ ዮሐንስን የመሸከም ያህል ደግፎ ወደ በረንዳ ወጡ:: ዮሐንስ የሚናገረው ሁሉ ያለቀበት ይመስል ዝም አለ::

«ዮሐንስ ቡናው በረደ□ኮ!» አለች ሶስና

«እሺ» አለና የግዱን ሁለት ጊዜ ተጎንጭቶ ሲኒውን አስቀመጠው:: የውጭ በር ተንኳኳ፣ ዘበኛው ከፍቶ ወጣና ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ መልሶ ዘጋው::

«ማነው? ምንድነው?» አለች ዓለሚቱ ወደ ዘበኛው ዞር ብላ፣ «ቤት ጠፍቷቸው የሚጠይቁ ሰው ናቸው» አለ ዘበኛው::

«እኛን የሚመርጅ አጻፋ ስላለ እንዳይሆን» አለ ተስፋዬ ዝምታውን ለመስበር::

«ጨዋታው አልቋል፣ እሸት እሸት የሆኑ መረጃዎች በእጃችን ገብተዋል:: ከዚህ በኋላ መንፈራገጥ ለመላላጥ ካልሆነ በቀር የሚያስገኝላቸው ጥቅም አይኖርም» አለች ሶስና በልበ ሙሉነት::



ሦስቱ ሲንሾካሾኩ ዮሐንስ ሹክሹክታውን ልብ አላለም:: ተስፋዬ እነርሱን ትቶ ወደ ቤት ገባና በስልክ ለባለቤቱ «ከፈለግሽኝ በዚህ ስልክ ቁጥር ደውይልኝ ዓለሚቱ ቤት ነው ያለነው:: ለአለገደች ስልክ ደውለሽ ተስፋዬና ዮሐንስ አንድ የተስፋዬ ዘመድ ሞቶ አስክሬን ይዘው ወደ ሆሳእና ከተማ ሔደዋል፣ ነገ ይመጣሉ ብለሽ ንገሪያት:: እኛ በዚያ በምታውቂው የዮሐንስ ችግር ላይ እየተነጋገርን ነው» በማለት አስረድቶ ወደ በረንዳው ተመለሰ::

«ዮሐንስ አንድ ጊዜ እፈልግሃለሁ» አለችና ዓለሚቱ ወደ መኝታ ቤት ይዛው ገባች::

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሰው ሳሎን ሁሉም ተቀመጡ:: «ለዛሬ ይህ ጉባኤ» እንደ መሳቅ ባለ ፈገግታ «እዚህ ላይ እልባት ተደርጎበት ይደር፣ ነገ ጧት ከቁርስ በኋላ ይቀጥላል:: አሁን ግሩም ድንቅ ራት ከለስላሳ ሙዚቃ ጋር፣ አዳርም እዚሁ ይሆናል» በማለት ውሳኔዋን አወጀች::

* * *

ዮሐንስ ሌሊቱን በዓይኑ እንቅልፍ ሳይዞር ነው ያደረ:: በእሱና በአሰገደች መካከል ጸንቶ የቆየውን ትዳር፣ ፍቅር የሞላበት ትዳር፣ ከኋላ ወደ ፊት፣ ከፊት ወደ ኋላ እያመላለሰ በዓይነ ኅሊናው ሲዳስስ ወገግ አለ::

ዓለሚቱ ወንድሟን አልጋዋ ላይ አስተኝታ፣ ለራሷ ፍራሽ ከአልጋው ግርጌ ዘርግታ ነው ያደረችው::

«አንድ ሌሊት፣ ግን ብዙ፣ በጣም ብዙ ሰዓቶች» አለ ዮሐንስ አልጋው ውስጥ እየተገላበጠና እየተዘረጋጋ::

«አይዞህ ጆኒ፣ የምንገኘው በድላችን ዋዜማ ላይ ስለሆነ መጽናናት አለብን»

«በድላችን ዋዜማ አልሽ? ይህ ባለ ብዙ ፈርጅ ትግል፣ እንዲያው በቀላሉ፣ ሙዝ-ላጥ-ዋጥ ዓይነት አደረግሽው? በመካከላችን ሌሎች ልጆቼ አሉኝኮ! ፀንቶ የቆየ ትዳርን ለማፍረስ የሕጉ ጉዳይ፣ ማለት ከሕግ አኳያ መመቻቸቱ ብቻ በቂ አይደለም:: የነበረው ፍቅር፣ ትውስታው፣ ስሜቱ፣ ባጠቃላይ ሕግ የማይገዛቸው ብርቱና ጠንካራ የግንኙነት ሰንሰለቶች እንዳሉ መታወቅ አለበት:: ይህ ደግሞ ያገቡ፣ የወለዱና የወደዱ ሰዎች ይበልጥ ያውቁታል» አለ ዮሐንስ የእህቱን በትዳር ጣጣ ውጣ-ውረድ ገና አለመፈተን በሚገልጽ ቅላጼ::

ዓለሚቱ ትከሻዋን አንገቷን እያዋቃች «መልእክቱ ደርሶኛል ጆኒ ጥይትክን አትጨርስ ግን የሞተም ዘመድ የለህ? የአንተና የአሰገደች ጉዳይ የአለቀ የደቀቀ ነገር ሆኖአል፣ በቃ! በቃ! አሁን ክቁርስ በኋላ በአፈጻጸሙ ላይ እንነጋገራለን» አለች ወደ ሌላ ክፍል እያመራች::

የቁርስ ገበታ ከፍ ካለ በኋላ «ከየት እንጀምር?» አለች ዓለሚቱ ሦስቱንም በአንድ ጊዜ ፍጥጥ ብላ እያየች፣

«ከተፈቀደልኝ እኔ አንድ ጥያቄ ብጠይቅ» በማለት ሰስና ወደ ዮሐንስ አሰገገች::

በዓይንና በግንባር ጥቅሻ ፈቀደላት:: «ዮሐንስ የልጆችህን መልክና ባሕሪ እስከ ዛሬ ልብ ለማለት ሞክረህ ታውቃለህ? በሌላ አባባል አንተን የሚመስሉበትን ወይም ከአንተ የሚጋሩትን ገጽታና ትክለ-ሰውነት በንፅፅር መልክ ለማስተዋል ሞክረህ ታውቃለህ?» የሰስና ጥያቄ ነበር::



«በምን ምክንያት? ጥርጣሬው ስላልነበረኝ ያልሽውን ንፅፅር እንኳን ለማድረግ አሳቡም ኖሮኝ አያውቅ» አለ ዮሐንስ በቀዘቀዘ ስሜት፣

«ደህና አሁን አንድ ባንድ አንተንና ልጆችህን እናመሳስል፣ ማለት የምትጋሩትን መልክና ባሕሪ እናነጻጽር፣ ግልጽ ነው ዮሐንስ?» አለች ሰስና

«ገባኝ ቀጥሉ» የዮሐንስ መልስ ነበር::

«ቅፅል-የቤት ስሙ «ባሪያው» የተባለውን አንጋፋውን ልጅ ደረጀን እንውሰድ፣ ደረጀ ባልሳሳት ዕድሜው ከአሥራ ስምንት በላይ ነው:: ቁመቱን እንይ፣ ገና ካሁኑ ታናሽ ወንድሙ ጌታሁን በልጦታል:: የአፍንጫው ቀዳዳዎች ስፋት ኳስ ይከትታሉ:: ያንተ አፍንጫ ግን ጣትህን እንኳ ስተት አድርጎ አያስገባም:: በዚህ ላይ ጥቁረቱስ - ምኑ ነው አንተን የሚመስል?

«ሌላውን ልጅ ጌታሁንን እንመልከት፣ የዓይኑ ጉደጓድ ወደ ውስጥ መራቅ ወይም የቅዱ ክብነት፣ የቅንድቡ ሽፋሽፍት መብዛት የአፍንጫው እንደ ፍየል ጭራ ፊኒር ማለት ከስርኑ ደግሞ ደፍጠጥ ማለት፣ በዚህ ላይ ችኩልነቱ፣ ቆጨባራነቱ፣ የትኛው ነው አንተን የሚመስለው? ይህኛው ምናልባት ትንሽ ከእናቱ መልክ ተጋርቷል ሊባል ይቻል ይሆናል፣ ካንተ ግን ጆሮው ካልሆነ በቀር ቅንጣት እንኳን የለውም» አለች በመሳለቅ::

«ጆሮን ከመልክ፣ አትበላምን ከሙያ የቆጠረው የለም» አለ ተስፋዬ በፈገግታ፣

በነገራችን ላይ፣ አባቴ «ሚስት ካላበለች ባሏን ትወልዳለች» ይሉ ነበር አለ ተስፋዬ የሰስናን ገምጋሚ አስተያየት በማጠናከር::

«ሌላው መልኬ ነው፡፡ መልኬ ወንድ ከመሆኑ በስተቀር የእናቱ ፎቶ ኮፒ ነው፡፡ መልኬ የሚለው ስሙ እንኳን ይኽንን ያረጋግጣል፡፡

የሴቷ ልጅ ማንነት የተረጋገጠ ስለሆነ የምለው የለም፡፡ ዮሐንስ ይቅርታ አድርግልኝ እኔ እንደ ድፍረት ካልተቆጠረብኝ እንዳቸውም ከአንተ አብራክ የተከፈሉ አይመስሉም፡፡ ይመስላሉ የምትል ከሆነ ይኽንን በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል - በማያጠራጥር መንገድ» አለች ሶስና ኮስተር ብላ፡፡

ተስፋዬ «እንዴት?» አለ ፊቱን ቅጭም አድርጎ፡፡

«በሕክምና ምርመራ» አለች ዓለሚቱ፡፡

«በደማችን መመሳሰልና አለመመሳሰል ማለትሽ ነው? የዮሐንስ ጥያቄ ነበር፡፡

«አዎ እንዳልከው እርሱም አንዱ ነው» አለች ሶስና፡፡

«ይህ ያህል ዘመን ከሚስትህ ጋር እየኖርክ አንዱም ልጅ አንተን ካልመሰለ መኻን ልትሆን ትችላለህ ነው የምትሉት፣ አይደለም!» ዮሐንስ እንደማልቀስ ባለ ስሜት ጠየቀ፡፡ የስሜቱን መጎዳት ተመልክተው ሦስቱም በዝምታ አንገታቸውን አቀረቀሩ፡፡

«ዮሐንስ» አለ ተስፋዬ እየተከዘ «ሶስና ያመጣችውን ንጽጽር፣ የማርያማዊት በላይህ ላይ መደቀል ጋር ተጋግዞ ወደ እውነት የበለጠ እንደ ሚያቀርበው ታይቶኛል በበኩሌ» አለ፡፡

«መልካም አሁን ከሞላ ጎደል ምክክሩ ወደ አንድ ጫፍ የደረሰ ይመስላል፡፡ የሕክምናውን ምርመራ ቅድመ - ዝግጅት ማን ያመቻች?» አለች ዓለሚቱ ውይይቱን ለመቋጨት፡፡

«እሱን ለእኔ ተውት፣ ለዚህ ጉዳይ አስተማማኝ የሆነ የራሴ ሰው አለኝ» አለች ሶስና፡፡



# ምዕራፍ 25

## የአሰገደች መወጫመድ

በዮሐንስ ቅሬት አደባባይ መውጣት፣ የአሰገደች ኀሊና እየታወከ መጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይኽንን መልካም አጋጣሚ ተጠቅማ ዮሐንስን ከቤት ንብረቱ ሙልጭ እንድታስወጣ በተለይ ወላጆቿ ጧት ማታ እየጎተጎቷት ናቸው፡፡

አንድ ቀን አሰገደች ሥዕል ቤት በተያዘ የሦስትዮሽ ስብሰባ «በዚህ ወርቅ ዕድል አንቺ ካልተጠቀምሽበት ነገሩን አዙሮ ጠምዝዞ እሱ እንደሚጠቀምበት ዕወቂ፡፡ እንደዚህ እየመከርንሽ ደግሞ አቅማማለሁ ብትይ፣ የኋላ ኋላ ለሚደርስብሽ ጥቃት ማንም ከጎንሽ እንደማይቆም ዕወቂው» አሉ አባቷ አቶ ደምሴ

«ከዚህ የባሰ ወንጀል የለም፣ የወንጀሎች ሁሉ ወንጀል ተፈጽሞብሽ እሱን ባሌ ነው ብለሽ ከተቀመጥሽ፣ ይህን ጥቃት የመጋራት ግዴታ የለብንም፣ እዚያው እንደ ፍጥርጥርሽ ሁኚ፡፡ የእኛም ወላጅነት እዚሁ ላይ ያበቃል» አሉ እናቷ በመረረ አንደበት፡፡

«አባዬ ምንድነው አንተ ደግሞ የምትለው፣ ብዙ ነገር እያወቅህ፣ ዮሐንስ□ኮ ክዷል፡፡ የቀረበበትንም ክስ ሊረታም ይችላል፡፡ ከዚህም ሁሉ በላይ ያችን ነገረኛ ሴት እንዲያሳፍራት እኔ ነኝ መኪናውን ያስቆምኩት፡፡ ይህ የሆነው በስውር በተቀነባበረ ሥልት ነው ለማለት አዳጋች፣ በጣም አዳጋች ነው፡፡ ዮሐንስ እንደዚያ ዓይነት ሴራ መሸረብ የሚችል ሰው አይደለም፡፡እኔ በእውነት እማዬ ልንገራችሁ፣እማዬ ሙች ሕሊናዬ

እየታወከ ነው:: ምክንያቱም ምን እንደሆነ አላውቅም::ካሁኑ ግራ ገብቶኛል:: ግን ዞሮ ዞሮ የእናንተን የወላጆቼን ምክር ላለመጋፋት በዮሐንስ ላይ መወሰድ ስላለበት ርምጃ ያለህን ነጥብ በዝርዝርና በቅደም ተከተል አባዬ በወረቀት ላይ አስፍረው:: ከዚያም በቅድሚያ ሦስታችን ብቻ እንነጋገርበት፣ ይኸስ ያረካችኋል?» አለች አሰገደች ለወላጆቿ ከበሬቷ ያላት መሆኑን በሚያንፀባርቅ ገጽታ::

«ጥሩ! ጥሩ! እግዚአብሔር ይባርክሽ፣ ይኸ መች ገደደ» አሉ አባት::

«አዎ! ከመቀደም ምንጊዜም ቢሆን መቅደሙ ነው የሚሻለው፣ ቢሆን ይሆናል ባይሆን ይቀራል» አሉ እናት፣ በቀል የጥቃት ማካካሻ መሆኑን ልጃቸውን በማስገንዘብ::

«እናቴ ግን ተበቃይ ነሽ፣ አባዬ ዲቃላ ቢያመጣ ምንድነው የምታደርጊው፣ ከቤት ንብረቱ ሙልጭ ታስወጭዋለሽ ማለት ነው?» አለች አሰገደች እየሳቀች::

«ምን ቆርጦት! እኔ ዘምዘም አመዶ የምን ሙልጭ ማስወጣት አመጣሽብኝ፣ ጉሮሮውን ፈጥርቄ ጭጭ ነው የማደርገው:: በስመ አብ ወልደ መንፈስ ቅዱስ፣ ምን አመጣሽብኝ፣ የሰይጣን ጆሮ ይደፈን» አሉ::

«አንድ ያባትሽ አገር ሰው! ደጃች ማናቸው?» ብለው ወደ ቤታቸው በስላቅ ፈገግታ ዞር አሉ እመት ዘምዘም::

«አታመጪው የለሽ ምን ያደረጉት ደጃማች?» አሉ አቶ ደምሴ በግራሞት::



«እኒያ ሚስታቸው ታማ በጣር አልጋ ላይ ሆና ስለ ደቀለቻቸው ልጆቿ ከተናዘዘች በኋላ ድና ያገር መዘበቻ የሆነችው?»

«ደጃች አምባዬ የዋኹን ነው የምትይ?»

«አዎ! አዎ! ደጃች አምባዬ የዋኹ» አሉ እመት ዘምዘም የዚያ ትልቅ ቤተሰብ ታሪክ የዲቃላ አይነተኛ ምሳሌ መሆኑን በማሰብ::

«ሴትዮዋ ራሷን ካጋለጠች በኋላ ዳነች:: ከዚያስ!?» አለች አሰገደች በማስተንከር::

«ከዚያማ በኋላ ገና በደንብም ሳታገግም፣ ይገድሏታል ተብሎ ሲጠበቅ፣ በቃሬዛ አሸክመው ወደ ወላጆቿ ስደዷት - ማፈሪያ!» አሉ አቶ ደምሴ ወርጨት ብለው::

«የዋኹ ከዚያ በኋላ የተቀጠለላቸው ስም መሆን አለበት?» አለች አሰገደች በመገረም::

«አዎ! ያባታቸውማ ስም አስታጥቄ ነው» አሉ አቶ ደምሴ::

«የሆነስ ሆነና የሴትዬዋ መጨረሻ ምን ሆነ?» አሰገደች ኩነኔዋን ለማወቅ በመጓጓት ያቀረበችው ጥያቄ ነበር::

«እሷም ወላጆቿም ውጉዝ - ከመ - አርዮስ (እንደአርዮስ የተረገማችሁ ሁኑ) የመባል ያህል ከሕብረተሰቡ ተገለሉ:: ኩነናው አላስኖራቸው ስላለ፣ እሷ በሕክምና ሰበብ ወደ አዲስ አበባ ተሰደደች:: እንደ ወሬውማ አስኮብላዩ ካስደቃዮቿ አንዱ ነው ይባላል:: ለዚህ ሁሉ ጣጣ የዳረጋት መልኳ ነው፣ አይቁመና! አፈር ይበላው ይሆናል!» አሉ አቶ ደምሴ ለውበት ያላቸውን ጉምዠታ እያሳዩ::

እመት ዘምዘም የባለቤታቸው ስሜት የፈጠረባቸውን መቅበጥበጥ እምቅ አርገው ለትረካው ጆሯቸውን የነፈጉ መሰሉ::

«አወይ እቴን ምነው ቁርባኑ ቀርቶባት ከነኃጢአቷ በሞተች ኖሮ» አለች አስገደች እንዷ መተከዝ ብላ::

«ከሆነስ መናዘዝ ነው የሚሻለው፣ ንስሐ ገብቶ፣ ሥጋ - ወደሙን ተቀብሎ፣ በምድር ሳሉ ጣጣን ጨርሶ ነው ከዚህ ዓለም መለየት» አሉ አቶ ደምሴ ከአበ ነፍሳቸው ተዘውትሮ የሚነገራቸውን መንፈሳዊ ትምህርት በማስተጋባት::

እመት ዘምዘም ገሸሽ አድርገውት ወደ ነበረው ውይይት በመመለስ፣ «ለነገሩ ዲቃላና ቁባት ድሮም ነበር፣ አንዳንድ ካሕናት መንፈሳዊ ልጆቻቸውን፣ ሚዜዎች የቃል ኪዳን እህቶቻቸውን፣ ባሎች ዋርሳዎቻቸውን አማገጡ መባሉን ስንታዘብ ኖረናል::

«እረ ቄሱ ቄስ ሻሽ የጠመጠሙት፣

ልቤን እንደቆሎ አሽተው ቆረጠሙት::

ሁሉ ይባላል:: መቼም የማይሄድ ወንድ አለ ተብሎ አይታሰብም:: የምግጫው ወሬ ግን በሴቷ ላይ ይገናል» አሉ::

«እማዬ ቅድም□ክ! አባዬን <ምን ቀርጦት ------ጉሮሮውን ፈጥርቄ ጭጭ ነው የማደርገው> በማለት ዝተሽ ነበር:: አሁን ደግሞ የተለሳለሰ አቋም የያዝሽ ይመስላል» አለች አስገደች እናቷን ለመሞገት::

«አምና! አሁንስ ቢሆን! ምንቀርጦት፣ የት ቆሞ፣ እንደነ ደጃች አምባዬ እዚያው በዚያው - እንዴት ተብሎ --»

አስገደች የእናቷን ድንፋታ አቋርጣ፣ «ጣውንቱን - ባሌን የተጋራችኝን ሴት አልወቃት፣ ካላወቅሁዋት ደምሴም መሄድ



ይፈቀድለታል ማለትሽ ነው?» ለሚለው የልጃቸው ፈታኝ ጥያቄ መልስ ለመስጠት እመት ዘምዘም ቆም ብለው አሰቡና «መቸስ ምን ይደረጋል፣ ሲሆን ሲሆን እግዜር እንደፈቀደው አንድ ላንድ ቢኮን ነው ደጉ፣ ታልሆነም ደግሞ፣ አዩኝ አላዩኝ ብሎ ምግጫው ካማላውቃት ሴት ጋር ቢሆን ይመረጣል፣ ወሬውም እንዳይደርሰኝ» ብለው በረዥሙ ተነፈሱ::

አስገደች ትዝብቱን ወደ አባቷ በመመለስና የእናቷን አስተዋይነት በማድነቅ፣ ሳቅ ብላ «አባዬ አንተስ እማዬ በላይህ ላይ ብትደቅል ..... ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ አንቺ....!» ብለው ከዘራቻውን ይዘው ብድግ ሲሉ አስገደች ሮጣ ወደጓዳ ገባች::

***

ሥራ ከመፍታት ልጄን ላፋታት እንደተባለው፣ አቶ ደምሴ ሰሞኑን በፈቃደኝነት የተያያዙትን፣ ልጃቸውን ከዮሐንስ የማፋታት ሴራ ሲያፋድሹ ሰንብተዋል:: ከራፖር ፀሐፊ እስከ ጠበቃ አማክረው የቃረሙረሚቸው የመሚገቻ ጭብጦች ለአስገደች ለማቀበል ከቤት የወጡት ማልደው ነው::

«እንዴ! .....አባዬ፣ ሳትደውልልኝ እንዴት መጣህ?» አለች አስገደች ከበረንዳው ላይ አባቷን እየሳመች::

«ደውዬ ነበር:: አንቺ መታጠቢያ ቤት መሆንሽን፣ ዮሐንስ ደግሞ በጧት መውጣቱን «ባሪያው» ነግሮኝ ነው የመጣሁት» አሉ አባቷ::

«አረፍ በል መጣሁ» ብላ ወደ መኝታ ቤት ስትገባ ልጆች አንድ ባንድ እየቀረቡ እያታቸውን ስመው ሲወጡ ማርያማዊት ወደ ኋላ ቀረት ብላ «አባዬንና እማዬን ሲያስታርቁ ነው

የመጡት?» በማለት ዓይኗን በጭንቀት እያቁለጨለጨች ጠየቀች::

«ተጣልተዋል እንዴ? ማን ይመስልሻል ጥፋተኛ?» አሉ አያት እራሷን እያሻሹ፣

«ሁለቱም ናቸው፣ ብቻ እሱ ምንም አላለም፣ እማዬ ግን ሁል ጊዜ ነው የምትጮኽበት» አለች እንደማልቀስ እየቃጣት::

«ሜሪ ቶሎ ወደ መኝታ ቤትሽ፣ እኔና አባዬ ሥራ አለን:: እሺ!» አለች አሰገደች::

ማርያማዊት እንደ ከፋት ፊቷን እንደ ከስከሰች ወደ መኝታ ቤቷ ስትሔድ አባትና ልጅም ከሳሎን ወደ ዋናው መኝታ ቤት ገብተው ከውስጥ ዘጉ::

«ታዲያስ እጅህ ከምን?» አለች አባቷ የመጡበትን ጉዳይ ዮሐንስ ወደ ቤት ከመመለሱ በፊት መጠናቀቅ እንዳለበት በሚጠቁም ችኮላ::

«ይመጣል የሚል ግምት ካለሽ ሳሎን መሆናችን ይመረጣል፣ አይመስልሽም?» አሉ አባት በሥጋት::

«አይ፣ አይ፣ ግድ የለም፣ ለመሆኑ ምን የሚያቆይ ጉዳይ አለን? ግን የሕግ ባለሙያ አማክረኻል?» አለች ወደ መጡበት ጉዳይ ፈጥኖ ለመግባት፣

«አዎ፣ ያለቀ የደቀቀ ነገር ነው፣ ብትፈልጊ በዮሐንስ ላይ የውጭውን አጥር በር ዘግተሽ ዞር በል፣ ከዚህ በኋላ ስዲቃላ እናትህ፣ ለቅምጥህ መርቂላታለሁ:: ይመችህ» ልትይው ትችያለሽ» አሉ አባት ለልጃቸው የልብ ልብ በሚሰጥ አነጋገር::

አሰገደች ለዘብ ባለ አነጋገር «ይኸንንስ አላደርግም፣ ምናልከህ አባዬ፣ ያገር መሳቂያ ልሁን እንዴ! እሱም ቢሆንም



የልጆቼ አባት፣ የሕግ ባሌ ነው□ኮ! ቀን አሳስቶት ቀንዳም ሰይጣን ጋልቦት ካልሆነ በቀር በተፈጥሮው ያን ያህል ሴሰኛም አይደለም:: ዮሐንስ ውስጡ ገር መሆኑን አውቃለሁ» በማለት ስትናገር እንባዋ በዓይኖቿ ግጥም አሉ::

«አይ የሴት ነገር ምን አስነካሽና ነው እንደዚህ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከብት ሆነሽ የጠበቅሽኝ? አንቺ ዘር አሰዳቢ፣ አንቺ የግም ጥላይ፣ እኔ ለውየው ሞቻለሁ ልኩን ባላሳየው» ብለው ሌላም ሌላም ከእርሳቸው የማይጠበቅ ዘለፋ እየተናገሩ ወጥተው ሔዱ::

አሰገደች በዚህ እድሜዋ አባቷ በአስታራቂ ሽማግሌነት የተሰየሙበትን ጊዜ አታስታውስም:: ችኩልነታቸውን፣ ከፍሬው ገለባነታቸውን፣ ጎረቤትና ወዳጅ - ዘመድ ሳይቀር ሲመሰክርባቸው ይከፋት ነበር::

«ደምህ መራር ስለሆነ ባትናገር ይሻላል:: ነገርህ ለሰው አይጥምም» የሚለው የእናቷ ምክር ከመቸውም ይልቅ ዛሬ ትክክል መሆኑን አሰገደች ተገነዘበች::

የምትለው ጠፍቷት ከሳሎን ቆማ ውጭ-ውጭውን ስትመለከት ባሪያውና መልኬ እየተሯሯጡ ዘው አሉ:: በእናታቸው በድን መስሎ መገተር ተደናግጠው «ምነው እማ! አቡሌ የትሔደ? አልቅሰሻል እንዴ? አይንሽ ምነው ቀልቷል?»

«እስቲ ተውኝ» አለችና ቆጭ አለች::

«እስከ መቼ ነው እንደ ሕፃን የምታዩን? እኛን የዚህ ቤተሰብ አባላት አድርጋችሁ የምትቆጥሩን ከሆነ፣ እንደ አባልነታችን በክፋውም በበጎውም መሳተፍ ይገባን ይመስለኛል:: በዚህ ቤተሰብ ውስጥ በአንቺና በጆኒ መካከል ስለተፈጠረው

አለመግባባት ከውጪ የስሚ ስሚ ነው ወሬው የሚደርሰን:: ከእኛ ከልጆቻችሁ የምትሰውሩት ምስጢር ምንድነው? አገር እንደ ፈለገ የሚያቦካውን ወሬ ከእናትና ከአባታችን መስማት ለምን አንታደልም? መቸም አንድ ቤት አንድ ጥፋት አለ:: ወይም አንቺም እሱም በየበኩላችሁ ጥፋተኛ ልትሆኑ ትችሉ ይሆናል:: ከሕፃንነታችን ጀምራችሁ ያስተማራችሁን አንድ ቁምነገር መኖሩን ላስታውስሽ <ምን ጥፋት ብትፈጽሙ ጥፋታችሁን ለመደበቅ አትሞክሩ፣ አውቃችሁም ሆነ ሳታውቁ በፈጸማችሁት ጥፋት ተፀፀቱ፣ ፈጥናችሁም ይቅርታ ጠይቁ:: ይህን አለማድረግ ጥፋቱን ወንጀል ከማድረጉም በላይ፣ በጥፋት አለመጸጸት ሰይጣናዊነት ነው> እያላችሁ ሁልጊዜ የምትነግሩንን፣ ለምን እናንተስ ለራሳችሁ አትጠቀሙበትም?» በማለት ደረጀ ጠየቀ::

አለገደች «ጥፋቱ ያንደኛችሁ ወይም የሁለታችሁም ሊሆን ይችላል:: ደግሞስ ማንም ይሁን ማንም፣ ያጠፋው ሰው ለምን ይቅርታ አይጠይቅም?» የሚለውን ሥጋን ዘልቆ አጥንትን የሚሰረስር እንደመታዘብ ያለ የልጇን የባሪውን አስተያየት በሃሳቧ አውጥታ አውርዳ ልቧ ክፉኛ ተነካ::

ጥፋቱን በዮሐንስ ላይ ለመላከክ «አባትህ□ኮ ሲመክር ብርቱ ለራሱ ከንቱ ነው» በማለት የባሪያውን የማያፈናፍኑ ጥያቄዎች ሳትመልስ በጎን በር ለማምለጥ ሞከረች::

«አይደለም! አይደለም! እማ እንደሱ ልትይማ አይገባም:: አንቺስ የበኩልሽን ምን አድርገሻል? ትዳሩ የጋራችሁ እስከሆነ ድረስ ችግሩንም በጋራ መፍታት ነው ያለባችሁ» አለ ደረጀ ከአምና ጀምሮ በስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ የተለማመደውን የመከራከሪያ ሥልት በመጠቀም::



አለገደች ያለፈ ምግባሯን በኀሊናዋ መለስ ብላ በማሰብና መሬት ጠብ በማይለው የልጇ አነጋገር ስሜቷ እንደገና የባሰውን ስለተነካ - «ልክነህ! አዎ! ስልጅ ይታየዋል» በማለት እንባ ያቋቱ ዓይኖቿን በአይበሉባዋ ነካካቻቸው::

የእናቱን በመንፈስ መሰቃየት ሲያስተውል የቆየው መልኬ «እኛ□ኮ ልናሳዝንሽ ብለን አይደለም እማ፣ አሁን በቃ እንሂድ» አለና ወንድሙን ጎተተው::

«አለግዬ ይቅርታ ቁስልሽን ሳላውቅ ቧጠጥኩና ረበሽኩሽ መሰለኝ» አለና ባሪያው የእናቱን ትከሻ እንደማቀፍ አድርጎ አጽናናት::

ይኸን ጊዜ አለገደች ይበልጥ ስሜቷ ስለተነካ በጠረጴዛው ላይ ተደፍታ ተንሰቀሰቀች:: ከአባቷ ጋር የተፈጠረው አለመግባባትም ከዮሐንስ ጋር በጀመሩት ሽምግልና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ በማሰብ ይበልጥ አለቀሰች:: ካሁኑ ብቸኝነት ተሰማት::

ከቤተሰብ፣ በተለይ ከአባትና እናቷ መገለሏ፣ ከባለቤቷ ጋር ገና ለገና ውጤቱ ባልተረጋገጠ የዲቃላ ጉዳይ ችኩላ በውል ሳይጠና አደባባይ በወጣ ቅራኔ ውስጥ መግባቷ፣ የልጇ የባሪያው ልብ የሚሰብር አነጋገር፣ የራሷም የቆዩ ድርጊቶቿ ተጋግዘው የውሃ ላይ ኩበት አደረጓት:: ከዘመድ አዝማድ ውጭ ሆና መንሳፈፏ ይህ ነው የማይባል፣ ልትቋቋመው ያልቻለችው የአካልና የመንፈስ ጭንቀት ፈጠሩባት:: ሥዕል ቤት እየዘጋጅ ባፈሰሰችው እንባ ዓይኗ መሟሟት የጀመረ መሰለ:: እህል የዞረበት ሳትዞር ውላ እያደረች ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የዮሐንስን ልቧ መናፈቅ ጀምሯል::

«የተያዘውን ሽምግልና ሠርዣለሁ ብል ከእናትና አባቴ እቀያየማለሁ:: ሆኖም በዚህ መስዋዕትነት ባሌን ማትረፍ ከቻልኩ ኪሣራው ትንሽ ነው የሚሆነው፣ በዚህ ላይ ልጆቼ ይቅር መባባልን፣ በጥፋት መፀፀትን ለእኛ አስተማራችሁ እንጂ እናንተ አታውቁትም እያሉኝ ናቸው» በማለት ኀሊናዋን አስጨነቀች::

በመጨረሻም የሽምግልናው ቀጠሮ አንድ ቀን ሲቀረው «ሽምግልናውን የጠየቅሁት እኔ ስለሆንኩ ትቼዋለሁ» ለማለት ወሰነች::

ይኸንን ውሳኔ የሚመለከት ማመልከቻ ጽፎ የሚሰጣት ሰው ማፈላለግ ያዘች:: በርካታ የምታውቃቸውን ሰዎችም ለማነጋገር ሞከረች:: በየምክንያቱ በዚህ አጭር ጊዜ ለመገናኘት እንደማይችሉ ሲነግሯት በዮሐንስ ላይ በወሰድኩት ርምጃ ተቀይመው መሆን አለበት ብላ ደመደመች::

«በቶሎ እንዲሆን እግዚአብሔር ስላልፈቀደ ነው፣ በሚቀጥለው ቀጠሮ ምክንያቴን ለእኔ በሚያመች መልኩ፣ ዮሐንስንም ይቅርታ ተጠየቅሁ ብሎ ራሴ ላይ እንዳይወጣ በሚገድብ አጻጻፍ በባለሙያ ተዘጋጅቶ ቢቀርብ ይሻላል» በማለት ራሷን አጽናናች:: «አዎ ሌላው ቢቀር ባሌን በትንሽ ኪሳራ አተርፋለሁ» አለች ጠቡ ቀርቶ፣ እርቃቸው ከወዲሁ እየታያት::



# ምዕራፍ 26

## የአሰገደችና አክሊሉ ውሳኔ

አክሊሉ የረዥም ጊዜ ፈቃድ ያሰደመወዝ ተሰጥቶት ዞር ብሎ ከርሟል:: ፈቃዱም ካለቀ በኋላ ሙሉ በሙሉ ወደ መደበኛ ሥራው ላለመመለስ እያቅማማ ነው:: አልፎ አልፎ አሳቻ በሆነ ሰዓት፣ በአሳቻ ልብስ ክሊኒክ ብቅ ካለ፣ ለአሰገደች እጅ መንሻ ሪፖርት አቅርቦ፣ አዲስ ትዕዛዝ ተቀብሎ ይሔዳል::

ፈቃድ ወስዶ ከቤት ሳይወጣ የልጁን እናት በማረሱ ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ አክሊሉን በቀን በቀኑ ይመርቁታል:: ወጥቶ ሲገባ ባዶ እጁን እንደማይመለስ ያስተዋሉ አንዳንድ ጎረቤቶች «እንዴት ነው! የዘበኛ ደመወዝ ይህን ያህል ያንቀባርራል?» እያሉ ናቸው:: አክሊሉ የወ/ሮ ይፍቱ ሥራን «አማቼን እዩልኝ» ዓይነት ማስታወቂያ አልወደደውም:: በዚህ ላይ የጎረቤቶቹ መጠራጠር ሥጋት ለቀበታል::

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ፣ አክሊሉ በዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ከወ/ሮ አሰገደች ጋር ለመመካከር ወደ ክሊኒክ ብቅ አለ:: እንደ መጣም ፊቱን አስወግቶ አመቺ ጊዜና ሁኔታ ለመጠበቅ ወደ ጥበቃ ኃላፊው ቢሮ አቀና::

«ዛሬ ከየት ተገኘህ፣ ሽዋዬ እንዴት ነች?» አለ አለቃውም ለሰላምታ እጁን እየዘረጋ::

«እንደ ጠየቅሃት» አለ፣ ከአልቅናው ይልቅ ላገር ልጅነቱና ለጓደኛነቱ ያለውን ቅርበት አጉልቶ::

«እውነትክን ነው፣ እንደቡዳ አንድ ቀን ብቅ ብዬ ጠፋሁ፣ ምንትለኝ!»

«ለባለቤቷ ፈቃድ ስጥተህ፣ ሥራው እንዳይተጓጎል ያለውን የሰው ኃይል አብቃቅተህ፣ በጎደለ ራስህን መድበህ በዋልከው ውለታ ክስሃታል፣ አልተቀየመችህም::»

«ጎሽ! ጎሽ! እንዲህ ነው እንጂ! ወደ ባዕድ አኜኮ ወደ ዘመድ መዋጥ ማለት እንዲህ ነው - ከሸንከው!» አለ አለቃው የአክሊሉን ጀርባና ትከሻ ቸብ ቸብ እያደረገ::

«በነገራችን ላይ፣ አንድ ተጨማሪ የጥበቃ ሠራተኛ ለመቅጠር ማስታወቂያ ወጥቷል፣ ዘመድ ካለህ» አለው አለቃው::

«ለምን አስፈለገ? አንተ ነህ ይቀጠርልኝ ያልከው?» የአክሊሉ ጥያቄ ግራሞት ነበረው::

«እኔ አልጠየቅሁም፣ አንተን ወደ ቢሮ ወይም አትክልተኛነቱን እጠቃለህ እንድትይዝ ለማድረግ ነው የሚል ወሬ ሽው ብሎኛል::»

«ወ/ሮ አሰገደች እንዴት አላነጋገሩህም?»

«እኔን ምን ያነጋግሩኛል፣ ካነጋገሩ አንተን ነው መሆን ያለበት» አለ አለቃው በለገጥ ፈገግታ::

«ነው እንዴ! በምን አንቀጽ ነው እሳቸው እኔን የሚያነጋግሩት?» የአክሊሉ ጥያቄ ኮስተር ያለ ነበር::

«እንደሚወራው ከሆነ፣ በእድገት ይሁን በሌላ ከጥበቃ ወደ ሌላ ሥራ ትቀየራለህ የተባለከው አንተ ስለሆንክ ነዋ!» አለ አለቃው ይለይለት በሚል ድፍረት::



አክሊሉ መርዶ አይሉት የምሥራች፣ በለማው ጭምጭምታ ግራ ስለተጋባ አለቃውን ተሰናብቶ ወደ አስተዳደር ቢሮ ሔደ:: ወ/ሮ አሰገደች ብቻዋን መሆኗን በመስኮት በኩል አረጋግጦ ገባ:: እጅ ነስቶ በሩን በጀርባው ከልሎ ተቀመጥ እስኪባል ጠበቀ:: የጀመረችውን እንደ ጨረሰች ቀና ብላ:: «አክሊሉ ነህ እንዴ! ጎሽ ስፈልግ መጣህ» አለች::

አክሊሉ ምንም መልስ ሳይሰጥ ባለበት እንደገና እጅ ነሳና ቆመ::

«ተቀመጥ» አለች ጠረጴዛው አካባቢ ያሉትን ወንበሮች በእጅዋ እያመለከተች::

ለወሬ ሹክሹክታ እንዲመች በስተቀኝ ረድፍ ባለው የመጀመሪያ ወንበር ላይ ተቀመጠ::

«እሺ! ሙግት እንዴት ነው?» የአሰገደች አጠያየቅ እንደወትሮው ሳይሆን ዘና ያለ ነበር::»

«በሸዋዬ በኩል ያለው ማስረጃ የሚያወላዳ አልሆነም:: የዳኛውም አቀባበል ደህና ነው፣ እሷ እንደ ነገረችኝ ማለቴ ነው::»

«ሰውየው የዋዛ እንዳይመስላችሁ:: እንዲህ በቀላሉ እጅ የሚሰጥ አይደለም፣ ተጠንቀቁ::»

«ካሉስ ዳኛውም እንደቴህ ቀደሙ አያዋክበውም:: ሲናገርም በጥሞና ያዳምጠው ገብቷል ነው የምትለኝ ሸዋዬ::»

«አቅሞት ይሆናላ! ምንቸገረው፣ ብር እንደሆን እንዳፈር ነው፣ ወይኔ አሰገደች» አለችና በረዥሙ ተነፈሰች::

«ከየት ያመጣሉ? ጊዜው ባለብሮች የከለሙበት ነው:: ያልከሰሙትም ቢሆኑ አንገት የደፉበት መስሎኝ» አለ አክሊሉ::

«በደህና ቀን የተዘረፈ ሀብት፣ እሱ አደጋሪ፣ አባቱ አድጋሪ በዝባዦች» አለች አሰገደች ለአክሊሉ ጥያቄ ከሚገባው ባላይ በሆነ መልስ::

«የእሳቸው ግማሽ ሀብት የእርሶስ አይደለም እንዴ!» የአክሊሉ ጥያቄ መረጃ ከመሻት ይልቅ የትዝብት ነበር::

«አክሊሉ እንዳትዘነጋ፣ በዚህ በእኛ ጉዳይ ለማወቅ ከተፈቀደልህ በላይ ለማወቅ ባትሞክር ደግ ነው:: ልክህን እወቅ፣ እኔ አደጋሪ አይደለሁም» አለች አሰገደች ከወንበሯ እንደ መነሳት ብላ::

አክሊሉ በአሰገደች ማስጠንቀቂያ ሳይደናገጥ «በዚህ ጉዳይ ሸዋዬ ከተረታች መጨረሻችን ምን ሊሆን ነው? በዚህ ነጥብ ላይ ላነጋገርዎ ነው ዛሬ የመጣሁት» በማለት የውይይታቸውን አቅጣጫ የሚቀይር ዱብ ዕዳ ጥያቄውን ወርውሮ ቀና አለ::

አሰገደች ለአክሊሉ ጥያቄ መልስ ከመስጠት ይልቅ፣ ጥያቄው ለምንና እንዴት ተነሳ በሚልና በጥያቄው ጀርባ ይኖራል ብላ ስለገመተችው ቋጠሮ ማሰላሰል ጀመረች:: አክሊሉ የአሰገደችን በዐሳብ መዋጥ ያላስተዋለ ለመምሰል በጠረጴዛው ላይ ያሉትን ወረቀቶችና መጽሔቶች እየነካካ መልሷን በትግሥት ጠበቀ::

ለዚህ፣ የአክሊሉ እንደ መርግ የከበደ ጥያቄ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ መልስ ስላልነበረ፣ ጥያቄውን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ፈንታ፣ ጥያቄውን ተተግና በጀርባ ለመቆየት ያህል «ይህን ነገር እንዴት አሰብከው? ምንስ አሳሰበህ?» በማለት ጥያቄውን ለማርገብ ሞከረች::



«የወንጀሉ ሴራ ከከሸፈ፣ የዚህ ድርጊት የመጀመሪያው ለለባ የምሆነው እኔ ነኝ:: የሴራው አቀነባባሪ እኔና እርሶ ብንሆንም፣ ወንጀሉን የፈፀምኩትና ያስፈፀምኩት እኔ አክሊሉ መሆኔ ይረጋገጣል:: አዎ! ሴራው ተጋለጠ ማለት አክሊሉ ዓለም በቃኝ ተወረወረ ማለት ይሆናል:: ይህ ነው ያሳሰበኝና እንቅልፍም የነሳኝ::»

አሰገደች «ሴራው ከሸፈ! ሴራው ከሸፈ! ከሸፈ!» የሚለውን ሥጋት አክሊሉ የገለጸበትን ኃይለ - ቃል እያሰላሰለች በዐሳብ ደመና ውስጥ ገባች:: አክሊሉ ያዥጎደጎዳቸውን ሌሎቹን ቃላት አሰገደች እየሰማች አልሰማቻቸውም::

አሰገደች ከተንሳፈፈችበት የጭንቀት ደመና እስክትመለስ አንዴ ጣራውን ሌላ ጊዜ ግድግዳውን እያየ ጠበቀ::

«በዚህ ጉዳይ ላይ የተማከርከው ሰው አለ? አክሊሉ አትደብቀኝ እውነቱን ንገረኝ::»

«በመጀመሪያ ይህን ጥያቄ እርሶ ለምን ይጠይቁኛል?» አክሊሉ ይህን ጥያቄ የጠየቀው ፊቱን ቅጭም አድርጎ ነበር::

«ግድ የለህም አክሊሉ፣ የተማከርከው ሰው ካለ ንገረኝና ጥያቄውን ለምን እንደ ጠየቅሁህ እነግርሃለሁ» የአሰገደች አነጋገር ተማፅኖ ያለበት መሆኑን የተረዳው አክሊሉ «በዚህ ጉዳይ ላይ እስካሁን ማንንም አላማከርኩም» አለ ረጋ ብሎ::

«.........<እስካሁን> አልክ አክሊሉ? ለምን እስካሁን? ከዚህ በኋላስ! ታማክራለህ ማለት ነው?»

አክሊሉ የአሰገደች ጭንቅ ስላስጨነቀው ላንድ አፍታ ዝም አለና:: «አዎና ለምን አላማክርም! ልበል ለጊዜው ለዚህ ጥያቄ

የተዘጋጀ መልስ የለኝም ልበል» አክሊሉ አማራጭ መልስ እስኪያገኝ በወሰደው ጊዜ አስገደች ከፋት::

«ንገረኝ እንጂ አክሊሉ!» አለች በተስለመለመ አይታና በደከመ ድምፅ::

«ይቅርታ ጥያቄው በጣም ከባድ ሆነብኝ:: ለጊዜው ለዚህ ጥያቄ የተዘጋጀ መልስ ስለሌለኝ ነው ዝም ያልኩት»

«ይህ□ክ! ላማክርም ላላማክርም እችላለሁ እንደ ማለት ነው፣ አይደለም እንዴ!» አለችና አክሊሉን በሌላ ጥያቄ ወጠረችው::

አክሊሉ እዚያው እተቀመጠበት ወንበር ላይ ቆርጠጥ ቆርጠጥ እያለ «ዛሬ እንዴት ነው ነገሩ ሁሉ ጥያቄ በጥያቄ ሆነሳ!»

«አዎ ጥያቄውን የጀመርከው አንተ ነህ፣ ያመጣኸው ጥያቄ ደግሞ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም:: ደግሞም እውነቱን ለመናገር ያለጊዜው የቀረበ ጥያቄ ነው:: ገና ምኑ ተያዘና! ከባለቤቴ ጋር በሽማግሌ ግብግብ ላይ ነን:: የዮሐንስና የባለቤትህ የሽዋዬ ክርክር ተጀመረ እንጂ አላለቀም:: አዝማሚያው ካላማረ አንቱ የተባለ ጠበቃ ተገዝቶ ዳኛውን በደህና ብር አሸጎ ማለቂያ የሌለው ክርክር ማድረግ ይቻላል:: ይህም ሁሉ ተደርጎ የማታ ማታ ዮሐንስ ከረታን፣ አንተ፣ ሚስትህና ልጅህ በ24 ሰዓት ወደ ጎንደር ትሸኛላችሁ::»

እንደሉ ከሆነ ዐሳብዎ፣ ለምን ከወዲሁ አንሸኝም?» አለ አክሊሉ የአስገደችን ዕቅድ ያለማመንታት ለመቀበል መዘጋጀቱን በሚገልጽ ስሜት:-



«ይቅርታ ጥያቄው በጣም ከባድ ሆነብኝ:: ለጊዜው ለዚህ ጥያቄ የተዘጋጀ መልስ ስለሌለኝ ነው ዝም ያልኩት»

«ይህ'ኮ! ላማክርም ላላማክርም እችላለሁ እንደ ማለት ነው፣ አይደለም እንዴ!» አለችና አክሊሉን በሌላ ጥያቄ ወጠረችው::

አክሊሉ እዚያው እተቀመጠበት ወንበር ላይ ቆርጠጥ ቆርጠጥ እያለ «ዛሬ እንዴት ነው ነገሩ ሁሉ ጥያቄ በጥያቄ ሆነሳ!»

«አዎ ጥያቄውን የጀመርከው አንተ ነህ፣ ያመጣኸው ጥያቄ ደግሞ በቀላሉ የሚመለስ አይደለም:: ደግሞም እውነቱን ለመናገር ያለጊዜው የቀረበ ጥያቄ ነው:: ገና ምኑ ተያዘና! ከባለቤቴ ጋር በሽማግሌ ግብግብ ላይ ነን:: የዮሐንስና የባለቤትህ የሽዋዬ ክርክር ተጀመረ እንጂ አላለቀም:: አዝማሚያው ካላማረ አንቱ የተባለ ጠበቃ ተገዝቶ ዳኛውን በደህና ብር አሸጎ ማለቂያ የሌለው ክርክር ማድረግ ይቻላል:: ይህም ሁሉ ተደርጎ የማታ ማታ ዮሐንስ ከረታን፣ አንተ፣ ሚስትህና ልጅህ በ24 ሰዓት ወደ ጎንደር ትሸኛላችሁ::»

እንደሉ ከሆነ ዐሳብዎ፣ ለምን ከወዲሁ አንሸኝም?» አለ አክሊሉ የአስገደችን ዕቅድ ያለማመንታት ለመቀበል መዘጋጀቱን በሚገልጽ ስሜት:-

«ክርክሩ! የዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ግብም የዮሐንስ ድባቅ መመታት መሆኑን አክሊሉ እንዳትዘነጋ»

«ክርክሩ'ኮ! ለውሳኔ ማደሩን ቀደም ብዬ ነግሬዎት ነበር:: ዳኛ ለማባባል፣ ጠበቃም ለመግዛት አሁን ጊዜው አይደለም፣ አልፏል:: ምናልባት ይግባኝ ከተባለ ሙግቱን በገንዘብ ኃይል

ለዓመታት ማራዘም ይቻል ይሆናል:: ይህም ብቻ አይደለም፣ ባለቤትዎ ፍርዱን በገንዘብ ኃይል ለማስለወጥ የሚሳናቸው አይመስኝም:: እርሶዎም ቀደም ብለውታል::»

«ታዲያ ምን ይሻላል ነው የምትለው?»

«እኛን ከወዲሁ ወደ ጎንደር መሸኘት ችግሩን ይፈታው ይመስለኛል::»

«አክሊሉ ይህን የሸኘት ጉዳይ ሌላ ጊዜ ረጋ ብለን ብናየው፣ ለዛሬ እዚህ ላይ ቢበቃን!» አለች አሰገደች::

«በዚህ ጉዳይ ላይ እኔም እሶም የምናማክረው ሰው እስከሌለ ድረስ የነገሩ ማደር አይታየኝም::»

«ለመሆኑ ባለቤትክን እንዴት አግባብተህ ልትወስዳት ትችላለህ?»

«አንቺን ከወዳጅ ዘመድ ጋር አስተዋውቃለሁ፣ ልጁንም በወላጆቼ አስመርቃለሁ፣ በዚያውም ጎንደርን ትጎበኛለሽ በሚል ማግባቢያ ይዣት እሄዳለሁ::»

አሰገደች የአክሊሉን የማግባቢያ ነጥቦች በፀሳቧ አመላልሳ፣ የእነሱ ከአዲስ አበባ መኮብለል ዮሐንስን ይጠቅማል ወይስ ይጎዳዋል! የሚለውን ማታ በሥዕል ቤቷ ለማለዘብ ወስና፣ «ነገ እዚህ ሳይሆን፣ ከዚህ በፊት ያመሸንበት ሆቴል እንገናኝ» አለችና አክሊሉን አግባባችው::

አክሊሉ እንደ ተለመደው እጅ ነስቶ ሊወጣ ሊል እንዲጨብጣት እጆዋን ዘረጋችለት፣ እንደ መሸኮርመም እያለ ጨበጣት:: ከዚያም እንደ ተለመደው እጅ ነስቶ ሊወጣ ሲል «እርግጠኛ ነኝ እስከ ዛሬ አክንባሎ ተሰብሯል!» አለችው::



«ነገ! ነገ! ነገ! እነግርዎታለሁ» ብሎ አክሊሉ ፈገግ እያለ ወጣ::

በማግስቱ አክሊሉና ሸዋዬ በተቃጠሩበት ሰዓት ተገናኙ:: እነ አክሊሉ ከአዲስ አበባ ተነስተው ጎንደር የሚሳፍሩበት ወጪ አሰገደች እንደ ጠበቀችው ቀላል አልሆነም:: ለጓዝ ማንሻ፣ ለስንቅና ለመቋቋሚያ በድርድር አሥር ሺህ ብር ለመስጠት አሰገደች ተስማማች:: ድርድሩ በሆቴሉ መኝታ ክፍል ምሳ ላይ ተጀምሮ ፍፃሜ ያገኘው አልጋ ውስጥ ነው:: ያ ባይሆን ኖሮ ሊፈርስም ይችል ነበር::

የሸዋዬንና የዮሐንስን ክርክር በተመለከተ፣ በቀጠሮው ዋዜማ የሸዋዬ እናት ዳኛው ጽ/ቤት ቀርበው «ልጄ ሸዋዬ ሕፃኑ ታሞባት ማሳከሚያ ስላጣች ጠበል ለመሞከር ወደ ገጠር ሔዳለች ብለው እንዲያስረዱ፣ ይህን ተልዕኮ ለማስፈፀሚያ እንዲረዳቸው «የቡና መግዣ» ተብሎ መቶ ብር እንዲሰጣቸው ተወሰነ::

***

አክሊሉ ከአሰገደች ጋር በደረሰው ስምምነት መሠረት ጓዙን ጠቅልሎ አዲስ አበባን ጥሎ አገር ቤት ለመግባት ቅድመ ዝግጅት ላይ ነው:: ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ከአሥር ሺህ ብር ጋር ታቅፎ፣ በእናት እጅ በወግ የታረሰች ዓይነ ግቡ ኮረዳ አስከትሎ እስቴ ለመግባት በሹመት የመምጣት ያህል «ኖር!» የሚያስብል ክብር እንደሚያጎናጽፈው ታስቦታል::

በሌላ በኩል ደግሞ «የአሥር ሺህ ብር ሚስጢር ሳይገለጽላት ሸዋዬን ይዞ መጓዝ ያዋጣል? ጎንደር ከገቡ በኋላ እሷም ልጁም ወደአዲስ አበባ የማይመለሱ መሆናቸውን ከወዲሁ

ልንገራት ወይስ አልንገራት? የኋላ ኋላ ሸዋዬ ብታምጽስ?» እክሊሉ የክፍል ትምህርቱን ሳያጠና ለፈተና እንደተቀመጠ ተማሪ ጥያቄዎቹን መልሶ መላልሶ ዳሰሳቸው:: አጥጋቢ መልስ አላገኘም:: «ከዚህ ሁሉ ለምን እኔ ሹልክ ብዬ አገሬ አልገባም?» ሌላ ከባድ ጥያቄ::

ሸዋዬ የእንግድነቷ ወረቾ ሲያልቅ የአዲስ አበባ ትዝታዋ «ተነሽ! ብረሪ!» እንደሚላት ታስበውና «ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ብሬን ቋጥሬ፣ እኔው ልግባ አገሬ» በማለት ቀደም ሲል አንስቶት የነበረውን ጥያቄ እንደገና ማለዘብ ጀመረ::

ሸዋዬ ካራስ ቤት ወጥታ እንደ ወትሮዋ ውጭ ውጭ ማለት ጀምራለች:: እናቷ ለልጅ ልጃቸው ካላቸው ፍቅር የተነሳ እንቅልፍ ሲይዘው እንኳ አያስተኙትም፣ ያዝሉታል ወይም ታቅፈው ቁጭ ይላሉ እንጂ::

በሸዋዬ ውጭ ውጭ ማት ውስጥ ውስጡን የተከነው እክሊሉ «ሕፃኑ ጡት የሚያስፈልገው መሰለኝ:: ወጣ ገባው በፕሮግራም ቢሆን......» አለና ከበሩ ደፍ ላይ ቆም ብሎ የሸዋዬን መልስ ጠበቀ::

የእክሊሉ አነጋገር ከሕፃኑ ጡት መጥባት በላይ ሌላ መልእክት እንዳዘለ የጠረጠረችው ሸዋዬ «እሽ፣ እነዚህ የከፍተኛ ኪነቶች እየጠሩኝ ነው እንጂ የት ስሄድ....» አለች ቀዝቀዝ ብላ::

«እናትሽም በሥራቸው ላይ ሞግዚትነቱ እንዳይከብዳቸው ብዬ ነው» አለ እክሊሉ መልእክቱን ከለል ለማድረግ::

«እሽ! አልኩ'ኮ እክሊሉ» በማለት ሸዋዬ ከቤት ወደደጅ ወጣች::

እክሊሉ የጉዞውንና የጓዙን ሁኔታ መወሰን ተስኖት



በዐሳብ በመዋዠቅ ላይ እንዳለ፣ መንግሥት በየምክንያቱ ከሠራዊቱ ለተገለሉ መለዮ ለባሾች አስቸኳይ ጥሪ አስተላለፈ:: እክሊሉ ሸዋዬና እናቷ ጥሪውን በራዲዮ ያዳመጡት ማታ ራት ላይ እንዳሉ ነው::

«ይህ ነገር አንተን ይመለከታል?» የወ/ሮ ይፍቱ ሥራ ጥያቄ በድንጋጤ የታጀበ ነበር::

«አይመስለኝም፣ ለማንኛውም ብቅ ብዬ እጣራለሁ» አለ እክሊሉ ረጋ ብሎ::

«እርፈህ ተቀመጥ፣ እጣራለሁ ብለህ ስትሔድ እዚያው <ግባ> ቢሉህስ?» አለች ሸዋዬ ገና ከወዲሁ ሥጋቷ እንደመርግ የተጫናት መሆኑን በሚገልጽ ጭንቀት::

«ቦርድ መውጣቴን እያወቁ፣ ግባ ካሉኝ መግባት እንጂ ምን አማራጭ ይኖረኛል?» አለ እክሊሉ አሁንም ረጋ ብሎ::

«አይሆንም! አይሆንም! እክሊሉ አንተ እዚህ አገር መሆንክን የሚያውቅ ስለሌለ እርፈህ ልጅህን አሳድግ» አሉ ወ/ሮ ይፍቱ ሥራ ኮስተር ብለው::

የዚህ ሠፈር ሰው ወንዱም ሴቱም ወታደር መሆኔን ያውቃል:: ጥሪውን ገሸሽ አድርጌ ስቀር ምን ይለኛል? በጥቆማ ከተደረሰብኝ ውደት ነው::»

«ገና ምንም ሳይለይ መነፋረቅ» አሉ እናቷ የሸዋዬን ማልቀስ አጣጥለው::

«አይዞሽ ቢሞትም ላገር፣ ቢኖርም ካገር ጋር ነው» አለ እክሊሉ ሸዋዬን ለማረጋጋት::

«ለማንኛውም አለመቸኮል ነው:: ከሔድክም ዋል አደር ብለህ በመጨረሻው ላይ ብቅ ትላለህ:: እስከዚያም የግቢው ቅዱስ

ገብርኤል ያውቃል» የሚለውን ያማቱን ምክር ተቀብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ሔደ::

አክሊሉ በማግሥግቱ ባንክ ካስገባው ብር ላይ 500 ብር ቆንጥሮ በማውጣት ግማሽ ያህሉን ለሸዋዬ ሰጣት::

የተቀበለችውን ብር እየቆጠረች «ምን ላድርገው?» በማለት ጠየቀችው::

«የቤቱንም ኪራይ ክፈይ፣ ለልጁም ወተት ለሌላም ለሌላም የሚሆነው አይታወቅም»የሚለው የአክሉሉ አነጋገር ክውስጧ ፈንቅሎ ያወጣው እንባ እንደጎርፍ እየወረደ «አክሊሉ ልትሔድ!» ብላ እላዩ ላይ ተጠመጠመችበት::

«እይዞሽ ላልሔድም እችላለሁ፣ ከሔድኩም ቶሎ ቶሎ የምንገናኝበትን መንገድ ከወዲሁ ለማመቻቸት እሞክራሁ» በማለት አጽናናት::

አክሊሉ ክአልባሳቱ መካከል ሻል ያለውን መርጦ በመልበስ፣ ፀጉሩን ተከርክሞ፣ ጺሙን ተላጭቶ ከሰዓት በኋላ ጃንሜዳ ብቅ አለ:: መግቢያው አካባቢ ጥቂት ካንገዋበበ በኋላ ወደ ውስጥ ገብቶ የሚያውቀው ሰው በዓይኑ ፈለገ::

«አዲስ ተመዝጋቢዎች በቀኝ በኩል፣ ጧት የተመዘገባችሁ በግራ ተሰለፉ» በሚል ትዕዛዝ መሠረት የተሠለፈው ተመዝጋቢ በሁለት አቅጣጫ መዝጋቢዎቹ ወደ ሚገኙበት ድንኳን በሥርዓት ተንቀሳቀሰ::

ቀደም ሲል የተመዘገቡት መለዮ ለባሾች በሙሉ ለሌላ የማጣሪያ ምዝገባ ወደ ታጠቅ ጦር ሰፈር መወሰዳቸውን አክሊሉ የሰማው ያለጭንቀት ነበር:: የዕለቱ ምዝገባ እንደተጠናቀቀ እነ አክሊሉም ወደታጠቅ ጦር ሠፈር ተጓዙ:: በሣልስቱ ሸዋዬ



በአንድ የቀድሞ ክብር ዘበኛ አባል ትብብር ታጠቅ ሔዳ አክሊሉን አገኘችው::

ሸዋዬ አክሊሉን ገና በሩቅ ሲመጣ አይታው አለቀሰች:: አጠገቧ ደርሶ ላዩ ላይ እስክትጠመጠምበት ድረስ አላስችል ብሏት እሱ እየመጣ ወዳለበት አቅጣጫ ራመድ ራመድ አለች:: ብርክ ስለያዛት እርምጃዋን አቋርጣ እቅፏን ዘርግታ ጠበቀችው:: ቃል ሳይለዋወጡ ተጠማጠሙ፣ ተመጫመጩ:: በሰፊው ለመነጋገር ጊዜ ስላጠረ ግንኙነታቸው በደብዳቤ እንዲሆን ተስማምተው ተለያዩ::

ከመለያየታቸው በፊት አክሊሉ ለሸዋዬ «እኔ በድርጎ (ራሽን) እኖራለሁ፣ ደመወዜን በሙሉ ተቆራጭ አደርግልሻለሁ» በማለት የምሥራች አበሰራት:: ውስጧ በአክሊሉ ናፍቆትና ስስት ታምቆ ስለነበር ብሥራቱን በውል አጢና አክሊሉን ሳታመሰግን ክእንባዋ ጭጋግ ውስጥ ተሰወረባት::

ከአንድ ሳምንት በኋላ፣ ሸዋዬ እናቷን ዶሮ ወጥ አሠርታ፣ ጥቂት ብሮች ቋጥራና ልጇን አዝላ ወደ ታጠቅ ማለደች:: ከመለስተኛ አውቶብስ ወርዳ ወደ ታጠቅ ለመሔድ ጋሪ በመጠባበቅ ላይ እንዳለች አንዲት ሴት ክፉኛ ስታለቅስ አይታ ለወሬ ጠጋ አለች::

«ሳልሰናበተው፣ የአንድ ቀን ስንቅ እንኳ ሳላስቋጥረው በድንገት እንደወጣ መቅረቱ ነው፣ ኤርትራ ዘምቶ ማን የተመለሰ አለ?» እያለች የምታለማው ዋይታ በሸዋዬ ውስጥ ልትቋቋመው ያልቻለችው ሽብር ለቀቀባት:: ሸዋዬም ልጇን ከጀርባዋ ላይ አውርዳ ታቅፋ እየዬዋን ለቀቀችው::

በመጨረሻም ልጆቻቸው፣ ባሎቻቸውና ወንድሞቻቸው የዘመቱ ቤተሰብ አባላት እርስ በርስ ተጸናንተው ወደ የመጡበት ተመለሱ::

አንድ ሁለት ልጆቻቸውን ለጦርነት የገበሩ እናት «ታጠቅ ለሰው ቁራ - ሰው ማድለቢያ፣ መቼ ይሆን ዕድሜህ አጥሮ የምትዘጋ? ድሮም ሥጋ ሜዳ ነበርህ ዛሬ ደግሞ የሰው ፍሪዳ ታዘጋጃለህ» በማለት ያሰሙት እሮሮ በጆሮዋ ላይ እያንቃጨለባት ሽዋዬ ወደ ቤቷ ተመለሰች::



# ምዕራፍ 27

## በሽምገላ - ሽንገላ

ቦታው ካዛንቺስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢ፣ ቀኑ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ነው:: ዮሐንስና አስገደች በየበኩላቸው የሰየሟቸው የቤተሰብ ሽማግሌዎች ከአንዱ በስተቀር ሁሉም ሰዓት አክብረው ተገኝተዋል::

ተሸምጋዮች አጥቢያቸው ስለሆነ በቂ ወንበርና ጠረጴዛ ያለውን አንድ ቢሮ ለመሰብሰቢያነት ከቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ጽ/ቤት አስፈቅደዋል::

አስገደችና ዮሐንስ ከየሽማግሌዎቻቸው ጋር በቤተ ክርስቲያኑ አጸድ ከለል ከለል ብለው ወግ ይዘዋል:: የዘገዩትም ሽማግሌ ስለመጡና ሰዓቱም ስለደረሰ በሰብሳቢው ጠያቂነት ወደ መሰብሰቢው ክፍል አመሩ:: ሁሉም የእጅ ሰላምታ እየተሰጣጡ ወደ ክፍል ተገባ:: ዮሐንስና አስገደችም ሳይቀሩ ተጨባበጡ:: የአስገደች አጨባበጥ ሞቅ ያለ ነበር::

ሰብሳቢው «እንደ ተለመደው ስብሰባችንን በጸሎት እንጀምር» ብለው ብድግ ሲሉ ሁሉም ተነሱ:: ከዚያም አባታችን ሆይንና ለቅድስት ድንግል ማርያም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ያቀረበላትን ሰላምታ በሕብረት ጸለዩና ተቀመጡ::

«ከየት እንጀምር?» ብለው ሰብሳቢው ንግግራቸውን በጥያቄ ጀመሩና ቀጠል አድርገው «.... ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ከመግባታችን በፊት ምናልባት ተሸምጋዮች የምትሉት ነገር ካለ ቅድሚያ እንስጣችሁ?» በማለት ጠየቁ:: እጠያየቃቸው አስገደችም ዮሐንስም ከተያዘው አጀንዳ ውጭ የተዘጋጁበት ጉዳይ እንደ

ሚኖራቸው ፍንጭ ያላቸው ይመስል፣ በሰብሳቢው አነጋገር ተደናግጠው፣ ሚስት ባልን ምን አዲስ ነገር ይዞ መጥቶ ይሆን ባልም ሚስቱን ምን አዲስ ነገር ይዛ መጥታ ይሆን በሚል ጭንቀትና የማወቅ ጉጉት ተሰራርቀው ተያዩ::

ዮሐንስ ያስወትሮው «ሳምሶናይት» ቦርሳ አንጠልጥሎ ስታየው «ከመቸ ወዲህ ነው ጠበቃ የተሆነው ድንቄም!» በሚል ሽሙጥ ልብ ብላው ነበር::

አምስቱ አረጋውያን ከባለ ጉዳዮች የሚመጣ ጥያቄ ካለ ጊዜ ለመስጠት በእርጋታ መጠባበቅ ላይ ናቸው::

ዮሐንስ ሳምሶናይቱን ከፍቶ የካኪ ፖስታ አውጥቶ ሳምሶናይቱን በመቆለፍ ላይ እንዳለ፣ አሰገደች ቀድማ በአክብሮት ተነስታ አንድ ነጭ ፖስታ ለሰብሳቢው በሁለት እጇ ሰጠቻቸው:: ፖስታው ሽምግልናውን እንደማትፈልገውና እንዲቋረጥ የጠየቀችበትን ማመልከቻ የያዘ ነው::

ዮሐንስም እንደ እርሷው በአክብሮት ካንገትና ከትከሻው ዝቅ ብሎ ዳጎስ ያለውን ፖስታ ለሰብሳቢው ሰጣቸው::

በዮሐንስ ፖስታ ውስጥ ዓለሚቱ ከፍርድ ቤት፣ ሰስና ከሐኪም ቤት ያሰባሰቢቸው፣

1ኛ/ የዶ/ር ወ/ሚካኤል ማዴቦ ኑዛዜ፣

2ኛ/ የዶ/ር ወ/ሚካኤል ማዴቦ ወራሾች የሰየሙት የቤተ ዘመድ ጉባኤ ውሳኔ፣

3ኛ/ ወ/ሮ አሰገደች ልጇ ማርያማዊት በዶ/ር ወ/ሚካኤል ማዴቦ ኑዛዜ የታቀፈች ቢሆንም ወራሾች በጋዜጣ በሚያወጡት ማስታወቂያ ውስጥ ስሟ እንዳይጠቀስ ለቤተ ዘመድ ጉባኤ ያቀረበችው የተማፅኖ ማመልከቻ፣



4ኛ/ የአውራጃው ፍ/ቤት የዶ/ር ወ/ሚካኤል ማዴቦ ሕጋዊ ወራሾች ከሕግ ሚስት የተወለዱት ብቻ መሆናቸውን በምስክርነት አረጋግጦ የሰጠው ውሳኔና ትእዛዝ፣

5ኛ/ የዮሐንስ መሐንነት የተረጋገጠበት የሕክምና ምርመራ ውጤት ሰነዶች ቅጂዎች ተካትተዋል::

እያንዳንዱን ጽሑፍ በቅደም ተከተል እናንብበው ወይስ ባጭር ባጭሩ በቃል ብትነግሩን ይሻላል?» በማለት ሰብሳቢው ሲጠይቁ ዮሐንስ ፈጠን ብሎ «መጀመሪያ እኔ ያቀረብኳቸው ሰነዶች አንድ ባንድ ከተነበቡ ምናልባት የወ/ሮ አሰገደችን ፖስታ መክፈትም እንኳን ላያስፈልግ ይችል ይሆናል» አለ ዮሐንስ ቅጥ በሌለውና በተሰባበረ ድምፀት::

«ምንድነው ነገሩ? አልገባኝም» አለች አሰገደች ኮስተር ብላ::

«ምን አስቸኮለሽ» አለ ዮሐንስ የታመቀ ስሜቱን በሚገልጽ የአካል ንቅናቄ::

የዮሐንስ ቁጭ ብድግ ማለት ድንፋታ የተቀላቀለበት አነጋገሩን ያዳመጡት ሽምጋዮች ጥያቄውን መቀበሉ ከበዳቸው:: በዚህ ላይ አሰገደችም አልተስማማችም::

«ባለጉዳዮቹ ለጥቂት ደቂቃ ገለል በሉልንና እኛ ብንነጋገር?» አሉ ከሽማግሌዎቹ አንዱ::

«የለም! የለም! እንደርሱማ መሆን አይችልም:: የቀረቡት ሰነዶች እናንተንም ከድካም እኔንና አሰገደችም በሐሰት ከመወነጃጀል የሚገላግሉን ስለሆኑ ሰነዶቹን ለማንበብ ድፍረቱ ይኑራችሁ» አለ ዮሐንስ ብድግ ብሎ::

አስገደች ከተቀመጠችበት እንደ መነሳት ብላ «እኔም ያቀረብኩት------ችግሩን የሚያቃልል -----» ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ ዮሐንስ ብድግ ብሎ «ዝጊ! አንቺ ነፍሰ-ገዳይ! አንቺ ወንጀለኛ! አንቺ ከሐዲ» እያለ በቁጣ ፈነዳ:: በተፈጠረው ሁኔታ በሽምግልና ላይ የተቀመጡት ሁሉ ተደናገጡ የሚናገሩት ጠፍቷቸው በዝምታ ተዋጡ::

«የማትፈልጉትና የማታነቡት ከሆነ ፖስታው ይመለስልኝ፣ የመሸማገሉም ጉዳይ እዚሁ ላይ ያበቃል» አለ ዮሐንስ::

«አስገደች ነፍሷ አንድ እንግዳ ነገር ሹክ ያለቻት ይመስል፣ ራሷ በራሷ ውስጥ፣ አካሏ በአካሏ ውስጥ እየሰመጡ፣ ዓይኗ በዓይኗ ውስጥ እየጠፋ፣ ቀለሙንም እየለወጠ፣ ትንፋሽዋ ከግልቢያ እንደ ተመለሰ ሠንጋ ፈረስ ፋር ፋር ማለት ሲጀምር ልብ ያላት ሰው አልነበረም:: የሁሉም ትኩረት ወደ ዮሐንስ ተስቦ ነበርና::

የአስገደች ተዝለፍልፎ መውደቅ ሽማግሌዎቹን የሚዙት የሚጥሉት አሳጣቸው:: በዚህ ግርግር ውስጥ «ዮ-ዮ-ዮሐንስ አንተ ባለህበት የምናዘዘው አለኝ» አለች አስገደች ቅዝት በመሰለና በተቆራረጠ ድምጽ::

ምን እንዳለች በትክክል ባይረዳም አንድ ነገር ለመናገር መሞከሯን ዮሐንስ አስተውሏል:: እንድትነቃ ተባለና አንድ ባሊ ውሃ ተቸለሰባት:: ከዚያም በአንደኛው ሽማግሌ መኪና ይዘዋት ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ነጎዱ::



የሁኔታውን መመሰቃቀል ጥግ ይዞ ሲያስተውል የቆየው ዮሐንስ ካኪ ፖስታውን ከጠረጴዛው ላይ አነሳ:: ትክ ብሎ ፖስታውን ተመለከተ::

«አቶ ዮሐንስ እስቲ ግድ የለህም ረጋ በልና እንነጋገር:: ችግሩ ምንድነው - ለመሆኑ - አውቀኸዋል!» አሉ ሰብሳቢው እንደቆሙ::

«ሁሉም ነገር እዚህ ላይ አብቅቷል:: ቅዱስ ዑራኤል በኪነ ጥበቡ በምድረ-ግቢው አሳይቷችኋል:: የቀረውን ሌላ ጊዜ በሌላ ሁኔታ ትደርሱበታላችሁ» በማለት ትቷቸው ወጣ::

# ምዕራፍ 28

## የበደል ካሳ

ዮሐንስ ከከሸፈው የዑራኤል ግቢ ሽምግልና እንደ ወጣ መኪናውን አስነስቶ ደሙ-ነፍሱን ወደቤቱ አመራ::

በመኪናው ጡሩምባ የተቀሰቀሱት ልጆቻቸው ወላጆቻቸውን ለመቀበል መጀመሪያ ሁለቱ ወጡ:: የሚናገረው የጠፋው ይመስል ልጆቹን ትክ ብሎ ተመለከታቸው:: ከመኪናው በመውጣት ላይ እንዳለ «አስጉስ! አስጉስ! አሉ አከታትለው:: የአስገደች ስም ሲጠራ ዮሐንስ በጩኸት ፈነዳ፣

«በቃ! በቃ! ሁሉም ነገር አብቅቷል! የአስገደችና የእናንተ ከእኔ ጋር የነበረው ድብብቆሽ ጨዋታ አብቅቷል:: ከአሁን ጀምሮ ወደ የአባቶቻችሁ መሄድ ትችላላችሁ፣ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» በማለት በረንዳ ላይ እንደ ቆሙ ትቷቸው ወደ ቤት ገባ:: በድንጋጤ በድናቸው የወጣው ሁለቱ ልጆች ባሉበት እንደ ጨው ዓምድ ተገትረው ቀሩ::

ሌሎቹ ሁለቱ ልጆች በጩኸቱ ተደናግጠው ከመኝታ ቤት ተንደርድረው ወጡ:: መናገር ፈርተው ከዮሐንስ ፊት ዓይናቸውን እያቁለጨለጩ ቆሙ::

«ምን ትጠብቃላችሁ» ውጡልኝ ነው የምላችሁ□ኮ! በማለት ወደፊት ራመድ አለ:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በባልና ሚስት መካከል ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የቆየው አምባጓሮ ተባብሶ፣ ዮሐንስን ያሳበደው ስለመሰለው፣ ደረጀ ሲፈራ ሲቸር የዮሐንስን ትከሻ ይዞ «በመጀመሪያ እስቲ አረፍ በል አባ!» በማለት ወደ



ፎቴው ለመውሰድ በመሞከር ላይ እንዳለ፣ ሌሎቹም ልጆች ዮሐንስ ላይ ተጠምጥመው ማልቀስ ጀመሩ::

«ደረጀ! አንተም አንተም! አንቺም! ልጆቼ አይደላችሁም —— እኔ መሐን ነኝ፣ አስገደች አራታችሁንም ከሌሎች አባቶች ነው የወለደቻችሁ:: የምነግራችሁ በትክክል ገብቷችኋል? እኔ የእንጀራ አባታችሁ —— አሳዳጊያችሁ እንጂ ወላጅ አባታችሁ አይደለሁም:: ሁላችሁም አባቶቻችሁ እነማን እንደሆኑ እናታችሁ ትነግራችኋለች:: ሂዱና ጠይቋት! እኔን ተውኝ፣ በቃ ይብቃኝ —— - ሳልሞት የሞትኩ የቁም በድን ነኝ::

«ደረጀ! እናንተም ትልልቆቹ ታውቃላችሁ ደቅለሃል ብላ ባልፈጸምኩት ወንጀል አደባባይ አወጣችኝ:: እርሷ ግን እናንተን በትዳሯ ላይ ማግጣ ወለደቻችሁ:: ይኼ ይፋ ሆኖአል:: ተረጋግጧል:: ከዚህ በኋላ የእርሷም ሚስትነት፣ የኔም ባልነት፣ የእናንተም ልጅነት «የዕቃ ዕቃ ጨዋታ ሆኗል፣ ስለዚህ እባካችሁ ውጡልኝ» ይላል::

«ጆኒ የፈለግኸውን አድርገኝ! የፈለግኸውን በለኝ እንጂ እኔ ከአንተ አልለይም:: አልወጣም፣ ብትፈልግ ግደለኝና እሬሳዬን አውጥተህ ጣለው:: አባቴ አንተ ነህ! ከአንተ ከዮሐንስ ሌላ አባት የለኝም::» ብሎ ደረጀ እግሩን አንቆ ተንሰቀሰቀ::

የደረጀ ተከታይ ጌታሁን ወደ መኝታ ቤት ዘው ብሎ የአባቱን ሽጉጥ ይዞ መጣ::

«ጆኒ ውጡ ልጆቼ አይደላችሁም ነው ያልከን! ነው! አይደለም? እኔ ከአንተ ሌላ አባት የለኝም! እናቴንም አልጠይቅም! ከዚህም ቤት አልወጣም! ያውልህ እረፈው ሬሳዬን አውጥተህ ጣል» ብሎ በሽጉጥ ተኩሶ ራሱን መታና ወደቀ::

ሦስተኛው ልጅ የጌታሁን ታናሽ ሽጉጡን ለማንሳት ሲንደረደር ዮሐንስና ደረጀ ያዙት። ዮሐንስ ጥይቶቹን አፈናጥሮ ሽጉጡን ከወረወረ በኋላ የወደቀውን ልጅ ቀና አድርጎ ተመለከተው፣ የዮሐንስና ሦስቱ ልጆች በድንጋጤ ተፋጠጡ። የወደቀው ልጅ «አባዬ! ጆኒዬ!፣ ጨርሰኝ! ጨርሰኝ! » እያለ ይጮኻል። ቀና ሲያደርጉት «ውሃ! ውሃ! » አላቸው ። ደሙ እየፈሰሰ ነው።

«ሆስፒታል እንውሰደው» አለ ደረጀ ዮሐንስን ቀና ብሎ እየተመለከተ፡ «አልሄድም! ድኜ የማን ልጅ ልሆን ነው የምታከመው? መኖር አልፈልግም። ተዉኝ ነው የምላችሁ!» ብሎ መሬት ላይ ተዘረረ።

«ደረጀ! ቶሎ በል ዘበኞችን ጥራ፣ ፍጠን፣ መኪናውን አስጠጋልኝ፣ ቢሞትም ሆስፒታል ደርሶ ይሙት» አለ ዮሐንስ ጌታሁንን ታቅፎ ለመውጣት እያመቻቸ።

በደረሰው አሰቃቂ ሁኔታ ደንግጣ ጥግ ይዛ በማልቀስ ላይ ያለችው የቤት ሠራተኛ ጋቢ አምጥታ ጌታሁን ላይ ጣል አደረገችበትና «ጌታሁኔ ለኔ ያድርገው ወይ እትዬ ጉድሁን አላዩ» እያለች ዮሐንስን ተከትላ ወጣች።

ጌታሁን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታ ደርሶ በተንቀሳቃሽ አልጋ (STRETCHER) ወደ ድንገተኛ የሕክምና ክፍል ገብቶ ሐኪሙን በመጠበቅ ላይ እንዳለ ሕይወቱ አለፈ። ዮሐንስና ደረጀ አስከትለውት ከነበረው ዘበኛ ጋር በለቅሶና ጩኸት ሆስፒታሉን አናጉት። በተለይ ደረጀ ለያዥ ለገራዥ አስቸገረ። «ወንድሜ! ጌታሁን! የእናቴ ልጅ...... አስከትለኝ! አለግዬ የትነሽ! እረ የትነሽ? ጌታሁንን ልጅሽን ተለናበቺ! ጉድሽን አላየሽ» እያለ ከአጠገባቸው



እየሮጠ ወደ ውጪ ለመውጣት ፈትለክ አለ። ዘበኛው እንደምንም ደርሶ ያዘውና መለሰው።

ወሬ አዳናቂው ከበባቸው፣ የሆስፒታሉ ሠራተኛና ታካሚው የሰው ባሕር ሠራ። ዘግይቶ የደረሰው ተረኛ ሐኪም ለጌታሁን የወጣውን ካርድ ከተመለከተ በኋላ ዮሐንስን ለማረጋጋት ሞከረ። ሰውንም ገለል አስደረገ። ዮሐንስ ግን መጽናናት (መረጋጋት) አልቻለም።

ጌታሁን የአባቱን ሽጉጥ ተኩሶ ራሱን መምታቱንና እዚህ ከደረሰ በኋላ ሕይወቱ ማለፉን ዘበኛው ለአንድ የሆስፒታሉ ሠራተኛ ነግሮ ኖሮ ወሬው ወዲያው ተስተጋባ።

«አስክሬኑ ወደ ሬሳ ማቆያ (MORGUE) ይረፍ፣ ቤተሰቦቹ የሆናችሁ የደረሰውን አደጋ ለፖሊስ ሪፖርት ብታደርጉ ይሻላል» አለ ሐኪሙ ምክርም ትዕዛዝም በተቀላቀለበት ቅላፄ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ከዮሐንስ ቤት በስልክ የተቀሰቀሰው ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ግልብጥ ብሎ የድንገተኛ ሕክምና አካባቢውን አጥለቀለቀው። የለቅሶው ጩኸት ሆስፒታሉን ከታች እስከ ላይ አናጋው።

***

ከጥቂት ሰዓታት በፊት በድንጋጤ ተዝለፍልፋ ዑራኤል ቤተክርስቲያን ተዘርራ የነበረችው አስገደች ብርቱ የሕክምና ርዳታ ቢደረግላትም ገና ነፍሷን አላወቀችም።

«እናቱ የት አለች!..........አስገደችስ!» ለሚለው የበርካታ ዘመድ አዝማድ ጥያቄ ዮሐንስ መልስ አልሰጠም። ሰምቶ እንዳልሰማ መሆንን ነው የመረጠው። ስለ ጉዳዩ ከዮሐንስ ቀጥሎ

የተሻለ መረጃ ያላቸው ተስፋዬና ዓለሚቱ፣ ስለአደጋው በስልክ የተነገራቸውን መረጃና የአስገደችን ሁኔታ፣ በዮሐንስ በኩል ተቆጥረው ከነበሩት ሽማግሌዎች ለማንጠር፣ ከዚያም ቀጣዩ ርምጃ ምን መሆን አለበት? ለሚለው ጥያቄ ከወዲሁ መልስ ለማግኘት ሥራ ተከፋፈሉ::

በአስገደች በኩል የተቆጠሩት ሽማግሌዎች በአስገደች ላይ ስለደረሰው አስደንጋጭና አሳዛኝ ሁኔታ ለወላጆቿ በስልክ ያሳወቁት እሷን ሆስፒታል አስተኝተው ከመሔዳቸው በፊት ነው:: እነ አቶ ደምሴ በልጃቸው ላይ በደረሰው አሰቃቂ ሁኔታ ከገቡበት አደናጋሪ ድንጋጤ ሳይወጡ እዚያው ሆስፒታል ውስጥ የልጅ ልጃቸውን ሞት ተረዱ:: አቶ ደምሴና ወ/ሮ ዘምዘም ለማይና ምድር ቢዞርባቸውም ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ አልተዘነጋቸውም::

«ከዚህ ጠንቀኛና መዘዘኛ ሆስፒታል አውጥተን ወደ ሌላ ሆስፒታል እንውሰዳት» አሉ ወ/ሮ ዘምዘም ወደ ባለቤታቸው ጆሮ ግንድ ጠጋ ብለው «ቆይ እስቲ፣ ረጋ በይ፣ እሷም ታማ ሆስፒታል የገባችበት፣ ልጅዋ ራሱን ገደለ የተባለበት ምክንያት በግርድፉ እንኳ ቢሆን ይጣራ:: ከዚያ በፊት እሷን ማንቀሳቀሱ ለኔ አልታየኝም:: ለዚያውም□ከ ገና ነፍስ አልዘራችም» አሉ አቶ ደምሴ እልህ እየተናነቃቸው:: «እኔ እንጃ በሕመሟ ላይ የልጇን ሞት ከሰማች.....» ብለው ወ/ሮ ዘምዘም ለቅሶ ሲጀምሩ «ወግጂ ወዲያ! ምን ገና ምኑም ሳይለይ መንዘርበብ» አሉ አቶ ደምሴ ለበቀል በማሸተል ላይ መሆናቸውን መደበቅ እስኪሳናቸው ደንፍተው::



ባልና ሚስት እንጃ ግራንጃ ላይ እንዳሉ ልጃቸው ሰይፈ ስድስተኛ ፖሊስ ጣቢያ የተላከበትን መረጃ ይዞ ደረጃውን በጥድፊያ የወጣበት ትንፋሽ አጥሮት እያለከለከ መጣ::

«የዮሐንስ እህት እትዬ ዓለሚቱና ጓደኛው ተስፋዬ ከጣቢያው አዛዥ ቢሮ ወጥተው ሲሄዱ ነው ያየኋቸው:: እንደገባኝ የአደጋውን ሁኔታ አስመዝግበው ነው የኼዱት» አለ ሰይፈ ሥላሴ::

«እውነትክን ነው ይመስላል» አሉ አባቱ የልጃቸውን አስተያየት በመቀበል::

«አባት አሁን ገብታችሁ ልትጠይቋት ትችላላችሁ» አላቸው አስገደችን እንደገና ጎብኝቶ የወጣው ዶክተር::

«አባቴነህ በሽታዋ ታውቋል?» አሉ አቶ ደምሴ ዶክተሩን ከተል ብለው::

«ነገሩ ከጭንቀትና ድንጋጤ የመጣ ይመስላል:: ያዘዝኩላት ልዩ ልዩ የምርመራ ውጤት እስኪደርስ በእርግጠኝነት በሽታዋ እንዲህ ነው ለማለት ያስቸግራል:: ያም ሆኖ አሁን ያለችበት ሁኔታ ለክፉ የሚሰጣት አይመስልም» ብሉአቸው ኼደ::

ቀድመው የገቡት እናትዋ አንገቷን ታቅፈው በማልቀስ ላይ እንዳሉ አባቷ ገብተው «እናቴነሽ! አሁን እንዴት ነሽ!» አሉ በአንድ እጃቸው አልጋውን በሌላ እጃቸው ከዘራቸውን ደገፍ ብለው ዓይን ዓይኗን እየተመለከቱ::

«ለጊዜው ደህና ነኝ፣ ግን እንዴት፣ ማን ነግሯችሁ መጣችሁ?»

«ሽማግሌዎችሽ» ነገሩን::

«የሆነውን ሁሉ ለማችሁ? ዮሐንስንና ልጆቼንስ አገኛ ችኋቸው? አባዬ! እማዬ! ከእንግዲህ አልረባችሁም፣ ልጆቼን ግን አደራ!» ብላ አስገደች ተንሰቀሰቀች::

«አይዞሽ አንድ ጊዜ የሆነው ሆኗል! አንቺ ጤናሽንና ራስሽን ጠብቂ:: ልጆቹ አባት ስላላቸው ምንም አይሆኑ» አሉና የነገሩን መነሻ ለማወቅ «ለመሆኑ ነገሩ ምንድነው?» በማለት ጠየቋት::

«አባዬ የሆነውን ምን ብዬ ልንገራችሁ? አፍም እንደበትም የለኝ:: የእኔ ነገር አክትሟል:: ድኜ እንኳን ብወጣ ዮሐንስ አይምረኝም:: ይገድለኛል:: እኔና ልጄን ማርያማዊትን መግደሉ የማይቀር ነው:: ድኜ እስክወጣ ዮሐንስ ለመታገስ ጊዜ የሚኖረው አይመስለኝም:: በማወቅም ሆነ ባለማወቅም ተሳስቼ ባሌን በድየዋለሁ:: እንደገናም ባልፈጸመው ድርጊት ወንጀዬ አደባባይ አውጥቼዋለሁ:: እኔን ቢገድል ነፍስ ገዳይ አያሰኘውም:: ልጄን ግን እንደምንም ብላችሁ አትርፉአት:: አባዬ! ልጄን! ልጄን! አደራ!» ብላ ተዝለፈለፈች፣ ዓይኗ ጣራ ላይ ተሰካ::

«ልጄን! ልጄን! ድረሱልኝ! ያገር ያለህ!» የሚለው የወ/ሮ ዘምዘም እሪታ የሆስፒታሉን ፀጥታ አናወጠው::

ማታውኑ አስገደች ወደልዩ ሕክምና ክፍል (Intensive care) ገባች:: ቤተሰቦቿ ከአካባቢው ገለል እንዲሉ ተደረገ::

ደረጀና መልኬ ዝርዝሩን ባይደርሱበትም እናታቸው በድንገት ታምማ እዚያ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መተኛቷን በጭምጭምታ ሰምተዋል::

«የተኛችበትን ክፍል ባውቅ ኖሮ ሹልክ ብዬ አስገን አይቼ እመጣ ነበር» አለ መልኬ ለደረጀ በሹክሹክታ::



«አይሆንም! አስጉና ጆኒ የተካረሩ ይመስለኛል:: አታይም እኛን እንኳን ከቤት ውጡ ሲለን:: በጥየቃ ወይም በሌላ ሁኔታ ወደ እሷ የተደረብን እንዳይመስለው፣ በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል::» በማለት ደረጀ ወንድሙን የትዕዛዝ ያህል አስተነከረ::

«እኔ ግን ጆኒን ለምኜ አስፈቅጄው ነገም ቢሆን እናቴን አያታለሁ» አለና መልኬ ዓይኖቹ እንባ አቀረሩ::

የነደረጀን ዱለታ በቅርብ ርቀት ሆና ስታስተውል የቆየችው ዓለሚቱ «ብርድ ነው ሂዱ፣ አባታችሁ መኪና ውስጥ ቆዩ» አለቻቸውና ወጡ::

የሆስፒታሉ ዘበኞችም አካባቢውን ለሌሎች ታካሚዎች እንዲለቁ ኮስተር ብለው ስለጠየቋቸው ዮሐንስና ቤተሰቡ ተግተልትለው ከሌላ ጥግ ላይ ተተገኑ::

ዓለሚቱና ተስፋዬ ውስጥ ውስጡን ባደረጉት ቅስቀሳ በቡድን በቡድን ሆኖ ለ15 ደቂቃ ያህል ምክክር ላይ የቆየው ቤተሰብ ዮሐንስን አግባብቶ ወደ ቤት ጉዞ ሆነ::

***

አደጋውን ዘግይቶ የሰማ ወዳጅ ዘመድ የዮሐንስን ቤትና ግቢ ከለቅሶ ይልቅ ሽብር የነገሠበት አስመሰለው:: ሁሉም እንደ ትውውቁ እየተቧደነ ይንሾካሾካል:: ዓለሚቱ፣ ተስፋዬና ዮሐንስም መኝታ ቤት ገብተው ከግማሽ ሰዓት በላይ ቆይተው ወደ ሳሎን ተመልሰዋል::

ደረጀ ከጥቂት ጓደኞቹ ጋር ወንድሙንና እህቱን ይዞ መኝታ ቤታቸው ውስጥ እንዲቆዩ ዓለሚቱ የሰጠችው ትዕዛዝ ተከብሯል::

ከሞላ ጎደል በሚያውቁቷ ምክንያት የደረሰውን አደጋና የአሰገደችን ሆስፒታል መግባት ያሰሙት የዮሐንስ ወላጆች ደረስ ብለው ወደ ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ ከዓለሚቱ ጋር በስልክ አንድ ሁለት ጊዜ ተገናኝተዋል::

የኼደው ሄዶ እዚያ ለማደር የወሰነው ኀዘንተኛ ወሬውን ጨርሶ በያለበት ማንጎላጀት ይዟል::

ከሰሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ስልክ ጭርር አለ::

ዓለሚቱ የስልኩን እጀታ አንስታ «ሀሎ» አለች::

«እኔ ነኝ ተክሉ ከሆስፒታል ነው የምደውለው»

«እህ እንዴት ነው? ምን አዲስ ነገር አለ?»

«የእትዬ አሰገደች ወላጆች በጣም እያለቀሱ ናቸው:: የሆስፒታሉ ሠራተኞችም እየተራወጡ ናቸው::»

«ሞተች ነው የምትለኝ! አሰገደች አሰገደች ሞተች!» አለች ሳይታወቃት ጮክ ብላ::

«ይመስለኛል እዎ!»

«ስማ ተክሉ ዕውነት ሞታ ከሆነ በደንብ አጣርታችሁ ወደ ቤት ኑ» አለችና ስልኩን ዘግታ ዮሐንስና ተስፋዬ ወዳሉበት ብቅ ብላ ጠቀሰቻቸው::

«ምነው?» አለ ዮሐንስ በእህቱ መደናገጥ እሱም ተደናግጦ::

«ተክሉ ከሆስፒታል ደውሎ ነበር:: አሰገደች ሳታርፍ አልቀረችም::»



ዮሐንስ የሰማውን ማመን አቅቶት «ምን!» አለ ድንጋጤ ባናረው ድምፅ::

ለዮሐንስ መልስ ሳትሰጥ ተስፋዬና ዓለሚቱ የመሸከም ያህል ደግፈው መኝታ ቤት አስገቡት::

ለተወሰኑ ሴኮንዶች ዮሐንስ አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ:: ሳይታሰበው እንደማልቀስ ቃጣውና መልሶ ተወው::

«እናንተ የምታረጉትን አርጉ፣ እኔ እዚህ ልቆይ» አለ ዮሐንስ በታከተ ስሜት::

«ዓለሚቱ እዚሁ ከሱ ጋር ቆዩ፣ እኔ አንዳንድ ነገር ልሥራ» ብሎ ተስፋዬ የእነሱን ስምምነት ሳይጠብቅ ወደ ሳሎን ወጣ::

ተስፋዬ ለዮሐንስ የበለጠ ቅርበት ያላቸውን ጥቂት ሰዎች ይዞ ዮሐንስ በቢሮነት የሚጠቀምበትን ክፍል አስከፍቶ ገባ::

ተስፋዬ ጠቅለል ባለ መልኩ፣ ከኋላ ተነስቶ፣ እነሱ በግርድፉ የሚያውቁትን ታሪክ ነግሯቸው የአሰገደችንም ሞት አረዳቸው::

አንድ ሁለቱ ኀዘን የፈነቀለውን እንባቸውን በማውረድ ብድግ ብለው ቆሙ::

«ወንድሞቼ ለማልቀስ ጊዜ አለን:: አሁን ኀዘናችንን ዋጥ አድርገን ስለ እናትና ልጅ ሥርዓተ ቀብር እናስብ» አለ ተስፋዬ አባባሉን ረገጥ አደርጎ::

«ምክክሩ ዮሐንስንና ዓለሚቱን ቢጨምር.....» አለ አንደኛው::

«ሊጨምር ይችላል፣ እስቲ በቅድሚያ እኛ ለምክክሩ መነሻ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ዐሳብ እንፈንጥቅ» አለ ተስፋዬ::

«ለቅሶው አስገደች ወላጆች ቤት ቢሆን፣ አስክሬኖቹም ከሆስፒታል ወደዚያ ቢወሰዱ የሚሻል ይመስለኛል:: ይቅርታ አድርጉልኝ ዮሐንስ በኀዘንተኛነት የሚያስቀምጠው ምክንያት ለኔ አልታየኝም:: ጌታሁንም ሆነ አስገደች ለዮሐንስ ምኑ ናቸው? ልጅ..... ሚስት...... ምን ሊባሉ ነው? ስለዚህ ለቅሶው እርሱን የማይመለከት ካልሆነ ዮሐንስ ኀዘን የሚቀመጥበት ምክንያት ሊኖር አይችልም:: ዕውነቱን ልንገራችሁ መሞትዋ በጀ፣ ይህች ከሐዲ ሸርሙጣ!» አለ ሌላው ተማካሪ::

«እኔ ይኽንን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ እደግፋለሁ» አለ ሦስተኛው ተማካሪ፣ የሚደግፍበትን ምክንያት እንደሚከተለው እየደረደረ::

«ይህቺ ሴት ራሷን በራሷ የገደለች፣ ለልጇም ሞት ምክንያት የሆነች ከይሲ ነች:: ዮሐንስንም በቁሙ ገድላው ነው የሞተችው:: ስለዚህ ዮሐንስ እንደገና በቁሙ ለቀበረችው ሴት ኀዘን ተቀምጦ ያገር መሳቂያ መሳለቂያ መሆን የለበትም:: ለሞተውም ልጅ እናቱን አባልጎ ያስወለዳት አባቱ ያልቅስለት እንጂ ዮሐንስ ምን በወጣው!»

«ቀሪዎቹ ሦስቱ ልጆቿስ ምን ይሁኑ?» የተስፋዬ የጭንቀት ጥያቄ ነበር::

«ዮሐንስ እስከ ዛሬ አሳድጓል አስተምሯል........ በቃ! ከዚህ በኋላ ኃላፊነት የለበትም:: የኔ አስተያየት ይኼ ነው:: ከዚህ የተረፈውን ለዮሐንስ እንተውለት» አለ አራተኛው ተማካሪ ፍርጥም ብሎ::

አምስቱም ተማካሪዎች በዚህ ለቅሶውና ኀዘኑ ወደ አስገደች ወላጆች ቤት ይገፋ በሚለው ዐሳብ ተስማምተው ዮሐንስንና እህቱን ለማሳመን መኝታ ቤት ገቡ::



ተማክረው ወደ መግባባት የደረሱበትን ውጤት ከነምክንያቱ ጭምር አስረድተው እንዳበቁ ዮሐንስ የሰማው ታሪክ የሚያውቀውና እስኪነቱ የተፈተነበት መሆኑን ከፊት ወደ ኋላ፣ ከኋላ ወደ ፊት መልሶ ቀልሶ አሰበ:: ብዙ ነገር በአንድ ጊዜ ታወሰውና ምንም ሳይተነፍስ መሬት መሬት እያየ ዝም አለ::

የወንድሟ ጭንቀት ያስጨነቃት ዓለሚቱ «እስቲ ትንፋሽ ፋታ እንስጠው» አለችና ብድግ አለች::

«አዎ! ዓለም ዕውነትሽን ነው:: ውሳኔው ትክክል ቢሆንም ቀላል አይደለም::» ብሎ ዮሐንስ እንደገና ተከዘ::

«ልጆቿ – እናታቸው መሞቷንና ለቅሶዋም ወላጆቿ ቤት መሆኑ ተነግሯቸው ወደዚያው ይላኩ፣ ከዚያ በኋላ እንደፍጥርጥራቸው ይሁኑ» አለ አንደኛው አማካሪ::

በልጆቹ የወደፊት ዕድል ላይ የተሰጠውን አስተያየት በማጠናከር «በሣልስቱ አባቶቻቸው ብቅ ብቅ ብለው ልጆቻቸውን ይጠይቁ ይሆናል፣ ማን ያውቃል?» አለች ዓለሚቱ በመደምደም::

ዮሐንስ የአማካሪዎቹን አስተያየት በጥሞና ካዳመጠ በኋላ «ለማንኛውም እስቲ ላስብበት ጊዜ ስጡኝ» በማለት ብቻውን ወደ መኝታ ቤት ኼደ::

«ሌሊቱም እየነጋ ስለሆነ እሱም ወገቡን ያሳርፍ፣ እኛም በየመኪኖቻችን ውስጥም ቢሆን ሸለብ እናድርግ» ተባብለው ከቤት ወጡ::

ዮሐንስ ልጆቹ ወደ አስገደች ወላጆች ቤት ይሸኙ በሚለው ሀሳብ መስማማቱን ከገለጸላቸው በኋላ «የእናታቸው ሞት ምን ተብሎ ይነገራቸው? ወይስ ከኼዱ በኋላ ይረዱ?» የሚል ጥያቄ ወርወር አደርጎ በተለይ ዓለሚቱን ትኩር ብሎ ተመለከተ::

«እዚሁ እርማቸውን አውጥተው ቢሸኙ ነው የሚሻለው» አለች ዓለሚቱ::

«ሌሎቻችሁስ ምን ትላላችሁ?»

«ዮሐንስ ለምን ይኸንን ለአንተ ውሳኔ አንተውልህም?» አለ ተስፋዬ::

«እኔ እናንተ በምትሉት እስማማለሁ» አለና ከተቀመጠበት የአልጋው ጫፍ ላይ ቀስ ብሎ ተነሳና ጎርደድ ጎርደድ አለ በትካዜ::

ልጆቹ የእናታቸውን ሞት እዚሁ ከተረዱ በኋላ ወደ አያቶቻቸው (የአስገደች ወላጆች) ቤት ይሸኙ በሚለው ዐሳብ ስምምነት ላይ ተደረሰና ተስፋዬ ሊያመጣቸው ኼደ::

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ልጆቹ እነ ዮሐንስ ካሉበት መኝታ ቤት ገቡና ወንዶቹ ጥግ ይዘው ቆሙ:: ማርያማዊት ግን «ጆኒ እማዬስ! የታለች! አስግዬስ!» ብላ በተቀመጠበት አንገቱ ላይ ጥምጥም አለች::

«አስገደች የለችም፣ እናታችሁ ሞታለች!» የሚል ድምፅ ክፍሉ ውስጥ አስተጋባ::

መልኬ ---- ሦስተኛው ልጅ ዘልሎ መሬት ላይ ተከለከለ:: ደረጀ «ኡ-ኡ-ኡ! ያገር ያለህ እናቴን! እናቴን! የት ነች? ሬሳዋን አሳዩኝ የታለ?» እያለ ከቤት በርሮ ወጣ:: ከዮሐንስና ከመማክርቱ በስተቀር ኀዘንተኛው በሙሉ በዕንባ ተራጨ::

ማርያማዊት ከዮሐንስ ላይ ተጠምጥማ አልላቀቅም አለች:: ደረጀንና መልኬን አባብለው ሳሎን ገብተው እንዲያለቅሱ ተደረገ:: ዮሐንስም ማርያማዊትን እንደታቀፈ ወደ ሳሎን መጣ::



ደረጀና መልኬ እያረፉ እንዲያለቅሱ ተስፋዬ እያፅናና ቢመክራቸውም መረጋጋት አልቻሉም::

ዮሐንስ ማርያማዊትን እንደታቀፈ ብድግ ብሎ ልጆቹን እንደምንም አግባብቶ አስቀመጣቸው:: እነ ደረጀ ከተቀመጡም በኋላ ጩኸታቸውን ገታ አድርገው እየተንሰቀሰቁ ናቸው::

«ስማ ደረጀ» አለ ዮሐንስ ድምፁን ዘለግ አድርጎ፣ «የእናታችሁ አስክሬን ያለው ወላጆችዋ ቤት ስለሆነ ወደዚያ ትሔዳላችሁ.....» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ «ጆኒ እኔ! እኔ! አልኼድም» አሉ ደረጀና መልኬ ሁለቱም በአንድ ቃል፣ በአንድ ድምፅ፣ በአንድ ጊዜ::

«እንደ ወንድማችን እንደ ጌታሁን ሬሳችን ነው ከዚህ ቤት የሚወጣው:: ትናንት አባታችሁ አይደለሁም ብለህናል:: እኛ ከአንተ ሌላ አባት የለንም፣ አናውቅም፣ አሁን ደግሞ እናት የለንም፣ የት ነው የምንኼደው? ከቤቴ ውጡ ካልክ እኔ በበኩሌ ወንድሜን፣ እናቴን፣ አንተንም አጥቼ በሕይወት መኖር አልፈልግም:: በቃ ይኸውልህ ወጣሁልህ:: ነገ ሬሳዬን ፈልገህ ቅበረው» ብሎ ወጣ:: መልኬም ተከተሎት ሮጠ:: ማርያማዊት ከእቅፉ ወርዳ አጠገቡ ቆማለች:: ጓደኞቻቸውና ሌሎችም ኀዘንተኞች እነ ደረጀን የመሸከም ያህል ደጋግፈው ይዘዋቸው መጡ:: ዮሐንስ ወደ በረንዳ ወጥቶ ይዟቸው ሳሎን ገባ:: ለቅሶ ቆሟል:: ዝምታ ሰፍኗል::

«ቁጭ በሉ» አላቸው ዮሐንስ እሱ እንደ ቆመ::

«ምን ቤት አለንና ነው የምንቀመጠው - እኔ አልቀመጥም» አለ መልኬ ተኮሳትሮ::

«ደህና ኑ» አለና በግራና ቀኝ እነሱን አቁሞ ማርያማዊትን ከፊት ለፊቱ አድርጎ ዮሐንስ አለቀሰ:: ልጆቹን ተራ በተራ እየተመለከተ ድምፅ ሳይወጣው እያነባ «ጮኬ ባለቅስ ይወጣልኝ ነበር፣ ግን ምን ብዬ ላልቅስ? የምለው ጠፋብኝ» አለና ሦስቱንም አቀፋቸው:: እነሱም አቀፉት:: ተቃቅፈው ተላቀሱ:: ኀዘኑተኛ ውንም አስለቀሱ::

በዚህ መኻል ዮሐንስ ጎንበስ ብሎ ከነበረበት ቀጥ ብሎ ግራ ቀኙን መመልከት ሲጀምር የስቅስቅታው ለቅሶ ቆመ:: በአንድ አፍታ ቤቱን ዝምታ ዋጠው::

ዮሐንስ እንደገና ዝቅ ብሎ ልጆቹን በዕቅፉ ውስጥ አስገባ፣ እነሱም ተጠመጠሙበት::

«ተፈጥሮ በደለችን፣ አስገደች ደግሞ የበደል በደል ፈፀመችብኝ:: እናንተ የበደል ካሳዎቼ ናችሁ:: ባልወልዳችሁም አሳድጌአችኋለሁና አባት እሆናችኋለሁ:: እናንተም ልጆቼ ሁኑ» አለና ሦስቱንም በእቅፉ ጨመቃቸው::

**ታሪኩ ተፈፀመ!!**

//